# - 14 -

# ባሕር ተሻግሮ ሕይወትን መሸጥ

ጉዞ ጉዞ ወልዶ ማለቂያው ቢጠፋ
ከሀገር ያልተመቸ ሰው ሀገር ቢከፋ
ወዳት ይሰደዷል ወዴትስ ሲጠፋ
መከፋትን ይዞ ቢጨልምም ተስፋ
ተመስገን ማለት ነው ነገም እንዳይከፋ

የመን ውስጥ በየቦታው የሚሰቃዩ ወገኖች መኖራቸውን ስለማውቅ ተዘዋውሬ ማየት ፈለኩ። በተለይ አደን በሚባለው የየመን ሁለተኛ ከተማ ኮርማክሰርና ሻባት የሚባሉት ቦታዎች ሀበሻው ከባህር እንደወረደ ኑሮ የሚመሰርትባቸው ናቸው። ከዜሮ ተነስቶ መቋቋም የሚቻልባቸው መሆና ቸው ብቻ ሳይሆን ብዙ ዝቅጠትና ክስረት ያለበት ነው። በስደት አማራጭ ማጣት ምን አይነት ኑሮ ውስጥ እንደሚያስገባ ለማሳየትም ስል ሄድኩ።

በመጀመሪያ እንደ እኛ አቆጣጠር ከ1941-1955 የየመን ዋና ከተማ መሆኑን ከሰነዓ ተቀብላ ወደነበረችው ትዕዝ ነው የተጓዝኩት። ወደአደን ለመጓዝ ግድ ሆኖ ሳይሆን የመን ከመጣሁ ካላየኋቸው ከተሞች አንዷ በመሆኗም እንደ አማራጭ ተጠቅሜ ነው። በዚህ ሰዓት የመን ውስጥ (እርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ስለነበረች) ማናቸውም ትላልቅ የክፍለ ሀገር አውቶቡሶች የውጭ ዜጋ አያስተናግዱም። ለህይወት ሀላፊነት ስለማይወስዱ በሚኒባሶች (ትንሽ ዋጋ ቢጨምሩም) ነው መጓዝ ያለብኝ። ስለዚህ ትዕዝን ልያት የሚለው ሀሳቤ አመዘነና ሚኒባሱ ላይ አንጠለጠለኝ።





ትዕዝ በአሁኑ ሰዓት ለየመን ሶስተኛ ከተማ ናት። ሰነዓ፣ አደን ቀጥሎ ትዕዝ ..የህዝቧ ብዛት ከሁለት ሚሊዮን እንደሚበልጥ ይነገርላታል። ከሰነዓ ጠዋት ሶስት ሰዓት አካባቢ ባብ አል-የመን/old Sana`a/ ከሚባለው አካባቢ ጉዞ ጀመርኩ። ከከተማ ስንወጣ ጀምሮ በተራራና ተራራ መካከል የሚወርደው መንገድ እንደ ጅረት ቁልቁል ወደታች እያምዘገዘገን ነው። ጠመዝማዛነቱ እንዳለ ሆኖ አልፎ አልፎም ቢሆን ዳገት ቢጤ ያጋጥመን ነበር። አንድ ዜማ ትዝ አለኝ። ‹‹...ጠመዝማዛው መንገድ ኮረብታ...ሽቅብ ቁልቁለት.. በረሃ አቋራጭ ጋላቢ ዳገት የሩቁን ከቅርብ አቀራራቢ....›› የሚለውን ለሾፌሮች የተዜመ የሀገሬን ዜማ እና ጋራ ሸንተረሩን አስታወሰኝ። ሙቀቱ በጠዋቱ በፍቅር እንደምትማርክ ልጃገረድ ልብስ ማስወለቅ ጀምሯል። ከመንገዱ ዳርና ዳር የሚታዩት ተራራዎች ያፈሩትን የጫት ምርት እዩት ብለው ለአይን ማረፊያ አድርገውታል። በጣም አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ሌላ አይነት ምርት አይታይም ሁሉም ጫት.... ጫት.. በቃ! ትልቁ ተፈላጊ እና አዋጭ ምርት ነው። ማበር፣ ደማር.. የሚባሉ መካከለኛ ከተማዎችን ከብዙ ጥቃቅን ከተሞች ጋር አቋረጥን። የሁሉም ፀዳት ከሰነዓ የባሰ ደስ የማይል ነው።

የደሴን መንገድ ያስታወሰኝ ጠመዝማዛ ጎዳና የገጠመኝ ኢብ ወደምትባለው ከተማ ስንቀርብ ነው። ኢብ ካየኋቸው የየመን ከተሞች ሁሉ ፀዳ ያለችና ፕላን ቢጤ የተቸራት ትመስላለች። ሶስት ፈርጣማ ተራሮች መሀል ግርማ ሞገስ ተላብሳ ቁጭ ብላለች። ትመቻለች። ወደ ትዕዝ በቀረብን ቁጥር አርባምንጭ አካባቢ ያለሁ እስኪመስለኝ ድረስ እርከን በእርከን ሆኖ ኮንሶን አስታወሰኝ። አረንጓዴነት ተላብሷል። ይህ ሁሉ አረንጓዴ ምርት ግን ደረቃማና ድንጋያማ መሬት ላይ ነው ቢባል ማን ያምናል? ቦታው ድንጋያማ ስለሆነ አፈር ከሌላ ቦታ አግዘው፣ ደልድለው ከ200-300 ሜትር ወደታች ቆፍረው ውሀ አውጥተው በመስኖ ያለማሉ።

ትዕዝ መግባታችንን ከጎኔ ያለው ወንበር ላይ የሚኒባስ ጊዜያዊ ጎረቤቴ ሆነው የተሰየሙት አዛውንት አበሰሩኝ። እንኳን ደህና መጣችሁ ብለው የቆሙ ሰዎች ሳይሆን ፋብሪካዎቹ ላይ አይኔን አንከራተትኩ። መግቢያው ላይ አደራደራቸው አቀባበል የሚያደርጉ ይመስላሉ። ሀገሬ ላይ የማውቀው ሸኖ ለጋ ቅቤን፣ አቡ-ወለድን ብስኩትን ከሚያመርቱት ፋብሪካዎችና ሌሎች በርካቶች ግራና ቀኝ ተደርድረዋል። ፋብሪካዎቹን ስናልፍ መንገዱ ለጥ ብሎ በቀኝ እና በግራ በተራራ ታጅቦ የተፈጥሮን ውበት ላደንቅ ግድ አለኝ። ረጅም ርቀት ከተጓዝን በኋላ ደረቱን የሰጠ ደማቅ ከተማ ውስጥ ራሴን አገኘሁት። በዚህ ቢበቃ ጥሩ ነበር። ተራራ ላይ ተጎብሮ ሜዳው ላይ ያለውን ከተማ አቆልቁሎ የሚያየው የከተማው

እምብርት መሆኑን ሳውቅ ወደዛ ማምራት አማረኝ። ታዲያ ማን አምሮት ይሞታል ተጓዝኩ እና አየሁት።

የትዕዝ ከተማ አቀማመጧ ከባህር ወለል በላይ 3070 ነው። አብዛኛው መሬቷ በተራሮች እና እርዝመቱ እስከ ቀይ ባህር ወደጎን ደግሞ እስከ ባብአል-ማንደብ የተባለው ቦታ ድረስ የተዘረጋ ስምጥ ሸለቆ አላት። የፍራፍሬ አይነት የሚበቅልባት ትዕዝ ብዙዎቹ ከተሞቿ ጥንታዊ እና እድሜ ጠገብ ናቸው። ትዕዝ ካሏት ጥንታዊ ከተማዎች መካከል ተጠቃሽ የሆነው ደግሞ ‹‹ጃበል ሀባሺ››/የሀበሻ ተራራ/ የተባለው ከተማ ሲሆን በአንድ ወቅት ይህ ከተማ ጠፍቶ እንደነበርም ይገለፃል። ትዕዝ ከተማ ጥንት እንደኛዋ ሐረር ከተማ በግንብ የታጠረች እና አምስት በሮች ያሏት ሲሆን በሮቹ አጠገብ አስራ ሶስት ሜትር ከፍታ ያለው የጠባቂዎች ዋልታ (ማማ) የተሰራለት ነው። ታዲያ ጥንት ነው። አሁን ሁለቱ በሮች ብቻ ናቸው ታሪክ እየተናገሩ ቆመው የሚገኙት።

ታክሲውን በሮቹ እንዳሉ በተነገረኝ አል-ካሂራህ አካባቢ ነዳው አልኩና እብስ ‹‹አል-ባብአል-ካቢር›› /ትልቁ በር/ እና ‹‹አል-ባብሞዉሳ›› /የሞዉሳ በር/ በመባል የሚታወቁት ሁለቱ በሮችና ትንሽ የግንቦቹ ቅሪቶችን አየሁ።

ትዕዝ ላይ ለአራት ሰዓታት አካባቢ ያደረኩትን ቆይታ አጠናቅቄ ወደ የመን ሁለተኛዋ ከተማ አደን አመራሁ። ስለአደን ከመነካካቴ በፊት ሌላ የትዕዝን ገጠመኝ ላውጋዎ... ሰኞ ጥር 21 ቀን 2004 ማታ ስልክ ተደወለልኝ። ከትዕዝ አይደለም። ከአዲስ አበባ ነው የተደወለው። ደዋይዋ ጅማ ከተማ ነዋሪ የሆነችው እህቴ ዓለም ተ/ሀይማኖት ናት። ሙራድ የሚባል ልጅ ወንድሙ ሞቶ ለለቅሶ ወደየመን ሲመጣ እንደሆነ ገልፃ ኤርፖርት ሄጄ እንድቀበለው አዘዘችኝ። ምንም ታናሽ ብትሆን እህት ነች እና ቃሏ መከበር ስላለበት አደረኩት።

ወንድሙ የመናዊ እሱ ጅማዊ ሆነው አይደለም። ወይም በስደት የመጣ ሀበሻ ወንድሙ አይደለም የሞተው። ትውልደ ኢትዮጵያዊ ናቸው ሁለቱም። ከሙራድ ጋር እንደተገናኘን ለዘመዶቹ ደዋወልን። ቀሪያ /ገጠር/ ለለቅሶ ስለሄዱ ኔትዎርክ አስቸጋሪ ስለሆነ ከኢትዮጵያ ሲደውል እንቢ እንዳለው ገልፀው እንግዳውን እነሱ ያሉበት እንዳደርስላቸው ጠየቁኝ። አሞት ስለነበር የእህቴም አደራ አለብኝ እና ያለማመንቷት አደረኩት። በተፈጠረው አጋጣሚ ከሀያ ቀን በኋላ ትዕዝን ለሁለተኛ ጊዜ ሳያት ተመለስኩ። አሁን ትዕዝንም አልፌ ስለሄድኩ ስለቦታው እንዳወራችሁ ነው ይህን ሁሉ ማለቴ። አቤት እኔ በቃ ያየሁትን መደበቅ አቃተኝ ማለት ነው?





ከትዕዝ በኋላ በእቅፏ የያዘችን ቶዮታ ካምሪን የሚጠብቃት ለጥ ያለ እና ጠመዝማዛ መንገድ ስለሆነ የሚጠብቃት ብናወራም ትኩረቱ መንገዱ ላይ ነው። ግራ ቀኙ ቁጥቋጦ ስለሆነ የሚያወላዳ አይነት አይደለም። ከቀኑ አስር ሰዓት በኋላ ነው። አየሩ አደብ ገዝቶ ማቃጠሉን ገታ ያደረገበት ጊዜ ስለነበር ሳናርፍ ከትዕዝ 90 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኘው ቱርባ ከተማ ደረስን። ኦሮምኛ ለምታውቁ ሰዎች ማሳሰቢያ ብጤ ትቼ ልለፍ ስያሜዋ ሌላ ትርጉም ስላለው ቱርባ ከተማ የሚለውን አፈር ከተማ ብላችሁ እንዳትተረጉሙት። ከዚህች ከተማ በኋላ 3 ኪሎ ሜትር ተጉዘን ለቅሶው ቦታ ተቀላቀልን። የመን ከመጣሁ ካየኋቸው ቦታዎች ሁሉ የፍቅር መንደር ነች። ከተወለኑት ትውልደ ኢትዮጵያዊ በስተቀር እኔ ብቻ ነኝ ሀበሻ። ልዩ ክብር.. ልዩ ፍቅር ነው ያሳዩኝ። ገጠሩን በሙሉ ዞሬ አየሁ። ከሶስት ቀን ቆይታ በኋላ ሀሙስ ስንመለስ ትዕዝን እንዳለፍን አይኔ ሁለት.. ሁለት እየሆኑ የሚጓዙ ጥቁርቁር ያሉ ልጆች ላይ አረፈ። ቆሻሻ ላስቲክ ይዘው በእግር ያዘግማሉ። ሳያቸው ገና ደሜ መሆናቸውን ደሜ ሲራወጥ አሳበቀልኝ።

ይቁም! እግር ወዲያው ፍሬን ረገጠ። ግን በምን እንግባባ? ኦሮሚኛ ካልሆነ አይሰሙም፣ አይናገሩም። እኔ ደግሞ በመስማት ደረጃ እሞክራለሁ እንጂ እሰማለሁ የሚባል አይነት ዕውቀት የለኝም።

‹‹ቢዬ ኬሰን ኤሳ..›› አልኩ የማውቃትን ያህል ሰባብሬ።

ሙራድ ሳቅ ቢልም አስተካክሎ ነገራቸው። ረስቼው እንጂ የጅማ ልጅ እያለ ያን ያህል ምን አስጨነቀኝ? ዘይገርም ሻሸመኔ ማለት ይሄኔ ነው። ከሙራድ ጋር አንድ ላይ ጅማ ናቸው። እነሱ ወደገጠር ስለሆኑ ነው። ርሃብ ከንፈራቸውን ኩበት አድርጎታል። እኔም ሆንኩ ሙራድ ጥለናቸው መሄድ አልቻልንም። ያለንን ብናካፍላቸውም አላረካንም። ወዴት እንደሚሄዱ ጠየቅናቸው። ረድዓ የምትባለው ቦታ እንደሚሄዱ ነገሩን። እዛ ለገበሬዎች ተቀጥረው ሰርተው ሳንቲም ሲያገኙ ወደ ሳዑዲ ለመሄድ ነው እቅዳቸው። ‹‹እንዴት እዛ ስራ እንዳለ አወቃችሁ?›› የሙራድ ጥያቄ ነበር። የተነገራቸው መሆኑንና እህታቸው ሳዑዲ እንዳለች ገልፀው ሚስኮል እንድናደርግላቸው ጠየቁን።

ውስጤ ቅጥል አለ። መንገዱን ስቃዩን የምታውቅ እህት ሳዑዲ ቁጭ ብላ ነው የጠራቻቸው። ይሄኛውም ጥፋት ሀላፊነት የጎደለው መሆኑን ባውቅም ይህን ስቃይ ያየች ሴት ወንድሟን ለሞት ትጠራለች ብዬ አላስብም። 5 ሰው ሆነን ታክሲዋን ሞልተናት ነበር። የት ላይ እንጫናቸው? ከኋላ እቃ መጫኛውን ከፍተን ውስጤ እያዘነ እንደ ሒቃ ጭነን ወደ 20 ኪሎ ሜትር አካባቢ ወሰድናቸው። ፍተሻ ያለበት ቦታ

ስንደርስ አወረድናቸው። አቅራርጠው እንዲሄዱ ነገርናቸው። ከዚህ በላይ ምንም ማድረግ አንችልም። ጉዞአችንን ወደሰንዓ ቀጠልን። ውስጤ ግን እያሰባቸው ነው።

በትዕዝ ዙሪያ የምለው ብዙ ቢኖርም አላማዬን እንዳያስረሳኝ ለጊዜው በቂ በሚለው ልለፈው። እናም ከትዕዝ በኋላ ወደ አደን ስሄድ በየቦታው ድልድይ ማየቱን አስታውሳለሁ። ግን ውሀ የሚባል የምራቅ ጠብታ ያህል አለመኖሩም ገርሞኛል። ታዲያ ይህን ግርምቱን ቋጥሬ ከምንዝ አልኩና አንዱን ‹‹ወንዝ ነው እንዳይባል ድልድይ ብቻ ነው ውሀ የለውም ለምንድን ነው?›› አልኩት ‹‹..ኢንሽ አላህ አንድ ቀን ሲዘንብ ወንዝ ይሆናል›› ብሎ አሳቀኝ። አደን እስክደርስ የተለየ ነገር የለም። ተራራ፣ የጫት እርሻ ነው። አደን ካየኋቸው ቦታዎች ግን በሳቷን የገረመኝ ነው ስለእሱ ማውጋት ፈለኩ። አደን በመጀመሪያ የገጠመኝ ኢትዮጵያዊ የኔ ቢጤ ነበር።

ሼክ ኮርማክሰር የሚባል ቦታ ነው። ‹‹ነፍሱ በባህር ከመጣሁ ቅርብ ጊዜዬ ነው እባክህ ለዛሬ እራት ላስቸግርህ?...›› ቢለኝም ከእኔ በፊት ባለመኪናውን ሲለምን እያየሁ ስለነበረ አልገረመኝም። ያው በባህር ሲገባ መለመንም ሆነ መኪና ማጠብ... የመሳሰሉት ያለ ነውና አዲስም አልሆነብኝም።

በአንድ ወቅት ጥበቡ የሚባል ልጅ ሰነዓ ከተማ ውስጥ ታዋቂ የሀበሻ ፀጉር ቆራጭ የነበረ አሁን ሀገር ቤት ያለ አናግሬ ነበር። የመን ውስጥ ማሳተም ጀምሬ ለነበረው ‹‹ጣዕም›› የተሰኘ ጋዜጣ ቃለ-ምልልስ ሳደርግለት ‹‹ባሳቷን የደህ ማረፊያ ሳሎን፣ ማገገሚያ፣ ማቋቋሚያ...›› ብሎ የነገረኝን ብዙ ታሪክ አስታወስኩ። ‹‹ማንም በባህር የመጣ የሚያርፍባት፣ በሀምሳ የየመን ሪያል ምሳ የሚበላባት፣ ሀበሻዎችና ሶማሌዎች በልመናም ሆነ በተለያየ ነገር እስኪቋቋሙ የሚከርሙባት...›› ብሎኝ ነበር።

ሲለምን ያየሁትን ልጅ ላወራው ፈለኩ።

እሱ ደግሞ የምሰጠውን ሰጥቼው ወደሌላ ሰው ዞሮ ስራውን ሊያጧጡፍ እንደቸኮለ ከሁኔታው ያሳውቃል። ታዲያ እንደሜትሮሎጂ ግምቱ መሆኑን ልብ በሉልኝ። የአየር ትንበያ ሳይሆን የፍላጎት ትንበያ ቢባልም ያስኬዳል። እራት አብረን እንብላ የሚለው ጥያቄዬን መጠነኛ ግልምጫ በታከለበት ሁኔታ ተቃራኒ መልስ ሰጠኝ።

‹‹ለእኔ እራት የምትከፍለውን ብትሰጠኝ ለነገ ሙሉ ቀን ትብቃቃዋለሁ›› አለኝ። በዶላር የማወጣ ብዙ የምመዝ መስሎት ይሆናል.. እኔም ‹‹..አቅምን አውቆ መኖር ጥሩ ነው ታላቅ ችሎታ ነው..›› የሚለውን ዜማ በውስጤ እያጠነጠንኩ እንደሆነ ማን በነገረው። ቀነስ ያለምግብ እና





መኝታ ያለበት እንዲጠቁመኝ መፈለጌን እኔ ካልነገርኩትስ በምን ያውቃል? እኔም ቀነስ ያለውን ቤት ፈልጌ እንደሆነ እና ለነገውም የሚሆን ልሰጠው እንደምችል በዛውም የሚቀንስ መኝታ ያለበት ሆቴል እንዲያሳየኝ ነገርኩት። ፍልጥ ፍልጥ የሚያክል ባቄላ ያለበት ፉል በላን። ‹‹..ኬሻ በጠረባ አለ እዛ ትደቅላለህ..›› የአሜሪካ ጊቢ ቋንቋ በመሆኗ የአዲስ አበባ ልጅ ይሆን አልኩና ጠየኩት። ትግራይ ሽሬ አካባቢ መሆኑን እና አዲስ አበባ ትራንዚት ሲያደርግ አሜሪካን ግቢ ሁለት ጊዜ እንዳደረ ነገረኝ።

‹‹ታዲያ ኬሻ በጠረባ ያልከው...›› አቤት ፍጥነቱ... ቀልቀል ያለ ፈጣን ምላሽ ሰጠኝ። ‹‹አሀ አልተግባባንም ማለት ነው ‹‹አነ ፈከርት ሙምኪን ትሽቷበናት?›› (ምናልባት ሴቶች ትፈልጋለህ ብዬ አስቤ ነው) አለኝ። አረቢኛ አነጋገሩ የከረመ መሆኑን ያሳብቃል። ለምን ዋሸኝ ስል በውስጤ አልጎመጎምኩ። ቢሆንም ሳልጠይቀው አላለፍኩትም። ደግሞ ለመጠየቅ! ‹‹አረቢኛ እንዴት ለመድክ የመጣሁት በቅርቡ በባህር ነው ብለኸኛል›› አልኩት።

«ወደየመን ስመጣ የመጀመሪያዬ አይደለም። ለሶስተኛ ጊዜ ነው። ወደሳዑዲ እሄድና ስያዝ ዞሬ በዚህ እመለሳለሁ።»

እንዴት አይነት ነገር ነው ይህን ስቃይ እያዩ የሚመላለሱትን ሁሉ አሰብኳቸው። ‹‹ለምን ይሆን የእሳት እራት ያደረገን? መጥፊያችንን ያስወደደን›› ብዬ የጻፍኳት ባለሁለት መስመር ግጥም ትዝ አለችኝ። ወዲያውም ትንሽ አንከስ ሲል አይቼ ለጠየኩት ጥያቄ የሰጠኝ መልስ ‹‹ከዚህ በፊት ስመላለስ ምንም ያልገጠመኝን ዘንድሮ ገና ጉድ ተሰራሁ ገላዬን አጣሁ። ተጫወቱብኝ..›› በቁጭት ራሱን ወዘወዘ እንባው ተንቆረዘዘ። «ገላህን ያጣኸው በምን ሰበብ ነው?›› አልኩት። እጄን አፈፍ አድርጎ ሲይዘኝ ደነገጥኩ። ጎኑ ላይ ወስዶ አስዳበሰኝ። ያበጠ ነገር ለመኖሩ አልተጠራጠርኩም። ግን ምን ሊያስረዳኝ እንደፈለገ አልገባኝም። አስደንጋጩን ዜና ያሰማኝ ግን እንዳልገባኝ ከነገርኩት በኋላ ነው። ‹‹ኩላሊቴን የተሰረኩ ጎዶሎ ሆኛለሁ እንደልብ አልንቀሳቀስም›› አለኝ።

ሰውነቱ ተብረከረከ። ፈራሁ ለእሱ አይደለም ለራሴ ነው የፈራሁት። ሳላስበው በስሜት ተውጬ የራሴን ኩላሊት አካባቢ ዳበስኩ። ተመስገን!!!.. አለ።

ከእዛ አካባቢ ቶሎ መሄድ አስቤያለሁ። የመን ከገባሁ ጀምሮ እንደዛን ቀን ፈርቼ አላውቅም። ይበልጥ መስማትና ማወቅ ፈለኩ። «እንዴት ሰረቁህ?» አልኩት መንተባተብ እና ፍርሃት በታከለበት ድምጸት።

የተሰረቀበት አካባቢ እዛው ሔደን ከሆነ ተሳስቼ ወደዛ ቦታ እንዳልሄድም ነው ለማወቅ የፈለኩት፡፡

ከባህር እንደወረድን ሀረጥ ድረስ እናደርሳችኋለን ሲሉ እውነት መስሎን ተሳፈርን ሶስት ነን፡፡ መሀል ላይ አቁመው አወረዱን፡፡ ገንዘብ አምጡ አሉን፡፡ የለንም ነበረና ታሰርን፡፡ የሚገርመው ሁላችንም ታመምን ምን እንደሰጡን አናውቅም በኋላ ራሴን ያገኘሁት ወደ አደን ከተማ መግቢያ አንድ ኪሎ ሜትር ሲቀረው ያለ ቦታ ነው፡፡ የሆነ ዛፍ ስር አድርገውኝ... ራሴን እንድመግብ ነው መሰለኝ አጠገቤ ምግብ አስቀምጠው ሄደዋል፡፡ ስነቃ ርቦኝ ስለነበር ጥርግ አድርጌ በላሁ፡፡ ከምን ያህል ሰዓት በኋላ ወይም ከስንት ቀን በኋላ ራሴን እንዳወኩ አላወኩም፡፡..›› እንባ ተናንቆት ንግግሩ ተቋረጠ፡፡

ምን ማለት እንዳለብኝ ግራ ገባኝ ሆድ ብሶኝ የተናነቀኝን እንባ ለቅቄ ቁስሉን ቀስቅሼ ሆድ እንዳላስብሰው ፈለኩ እና ርዕስ ለማስለወጥ ‹‹ቅድም ሴቶች ከፈለክ ብዬ ነው ያልከኝ በገንዘብ የሚሰሩ ሴቶች አሉ እንዴ?›› አልኩ፡፡ እግዚአብሄር ይስጠው ልብ ሳይለው ለጠየኩት ምላሽ ሰጠኝ፡፡

‹‹በሳቲን በሁለት መቶ፣ በሶስት መቶ፣ እስከ አምስት መቶ የሚሰሩ አሉ፡፡ ታዲያ አዳር ሙሉ አይደለም፡፡ ቀምሰህ ወደ ምትተኛበት አንዱ ጥግ ሄደህ መደቀስ ነው፡፡ ተረኛው ደግሞ...›› የሚሰሩት ሶማሊያዊያን እና ኢትዮጵያዊያን እንደሆኑ ነገረኝ፡፡ ኀበዝ ልብ በሉ ይሄ የተጠራው ብር እዛው በሳቲን ውስጥ ካልሆነ ከዛ ክልል ውጭ ምሳ እንኳን የሚገዛ አይደለም፡፡ ታዲያ ምን ያህል ቢቸግር ነው ስደት ተወጥቶ ገላን ቁርስ እንኳን በማያበላ ሳንቲም መሸቀጡ፡፡ በሳቲን የተባለው ቦታን ለማየት የነበረኝ ጉጉት በእጥፍ ጨመረ፡፡ እንደ ሰባተኛ በዝቅተኛ ሳንቲም የሚቸረቸረው ሰውነት ግን አምሮኝ አይደለም፡፡ ወገኔ በስደት አለም የሚኖረውን ኑሮ ማየት.. ለእለት ጉርስ በማይሆን ገንዘብ ገላን የሚሸቅጡበትን ህይወት ማየት ነበር ሀሳቤ፡፡ በማግስቱ ያየሁት ነገር ግን በጣም ተስፋ የሚያስቆርጥ ሆኖ አገኘሁት፡፡

ስለበሳቲን አቆራቆር ለማጣራት ሞከርኩ፡፡ በUNHCR ነው የተቆረቆረው፡፡ ስደተኞች ለማሳረፊያ ነው ከየመን መንግስት የተረከበው፡፡ ሶማሊያ እርስ በእርስ ጦርነት መናወጥ በጀመረችበት ወቅት በርካታ ስደተኛ ሶማሊያዊያን አርፈውበት ነበር፡፡ አሁን ግን ሶማሊያዊያን ብቻ አይደሉም ያሉበት፡፡ ኢትዮጵያዊያን ኑሮን መቋቋም ያቃታቸው የመናዊያንም አሉበት፡፡ ላየው ጓጉቼ አልቀረሁም፡፡ በጠዋት ካደርኩበት ኮርማክሰር ሻባት የተባለ ቦታ ተነሳሁ፡፡ በነገራችን ላይ ኮርማክሰር ሻባት ማንኛውም ሀበሻ እና ሶማሊያዊያን ከባህር እንደወረደ የሚያርፍበት መኪና ማጠብ የሚጀምርበት





ቦታ ነው፡፡ በባህር አደን ብቅ ያለ ኮርማክሰር ሻባት የሚባለው አካባቢ ያላረፈ፣ ጎኑን ካርቶን ላይ ያላሳረፈ የለም፡፡ በቡሌዋ(ትርፍ፡ራፊ) የተጎዳ ጎኑን ያልጠገነ አይኖርም፡፡ ሻባት ሜዳ አለው፡፡ መኪና በብዛት ይቆምበታል፡፡ እዚህ አካባቢ ማንኛውም ስደተኛ መኖር ይችላል፡፡ መጥቶ ሻባት የገባ ቀን መኪና ጠርጎ የሚበላበት ቦታ ነው፡፡ ሶማሊያውያንም አሉበት፡፡ ወንዶቹ መኪና ይጠርጋሉ ሴቶቹ ግን ከመለመን ውጭ በፍጹም ሌላ ስራ አይሞክሩም፡፡

እንግዳ ለሆነ ሀበሻ ልጥረገው ‹‹መሳ›› ትላለህ፡፡ ልጠበው ‹‹ልቀስሉ›› ትላለህ ይባላል፡፡ ይህችን ሁለት ቃል ያጠናና ወዲያው ጨርቅ ተሰጥቶት ወደስራ ይገባል.. አሉኝ ስለ ቦታው የጠየኳቸው፡፡ ኮርማክሰር ሻባት ለስደተኛው እናት ነች ይሉዋታል፡፡ ለእኔ ግን ችግር ሆናብኛለች፡፡ ምክንያቱም ሆቴል ውስጥ አልጋ ይዞ መተኛት አልቻልኩም፡፡ ሆቴሎች መታወቂያዬን ያዩና ኢትዮጵያዊ ስለሆንክ አይቻልም ይሉኛል፡፡ ለምንድን ነው ለኢትዮጵያዊ የማይፈቀደው? ጠየኩ፡፡ በUNHCR ወረቀት በወቅቱ ባለው ችግር ምክንያት ነው ይሉኛል፡፡ ምክንያቱ ግን እሱ አልመሰለኝም፡፡ አደን ማደሪያ ስለሚያስቸግር ይቀበሉሀል ብለው ስልክ ቁጥራቸውን የሰጡኝ ቶፊቅ የሚባል ልጅ እና አሊ ሀበሽ የሚባል ሰው ነበሩ፡፡

አሊ ሀበሽ በባህር ተሻግሮ አደን የገባ ሁሉ ያውቀዋል፡፡ የሚገርመው ነገር ገና ሶማሊያ እያለሁ ስለሱ ደግነት ሰምቻለሁ፡፡ የመናዊ ዜግነት ያለው የኤርትራ አፋር ነው፡፡ ቤቱን ማንም ማደሪያ የፈለገ ሰው ያድርበታል፡፡ ወደ ሳዑዲ በህገ-ወጥ መንገድ አመላላሽ ቢሆንም የስራቤትን ለማንም ያበላል፡፡ ባህር ለተሻገረ ትኩስ ስደተኛ ሲያበላ የኖረ ነው፡፡ የፈለገ በደግነቱ ቢነሳ እሱ ጋ ሄዶ ማደሩን ያልፈለኩት በህገ-ወጥ ካጓጓዘበት የወገኔ ደም ላይ ድርሻ ዘግኜ ላለመስተናገድ ነው፡፡ ለቶፊቅ ሁለቴ ብደውልለትም ስራ ቦታ ሆኖ መምጣት አልቻለም፡፡ ሼክ ብለህ ተሳፈር እና እዛ መኝታ ታገኛለህ አለኝ፡፡

መጨነቄን ያየ አንድ አዲስ ከባህር የወረደ ልጅ ‹‹ለምን ከእኛ ጋር አትተኛም?›› አለኝ፡፡ ካርቶኑን ሊያጋራኝ መፍቀዱ ደስ ብሎኛል፡፡ ለመጎብኘት ሄጄ ማደሪያ በማጣት ካርቶን ላይ መተኛቴ ባለካርቶኑ ቱሪስት ያሰኘኝ እንደሆን እንጂ እኔስ ለመተኛት ችግር የለብኝም፡፡ ማንኛውንም ነገር እንዳመጣጡ መቀበል ለምጃለሁ፡፡ እድሜ ለስደት፡፡ ስልክ ደጋግሜ ስደውል መጨነቄን የሚመለከት ሌላም ልጅ ነበር፡፡ ‹‹ወደሼክ የሚሄድ ታክሲ የማገኘው የት ነው?›› አልኩት፡፡ ዘይኑ ይባላል፡፡ ምን እንደምፈልግ ጠየቀኝ እና ነገርኩት፡፡ ‹‹ኧረ ማደሪያማ ፍለጋ አትንከራተትም፡፡ እኔ ቤት እደር›› አለና ገላገለኝ፡፡ አላመነታሁም፡፡ ተከትዬው ሄድኩ፡፡ ጠዋት መልሶ

ኮርማክሰር ሻባት የሚባለው ቦታ አደረሰኝ። ከዛ ወደበሳቲን ለመሄድ የሚያግዘኝን ታክሲ አሲዘኝ አልኩት።

‹‹አታውቀውም አይደል ላድርስህ?›› አለኝ። ይሄኛው ሀሳብ የተቀደሰ ብቸኝነቴን የሚቀርፍም ነውና ደስ አለኝ። ሼክ የሚባለው ቦታ ድረስ በታክሲ ከዛ ደግሞ መትት ባለክፍትፍት መኪና (ኮስተር የሚሉት) በሳቲን ድረስ ሄድን። ከታች ክፍት ሆኖ አቧራ ይገባል። እንደምንም አቧራውን እየታጠንን ሄድን። የስደትን አስከፊ ኑሮ ለመግፋት የሚኖሩበት ሰፈር አስጠሊታነቱን ገና ከውጭ ተረዳሁት።

ለአይን የሚስብ ምንም ነገር የሌለበት ውትፍትፍ በብሎኬት የተገነቡ ልስን የሌላቸው ክፍትፍት ቤቶች ናቸው ያጋጠሙኝ። መጀመሪያ ድሪያ የሚሰሩ ሶማሌዎችን ነው በብዛት ያየሁት። የማይሰፉት አይነት የለም። ትኩስ አሳ ገበያው ላይ በብዛት ተዘርግቶ ዝንብ ከቦታል። ትኩስነቱን ለማጥፋት እነሱም የድርሻቸውን ልሰውት (ቀስመውት) ሲተርፋቸው ነው የሚሸጠው ማለት ይቻላል። ‹‹እሽ!!..›› ተብለው በቅጠል ካልተባረሩ አሳውን ማየት አይቻልም። ለጥምቀት ጃንሜዳ ሄደን ከበው ሲጨፍሩ ጨፋሪውን ለማየት ተቸግረን እንደምንጠራራው፣ እንደ ምንታገለው ሁሉ እዚህም ዝንቦቹን ታግለን አባረን ካልሆነ አሳው አይታይም። ዝንቦቹ ጠዋት አሳውን ከበው ይውላሉ። ከሰዓት በኂላ አሳውን በልቶ ጫት ሊገዛ የመጣውን ከበው እዛው ቦታ ላይ ሲያቢችሩ ይውላሉ። ቦታው ላይ ጠዋት እስከ ስድስት ሰዓት አሳ ይሸጥበታል። ከሰዓት ደግሞ ጫት በቦታው ይተካል። ምግብ ለደሀው ስደተኛ በጣም በርካሽ አለ። ሌላ ቦታ በ200 ሪያል የሚሸጠው ሩዝ በ100 ሪያል፣ ከሆቴል ቤቶች ተርፎ የተመለሰ ከሆነ ደግሞ በ50 ሪያል ይገኛል። በሳቲን ጦም አይታደርም የሚሉትም ለዚህ መሰለኝ።

አሚሪካን ጊቢ ኪሻ በጠረባ የሚባለው አይነት መኝታ ቤቶች አሉ። ያውም ከነትኋኑ፣ ተባዩ...መሬት ተደርድረው መተኛት..ለነገሩ ቤት ውስጥ አደርክ ውጭ ምን ለውጥ አለው? ቤቱም ከውጭው የማይሻል ክፍትፍት ነው። በዛ ላይ ሙቀት ስለሆነ ራቁት ነው የሚታደረው። ..ይሞላልኛል ብለው ተሰደው አልሆን ብሏቸው ገላቸውን በርካሽ ሸጠው የሚያድሩ ስጋ አደሮችም (ጭን አደሮች) አሉ። አብዛኛዎቹ አሳዛኝ የሆነ ፊት እና የልመና አስተያየት አላቸው። ገላቸውን የሚሸጡ ሳይሆን ምጽዋት የሚጠይቁ ነው የሚመስሉት። ይሄም ኑሮ ሆኖ ገበያ አጥተው ጦም ላለማደር የልመና ያህል መቁለጭለጭ...ማንም ይህን ትእይንት የሚያይ ሊሰማው የሚችለውን ያህል አዝኜ ቅኝቴን ቀጠልኩ።

ገና በጠዋቱ ካርታ መጫወቻ ቦታዎች ይሞላሉ። አብሮኝ ያለው ወዳጄ ‹‹ካርታ መጫዎቻውን ማየት ትፈልጋለህ?›› አለኝ። አባባሉ ሌላ





ውስጠ ወይራ ነገር ይኖረው ይሆን ብዬ አገላብጬ አጤንኩት። የምን ካርታ ነው? አልኩት። ‹‹ፋራ!›› የሚል ቅኝት ያለው እይታ ይመስላል አስተያየቱ። ራሱን እንደ አራዳ ያየም መሰለኝ።

‹‹እንዴት ካርታ አታውቅም? ቁማር ጨዋታ አልሞከርክም?..›› አለኝ። አላውቅምም አውቃለሁም አላልኩትም። እሱ ግን ቀጠለ። ‹‹..ካርታ ስትጫወት ከበላህ ወደ ውስጥ ያስገቡሀል ካላሸነፍክ፣ ከተበላህ ምን ልትሰራ ትገባለህ። እነሱም አያስገቡህም። ወደውስጥ ከገባህ ሴት አለ። ተዘጋጅታ ተዘርግታ ትጠብቅሀለች..›› አለኝ።

‹‹ካርታ ካልተጫወትክ ቀጥታ ሴቶቹ ጋር መግባት አትችልም?›› አልኩት።

‹‹ኧረ! ትችላለህ እነሱ በር ላይ ቆመው ይጠሩሀል እኮ አሁን ጠዋት ስለሆነ ነው የሌሉት። በዛ ላይ ካርታ መጫወት ቻልክ አልቻልክ ከፈለክ ቀጥታ መግባት ትችላለህ።››

ጠለቅ ብሎ የሚያውቀው መሰለኝ። ደንበኛ ይኖረው እንደሆን ጠየኩት። ‹‹ኧረ!..›› አንገፈገፈው። ‹‹ምነው ሚስቱን አይተሀታል አይደል እሷ ካለች ምን ልሰራ እመጣለሁ?››

ስህተት ማሰቤ ስህተት አናገረኝ። ቤቱ ሲያሳድረኝ አይቻለሁ ሚስቱን። በስህተቴ ራሴን ወቀስኩ። እስካሁን ባየሁት ኢትዮጵያዊያን፣ ሶማሊያዊያንና የመናዊያን በቦታው ይተራመሳሉ። ‹‹እስኪ አንዱ ጋ እንግባ›› አልኩት። ገባን። ያደረ ይሁን የጠዋት የመጠጥ ጠረን አለ።

እንደገባን ምን እንደምንፈልግ በአይን ጠየቁን። ዞሬ እሱን ከማየት በስተቀር ምን ማለት እንዳለብኝ ግራ ተጋባሁ። ራቅ ብለው ተቀመጡት አረቂ እንደሚጠጡ ሽታው ነግሮኛል። አፌ እንዳመጣ የሚጠጣ ስል ‹‹በለዲ ወይስ..›› ምንድን ነው በለዲ የሚል ጥያቄ አብሮኝ ላለው ዘይኑ አቀረብኩ። ‹‹እዚሁ የሚሰራ ነው። የሀገር ውስጥ ስራ ማለት ነው ከፈለክ ጠላም አለ። ግን ጠላው ይሻላል። በለዲው እኮ በጣም መጥፎ ነው። ደም ያስተፋሀል። መጠኑ ይነስ እንጂ በረኪና ሁሉ አለው።..››

ጠላውን አዘዝን። በቴምር ነው የሚጠመቀው ስለተባለ ሁለቴ ፉት አልኩለት። ቀረቦ ቀረቦ ይላል። ግን እርሾ እንደ ጌሾ ስለተጠቀሙ ልብ ይፍቃል። ልብ የሚፍቅ ሌላው የገጠመኝ ደግሞ... [illegible] የማትበልጥ ቀይ ደስ የሚል ፈገግታ ያላት ልጅ ብቅ አለች። ጥርሷን አሟት ያደረች ትመስላለች። አዳር ስትቅም ቆይታ ይሁን ኢጃባና እንደሚበለው በጠዋቱ ከረሜላ የያዘች ያስመሰላት ጫት በትንሹ

ወጥራለች። አብሮኝ ያለው ዘይኑን እንዳየችው ስሙን ጠርታ «ሳንቲሜን አምጣ በዛው ጠፍተህ ዛሬ የምትመጣው 300 ሪያል እንዳለብህ ትረሳዋለች ብለህ ነው?..» አለችው። ዘይኑ[13] አፈረኝ። ሚስት አለኝ ምን አስራለሁ? ብሎ ሲያፈጥብኝ ተሳስቻለሁ ብዬ ራሴን የወቀስኩት ታወሰኝ። የለኝም ሲላት «የእናትህ እንትን መሰለህ በዱቤ ጠልዘህ የምትጠፋው አምጣ» ብላ ብዙ ሰደበችው። ልክፍልለት ስል ወደ እኔም ዞራ ከናዝሬት በታች ባሉ ልጆች ጥርስ አይነት የወየበ ፈገግታ ለግሳኝ «ለቦታው አዲስ ነህ መሰለኝ ከዚህ አይነቱ ጋር.».ብላ ጸያፍ ስድብ አቀበለችው። ሌላም ጠይም ግፋ ቢል ከ25 አመት የማትበልጥ ጉስቁልና የተጫወተባት ልጅ እግር ወጣች። የእሷ ጎልቶ ፊቷ ላይ ስለታየ ጉስቁልናዋን ተናገርኩ እንጂ በዚህ አስጠሊታ የስደት ጎዳና ያልቀመሰው አለ?.. ስንቸገር አድረን በጠዋት ተነፈስ ልንል የመጣን መስሏቸው መሰለኝ ሌሎችም ቀስ ቀስ እያሉ ወጡ።

ጠላውን ባልጠጣውም ሂሳቡን ከፍለን ወጣን። በርካታ ህጻናትን ማየቱም ቁጭራ ሰፈርን በየመኗ አደን ልንመሰርት የምንታገል ያስመስለናል።

እንጀራ ጉልት ተቀምጠው የሚሸጡ አሉ። እንጀራ በወጥ ግማሽ እና ሙሉ ተብሎ ይሸጣል። ሽልጦም(ጢቢኛም) በሚጥሚጣ ሲሸጥ አይቻለሁ። ሀገሬ ያለሁ ሁሉ መስሎኛል። የቀን ሰራተኞች በሚጥሚጣ ሲበሉ አይቼ ስለማውቅ። መደዳውን የተሰለፉ ጽዳት የጎደላቸው መቃሚያ ቤቶች አሉ።

ሺሻ ይጨስባቸዋል፣ በዚሁ ኑሮ ሀሺሽም የሚያጨስ አለ።
ይጠጣል
ይዘሞትባቸዋል
ይቆመርባቸዋል። የህይወት ዝቃጭዋን ለመኖር ህይወትን ሽጦ ባህር ተሻግሮ መሰደድ አስከፊ ከሚባለውም በላይ ነው። ከዚህ የተሻለ ህይወት ሀገር ላይ ታጥቶ ይሆን?

[13] ለዚህ ታሪክ ስል ትዳሩ ላይ ችግር ላለመፍጠር አንድ ቀን በስደን ያሳደረኝ፣ መንገድ ላይ ከማደር ያዳነኝ ወዳጄን ስም ቀይሬ ዘይኑ ያልኩት ትክክለኛ ስሙ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ።





# - 15 -

# በ UNHCR ቢሮ በር ላይ የተፈፀመ ግፍ

ከመኖሩ ተርታ ከተደመረልኝ
ከህይወቱ ተርታ ከተመደበልኝ
ለእኔ ግን የለሁም ለእናንተ አለሁ
ለአይን ታይቼ እንጠራወዛለሁ

እዚህ ጋር ቆም ብለን ለደቂቃ እናስብ። አጣጥመህ ስደት እንዲህ ነው ብለህ ወስነህ እንድትወጣ አሁንም በስደት የስቃይ ገፈት ከቀመሱት ውስጥ አንድ ታሪክ ላቋድስህ ነው። ኡስማን አብዱ ይባላል። የመን በስደት ሰንበት ብሏል። በUNHCR ቢሮ ተመዝግቦ ማሟላት ያለበትን አሟልቶ የስደተኛነት ማረጋገጫውን /Refugee Mandate/ ወስዷል። ሚስቱ እና ሁለት ልጆቹ ታፍነው ወደ ሶማሊያ ተወሰዱ። «Refugee Mandate ቢሮው ሰጥቶኝ ሳለ እንዴት ይህ በደል ይፈጸምብናል?» ይላሉ። «...ቢሮውን ለደረሰብን በደል መፍትሄ ይሰጠን..» ብለው ይጠይቃሉ።

UNHCR በር ላይ ለአራት ወር የተቀመጡት ባልና ሚስት ለደረሰባቸው በደል የተሰጣቸው መፍትሄ በፖሊስ ድብደባ እንዲነሱ ማድረግ ነው። በዚህን ሰዓት ግን በድብደባው ኢፍቱ የ5 ወር እርጉዝ ነበረችና አስወርዳለች። ይህን ቃለ-ምልልስ ሳደርግ እሷ በጥሩ ጤንነት ላይ ባለመሆኗ ከባለቤቷ ኡስማን አብዱ ፊቶ ጋር ብቻ ነበር ያወራነው። ኡስማን ሙሉ ለሙሉ አማርኛ ስለማይችል በአስተርጓሚ ነው የተግባባነው። እንዲህም ያለ ግፍ አለ ወይ? ያሰኛል።

በመጀመሪያ ያቀረብኩለት ጥያቄ ‹‹እኔ እዚህ ሀገር እንደመጣሁ ጅዋዛት(ማግሬሽን) እስር ቤት እያለሁ ታስረህ መጥተህ ነበር። በዛን ጊዜ ኢትዮጵያ እያለህ ዝዋይ ታስረህ እንደነበር ነግረኸኛል በምን ምክንያት ነበር የታሰርከው?..›› የሚል ነበር።

እኔ የባሌ ክፍለ ሀገር መዳ ወላቡ ልጅ ነኝ። ያኔ እኔ ብቻዬን አይደለም የታሰርኩት። የአነግ ደጋፊ ናችሁ ተብለን ብዙ ሆነን ነበር ዝዋይ ዲሴት ላይ የታሰርነው። ብዙዎቻችን ከዚያ በፊት አማሬሳ ለአንድ ዓመት ታስረናል። ዝዋይ ተሸጋግረን 3 አመት ከታሰርን በኋላ ፍ/ቤት አቆሙን። ተፈታን።

በሶስት አመት ውስጥ የነበረው ሁኔታ እንዴት ነው? ቀይ መስቀልስ አልጎበኛችሁም? የሚል ጥያቄ ሳቀርብለት ቅር እያለው ‹‹..ቀይ መስቀል መጥቶ ጠይቆናል። መዝግቦናል። የነበረውን ስቃይ ዛሬ ባወራው ለማመን ይከብድሀል። ማስታወስ ያስጠላል›› ሲለኝ እኔም ማስጨነቅ አልፈልኩም። ቀጣዩን የሚነግረኝን ታሪክ መጠበቅ ጀመርኩ።

በኋላ እንዴት ወጣን መሰለህ? በ1993 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተነስቶ.. የተማሪዎች አመጽ በመላ ሀገሪቱ ሲቀጣጠል እኛ ተለቀቅን። በታው አደገኛ በዘኔዎች ለተባሉት እና ለሌሎቹ አመጹን ያቀጣጠሉ ወጣቶች መቀጫ ስላስፈለገ ተፈታን። ያኔ ቀይ መስቀል ሲጎበኙን መዝግበውን ስለነበሬ ወደ አዲስ አበባ ሄድን። በምዝገባው መሰረት ወረቀት ጻፉልን። ወደ ቤተሰብም ከተቀላቀልን በኋላ መቀመጥ አልቻልንም። በትልቁም በትንሹም ይተናኮሉን ጀመር። የተሰጠን ስም በአካባቢው ጥሩ እይታ ስላልፈጠሬ አላኖረንም። ህዝቡም ተጠራጠረን። ሀገር ለቅቄ ወደ ሶማሊያ ገባሁ። ሶማሊያ ውስጥ የሚቀመጡ ሰላዮች አሉ ተባልን።[14]

እነሱን ፍርሃትም ጥንቃቄም አርገን አንችላቸውም ብለን አብረውኝ ከነበሩት ጋር ተመካከርን። ሶማሊያ መኖር አልቻልንም። ያለን አማራጭ ወደ የመን መሻገር ነውና በባህር ተሻገርን። ለኢትዮጵያዊያን ሶማሊያ መኖር አስቸጋሪ ነው። ኑሮው ይከብዳል። ከሀገርህ ያልተሻለ ሀገር ላይ መኖር ነጻነት ፍለጋ እንደሆነ እኔም አንተም ሌላውም..ሁላችንም እናውቀዋለን። አንተስ ብትሆን በዛው ነው የመጣኸው ኑሮውን እንዴት ገፋኸው? ሶማሊያ በነበርክ ሰዓት ብዙ ችግር ሲገጥምህ ወይም ሰዎች ሲገጥማቸው ልታይ እንደ ምትችል እገምታለሁ። እንዴት ነበር?..(ጎበዝ እኔኑ በጥያቄ አጣደፈኝ። በአጭሩ ነገሬ ወደ እሱ ታሪክ ገባን። ለእናንተ እንዳልደግመው አልፌዋለሁ።)

[14] ይህን ወሬ ደላላዎች ሰዉን እያዋከቡ ለመውሰድም በብዛት ይጠቀሙበታል ውሸት ነው እውነት ነው ለማለት ግን መረጃ አላገኘሁም።





ሶማሊያ ውስጥ በጣም..በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ነው። ሬሳ በየመንገዱ ተጋድሞ ነበር። የእኛን ሴቶች እየደፈሩ...መናገሩ ያሳፍራል። ከሴቶች አልፈው ወንድ ሁሉ እየደፈሩ ታያለህ። ለሁለት ለሶስት ሆነው ይደፍራሉ። ተርበን..ተደብድበን በግፍ ተጭነን ነው የባህር ጉዞ የጀመርነው። ጀልባዋ ላይ የሚሰሩት 3 ሶማሌዎች ጠጥተው ሰክረው በዱላ ጭንቅላት.. ጭንቅላታችንን እያሉ ያሰኛቸውን ወደ ባህር እየወረወሩ ተሰቃይተን ነው በአውሮፓ 2003 ዓ.ም የየመንን መሬት የረገጥነው።

የየመንን መሬት ከረገጥኩ በኋላ ለአንድ አመት አል-ቀረስ የተባለው ካምፕ ውስጥ ቆየሁ። ቀይ መስቀል የሰጠኝን ወረቀት አሳይቼ ቆይ መፍትሄ ይሰጥሀል እየተባልኩ ምንም መፍትሄ ሳይሰጠኝ አንድ አመት አል-ቀረስ ተቀመጥኩ። ከዛ ጠፍቼ ወደ ሰነዓ መጣሁ። አንድ ወር እንደሞላኝ ከምተኛበት በረንዳ ላይ ያዙኝና ጅዋዛት /ኢሚግሬሽን እስር ቤት/ ወሰዱኝ።»

«ይሄ ማለት በ2005 መጨረሻ አካባቢ እኔና አንተ እስር ቤት በተገናኘን ጊዜ ነው መሰለኝ? አስታውሳለሁ ስትመጣ በጣም ርቦህ ምግብ ነበር የፈለከው» አልኩት በመሀል

አዎ!..ያኔ አንተ ጣራው ክፍት ብረት ሆኖ ተሰርቶ ለጸሀይ መሞቂያ ተብሎ በተሰራው ውስጥ ነበርክ..እኔ ግን የነበርኩበት ቦታ በጣም ችግር ነው። ለቀይ መስቀል ብንጮህ ትንሽ አገዙን እንጂ UNHCR ዝም ነው ያለን። ከእስር እንደ ወጣሁ UNHCR ስሄድ እምቢ አሉን። ቀይ መስቀል ሁለት ጊዜ ደብዳቤ ጽፈው ሰጡን። በዚህ ምክንያት ተቀበሉኝ።

‹‹እርግጠኛ ባልሆንም እስር ቤት ከተገናኘን በኋላ ነው አግብተህ የወለድከው። ጎበዝ ነህ ፈጠን ብለህ ሁለት ልጅም አድርሰሀል። ከዛ በኋላ የልጆችህ እናት ኢፍቱ ታስራ ወደ ሶማሊያ የተወሰደችበት ሁኔታ ነበር። እንዴት ወደ ሱማሊያ ወሰዷት?» በመሀል የወረወርኩት ጥያቄ ነው።

‹‹አማርኛ ከእኔ የባሰ አትችልም። ሶማሌ ነሽ አሉና ወደዛ አሳፈሯት። እሷ ሳትሄድ (ሳትጠረዝ) በፊት እኔ ሶስቴ ታስሬ ነበር። ሶስት ጊዜም በብር አስፈታችኝ። ስራም አጣሁ በአጋጣሚ ከእሷ ጋርም በትንሽ ነገር ተጋጨን። ተለያየንና ሌላ ቦታ መኖር ጀመርኩ። በዚህ ወቅት ነው ለአንቺ ስራ አገኘንልሽ እናስገባሽ ያሏት። እስከ 9 ሰዓት በመቶ ዶላር እሰራለሁ አለቻቸው። ከዛ በተሻለ እናስገባሽ ብለው አስቸገሯት። ስራ ስትሆን ልጆቹን የምታስቀምጥበት ጠባቂዎች አሉ። ከስራ ስትወጣ ከእነሱ ጋር ልታመጣ ስትሄድ እዛ ጠበቋት። ስራ እናስገባሽ ብለው ካናገሯት ውስጥ አንዱ እና ሁለት ፖሊሶች ናቸው። ከነልጆቿ መኪና ላይ አስወጧት። እስር

ቤት ወሰዷት:: ከዛ ተጫወቱባት:: ደፈሯት..አንገላቷት...ደሟን እያዘራች ፖሊስ ጣቢያ ወሰዷት:: ከተወሰነ ቀን በኋላ መታሰሯን ሰማሁ:: የት እንዳለች ሳፈላልግ አንቺ ኢትዮጵያዊ አይደለሽም ሱማሌ ነሽ ብለው ወደ በርበራ ወደብ አሳፍረዋታል ተባልኩ:: የማደርገው ጠፋኝ:: እሷ ግን ከበርበራ ወደብ ወደ ሃርጌሳ UNHCR ቢሮ ሄዳ የገጠማትን ብትናገር እኛን አይመለከተንም ይሄ መታወቂያ እዚህ አይሰራም:: የመን ሄደሽ አመልክቺ አሏት:: ያላት አማራጭ ከሁለት ልጆቿ ጋር ወደ ቦሳሶ መሄድ ስለሆነ ሄደች:: የማደርገው አጣሁ:: በየፖሊስ ጣቢያው እያስፈለኳት እያለ ነው ይህን የሰማሁት። በሌላ በኩል UN እና ቀይ መስቀል ለመልከቻለሁ:: ወረቀትም አስገብቻለሁ:: ሁለቱም ልጆቼ አብረዋት ነው ወደ ሱማሊያ የተወሰዱት:: የመጀመሪያው ልጁ 2 አመት ከ6 ወር ሁለተኛው 1 አመት ከ5 ወር ነው:: ከሀርጌሳ ወደ ቦሳሶ እንደገባች ታማ ወደቀች:: ሲያነሷት መታወቂያዋን ሲያዩ አጋጣሚ አንድ የሚያውቃት ሰው አገኛት:: እሱም ለእኔ ወደ የመን ደወለልኝ:: በዚህን ጊዜ ነው ሱማሊያ ውስጥ ያለችበትን ሁኔታ በትክክል ያወኩት:: ወዲያው ቀይ መስቀል ገብቼ ሱማሊያ ቦሳሶ መሆኗን አሳወኩኝ:: እነሱም ቦሳሶ ወዳለው ቀይ መስቀል ተደዋወሉ:: UN ግን አያገባንም አሉኝ::

እዛ ያለው ቀይ መስቀል በረዳት ብር ጤንነቷ መለስ ሲል ወደ የመን ለመሻገር ጀልባ ላይ ከሁለት ልጆቿ ጋር ወጣች:: ማዕበል ተነስቶ አቅጣጫቸውን ስላስቀየራቸው ላንድ ሳምንት ባህር ላይ እንድትቆይ ተገደደች:: ማዕበሉ ከቆመም በኋላ ጉዞ ሲጀመሩ ያሉበትን አውቀው መንገዳቸውን እስኪያስተካክሉ ብዙ ሰው ከ54 ሰው በላይ አልቀዋል:: የእግዚአብሄር ነገር ከነልጆቿ ተረፈች:: ቀይ መስቀል ነግሬ ስለነበር እነሱ ባህሩ ድረስ ሄደው ተቀበሏት:: እሷ ራሷን ስታ ወድቃ ልጆቹ ተኝተው አገኙዋቸው:: ያ-ሁሉ ሰው ሲያልቅ ህጻናቱ በመትረፋቸው ደስ አለኝ። ሌላስ የጤና ችግር ገጥሟቸው ይሆን? የሚለው አሳቤ ስንቅር ሲልብኝ ‹‹በልጆቹ ላይ የደረሰ ነገር የለም?›› ስል ጠየኩት።

‹‹እስከ አሁን በጤንነታቸው ላይ የደረሰ ነገር ወይም የተፈጠረ ችግር የለም:: አልሀምዲሊላሂ›› እጆቹን ወደ ፈጣሪው ዘረጋና ምስጋና ነገር አልጎመጎመ - ወጥቶ የማይሰማ እሱና ፈጣሪው መሀል ያለ ንግግር። በእርግጥ እድለኛም እድለ ቢስም ሆኖ ነው ያገኘሁት። ቀይ መስቀል ከሚገባው በላይ ረድተውታል። ቀጠለ... ‹‹ቀጥታ ወደ ሳኡዲ ጀርመን ሆስፒታል ወስደው ለ1 አመት ነጻ ህክምና ባጀት አወጡና አሳከሟት:: የሚያሳዝነው ግን UNHCR ትብብር ሊያደርግላት አልቻለም:: አልፈለገም:: ይህ ሰብዓዊነት የጎደለው መድሎ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ላይ የሚፈጸም በመሆኑ ታውቀዋለህ? ሁሉም ያውቀዋል:: ከባህር ከወጣች ጀምሮ ለ4 ወር ያህል በተከታታይ ወረቀት ብናስገባ ምንም መፍትሄ ሊሰጡን አልቻሉም::





ከዚህ በላይ ምን ችግር አለ? መፍትሄ ስጡኝ ብላ እዛው UNHCR መግቢያ በር ላይ ተቀመጠች:: መፍትሄ ካልተሰጠኝ አልነሳም ብላ በቆርቆሮ በካርቶን መጠለያ ሰርታ 3 ወራት ብትቀመጥም ዞር ብለው ሊያዩዋት አልፈለጉም::››

አሁን እሱ ሲያነሳው ያስታውስኩት ነገር ሚስቱ UNHCR በር ላይ ስትቀመጥ ከሁለት ልጆችዋ ጋር ነበር። አይቻታለሁ። እሱ አልነበረም:: ‹‹አንተ ለምን አብረሃት አልተቀመጥክም?››

እዛ አካባቢ ካገኙኝ ፖሊሶች እየደበደቡኝ ተቸገርኩ:: እሷ ሴት ስለሆነች አይመቷትም ብለን ነበር:: ከ3 ወር በኋላ ግን ከUNHCR በር ላይ እንድትነሳ ያረጓት በዱላ ደብድበው ነው? ያውስ ቀላል ደበደቧት መሰለህ?..››

እዚህ ሀገር ለሴት ክብር አለ ሲባል እሰማ ነበር። መስማት ብቻ አንጂ በማየት አልታገዘም። እንዴት ሴት ልጅ መቱ የሚለው ሲታሰበኝ ‹‹ማነው የደበደባት?›› የሚለውን ለራሴ ጠየኩኝ:: ምላሹ ግን ያለው እሱ ጋር ነበር እና ጥያቄውን ለእሱው አሳለፍኩት።

የUNHCR ቢሮ ሰራተኞች ፖሊስ ጠርተው አስነሱልን አሏቸው:: መፍትሄ ካልተሰጠን አልነሳም ስትል ቆመው እያዩ ፖሊሶቹ ደበደቧት:: የ5 ወር እርጉዝ ነበረች ደም በደም ሆነች:: በመሀል በእርግጫ ተመታች። ደም በደም ሆነች:: በመሀል በእርግጫ ተመታች። ያስወረዳት:: ተደብድባ እንኳን ህክምና እምቢ ብለው ቀይ መስቀል ነው ያሳከማት ወረቀቷን ማየት ትችላለህ» አለኝ::

ቃለ-ምልልሱን ባደረግንበት ወቅት ሚስቱ ከተመታች እና ጽንሱን ካስወረደች ስድስት ወር አልፏት ነበር። የሚስትህ ጤንነት በምን ሁኔታ ላይ ነው? የሚለውንም ጥያቄ ወረወርኩ:: ‹‹ህክምና እየተከታተለች ነው:: ግን አሁንም ደም አልፎ..አልፎ ይፈሳታል:: ውጋት ያዘኝ ብላ አብሶ እየሩ ቀዝቀዝ ሲል ትጮሀለች:: ያው እነሱ የፈቀዱትን ህክምና ነው የምታደርገው በግል አቅም የለንም:: የጤና ችግር ይዟት እስከ አሁን ከአልጋ አልተላቀቀችም:: ከ6 ወር በላይ ተኝታለች:: ለልጆቼ ብቻዬን ስርቼ ለማሳደግ ባለመቻሌ ችግር ላይ ነኝ:...››

ኡስማን ችግሩ በዚህ ብቻ አልቆመም:: አጠቃላይ ስደተኛው የመን በነበረባት ችግር ምክንያት ከየመኖሪያው ተፈናቅሎ መፍትሄ ይሰጠን በጦርነት ልናልቅ ነው ብሎ UNHCR በር ላይ በተቀመጠ ሰዓት በ03/07/2011 ስደተኛውን ወታደር በአስለቃሽ ጭስ፣ በጥይት፣ በዱላ.. ሲደበድቡ የእድል ጉዳይ ሆኑ አንገቱ ላይ በጥይት ተመቶ በህክምና ተርፏል::

# - 16 -

# ሆድ ለባሰው...

በርሃብ አበቀን
ሰደት በታትናን
ምኞቱ ዝም አልከን
እንዲህ ባከነን
የትም ወድቀን...

ሁላችንም በየቤታችን ያለውን ድህነት እናውቀዋለን። ይህን ድህነት ለመዋጋት ዋጋ ከፋይ፣ ችግር መካች የምናደርገው ማንን እንደሆነም እናውቃለን። በቤት ውስጥ ያሉ ሴቶቻችንን ወደ አረብ ሀገር በመላክ ነው። ነገር ግን የቤተሰብን ኑሮ ለመቀየር የተሰደደችው እህታችን ፈተናን ማን አየው? በየአረብ አገሩ የሚኖሩ ዜጎቻችን እንደምን እየኖሩ እንደሆነ ገንዘቡንስ እንዴት እንደሚያመጡት ምን ያህሉ ቤተሰብ ያውቃል? የአረቡን አለም እውነታ ሳያውቅ ልጁ ብደወለች፣ ለዚህ ነገር ገንዘብ ላኪ ልበሳት... አሁን ገንዘብ ስትልክ ይህን እንገዛና..ይህን እናደርግና..የሚል አባት፣ የምትል እናት...እህቴ በደወለች፣ ፍቅረኛዬ በላከች እያለ የእርዳታ ብር እየጠበቀ የሚኖረው ወጣትስ ገንዘቡ እንዴት እንደሚመጣ ያስበዋል? ልጁ በአመቷ አረብ አገር ሄዳ ታክሲ ገዛች። ቤት ሰራች፣ ወርቅ በወርቅ፣ ገንዘብ በገንዘብ አንበሸበሸችኝ ብሎ የሚኖረው ቤተሰብስ የአረቦችን ምድር ብር የሚፈልቅበት አድርጎ ነው የሚያስበው ወይስ እውነታውን እያወቀ «የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው..» እያለ ነው የልጆቹን ደም እና ወዝ (ደመ-





ወዝ) እየበላ የተቀመጠው? ካላወቀ ልጁ፣ ፍቅረኛው፣ ሚስቱ፣ እህቱ..ለእሱ ስትል ስንት ምን ዓይነት ፍዳ እያየች እንደሆነ ለማወቅ ቢጥር ጥሩ ነው።

በርግጥ በልጆቹ ብዙ ቤተሰብ አልፎለታል። ከትላንት ጨለማ ወጥቶ ብርሃን አይቶ ይሆናል። ልጆቹ የሚኖሩበትን ህይወት ባያይም ባይሰማም ‹‹ተመስገን›› ብሎ ይኖራል። ግን ማንም ወደ ስቃይን አያይም። በመጥፎ ቦታ እንኳን ቢሰለፉ ለቤተሰብ ኑሮ ለማሳለፍ ከመንገት አንጻር ሊሆን ይችላል።

አረብ ሀገር ለሁሉም ጎርብጧል፣ ሁሉም ተበድሏል፣ ሁሉም ጉዳት ድርሶበታል አያስብልም። በለስ የቀናቸው ሞልተዋል። የቤተሰብ ችግር ቀርፈው ለራሳቸውም ጥሪት የቋጠሩ ጠንቃቃ እና አላማ ያላቸውም ብዙ ናቸው። አላማ ኖሯቸው እድልና አጋጣሚ ፊቱን አዙሮባቸው የለፉበትን ያጡ፣ ምላስ ጠልፏቸው ለፍቅር ሲሉ የለፉበትን በትነው እድሜያቸውን አባክነው በዜሮ ፎሪ የወጡም ቤቱ ይቁጠራቸው። ሁሉም የየራሱ ፍላጎትና አላማ ቢኖረውም ሳይሳካለት ሲባዝን የከረመውን ቁጥር ማስላቱ ግን ያማል። በችግሯቸው ተገደው ራሳቸውን ለገበያ ያቀረቡ የመኖራቸውን ያህል ፈልገው ደግሞ በመጥፎ ስራ የሚሰማሩም መኖራቸውን ግምት ውስጥ መክተት ያስፈልጋል።

‹‹ሆድ ለባሰው..›› የሚያስተርትም ውል ያጣ የመከራ ቋት የሚገፉ እህቶቻችን መኖራቸውን ማሰብ ግድ ይላል። እስኪ እንይ...

መሰረት ትባላለች ሁሌም ስትታይ ደስተኛ ነው የምትመስለው። መሳቅ፣ መጫወት የግል ሀብቶቿ ናቸው። ሁሉን በሆዷ ይዛ ለሁሉም ጥርሷን ብልጭ፣ ፊቷን ብርት ታደርጋለች። ደስ የሚል ጠይም ፊት አላት። ስደትን በተመለከተ ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ጥናት ሳደርግ ሰዎችን አፈላልጎ ማነጋገር ነበረብኝ። መረጃ ለማግኘት ያለውን ውጣ ውረድ በመጀመሪያ ደረጃ ያጠነከረው ድብቅነት እና እፍረት ነበር። ይህን መሰናክል ለማለፍ ስል ሴቶቹን ሴቶቹ እንዲያናግሩልኝ አደርግ ነበር። ይህን በማድረግ ከተባበሩኝ ውስጥ ዋናውን ሚና የተጫወተችው ጻህይ በየነ ስትሆን በመቀጠል ሔለን ገ/እግዚአብሄር፣ እስመረት ገ/እግዚአብሄርን ጥሩ መረጃዎችን በማቅረብ አሁን አዲስ አበባ ቢገቡም ሰብለወርቅ ታደሰ የሳሪስ ልጅ እና አይናዲስ ኢደሳ የቃሊቲ ልጆች ነበሩ። ምስጋናዬ ዘውትር አይለያቸውም። ከእነዚህ ልጆች መካከል አንደኛዋ መሰረት የተባለችውን ልጅ ጠቆመችኝ። ልጅቷ ለእሷ ልትነግራት ያልደፈረችው አሳዛኝ ታሪክ እንዳላት እሷ ማግባባቱ እንዳልተሳካላት ነው የነገረችኝ።

ልጅቷን እንደምንም አገኘኋት እና ቀጠሮ ያዝን፡፡ በተገናኘንበት ሰዓት የየመንን ምድር ከረገጠች ሰባት አመቷ ነው፡፡ የመን ረጅም ሰዓት ለማውራት፣ ሰው ቤት ግብገባ ሲባል፣ ሰርግ፣ ልደት ላይ፣ ለቅሶ ቤትም ቢሆን ሰብሰብ ብሎ ጫት መቀነጣጠብ የተለመደ ነው፡፡ እኔ እና እሷ ስንገናኝ ትቅም እንደሆነ ቡና አቀራርቤ ልጠብቅህ ስላለችኝ ተዘጋጅቼ ጫቱን ውሀዬን ለእሷም ጭምር ሰንቄ ነው የሄድኩት፡፡ አፋችንን አበስንና ወጋችንን ቀጠልን፡፡ የመጣችው በባህር ነው፡፡ የየመንን ምድር ከመርገጧ በፊት ባህሬን የስድስት ወር ቆይታ አድርጋለች፡፡ ከባህሬን ለምን ወደ ኢትዮጵያ እንደ ተመለሰች እና ለምን በባህር ዞራ የመን እንደመጣች ለማወቅ ጓጓሁ፡፡ እሷን ለማናገር ከልምምጥ ባላነሰ ሁኔታ ማስረዳት ይጠበቅብኝ ነበር፡፡ ያውም ልምምጡ እንዲህ ነው ተብሎ የማይገለፅ ትዕግስት አስጨራሽ ነበር፡፡

‹‹ተወኝ!..ተወኝ!..እንዲሁ የውስጤን በውስጤ ይዤ ለይምሰል ሰው መስዬ ልኑርበት፡፡ መስሎ መታየት ታውቃለህ አርቲፊሻል ሳቅ እሱን ልሳቅበት..ቁስሌን ነካክተህ ላታድነው አታመርቅዘው፡፡ ከእነ ህመሜ፣ ከእነ ቁስሌ፣ መኖር የቻልኩት ድረስ ልታገል፡፡ በዚህ ዙሪያ ባናወራ… ልትተወኝ ፍቃደኛ ነህ….›› አለችኝ፡፡ ይበልጥ ትዕግሥት ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ፡፡ የማዕድን ቁፋሮ የመቆፈር ያህል ታግዬ፣ ታግሼ ለምኜ በኋላ ጥሩ ነገር እንደማገኝ ገምቻለሁ፡፡ የመጀመሪያው ቀን የምችለውን ያህል ለማግባባት ሞከርኩ፡፡ በሌላም ቀን ተገናኝተን ሌላ ዙር የማሳመን ሙከራዬን ቀጠልኩ፡፡ ታሪኳን ስትጀምር የሚንዠቀዠቀው እንባዋ የእኔንም ስሜት ነክቶ እንባዬን አስፈሰሰው፡፡ ልብ በሉልኝ ከ55 ሰው በላይ ቃለ ምልልስ ሳደርግ በብዙዎቹ ታሪክ አብሬያቸው አልቅሻለሁ፡፡ ሁላችንም ለማልቀስ የተፈጠርን ትውልድ እስክንመስል አልቅሰናል፡፡ እስከመቼ በየሰው ሀገር ተሰደን ስናለቅስ እንኖራለን? የፈሰስ እንባችንስ የሚቆጠርልን መቼ ነው? በቃ! አንባልም? ስፍሩ፣ ዋንጫው አልሞላ ይሆን? እንባችን ዋንጫ ቀርቶ በርሜል፣ በርሜል አልፎ ወንዝ አይሞላ ይሆን..?›› ብዙ ብዙ አሰብኩ፡፡ አባይ ብቻ ሳይሆን እንባችንም ይገደብ፡፡

‹‹ስማኝ ግሩም የእኔን ታሪክ ሰምቶ ከማዘን፣ ከንፈር ከመምጠጥ ውጭ ተሰምቶህ አንተ ያነባኸውን ያህል ሊያነቡ ይችላሉ፡፡ ግን ከመሰደድ ወደኋላ አይሉም፡፡ ችግር መጥፎ ነው እያየህ እሳት ውስጥ እንድትገባ ያደርግሀል፡፡ እንደ እኔ አይነቱ ርሀብ የሚያዳፋው ምግብ ፍለጋ መንዝ ስላለበት የስማውን ችግር፣ ያየውን ተጎድቶ የተመለሰ ወገኑን ይረሳና ይሰደዳል፡፡ እኔ ያለውን ችግር ሰምቻለሁ፡፡ አይቻለሁ፡፡ ስለዚህ የእኔ ታሪክ ምንም አይፈጥርም፡፡ አይለውጥም፡፡ ተወኝ!!..መሳቂያ መሳለቂያ ለቤተሰቦቼ ማፈሪያ ለመሆን ካልሆነ ምን ሊጠቅም?..››





በጥያቄ ተሞልታ ስታፈጥብኝ ፈራኋት፡፡ አይኖቿ ፈጠው ዘልቀው ውስጤን የሚመረምሩ መሰለኝ፡፡ ለማሳመን ያልቆፈርኩት ጉድጓድ ያልናድኩት ተራራ የለም፡፡

ሮዝማን የሲጋራ ፓኮዋን ከቦርሳዋ አውጥታ ለኮሰች፡፡ ዝምታ ጋርዶናል፡፡ ሁለት ሶስቴ ሳብ ቡልቅ..አድርጋ በጭሱ ውስጥ አሻግራ እያየች ‹‹እሺ ምን እንድነግርህ ፈለክ?›› አለችኝ ሁኔታዋ አስፈራኝ፡፡ ታሪኳን ሳልሰማ አሳዘነችኝ፡፡ ‹‹እስኪ ባህሬን ከሄድሽበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ንገሪኝ ከዛስ ለምን ወደ የመን መጣሽ?››

ደጋግማ ግንባሯ ቋጠር ፈታ ቋጠር ፈታ አድርጋ ‹‹በመጀመሪያ ይህን አስጠሊ ቴፕህን ዝጋልኝ፡፡ ያስፈራል፡፡ በእውነት ሰዎች በተሰበሰቡበት ገመናዬን የምናገር እስኪመስለኝ ድረስ አስፈርቶኛል፡፡ እንደ ልቤ ነጻ ሆኜ ማውራት የምችል አልመሰለኝም..›› አለችኝ፡፡

‹‹ግን እኮ እንድቀዳሽ ፈቅደሽልኛል›› አጠፋሁትና ወረቀትና ስክርቢቶ ይዤ ልረሳቸው የምችለውን ነገሮች ብቻ መመዝገብ ፈለኩ፡፡ ለማንኛውም ሽንት ቤት ደርሼ ልምጣ ብዬ ሞባይሌን ሪከርድ ላይ አድርጌ ደረት ኪሴ ዶልኩት፡፡

‹‹የአዲስ አበባ ጨርቆስ አካባቢ ልጅ ነኝ..›› ስትል ጀመረች፡፡ ‹‹..ዝቅተኛ በጣም ዝቅተኛ ከሚባል ማህበረሰብ እንኳን እጅግ ዝቅተኛ ከሆነ ቤተሰብ ውስጥ ነው ተወልጄ ያደኩት፡፡ መማር አልቻልኩም፡፡ ጨርቆስ ገበያ ውስጥ ጉልት እቸረችር ነበር፡፡ እናቴ ስትታመም ታናሽ ወንድሜን ጨምሮ መብላት አልቻልንም፡፡ ሸርሙጥና ጀመርኩ፡፡ ቁራ /ቡልጋሪያ/ ደሴ ሆቴል፣ አብነት አካባቢ ቅዳሜ ቡና ቤት፣ በአካል ፀ፣ አራት ኪሎ ዘውዲቱ ሆቴል፣ ሳምሶን….ኤጭ!!..ዝርዝሩ ምን ያደርጋል…ስራሁ ጠብ አይልም፡፡ ቤተሰቦቼን ከችግር አላወጣሁም፡፡ እድል ስትቸገረ ሳይሆን ላሰው ነው ፊቷን የምታዞረው፡፡ እድል ራሷ ሸርሙጣ ነች፡፡ ካለው ጋር ታሸቃብጣለች፡፡ ሌባ ይመስል ኪስ ኪስ ታያለች፡፡ በመልክ መተናነስ ሳይሆን ዝበያው ወደ እኔ አልዞር አለ፡፡ በዚህ ስራ ላይ እያለሁ በከፋኝ ሰዓት አብዱራህማን አልራሚ የሚባል ባህሬን የሚኖር ሰው ተዋወኩኝ፡፡ የመናዊ ትውልደ ኢትዮጵያዊ ነው፡፡ አሳዘንኩት መሰለኝ ሊረዳኝ ፈቀደ፡፡ ፓስፖርት እንዳወጣ 500 ብር ሰጠኝ፡፡ የሚገርምህ ምንም አይነት ነገር ከእኔ በውለታ አልፈለገም፡፡ በዚህ እርዳታው ሁሌም ሳመሰግነው እኖራለሁ፡፡

‹‹ፓስፖርቱን አውጥቼ ሰጠሁት፡፡ ባህሬን ሲሄድ ይዞልኝ ሄደ፡፡ እዛ ለሚያውቀው ደላላ እንደሰጠ ስልክ ደውሎ ነገረኝ፡፡ ከሁለት ወር በኋላ ተደውሎ ቪዛ መጣልሽ ተባልኩ፡፡ የሚያስፈልጉትን ነገሮች ጨራርሼ ባህሬ

እስክገባ ያለምኩትን ህልም ሳስታውሰው አፍራለሁ። ቤተሰቦቼን ረድቼ፣ ተለውጬ እነሱንም ለውጬ..ተወው እባክህ ያሰብኩት ያለምኩት ሁሉ ጉም ሆነ። በነነ...ተነነነ...

ባህሬን ዋና ከተማ ማናማ ስደርስ ከአየር ማረፊያ የተቀበለኝ አረብ ነው። ደላላው ነበር። መክተብ /ቢሮ/ ወሰደኝ። ትንሽ ከተማዋን ያየሁት እስከ ቢሮው ሲወስዱኝ ነው። አሰሪዎቼ እስኪመጡ የክብር እቃ መስዬ ተጎለትኩ። አያናግሩኝም። አላናግራቸውም። ላናግራቸው ብልስ በምን ቋንቋ? አያቸዋለሁ ያዩኛል። ከአንድ ሰዓት በኋላ በአንድ መኪና አባትና ልጅ መጡ። ሻንጣዬን ጭኜ ከኋላ ገባሁ። ከከተማው ወጥቶ ተኩል ሰዓት ያህል የሚያስኬድ ቦታ ነው ቤታቸው። ግቢ ውስጥ እንደገባን ሻንጣዬን አወረድኩ አባትዬው ልጁን ጠርቶ ገንዘብና የመኪና ቁልፍ ሰጥቶ ላከው። ሻንጣዬን ጠልጠል አድርጌ ከኋላ ተከተልኩ። ምድር ቤት የሆነ ክፍል አሳየኝ እና ሻንጣዬን አስቀመጥኩ። አንድ ፒጃማ ነገር ይዞ መጣ። ባኞውን አሳየኝ እና እንድታጠብ በምልክት ነገረኝ። ‹‹ጥሩ ሰዎች ናቸው ማለት ነው..›› ብዬ ፈጣሪዬን አመስግኜ ስለ ደካከመኝ ለመታጠብ ገባሁ።

ታጥቤ ስወጣ ሰውዬው ክፍሌ የተባለው ውስጥ ያለችው አንድ ወንበር ላይ ተቀምጧል። ልብሴን የሚያስተካክል መስሎ ተጠጋኝ። አነቀኝ። የሚፈልገውን ላለማስፈፀም ትግል ጀመርኩ። ከኪሱ ብር አወጣና በእጁ ሊያስጨብጠኝ ሞከረ። ኢትዮጵያ እያለሁ ምን እንደምሰራ ያወቀ መሰለኝ። ደነገጥኩ። ቢሆንም ገላዬን በዙር በአዳር እየተመነኩ ከመቸርቸር ለመዳን ነው ስደት የመጣሁትና የአላስነካም ትግሌን ቀጠልኩ። በሬ በጥፊ መጣል በሚችል ግዙፍ እጁ በቡጢ ነረተኝ። ወደኩኝ። በእርግጫ ደገመኝ። መከላከል አልቻልኩም። አሰረኝ እና የፈለገውን አደረገ። በመደበኛው ቦታ ጨርሶ እሱ እረፍት ሲያደርግ እኔ እንደታሰርኩኝ ነው። ቀጠለና ትክክለኛ ባልሆነ ቦታ ደገመ /እሷ የተጠቀመችበት ቃል ሌላ ነው/። ህመሙን ግድ ሆኖብኝ ቻልኩት። የመኪና ድምጽ ሲሰማ ጥሎኝ ወጣ። ትንሽ ቆይቶ ልጁ መጣ። ታስሬ ሲያየኝ በቀጥታ ልብሱን ማወላለቅ ጀመረ። እሱም በአባቱ ድርጊት ላይ ተደመረ።

ከዚህ በኋላ ምን ማድረግ እችላለሁ የመኝታ ቤቴን ቁልፍ እየተቀባበሉ ለሁለት የሚያደርጉትን ቀጠሉ። የሰውየው ሚስት ማለት የልጁ እናት ታማ ሆስፒታል ተኝታ ነበር። እሷን በማስታመም ላይ የነበረች አንዲት ፊሊፒንሳዊት ገና ስታየኝ አዘነች። የተያየነው ከ13 ቀን በኋላ ነበር። እሷ ስለለመደችው እኔ ላይ ሊደርስ የሚችለውን አስባ ነው ማዘኗ።

ማታ ላይ መኝታ ቤቴ በር ላይ ሆነው አባትና ልጅ ያወራሉ። አባት እኔ ጋር ልጅ ደግሞ ፊሊፒንሷ ጋር ገቡ። ይሄ ሁኔታ በዚሁ ዓይነት





በየቀኑ ቀጠለ። ተመካክረን ሁለታችንም አንዳችን መኝታ ቤት ለመተኛት ሞከርን። (ታዲያ ምክክራችን በምልክት ነው) ሁለቱም አንድ ላይ ገብተው ስራቸውን እየተያዩ ቀጠሉ። ምን አይነት ሀገር ነው አባትና ልጅ የማይተፋፈሩበት? ሀገሩ ግብረ-ገብ የሚባል ነገር የሌለበት መሆኑን ለማወቅ ከዚህ በላይ ምን ማረጋገጫ ያስፈልጋል።

ወር ላይ የወር አበባዬ ቀረ። ለማን ላማክር? ለእሷ እንዴት ላማክር? በምን ቋንቋ? ከፊሊፒንስዋ ጋር በምችላት ጥንጥዬ እንግሊዘኛና በምልክት ነው የምንግባባው። እንደዛው አድርጌ ነገርኳት። እሷም የምታደርገው ግራ ገባት። እንዲሁ እንደተጨነቅን ሁለተኛው ወር ሞላ። ምንም ጠብ የሚል ነገር ጠፋ። የምን እንደሆነ የማላውቀው 5 ኪኒን ሰጠችኝና ዋጥኩ። ትንሽ ቆየና ቁቅታ አጣደፈኝ። ከዛ ቢጠበቅ ቢጠበቅ ምንም የለ። የተለያየ ነገር ሞከርኩ። ተልባ ቀቅዬ ጠጣሁ። ፓፓዬ፣ ኪኒን፣ ማር በዛ አድርጌ በጥብጬ እስኪያስቀምጠኝ..ምንም የለ ሶስተኛው ወር ገባ። በዚህን ጊዜ ሁሉ አባትና ልጅ ከድርጊታቸው አልተቆጠቡም። ፊሊፒንሷ የሰጠችኝ 5 ኪኒን የወሊድ መቆጣጠሪያ ነው። አስጠሊታ ድርጊታቸውን ከመላመዷ ብዛት እንድትከላከል ገዝተው ሰጥተዋታል። ደግሜ 12 ክኒን አንድ ላይ ዋጥኩ። አሁንም ከቁቅታ በቀር ምንም። ይባስ ብሎ ህመም ሁሉ ጀማመረኝ።

ቅናት ፍጥነታቸውን ጨምረው በረሩ። ሆዴ እየገፋ መጣ።

የሰውየው ሚስት በሚገፋ ጋሪ ነው የምትንቀሳቀሰው። እሷን ማንቀሳቀስ፣ ማጠብ፣ ማልበስ፣ ሽንት ቤት መውሰድ ነው ስራዬ። ያስመጡኝም እሷ የመኪና አደጋ ሲደርስባት እንዳገለግላት ተብሎ ነው።

ስድስት ወር ሞልቶኝ ሆዴ ገፍቶ ማስታወቅ ሲጀምር ሴትዮዋ ልጁን ግደላት አለችው። እኔ አልሰማሁም ፊሊፒንስዋ ናት በምልክት የነገረችኝ። ተጠንቅቄ መጠባበቅ ጀመርኩ። ይሄን ሁሉ በደል ችዬ ደግሞ ሊገሉኝ? ከመሞቴ በፊት አንዳቸውን መግደል እንዳለብኝ ወሰንኩ። ከቀናት በአንዱ ጎደሎ ቀን (ለካ ለእኔ ሁሌም ጎደሎ ነው ረስቼው ነው) ኩሽና እያለሁ. ልጁ መጣ። እጁ ላይ ገመድ ይዟል። አንገቴ ላይ ሊያጠልቀው ሲል ቀድሜ ቢላዋውን ሰነዘርኩ። እጁ ላይ ወጋሁት። እንዳያሳስሩኝ ጉዳቸው ሊወጣባቸው ሆነ። ቀይ አስመትተው የ7 ወር ደሞዜን ሰጥተው ወደ ኢትዮጵያ መለሱኝ።

ለደም ምርመራ እና ለተለያየ ነገር ብድር ተገብቶ ተሳፍሬ ዛሬ ቤተሰቤ የሚለወጥበትን ነገር፣ የናፈቅነውን ገንዘብ ሳይሆን ፅንስ ይዤ ተመለስኩ። ምን ብዬ ወደ ቤተሰቤ ልቀላቀል ሌላስ የት መሄጃ አለኝ።

አውጥቼ አውርጄ እናቴ ጋር ሲመሽ ገባሁ። ከያዝኩት ብር ላይ የገባችውን እዳ እንድትከፍል አደረኩ። 23 ቀን ከቤት ሳልወጣ አሳለፍኩ። ምን አይን አለኝ ትሰራለች ተብዬ ሄጄ ሆዴን አንገፍጥጬ ስመለስ እውነት ማን ተገዳ፣ ተደፍራ ነው ብሎ ያምናል እዚህ ከነበረው ህይወቴ ጋር አያይዘው እዛም ሸረሞጠች ነው የሚሉኝ። እውነቱን ግን እኔና እግዚአብሄር ነን የምናውቀው። የሀገሬቷን ከተማ እንኳን ስሄድ እና ስመጣ ብቻ ነው ያየኋት። እንኳን ሰዉ እንደሚያስበው ልሆን።

በኋላም ህመም እየጨመረብኝ ሲመጣ ጤና ጣቢያ ሄድኩ። ምርመራ አደረኩኝ። ሰባተኛ ወሬ ላይ ግን የቁም ሞቴን አወኩ። በተደረገልኝ ምርመራ የHIV ቫይረስ ተሸካሚ መሆኔን ተነገረኝ። ተስፋ ጎህ ሄድኩኝ። ይህ ታሪኬ እዛም ተመዝግቦ አለልህ። (የምትነግረኝን ነገር ሁሉ ግራ አጋባኝ። ስቤት ውስጥ ገብቼ የመን ከመጣች ሰባት አመት፣አመት ከሁለት ወር ተስፋ ጎህም ተረድታለች። ስምንት አመት..ታዲያ እስከ ´አሁን ሰላም ነች። እንዴት? እድሜ ማራዘሚያውን ትጠቀም እንደሆን ብዬ ጠየኳት) በፍፁም። ሌላው የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ያረገዝኩት መንታ መሆኑን ስምንተኛ ወሬ ላይ በተደረገልኝ ምርመራ ማወቄ ነው። ደነገጥኩ። መደንገጥ ሲያንሰኝ ነው። በቦሐ ላይ ቆረቆር እንዲሉ በችግር ታጠርኩኝ። ጊዜውን ጠብቆ መንትዮቹ ልጆች ተወለዱ። በአንዴ የሁለት ልጆች እናት ሆንኩ። ልጆቹ ግን ከቫይረሱ ነፃ በመሆናቸው እግዚአብሄርን አመሰገንኩት። በቅጡ የምታረስበት ስላልነበረኝ ተስፋ ጎህም ሌሎቹም ጋ እሯሯጥ ጀመር።

በዚህን ጊዜ የሰፈርተኛው አፍ አላኖር አለኝ። ‹‹..በዶላር እኮ ነው የሚልክላት፣ ከአረብ ነው የደቀለችው፣....›› ጆሮዬ እስኪገማ እስኪገለማ የምሰማው ሁሉ በዛ። አደነዘዘኝ። በሽተኛነቴን አንስተው ሲያወሩማ ከተሰበረው ልቤ ጋር ራስሽን አጥፊ አጥፊ ይለኛል። ሁለት ሶስቴ ራሴን ለማጥፋት ሞከርኩኝ። አልቻልኩም። ብን ብዬ ለመጥፋት በምፈልግበት ጊዜ አንድ ጓደኛዬ የነበረች ልጅ የመን ከርማ መጣች ሲባል ሰማሁ። እንኳን ሰላም መጣሽ ለማለት ሄድኩኝ። ዜናው ከእኔ ቀድሞ ደርሷት ስለነበር ተቃቅፈን ተላቀስን። የደረሰብኝን በሙሉ ነገርኳት። እሷም ኮንትራት ቤት እያለች የሰውየው ልጅ ያስቸግራት እንደነበር ብዙ በደልም እንደ ደረሰባት አወራችኝ። የእኔው ግን ልዩ ነው። ስለየመን ብዙ ስታወራኝ በባህር የሚሄዱ እንዳሉ ሰማሁ። ልቤ ሻቀለ። ታዲያ ሁለት ልጆቼን ይዤ ምን ላድርጋቸው? ከጥቂት ቀናት ቆይታ በኋላ ተመልሼ ጓደኛዬጋ ሄድኩኝ። ያለብኝን ችግር እና በባህር ወደ የመን መሄድ እንደምፈልግ ነገርኳት። የመን ዋና ከተማ ሰነዓ እንደምትኖር እና ስልክ ቁጥሯን ከ500 ብር ጋር ሰጥታኝ ብር ይህ ብቻ እንደማይበቃኝ ነገረችኝ።





ተጨማሪ ገንዘብ ፍለጋ የእናቴን ጌጣጌጥ እሸጣለሁ አልል ምን የደላ ኑሮ ኖረን ጌጥ ትገዛለች? የማደርገው ግራ ገባኝ። ከተስፋ ጎህ የሚሰጠኝን ጨመርኩና ከአንዱ መቶ ከሌላው 50 እያልኩ 900 ብር ሲሞላልኝ ልጆቼን ለእናቴ ሰጥቼ ጉዞ ጀመርኩ። መሄጃ ነው የተባለበት ጅጅጋ ደረስኩኝ። ደላሎቹ አሯሩጠው ድንች እና ሽንኩርት በተጫነበት መኪና ከሶስት ወንዶች ጋር ጫኑኝ። ከግማሽ ቀን ጉዞ በኋላ የሆነ ጫካ ውስጥ የማደሪያ ቦታ ነው ተብሎ ወረድን። የሚገርመው ነገር ጫካ ጫካውን ስለሆነ የሄድነው አንድም ከተማ አላየንም። ማደሪያ በተባለው ጫካ ዝርፊያም ሲፈፀምበት አየሁ።

እኔም ፈጸምኩበት። እነሱ ሊዘርፉኝ የፈለጉት ሴትነቴን ነው። ያለብኝን ችግር አውቀዋለሁ። የጤናም የገንዘብም ችግር አለብኝ። እሱ በሽታዬን ሊጋራ ሲታገለኝ ከኪሱ ቦርሳውን አውጥቼ ብሩን ተጋራሁት። በሌላኛው እጁ እና እግሬ ጭኔን ላለማስከፈት ታግዬ ነበር። ቦርሳው እጁ መግባቱን እንዳረጋገጥኩ በእርግጫ እንትኑን መታሁት። ሮጬ ወደ ጫካው ከገባሁ በኋላ ፈተሸ..ፈተሸ አድርጌ ካገኘሁት የሶማሊያ ሽልንግ ሌላ 50 ዶላር እና 300 የኢትዮጵያ ብር ወስጄ ፓንቱ ውስጥ ደበኩ። ተመልሼ ወደ እነሱ ስሄድ ቦርሳውን በሻርፔ ሸፍኜው ነበር።

‹‹አፍዋን ያ ሀቡብ›› በአረቢኛ ይቅርታ ጠየኩት። የማግባባው መስዬ አውልቆ ያስቀመጠው ጃኬቱ ኪስ ውስጥ ከተትኩለት። ‹‹የትም ተወለድ ጨርቆስ እደግ›› የሚለውን ለራሴ በውስጤ አልኩት። ፈርቶኝ ይሆን ይቅርታ ስላልኩት ሳይነካኝ አደረ። በማግስቱ አንድ ከተማ ነገር ስንደርስ ተሰወርኩባቸው። ገረዊ ትባላለች አሉኝ ከተማዋን። ሌላ ከብት የጫነ መኪና ለምኜ ወደ ቦሳሶ ሄድኩ። ቦሳሶ በጣም አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታ ቆየሁ።

ከ17 ቀን በኋላ ጀልባዋ የምትነሳበት ጊዜ ሆነና ምሽት ላይ ከከተማ ወጥተን መጫኛው ቦታ ሄድን። ሶማሊያውያኑ የጀልባዋ ሾፌሮች ሴቶችን ወደ ኋላ አስቀርተውን መጨረሻ ላይ ጫኑን። የተሻለ ቦታ ቢሰጡንም መጨናነቁ አልቀረልንም። ለ38 ሰዓታት ተጉዘን ቤራሲ የሚባለው የየመን ድንበር ላይ ጣሉን። ከእጥረቴ ጋር መሬት ለመርገጥ ስታገል ውሀው ከአናቴ በላይ እየዋለ ልሰምጥ ወደላይ ወደታች እያልኩ የባህሩን ውሀ እስክጠግብ ጠጣሁት። የበደሌ ካሳ ልበላቸው የበደሌ ተጨማሪ መቀጣጫ ሁለቱ ልጆቼ በሀሳቤ ታዩኝ። እነሱን አሳድጋለሁ ብዬ ባህር መቅረቴን አሰብኩ። ለእኔም ቢሆን እልጋ ስይዝ ራሴን የማስታምምበት ሳንቲም ለመያዝ አስቤ ህይወቴ ባህር ላይ መቅረት ስለሌለበት ‹‹ዋይይ!!!...›› እንዴት ብቅ ጥልቅ በምልበት ሰዓት እንደጮህኩ አላውቀውም። አንድ

ሶማሊያዊ አቅፎ አወጣኝ። ምን ያህል እንደሆነ ባላውቅም የጠጣሁትን ጨዋማ ውሀ አስተፋኝ። ቀኑን ሙሉ በውሀው ምክንያት አሞኝ ዋለ።

አሞኝም ቢሆን መንዛችንን ቀጥለናል። አብረውኝ የነበሩት ልጆች «አይዞሽ» እያሉ አደን የምትባለው ከተማ ድረስ ሄድን። ቀጥታ ከተማዋ ውስጥ አልገባንም በሳቲን የሚባለው ቦታ ነው ይዘውኝ የሄዱት። ኡስማን እና ፈቲያ የሚባሉ ባልና ሚስት የአርሲ ልጆች ጋ አሳረፉኝ። ፈቲያ ደግ ነች። የምቀይረው ልብስ እና ከላይ የሚለብሱት ጥቁር ከለር ያለው ባልጦ የሚባለው ልብስ ሰጠችኝ።

አርብ እለት አደን ይዛኝ ሄደች። እዛ እንደደረስን ክርስቲያን ስለሆኑ ይርዱሽ ብላ (ፕሮቴስታንቶቹ ጋ) ጊቢውን አስገብታኝ ተመለሰች። መፍራቴን አይቶ ይሁን አዲስ መሆኔን አውቆ ደረጀ የሚባል ልጅ /አሁን ካናዳ ነው ያለው/ ደስ የሚል አቀባበል አደረገልኝ። መቸገሬን ሁሉ የተረዳ መሰለኝ። ትህትናው ራሱ ያስደስት ነበር። «አዲስ ነሽ?» አለኝ። ለሀገሩም ለእምነቱም አዲስ መሆኔን ነገርኩት። እነሱ ፕሮቴስታንት እንደሆኑ በሁኔታቸው ተረድቻለሁ። እኔ ደግሞ ጨርቆስን እያልኩ ስምል ያደኩ የጨርቆስ ልጅ ነኝ።

«ከኮንትራት ጠፍተሽ ነው?»

«የምን ኮንትራት በባህር ነው የመጣሁት»

«መቼ?»

«እሮብ እለት ነው የገባሁት»

«የት አረፍሽ?»

«ሶማሌዎቹ በብዛት ያሉበት ቦታ ነበር ያረፍኩት...» ቦታው ስም ለጊዜው ጠፍቶኝ በምልክት ነገርኩት።

«በሳቲን?»

«እ..እ..እ..» ስላወቀልኝ ደስ አለኝ።

«አይዞሽ በቃ! እዚህ እንድትረጂ አደርጋለሁ። አስከዛው ልጆች አሉ እነሱ ጋ ትሆኛለሽ። አይዞሽ...» አማኝ ሊያደርጉኝ መጣራቸው እንደማይቀር ገመትኩ።

«እሺ እግዚአብሄር ይስጥልኝ!!..» ማለት ያለብኝ ይህንኑ ነው። በእርግጥም በጣም ጥሩ ልጅ ነው። ከልጆች አገናኘኝ ብዙም ረዱኝ። እዛ ያሉት ፕሮቴስታንቶች ብዙዎቹ ጥሩዎች ናቸው። ኤፍሬም የሚባል እዛው አማኝ የሆነ ልጅ ስራ በጥሩ ደሞዝ አስገባኝ። ህብረታቸው፣ ፍቅራቸው፣





መከባበራቸው ደስ ይላል። መጥፎ ጎን ቢኖርባቸው እንኳን ጥሩው ስራቸው ይሸፍነዋል። ሁለት ሆነው ከሚኖሩ ሴቶች ጋር ተዳብዬ ተከራየሁ።

በመጨረሻም እናቴ አይሆኑ ሆና የምታሳድጋቸው ልጆቼን እኔም እየላኩ ማጉረስ ቻልኩ። ውስጤ በደስታ ተሞላ። ነገ እኔም አልጋ የምይዝ ልክፍተኛ ነኝና የሰው እጅ እንዳላይ ለእኔም ቆጥቤ አስቀምጣለሁ። ስራ ስራ አድርጌ ለጉድ የፈጠራት የእሷ ሳያንሳት በልጅ ሰቆቃ የምትቀጣ እናቴ ጋ እሄዳለሁ። ያለእሷስ ማን ሊያስታምመኝ ይችላል። ዘመድ አዝማድ የለኝ። ያለዘር ተፈጥሬ ሳይሆን እኔን ለማሳደግ ስትል በምትሰራው ስራ ሁሉም ስለራቋት ነው ዘመድ ያጣሁት። አዎ!! ጭኗን ሸጣ ልጇን የምታሳድግ ሴትን ማን እህቴ፣ ዘመዴ ይላታል? እኔን ለማሳደግ የህይወትን ዝቃጭ መንገድ ተጉዛበታለች። በዛው ስቃይ ወንድም ተደግሞልኛል። በዛ ሰበብም ዘመድ አዝማድ ተጠይፏታል። ሁሉ እርቋታል ብቸኛ ነን። ለእኔም የምትኖረኝ አስታማሚ እሷ ብቻ ናት።

ማህበረሰቡ አንገዋሎ ከተፋቸው፣ ከናቃቸው ጨለማን ተገን አድርጎ ለስሜቱ ከሚፈልጋቸው ሴተኛ አዳሪዎች አንዷ እናቴ ነበረች። እናቴ ስትታመም ለማስታመም እኔም አንዷ ሆኜ ሰርቻለሁ። አሁን ደግሞ ደረሰችልኝ ብላ ስትጓጓ በቁም ያለ ሬሳ ሆንኩባት። ታሳልፍልኛለች ስትል ላልፍባት ነው። የእኔም ሀሳብ ቢሆን እሷን ከእዛ ህይወት ማውጣት ነበር። ተጨማሪ ችግር ልሆንባት ነው እንጂ ምኑን አወጣኋት? ለመከራ የፈጠረን ከመከራ የማንወጣ ሆነን። አሁን ግን ትንሽ ትንሽ እሷንም በመርዳቴ ደስተኛ ነኝ። ተስማማኝም። የሰፈር ጓደኛዬ በሰጠችኝ ስልክ ቁጥር ሁሌ እደውልላት ስለነበር ከአንድ አመት በኋላ ስራ ፈታሁ ስላት ነይ ብላኝ ወደ ሰነዓ መጣሁ።

ሰነዓ ከመጣሁ በኋላ የሚያውቁኝ ሁሉ ስስቅ ስጫወት ነው። ደስተኛ ነው የምመስላቸው። የውስጤን ግን እኔ ነኝ የማውቀው። የወንድ ጓደኛ አለመያዜን፣ ወይም የጠየቀኝን ወንድ ሁሉ እንቢ ማለቴን ጥንብ እርኩሱን አውጥቼ መመለሴ ግራ ያጋባቸዋል። ይህን ባህሪዬን የነገረችህ ካሰች[15] ነች። ሁሌ ለምን ወንድ ጓደኛ አትይዢም ትለኝ ነበር። እኔ ግን በፍቅር እብድ ያልኩበት ፍቅረኛ እንዳለኝ አድርጌ ማውራት፣ ማስወራት ጀመርኩ። የእኔ ህይወቴ በግፍ መበላሸቱ አንሶ የሌላውን ሰው ህይወት ማበላሸት አልፈልግም። ያለሁት ስደት ነው። ያውም የአረብ ሀገር ስደት ሴት ልጅ ብዙ ግፍ የሚፈጸምባት ቦታ ነኝ። በሰው ላይ ምንም አይነት

---

[15] ካሰች ለመሰረት ቅርብ ጓደኛዋ ስትሆን ካሰች ለምትቀርባት፣ ለሰፈሯ ልጅ ነግራ ነው እኔ የሰማሁት። ካሰች ሲሳይ የሳሪስ ልጅ ነች።

የበቀል እርምጃም ሆነ በእንዝህላልነት ጉዳት ላለማድረስ እጠነቀቃለሁ:: ምክንያቱም ያ-ሰው መልሶ እንደኔ አይነቷን ወገኔን (እህቴን) ያበላሻል:: ግን ምን ያደርጋል ባልፈልገውም አንድ ቀን የሰው ህይወት ማበላሸቱ ራሱ ፈልጎኝ መጣ::

ሰነዓ እንድመጣ የጠራችኝ ጓደኛዬ በ1983 ዓ.ም በስርዓቱ ለውጥ ምክንያት ወደ የመን ከተሰደዱት የባህር ኃይል ባልደረባዎች መካከል አንዱን አግብታ ነበር:: እነሱ ነገሮች ተሳክተውላቸው ወደ አሜሪካ ሲሄዱ ጠራችኝና በእሷ የምትሰራበት ቦታ ተካችኝ:: አሁን አሜሪካን ነው ያለችው ያቺ ጓደኛዬ:: ምግብ አብስላ ጥሩ ክፍያ ይከፈላታል:: እኔ እንድጠቀም ብላ ለ15 ቀን ያህል አለማመደችኝ:: አሰሪዋ ትውልደ ሀበሻ ነው:: በጣም ተግባቢ፣ ተጫዋች፣ ተላፊ ነው:: ሚስቱም ትውልደ ሀበሻ ስለሆነች በጣም ወደዱኝ:: አዳሪ እሰራና ሀሙስ..አርብን አሁን ያየሀቸው ልጆች[16] ጋር እካሰችና መስከረም ጋ ነው ያለሁት:: እነሱ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ እኔ ቤቱን አዘገጃጅቼ እጠብቃቸዋለሁ:: ሀሙስ ስለምቅም ስለማጨስ አርብ ቤተክርስቲያን መሄዱ ማርከስ ይመስለኛል:: አልሄድም::

የሚገርምህ ባልና ሚስቱ ፍቅራቸው ለእኔ ያላቸው ነገር ሁሉ ይገርማል:: ለእኔ ጎዶሎ ቀን የሆነብኝ ህዳር 12/ 2001 በኢትዮጵያ አቆጣጠር የህዳር ሚካኤልን ቡና ላፈላ ስዘገጃጅ የሚካኤልን ቡና መጠጣት እፈልጋለሁ አለኝ:: ፍቃደኛ መሆኔን ሲደርስ እንደምጠራው ነገርኩት:: የማፈላው መኝታ ክፍሌ በመሆኑ ሲደርስ ጠርቼው መጣ:: ለካ እሷ ወጥታ ነበር:: ቡናውን ጠጥቶ ብቻ ሳይሆን አስገድዶ ተገናኝቶኝ ወጣ:: ለማንም አላካፍልም ብዬ የያዝኩት በሽታዬን እንዳይጋራ ብዬ ‹‹እኔ በሽተኛ ነኝ›› አልኩት::

‹‹ይቺ..ይቺ አሁን የመጣች የሀበሻ ፋሽን ናት?››

‹‹አይደለም እመነኝ እኔ በሽተኛ ነኝ::›› መንጭቀው ልሄድ ስል ጥብቅ አድርጎ ያዘና ጣለኝ:: ብጮህም ዋጋ አልነበረውም:: የፈለገውን አደረገ:: ያልፈለኩትን ወሰደ:: በዛች ምሽት ስራዬን ጥዬ ወጣሁ:: ሶስት አመት ስሰራ ምንም ያልመሰለው የዛን ቀን ምሽት ምን እንደነካው አላውቅም በውስጥ ቁስሌ ላይ ሌላ የውስጥ ቁስል ጨመረብኝ:: አሁን ምንም ጥሩ ነገር አይሰማኝም:: ሰው አስጠልቶኛል:: በቃህ እባክህ አንተም ያው ነህ አስጠላኸኝ...የሚያቃጥል ቁስሌን ፈቀፈከው...››

ከዚህ በኋላ ምንም ላለመነጋገር ብትወስንም ጥቂት ጥያቄ በአጭሩ ብያት አሁን ወደሀገር መግባት አላሰብሽም? በዚህ ሁኔታ ሌላ ሰውም ቢያስገድድሽ የፀፀትሽን ሁኔታ የምትጨምሪ አይመስልሽም? አልኳት::

[16] ከቤተክርስቲያን ሲመጡ ሁለት ልጆች አይቼ ነበር:: ሳፊያ የሚባል አካባቢ ነበር የሚኖሩት





‹‹ፓስፖርት ስለሌለኝ በነጭ ወረቀት ለመውጣት እፈልጋለሁ:: ያ ትውልደ-ሀበሻ ያልኩህም ሰው ዛቻው አላስቀም አላስቀምጥ ብሎኛል:: ‹‹እገልሻለሁ›› ይላል:: እኔ ቀድሜ በሰው ጭካኔ የሞትኩ ሰው ነኝ:: ዳግም በሰው እጅ ልሞት አልፈልግም:: ሀገሬ እገባለሁ›› አለችኝ:: ቴፑን (መቅረጸ ድምጹን) ብትፈራም በሞባይል ስልኬ እንደቀዳኋት ነግሬያት ፎቶ ላነሳት ፍቃድ ጠየኩ:: ፈቅዳልኝ አነሳኋት:: ቤቱ ጨለምለም ያለ ስለሆነ ጎልቶ ባይወጣልኝም የጀርባ ገጹ ላይ ተጠቅሜበታለሁ::

ይህን ቃለ-ምልልስ ያደረግነው መስከረም 4 ቀን 2002 ዓ.ም ነው::

ከሶስት ወር በኋላ የሆነች ልጅ አሮሻን የሚባለው አካባቢ በመኪና ተገጭታ ሞተች:: ሬሳዋ ያለው ጁሜሪ የተባለው ሆስፒታል ነው ተባለ:: ከጥቂት ቀናት በኋላ ለብዙ ሰው በሚያደርገው በጎ አድራጎት ስራው የምወደው ኤቢ ደመቀ እና ጆኒ[17] የተባሉት ልጆች እና ሌሎች ሀበሾች ልጅቷን ለመቅበር ሰዉን ማስተባበር፣ ሳንቲም ማሰባሰብ እንደ ጀመሩ ሰማሁ:: ሆስፒታል ፍሪጅ ውስጥ የቆየው የልጅቷ ሬሳ ተቀበረ:: ከ5 ወር በኋላ ቤተክርስቲያን ስሄድ አንድ ጊዜ መሰረትን ቃለ-ምልልስ ሳደርጋት አብረውኝ ነው የሚኖሩት ያለችውን ልጅ አገኘኋት:: አላወኳትም ሰላም ብላኝ ‹‹የመሰረትን መሞት ሰማህ አይደል?›› አለችኝ::

ሰማይ ምድሩ ዞረብኝ:: የምናገረው ጠፋኝ የሰው ልጅ ከፍጥረት እስከሞት እንዴት በእንግልት ብቻ እንዲያልፍ ይፈረድበታል? እንዴትስ በአንድ ጊዜ የመከራ ቋት ይዘረገፍበታል? ለምን? ከራሴ ጋር ብዙ ብዙ ተሟገትኩ:: በራሴ ከደረሰብኝ በደል እና ፈተና ይበልጥ የዚህች ልጅ ስቃይ እና ህይወት እስካሁንም ውስጤ ጉልህ ጠባሳውን ጥሎ አለ::

[17] ኤቢ ደመቀ ይህቺን ልጅ ጁሜሪ ከተባለው ሆስፒታል አውጥቶ መቅበር ብቻ ሳይሆን በርካታ ቦታ ላይ ለወገኖቹ የሚያደርገው ድጋፍ ያኮራኛል:: ጆኒም (ዮሐንስ በቀለ) ማሙሽ የተባለውን የአዕምሮ በሽተኛ አስታሞ ቤተሰቦቹን ጎንደር•አፈላልጎ ሰዉን ሳንቲም አዋጡ ብሎ ለሀገሩ ከማብቃት ጀምሮ ለበርካታ ወገኖቹ ከባህር ሲመጡ ከረንቡላ የሚያጫውትበትን ቤት ለማደሪያነት ከመፍቀድ ጀምሮ ብዙ በጎ ሥራዎች ላይ የሚሳተፍ ልጅ ነው::

# - 17 -

# የጠላት ልጅ

እስካሁን ደህና ነኝ አልሓም`ዱሊላሂ
የከፋም ቢመጣ ላልርቅህ ወላሂ
ቃል እገባለሁኝ ከስርህ ላልጠፋ
አንተም ቃል ግባልኝ ጭራሽ እንዳይከፋ
ቀና አድርግልኝ ልጅህ አልከፋ

ዛሬ ዛሬ ስደት ውርደት መሆኑ ቀርቶ ክብር ሆኗል። ብዙ ሺህዎች ገንዘብ እየተከፈለ ሀገር መልቀቅ ዛሬ ኩራት ነው። ውጭ ሀገር ልጅ አለው፤ ልጅ አላት፣ ዘመድ አላቸው... ደረት ያስነፋ ጀምሯል። በዚህም የተነሳ ዛሬ ዛሬ ሰው እሀገር እንዳይቀር የተባለ ይመስል እንጎርፋለን - ወደ ስደት። ዘርፈ ብዙ ችግር ጠርተን ኩንታል ሰበብ ደርድረን እንሰደዳለን። ምክንያቶቻችን ብዙ ናቸው። ሰላም ማጣት፣ ኑሮ ማጣት፣ ጦም ላለማደር ሽሽት...እከሌ ሄደ ብሎ ይከፋው ይድላው ሳይታወቅ መከተል...መከተል... ጭራ ይመስል መከተል። በአብዛኛው የአረብ ሀገራት ስደት በመከተል ላይ የተመረኮዘ ነው። ችግር እንዳለ እየተነገረ ችግር እቀርፋለሁ ብሎ እሳት ውስጥ መግባት።

ሙህባ የአሁኗ እንግዳዬ ይህንን እውነታ ታስረግጥልናለች። ኢንተር ሶስ የሚባል ግብረ ሰናይ ድርጅት ከሀረጥ 3 ልጆች ተደፍረው የመጡ ህክምና እየተሰጣቸው ነው የሚል መረጃ አገኘሁና ወደዛው ሄድኩ። ከሴቶቹ (ተደፈሩ ከተባሉት) ጋር እንዳልገናኝ ሰራተኞቹ ከለከሉኝ። መኖሪያቸውን አውቄ ስለአደጋው ለመጠየቅ ቢሮ ስገባ በዘበኛ ውጣ ተባልኩ።





ውጭ ላይ ሌላ አንዲት ልጅ ታለቅሳለች ሁለቱ ያባብላሉ። ምን ሆና ነው ለማለት ስጠጋ አንደኛዋን በአይን አውቃታለሁ። ዘይነባ ትባላለች። በፊት ያስጠጉኝ ልጆች ሰፈር ነው የማውቃት። ለምታለቅሰው ልጅ ቦታውን ሊያሳዩዋት እንደመጡ ነገረችኝ። የምትፈልገውን ነገር ሊያደርጉላት ስላልፈቀዱ ነው የምታለቅሰው አሉኝ። ምን እንደ ጠየቀቻቸውም ነገሩኝ። አሁን ይበልጥ ቀርቤ ማናገር እንዳለብኝ አሰብኩ። ሙሀባ ትባላለች ብያችኋለሁ። ዘይነባ አሊና ከድጃ ይመር የሚባሉ ልጆች አብረዋት ያገኘኋቸው ናቸው። ከብዙ ቀን ማግባባት በኋላ ተሳክቶልኝ ሙሀባን ቃለ-ምልልስ አደረኳት።

«ጅቡቲ ለአራት አመት ስቆይ የዕለት ጉርሴን ከመሸፈን የዘለለ ጥንጥዬ ሳንቲም ለቤተሰቤ ልኬያለሁ። ከደከምኩበት ድካምና ከጨረስኩት ጉልበቴ፣ ካቃጠልኩት ጊዜዬ አንፃር ልፋቴ፣ ስደቴ ከንቱ ነው ማለት ይቻላል። ጅቡቲ ያለ ኢትዮጵያዊ ሁሉ አማራጭ በማጣት ነው እንጂ የሚኖረው ተመችቶት አለመሆኑን አስረግጬ መናገር እችላለሁ። ያገኘውን በልቶ ካርቶን ለብሶ የሚያድረውን..ለዕለት ጉርሱ የሚያጣውን ስታይ ሆድ ነው የሚብስህ። እኔም ብመለስ ምን እሆናለሁ የሚል እያሰብኩ አማራጭ በማጣቴ ለአራት አመት ኖርኩ። ከጅቡቲ ወደ ኢትዮጵያ ብሎም ወደ ትውልድ መንደሬ ሰንበቴ[18] የተመለስኩት በአባቴ ሞት ምክንያት ነው። መምጣቴን ሰምተው ሊያስተዛዝኑኝ የመጡ ሁለት ልጆች በሶማሊያ አድርገው ወደ የመን ሊሄዱ እንደሆነ ሲያወሩ ሰማሁ። ምናልባትም ከጅቡቲ ቢሻል ብዬ አብሬያቸው መጓዝን መረጥኩ። ለነገሩ ጅቡቲም ስሄድ እንዲሁ ልጆች ልንሄድ ነው ሲሉ ተከትዬ ነው።

ቦሳሶ እስክደርስ የገጠመኝ ሁሉ ሰዉ እንደሚያወራው አይደለም። እንዳጋጣሚ ይሁን አብረውኝ ባሉ ልጆች መንገድ ማወቅ ምክንያት ይሁን ፈጣሪዬ የተማጸንኩትን ሰምቶኝ.. በሰላም ነው የደረስኩት። በመሀል ወደ የት እንደሄዱ ሳላውቅ አብረውኝ የነበሩት ሁለት ልጆች ቦሳሶ በገባን ማግስት ጥለውኝ ጠፉ። «መጣን ገላችንን እንታጠብ» ብለውኝ ነበር አካሄዳቸው። ውሉን ባላወኩት ምክንያት ተሰወሩብኝ። የምገባበት ጠፋኝ። ያረፍነው ካሳሁን የሚባል የራያ ልጅ ጋር ነበር። ብነግረውም አይዞሽ እኔ አሳፍርሻለሁ ከማለት ውጭ እንፈልጋቸው ስላላለኝ ከፋኝ። እነሱስ ማንም እንደሌለኝ እያወቁ እንዴት እንዲህ ያደርጉኛል? ከመጀመሪያውኑ አብረውኝ መጓዝ እንደማይፈልጉ አይነግሩኝም ነበር? እያልኩ በሀሳብ ስብሰከሰክ ውዬ አደርኩኝ። ቀኑ ሌት ሌቱም ድቅድቅ ጨለማ ሆኖብኝ ስገላበጥ እንዲሁ ነገር ስገነግን..ሳኝክ ስተፋ እንቅልፍ ዝር ሳይልብኝ ነጋ። በማግስቱ ረፋዱ ላይ

[18] ሰንበቴ ለደብረሲና ቅርብ ርቀት የሆነች አነስተኛ የገጠር ከተማ ነች

መሀመድ ደሬ የሚባለው ደላላ መጥቶ ሙሀባ ሲራጅ እያለ ያጠያይቅ ጀመር:: ልጆች ጠቆሙት መሰለኝ መጥቶ «አንቺ ነሽ?» አለኝ:: ስሜን ማወቁ ገረመኝ:: ወዲያው ትዝ ሲለኝ እንደገባን ደላላ የተባሉትን ሁሉ የትኛው ከየትኛው በምን ይሻላል እያሉ ያጠያይቁ ስለነበር ነግረውት ይሆናል የሚል እሳቤ መጣብኝ:: «አዎ!..ሙሀባ ነኝ ምነው?» አልኩት::

«ንጉሱና ፉዓድ እዚህ አካባቢ ባሉ ሰዎች ተይዘዋል:: ሲደበድቧቸው ገንዘብ ስላልያዙ ዘመድ ካላችሁ አስልኩ ጆልባም እኛ እናሳፍራችኋለን ስላሏቸው የያዙት ገንዘብ አንቺ ጋር መሆኑን ስለነገሯቸው እየፈለጉሽ ነው:: ካልተደበቅሽ አይለቁሽም::..ውሰድና ደብቅልን እንዳይጎዷት ብለውኝ ነው›› አለ:: ይሄማ ወገኔ ነው አይጎዳኝም ብዬ አመንኩት:: ደግሞ ገንዘቡን እንዳይነጥቋቸው ፈርተው ይሆናል እኔ ጋ እንዳለ የተናገሩት ብዬ ገባኝ ዝም አልኩ:: ‹‹ተነሽ..›› ሲለኝ አብሬው ሄድኩኝ:: አጃጅሎ ለካ የታፈኑበት ቤት ነው የወሰደኝ:: እነ ንጉስ ገና ሲያዩኝ እንዳልናገር የሚማጸን አይነት ገፅታ እየሁባቸው:: ሴቷ ወደእኔ ስትንደረደር መጣች::

‹‹የታለ ገንዘቡ?..›› አጠያየቋ እኔ ጋ ያስቀመጠች ትመስላለች::

‹‹የምኑ ገንዘብ?» ስላት በጥፊ አጎነችኝ::› ዞረብኝ:: ወዲያው የመጣልኝ ሀሳብ ገርሞኛል:: ‹‹ውይ የያዝነውን ከሆነ ለመንገድ ተብሎ መሳፈሪያ ለአቶ ሰለሞን ከፈልኩ እኮ›› አልኳት:: ወዲያው ወደ ውጭ ወጣች እና ልጁን ጠራችው:: ተነጋግረው ተመለሰች::

‹‹አሁን አጣራለሁ:: ጉዳችሁ ይፈላል:: እናንተም አራዳ ሆናችሁ ልታታልሉን ነው? በእኛ መሳፈር ያልፈለጋችሁት ለምንድን ነው?..›› ጉዳችን እንደሚፈላ አወኩኝ:: ምን ማድረግ እንዳለብን ግራ ገባኝ ከንጉሱና ፉዓድ ጋር እንዴት ልነጋገር? ከፊታችን ቁጭ ብለዋል:: በአይን ማናገር አልሆነልኝም:: የመጣው ይምጣ አልኩ እና ዝም ብዬ ተቀመጥኩ:: የተላከው ልጅ ሲመጣ ‹‹አዎ ሶስቱም ከፍለዋል ብኋል ጋሽ ሰለሞን›› የሚል መልስ ይዞ መጣ:: ‹‹አንዳችሁ ከአንድ ሰው ጋር ሂዱና አስመልሳችሁ ገንዘቡን ይዛችሁ ኑ..›› አለች:: ንጉሱ የከፈለው እሱ ስለሆነ መልሰው ከሰጡት ለመጠየቅ ከሰው ጋር ተላከ:: እንዳመጣልኝ ተናግሬ እውነት መሆኑ ገረመኝ:: የሚያሳዝነው ግን አቶ ሰለሞን የተባለው ሰው አልመልስም አለ:: ሲደበድቡን ቆይተው ፖሊስ አስመጡና አስያዙን:: ይሄን ሁሉ ለምን እንደሚያደርጉ አላወቅንም::

ቦሳሶ ያለው ፖሊስ ጣቢያ መፈጠረህን የሚያስጠላ ነው:: ሽንት ቤቱ ፈንድቶ በታሰርንበት ክፍል መሀል ይወርዳል:: ሽታው አይጣል ነው:: ፖሊሶቹ ማታ ላይ በየተራ እየጠሩ አናገሩን:: ‹‹ለምን አታለላችኋቸው? 15 ቀን ዱቤ የበላችሁበትን ይዛችሁ ልታመልጡ ነበር አይደል? በሉ ክፍሉና





ትወጣላችሁ›› አሉን:: ቋንቋ ስለማውቅ ፈጠራ ነው ስላቸው እኔን የሚሰሙበት ፍላጎትም የላቸው:: ቋንቋ ሁላችንም የማንችል መስሏቸው የሚያስተረጉምልን ልጅ አምጥተው ነበር:: የእነሱ ያሳሰሩን ቡድን ነው:: መጀመሪያ ፉዓድን አናግረውት ተመለሰ:: ቀጥሎ ንጉስን አናገሩት:: እኔን ካናገሩኝ በኋላ የነበሩት ሶስት ፖሊስና ኢትዮጵያዊው አስተርጓሚ ናቸው:: በሩን ከውስጥ ዘግተው «ልጆቹን ማትረፍ የምትችይው አንቺ ነሽ አሉና..››

ሙሀባ ንግግሯን በእንጥልጥል ተወችውና እፍረት ስለሸበባት እቀረቀረች:: እንድትናገር ማደፋፈር ብቻውን አላናገራትም:: ‹‹ስሚኝ ሙሀባ እኔ ራሴ በዛ መንገድ ነውና የመጣሁት ሁሉን አውቀዋለሁ:: እንኳን ሴት ወንድ የተደፈረ አይቻለሁ:: የእነሱ ፍላጎት የተለመደ ነው::..ያው ሴትነትሽን እንየው ማለታቸው አይቀርም›› አልኩና መንገዱን ጠረኩላት::

‹‹እእ...! ልክ ነህ:: በቃ! ያው ያልከውን ፈለጉ:: እምቢ ብል ማን ሊሰማኝ? ማንስ ያስጥለኛል? ወገኔ ያልኩት አማርኛ የሚያወራኝ ኤልያስ የሚባለው ነው ቀድሞውኑ ሱሪውን እየነካካ ያለው:: ያው የፈለጉትን...›› ታወሳት መሰለኝ እንባዋ መጣ:: በዝምታ ጠበኳት:: ከረጅም ዝምታ በኋላ ‹‹ደሀ ሆኖ መፈጠር ምንኛ በሽታ ነው?›› አባባሏ ጠልቆ ተሰማኝ:: እውነት ነው:: ድህነት አይደል ለዚህ አስከፊ ህይወት የዳረገን? እሷ ንግግሯን ቀጥላለች:: ‹‹...አዎ ደሀ ሆኜ ባልፈጠር እንደ እኩዮቼ በተማርኩ ነበር:: ጅቡቲ ሄጄ እድሜዬን ያለ ፋይዳ ባልጨረስኩ ነበር:: ይሄው በዚህም አምጥቶ ለሰው መጫወቻ ያደረገኝ ድህነት ነው:: ልንገርህ ከምችለው በላይ ለአራት ሆነው እስኪበቃቸው ተጫወቱብኝ:: በዛ ቢበቃቸውስ? ክፍል ለይተው አስ ሩኝ:: ፍርሃት እና ጭንቀት ሊያሳብደኝ ደረሰ:: ሌሊት ላይ አንድ ሰው ገባ:: ሊለቁኝ መስሎኝ ብድግ ስል በትንሽዬ ዝርግ ሰሀን የዋለ ሩዝ እና በቆርቆሮ ሻይ አስቀምጦልኝ ወጣ:: እርቦኝ ስለነበር ጥርግ አድርጌ በላሁት:: ከተኩል ሰዓት በኋላ ተመልሶ መጣ:: ጅቡቲ ስለነበርኩ ሶማሊኛ ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም ትንሽ ትንሽ አውቃለሁ:: ‹‹ምን ፈለክ?›› አልኩና አፈጠጥኩበት::

‹‹ፍቃደኛ ከሆንሽ ያለምንም ችግር ሶስታችሁም ከዚህ እስር ቤት ትወጣላችሁ:: እንቢ ካልሽ ግን ‹ሀሺሽ ተይዞባቸው ነው› ብዬ እዚሁ ከአመት በላይ ትማቅቂያለሽ::››

አሰብኩ አሰምኩ:: የፈለገው ይምጣ ብዬ ወሰንኩ:: ‹‹ውጣ!.. አለበለዚያ እጮሀለሁ›› ይፈራል ብዬ ነው::

‹‹የጣቢያው አዛዥ እኔ ነኝ ከፈለግሽ ጩኺ...›› በጥፊ ሁለቴ አጮለኝ:: እሪታዬን አቀለጥኩት:: ሌሎች ሁለት ፖሊሶች መጡ:: በጮሁኩ ቁጥር ራሴ ላይ ችግር እንደምፈጥር ነግሮኝ እጅና እግሬን እንዲያስሩን

ለሁለቱ ነገራቸው። አሰሩኝ እና ወጡ። እንደፈለገ ተጫውቶብኝ ለእነሱ ጥሎኝ ወጣ። የመደፈር ጥሩ ባይኖረውም የእሱ ይሻል ነበር። ለሁለት ከፊትና ከኋላ ያጣድፉኝ ጀመር። አንደኛው ጡቴን አጨማመቁ ለስሜት ብሎ ሳይሆን ገንጥሎ ሊወስደው ያሰበ ይመስል በጣም አሳመመኝ።

በተከታይ ቀን የቀን ተረኛዎቹ ሲጫወቱና እነሱ ሲሄዱ ደግሞ የማታዎቹ እንደዛው..ብቻ ተወው። ሰው አልመሰልኳቸውም። የሰውነት አዘኔታም ያላቸው አይደሉም። ለነገሩ እነሱ ባያዝኑ ምን ይገርማል የሀገሬ ልጆችስ ጨክነውብኝ የለ። በዚህ ሁኔታ በቀን አንዳንድ ዳቦ እየሰጡ ሶስት ቀን አሰሩን። በሶስተኛው ቀን ልጆቹ ወንጀል ሰርተው ታስረዋል ጀልባውን አልተሳፈሩም ገንዘቡን መልስላቸው ብለው ሰለሞንን ተቀበለውታል። ለካ አላማቸው በማግስቱ ልንሄድ ስለነበር አስቀርተው ገንዘቡን መውሰድ ነበር። ገንዘቡን ሲወስዱ እኛን ለቀቁን። ብሩን ፖሊሶቹ እና ያሳሰሩን ተካፍለው በሉት።

በምናችን ባህሩን እንሻገር? ቀይ መስቀል ተመዝግበን በቀን አንዴ የሚያበሉትን ምግብ እየጠበቅን እየበላን ለፋዓድ ከሳዑዲ ወንድሙ ገንዘብ እስኪልክለት ተወር በላይ ተቀመጥን። ሲላክለት ተሻገርን። ደግሞ ባህሩ ላይ ንጉስን ሶማሌው ካልተኛሁህ አለው። እንቢ ቢለው ደበደቡት። ወደ ባህር ጣሉት። ብንጮህ ብናለቅስ ትርፋችን ዱላ ሆኖን መሬት ረገጥን። አይናችን እያየ ባህር በላው።››

እንባዋ ጉንጯን እያጠበ ቁልቁል ወረደ። ታማ ከተኛችበት መኝታ ቀና ለማለት ሞከረች። አቃታት። «ታዲያ ለምን ኢንተር ሶስ ሄድሽ? የጤና መታወክ ገጥሞሽ ወይም ድጋሚ መደፈር ደርሶብሽ?» ስል ጠየቅኳት።

‹‹አይ አንተ! የበፊቱ አልበቃ ብሎ ድጋሚ? የመን ከገባሁስ ምንም አልነካኝ። እናቴ አብልተው በመኪና ሸኝተው ነው እዚህ የደረስነው። የሚገርምህ ጅቡቲም ስቆይ አንድ ነገር እንዲህ ያለ መልክስክስ አልገጠመኝም። ሶማሌ ነው ጉድ የሰራኝ። አሁን ጸንሼ ነበር። እሱን ያባርሩልኝ (ያስወርዱልኝ) ብዬ ነዋ! ይንተር ሶስ የሚሉ የሄድኩ..ተገድጄ ስደፈር የመጣ ልጅ ላኖረው ነው ገድዬው በወንጀል ልጠየቅ?..የእነዛን አረመኔ የሶማሌ ፖሊሶች ልጅማ አሳድጌ እድሜዬን በንዴት አልኖርም…››

ልክ ነች ስል አሰብኩ። ግፍ የፈጸሙብንን ሰው ልጅ ወልደን የምሳደግ ስንቶቻችን ነን? ድፍረቱስ ፍላጎቱስ ይኖረን ይሆን? ምን አይነት አስቸጋሪ ነገር ነው? እንዴት ያደርጓት ይሆን?

‹‹ታዲያ ምን አሉሽ?›› ለማወቅ ጓጓሁ።





‹‹አይሆንም፤ እንዲህ አይነት ነገር አንሰራም ብለው ከቸቹ። እኔ ደግሞ እሞታታለሁ አልወልድም..አልኩ። እነሱም ይሄ ጽንስን ማስወረድ የእኛ ተግባር አይደለም እያሉ ነበር። እኔ መርዝም ቢሆን ጠጥቼ እሞታለሁ እንጂ ይህን የሴጣን ቁራጭ አልወልደውም። ብወልደው እንኳን እገለዋለሁ።››

አባባሏ ሰቀጠጠኝ።

ግን ምን ታድርግ? እሷ ቦታ ብሆን ምን ነበር የማደርገው? እናንተስ? ውሳኔያችሁ ምን ይሆን ነበር? መውሰድ ወይስ ማስወረድ? አስገድዶ፣ አስሮ፣ ደብድቦ ..የደፈረን ሰው ልጅ ወልዶ ለማሳደግ ማሰቡ ራሱ ይከብዳል። ህሊናንም ይጎዳል። ግን በርከት ያሉ ጥቃቱ የገጠማቸው ሰዎች ‹‹ላም እሳት ወልዳ እንዳትልሰው ፈጃት እንዳትተወው ቆጫት…›› እንዲሉ አይነት ሆኖባቸው ወልደው የሚያሳድጉ ሞልተዋል።

በመጨረሻው ላናግራት የሄድኩ ቀን በጣም ታማ ነበር። ያዘኑላት ሰዎች ገንዘብ አዋጥተው ሰጧት። ጽንስ የሚያጨናግፍ መርፌ አስወግተው ያልተፈለገውን ጽንስ አስወግደውላት እንዳስወረዷት አወቅኩ… በእጅጉ ታማ ነበር። ብሞትም አንድ ሰው ይስማኝ ብላ ነው ስለሁኔታው የነገረችኝ።

ተሰባብቻት ስወጣ ግን አብረዋት ከነበሩት መካከል ንጉስ የሚባለውን ባህር ላይ ወረወሩት ያለችኝ ደግሞ ደጋግሞ ታሰበኝ። ፋዓድስ የት ይሆን? ሳልጠይቃት የሚል ሀሳብ መጣብኝ…ግን ወዲያው ሌላ ሀሳብ ውስጤ ተጸነሰ።…ከተስፋይቱ ምድር ሳዑዲ አረቢያ ከትሞ ይሆናል የሚል። ይህ ሁሉ ስደተኛ የሰው ልጅ ስቃዩን የሚያይባት ሳዑዲን የተስፋ ምድር አድርገው ተጓዦች ናቸው። ወይ መረጃ ማጣት…

# - 18 -

# ማንም ፈልጎ አይሸረሙጥም!

ህገጋቱን ጥሰን ሆነን እራሙቻ
ተጣድፈን ለሲኦል ለሀጢያት ዘመቻ
በሱስ ተጠምደን ስንናውዝ ቢያይ
ዘማዊነት ነግሶ ምድር ስትጨቀይ
ንገሩኝ እስኪ ምናለ እግዜሩ
እሳዘነ ይሆን ሰውን በመፍጠሩ?

ወደንም ሆነ ሳንወድም የምንሰራው ስራ ለሀገር ሊያኮራም ሊያሳፍርም ይችላል፡፡ ሊያኮራ የሚችለው የግድ ባንዲራ አውለብልበን አለያም በምርምር ግኝት አስመዝግበን ብቻ አይደለም፡፡ ከሀገር፣ ከቤተሰብ፣ ከቀዬ አርቆ ያስወጣን አላማ አሳክቶ መመለስም ለቤተሰብ ማጉረስም ኩራት ነው፡፡ የሚያሳፍረው ዓላማ የለሽ ሆኖ ዝቃጭ ኑሮን መግፋት እንዲሁም መጥፎ ቦታ ተሰልፎ መገኘት ነው፡፡ በአረብ ሀገር ያሉ ሴቶችም ሆኑ ወንዶች የሚሰሩት ነገር ከዚህ የተለየ አይሆንም፡፡ ያኮራል አለያም ያሳፍራል፡፡ እንደአለመታደል ሆኖ ጥቂቶች ከደረሰባቸው መከራ ለመውጣት ያላቸው ብቸኛ አማራጭ ይሆንና እንደዋዛ መጥፎውን ድርጊት ይገቡበታል፡፡ ከ70% እና ከ80% በላይ የሚሆኑት ለሽርሙጥናም ሆነ ለሌላ አስከፊ ስራ የሚዳረጉት ወደው እንዳልሆነ ካነጋገርኳቸው ሰዎች ለማወቅ ችያለሁ፡፡ መጥፎ የሚባለው ህይወት ውስጥ እንዳይገቡ ማድረግ የሚቻለው እንዴት ነው? የሚለውን ማሰብ ግድ ይላል፡፡ ምላሹም ለስራ ሲሄዱ የሚፈጸምባቸው ግፍ እንዲቆም ማድረግ ብቸኛው አማራጭ ነው፡፡





ህይወት ጉዞዋ እኛ በፈቀድነው ብቻ ሳይሆን ባልፈቀድነውም ይሆንና ያላሰብነው አረንቋ ውስጥ ትዶለናለች፡፡ በአንድ ወቅት ዱባይ የመኖሪያ ፍቃድ የሌለውን ማፈስ ተጀመረ፡፡ ይህ ችግር ሲከሰት አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ስደተኞች መኖሪያ ፍቃድ አልነበረውም፡፡ ምክንያቱም በኮንትራት ስራ እየሄዱ በሚደርስባቸው ግፍ ተማረው ሲጠፉ ፓስፖርታቸው ቀጣሪዎቻቸው እጅ ስለሚቀር ነው፡፡ ታዲያ አፈሳው መኖሪያ ወረቀት ለሌለው ሰሪ በአንገት የማስወለቅ ያህል ከባድ ምጥ ነበር፡፡ ከተያዙ የአይን አሻራ ተነስተው ወደ ሀገራቸው ይጠረዛሉ/ይላካሉ/፡፡ ማንም አይን አሻራ የተነሣ ስደተኛ ደግሞ በድጋሚ ወደ ዱባይ መመለስ አይችልም፡፡ ስለዚህ ስደተኛው የነገ ሕይወትን ችግር ውስጥ ላለመክተት ያለው አማራጭ ሳይያዝ በራሱ ጊዜ ሀገር ገብቶ በቪዛ ዳግም ወደዱባይ መግባት ነው፡፡ እናም ስደተኞቹ ሳይያዙ ወደኢትዮጵያ ለመግባት በየመን በኩል እንደጉድ ይጎርፉ ጀመር፡፡ ይሄ ደግሞ በህገ-ወጥ አንጓጕች ነው የሚከወነው፡፡ ምክንያቱም የመን የዱባይ ድንበርተኛ ስላልሆነች የኦማንን ድንበር ጥሶ በጨለማ በጫካ መጓዝ ግድ ነው፡፡ በዚህ አስቸጋሪ የጉዞ ወቅት በየመንገዱ የተደፈሩ፣ የታሰሩ፣ የተዘረፉ እና ሌሎች ብዙ ችግሮች ያስተናገዱ ሞልተዋል፡፡ በለስ ቀንቷቸው ምንም ሳይገጥማቸው የገቡም በርካታ ናቸው፡፡

ብቻ ምንም ይሁን ምን ተጠርዞ ከችግር እና ስራ አጥነት ጋር ሀገር ቤት ገብቶ የቤተሰብ ጥገኛ ከመሆን የደረሰውን ግፍ ተቀብሎ የመን መግባት አማራጭ የሌለው ብቸኛ አማራጭ ነው፡፡

በዛን ወቅት የመን የመጣችሁ ከህገ-ወጥ አንጓጕቹ ጀምሮ በየመንገዱ እያንዳንዳችሁ የደረሰባችሁን መከራ ታስታውሳላችሁ፡፡ ዱባይ ያላችሁ፣ ወደሌላ ሀገር የተዘዋወራችሁም ሆነ ኢትዮጵያ የገባችሁ የምትረሱት አይደለም፡፡ በፖሊስ ተይዘው ሲደበደቡ የከረሙ፣ ገንዘባቸውን የተነጠቁ፣ ጥቂቶች የተደፈሩ ነበሩ፡፡

እዚህ የመን ውስጥ ጉዳያችሁን አስፈጽማለሁ ብለው አሳር መከራችሁን ያሳዩዋችሁ ብዙ ወገን ተብዬዎች ነበሩ፡፡

እዛ(ዱባይ) የምትሰሪውን እዚህም ስሪ ብለው አሳልፈው ለአረብ የሸጧችሁንም ታስታውሳላችሁ ብዬ አስባለሁ፡፡ ሰነዓ ዳይሪ አካባቢ አንድ ከእኔ ጋር የተያያዘ ክፍል ቤት የተከራየ አንዋር (ስሙ የተለወጠ) የሚባል አረመኔ፣ እንዴት ጥቂቶቻችሁን የማገት ያህል ለፖሊስ አሲዛችኋለሁ ብሎ እያስፈራራ ገንዘባችሁን ነጥቆ፣ ሴትነታችሁን ጠልቆ እንደተጫወተበት አውቃለሁ፡፡ ወገኖቹን ያሰቃይ የነበረ በፊት የመን የኖረ ከዱባይ ከመጣ አረመኔ ጋር ተጠማምዶ ነበር፡፡ ጉዳይ አስፈጽማለሁ ብለው የወገናቸውን

ደም ከሚመጡት አንዱ ይህ ሰው ሲሆን ጎረቤቴ በመሆኑ ሁሉን ለማየት በቅቻለሁ።

በአንዴ 40ና 50 ሰው እያመጣ የሁላችንም ቤት አቅሙ እስከፈቀደ አስተናግዷችኋል። እኔ በዛውም መረጃዬን ሰብስቤያለሁ። ከሰባት ልጆች ጋርም ቃለ-ምልልስ አድርጌያለሁ። ለአሁን የአንዷን ላቅርብላችሁ።

ደስ የሚል ቁመና ያላት «..ቁመትሽ ሎጋ ነው የእኔ አለም..» የምታሰኝ ጠይም ናት። የደስ ደስ ያላት። ከጊዜያዊ ምቾት ውጭ ድህነት ሽንቁጥ አድርጎ እንዳሳደጋት የሚያስታውቅ ገጽታ አላት። ይህ ደግሞ አዲስ ነገር አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብ 95 ከመቶ የቀመሰው ጽዋ ነው።

ከዱባይ በአማን አድርጎ ያመጣቸው ሰው 16.000 ድርሀም ዘርፏታል። ሁሉም ሲሰሙ ደነገጡ። «..በቃ! አይዞሽ አንቺ ጤና..» ከሚል ማጽናኛ ጀምረው ብዙ ማባበያና መረጋጊያ ቃላት አዋጥተው ጣሉላት። አንዷ «ባክሽ ሼባውን ላክልኝ በይው» አለቻት - በሀዘኔታ ራሷን በራሷ የመሳም ያህል ደጋግማ ከንፈርዋን መጣላት ስታበቃ።

«ወዶ ነው የሚልከው!..» ካለች በኋላ ሞባይል ስልኳን አንስታ ቁጥር ነካካች። ይጠራል አይነሳም። መደወሉን ተወችውና ጨዋታቸውን ጀመሩ። በመሀል አንዷ «16000 ድርሃም በኢትዮጵያ ስንት ነው?» ስትል ጠየቀች። «ወደ 35000 ብር አካባቢ መሰለኝ» አለች ሌላኛዋ።

«ወይኔ! እንዴት ተጎድተሻል?..» ብላ ምንዛሪውን የጠየቀችው ልጅ በሀዘኔታ ስትናገር የጠፋባት ልጅ ግን ምንም ሳይመስላት «ተዉት!.. ተዉት ተመልሼ ስሄድ በአንድ ሳምንት ጠባ.. ጠባ ባደርግ የማገኘው ነው...» አለች የቀልድ እያስመሰለች አውራ ጣትዋን ቀጥ አድርጋ ወደ አፏ እያስጠጋች። ጠላታችሁ ድንግጥ ይበል አመዴ በነነ። በየቋንቋው ሁሉ የድንጋጤ አይነት የተለያየ ከሆነ የሁሉንም አይነት ድንጋጤ ደነገጫለሁ ማለት እችላለሁ። የዚህ ዓይነቱ መረንነት ከየትኛው ዩኒቨርስቲ ይሆን የተማረችው? ይህንን እያሰላሰልኩ ብቻዋን የማናግርበትን ሁኔታ አቀድኩ። ያለሁት ቤቴ ውስጥ አይደለም። አንዱ ቤት ውስጥ ያለውን አራት ክፍል ቤት ለአራት ነው የተከራየነው። ሁለቱን ክፍል 2 ባልና ሚስቶች ሁለቱን ደግሞ ወንደ ላጤዎች ነን የተከራየነው። የመን ሰዉ ሰብሰብ ሲል ጫት መቃም የተለመደ ነው። ሚሚ የምትባለው ባለትዳር ሴት ጋ ተሰብስበው እየቃሙ ነበር።

እንደ ወትሮዬ ብየዳ እሰራበት ከነበረው ድርጅት ደክሞኝ «..ብቸኝነቴን ነው እኔ ማስታውሰው..» ለማለት ወደ ክፍሌ ስገባ ነው ጠርተውኝ የተቀላቀልኳቸው። ካልጠሩኝ በሬን ዘግቼ ብቻዬን መቀመጥ ነው የምወደው። ግን አሁን ደግሞ ከዱባይ የመጡት እንግዶች ቴሌቪዥን





ማየት ይፈልጋሉ። አረፍ ማያ ቦታ ይፈልጋሉ። ለዚህ ስል በሬን ሳልቆልፍ ነው የምሄደው። ባይጠሩኝ ኖሮ ስል ተመኘሁ።

አባባሏ አስጠላኝ። ተነስቼ ብወጣ ሁሉ ወደድኩ። አብዛኛዎቹ የየመንን መቆሸሸ አይተው እነሱ የዘመኑ፣ እኛ ኋላቀር የቀረን ሁሉ ስለሚመስላቸው የሚያደርጋቸውን፣ የሚሰራቸውን ያሳጣቸዋል። በዛ ያሉት ሺሻ ላይ አፋችሁን ለጉሙ የተባሉ ይመስል ተያይዘውታል። እየማጉ የሚተፉት ጭስ ቤቷን ኩሽና አስመስሏታል። እርግጠኛ ነኝ የእናታቸውን ጡት እንኳን እንዲህ አልመጠጡም። ከጡጦ ቀጥታ ወደሺሻ የተሸጋገሩ ነው የሚመስሉት። ዱባይ እንደየመን ጫት ስለማይገኝ ሻይ ቅጠሉን ከካሮት ወይም ከመቅዶኒስ ቅጠል ጋር እንደጫት ጉንጫቸው ውስጥ ወጥቀው ተክዚና መያዝ ለምደዋል። አሁን የመን ላይ ደግሞ ጫቱ ራሱን ወጥቀውታል። ከመካከላቸው ሁለቱ ልጆች ግን ዱባይ የለመዱትን ነው ያደረጉት። እኔም የዚያኔ ነው ዱባይ የተክዚናቸው ምስጢር ያወኩት። ምስጢር ካወጣሁ ይቅርታ!! ዱባዮች።

ግማሽ የሚሆኑት ከምኑም የሌሉበት የእህል እና ውሀ ሱስ ብቻ ያለባቸው ናቸው። እነዚህ ጨዋታቸው ደርዝ ያለው በእርጋታ የተሞሉም ናቸው።

ከላይ የጠቀስኳት ልጅ ስልኳ እረፍት የለውም። እሷም ጎበዝ ደዋይ ነች። አንዱ ጋር ትደውልና «ያ-ባባ መንገድ ላይ እኮ ተዘረፍኩ። አንተ ነህ እዛ ከደረስኩ በኋላ ላክልኝ ስልህ...» ይሄ እኮ ያ-ባለሆቴሉ ነው ትላቸዋለች አብረዋት ላሉት። ትንሽ ትቆይና ደግሞ ትቀጥላለች «..ወላ! ወላ! አሁን ካርድ መግዣ የሚሆን ሳንቲም እንኳን የለኝም። ዛሬውኑ ላክልኝ...» ስልኩ ይዘጋል። ዱባይ የሚጠቀሙበት ቁጥራቸው ስለሆነ ሲደውሉም ሲደወልላቸውም ይቆጥራል። ሌላው ጋር ይደወልና ካርድ ግዛና ላክልኝ ይባላል። ይሄኛው ደግሞ ገና ዱባይን ስረግጥ የገባሁበት ቤት የሴትዮዋ ባል ነው። በጥርጣሬ ልትገለኝ ሆነ ገፋሁበት በቃ!.. እንደገና ትደውላለች። ይሄኛው.. ደግሞ ከፍሬሀይወት ጋር የተደባደብንበት ነው። ...ጉድ ነው ድንገት ግሩም ብልግና አወዳድሮ ይሸልማል ብለዋት እንዳይሆን እንዲህ የምትሆነው አልኩና ተነስቼ ክፍሌ ገባሁ። ያወቀች የዘመነች መስሏት ደርዝ አጣች።

ወደ ሀገር የሚገቡበትን ጉዳይ አስጨርሳለሁ ብሎ ያመጣቸው ልጅ ገንዘብ እንደ ተላከላት ካወቀ እንደሚነጥቃት ስላወቀች በእኔ መታወቂያ በስሜ ከሁለት ሰው ተልኮላታል። የሚገርመው ግን አንዴ ካወጣሁላት ላይ ሁለት ሺህ ድርሃሙን ለሱዳናዊ ባሏ ልኬያለሁ። የባልዋን ስም ነግራኝ ላክለት ብላኝ እኔም ልኬያለሁ። ግን ከእነዚህ ሁሉ በልታ ለሱ እንዴት

እንደላከች ጠየኩ:: ..እጋጣሚዎች ተገጣጠሙና ጉዳይ የሚጨርስላቸው እና ያስመጣቸው ሰው ከሚስቱ ሲጣላ ሸሽተው ሶስት ሆነው እኔ ቤት አደሩ:: መኝታዬን ለቅቄላቸው አረቢያን መጅሊሱ ላይ ጋደም ብዬ መረን ከለቀቀችዋ ልጅ ጋር ማውራት ቀጠልን:: ሁለቱ ሸለብ አድርጓቸዋል:: ለምንድን ያንን መረን ቃል እንደተጠቀመች፣ ድርጊቱን ብታደርገው እንኳን እንደጀብድ በዛ ሁሉ ሰው መሀል ማውራቷ አግባብ እንዳልሆነ ነገርኳት:: ሌሎቹንም ወደዛ ተግባር መምራት ነው::

ፊቷ ልውጥውጥ አለ:: እፈጠጠችብኝ:: ሶስት አራት የተሻሻሉ የብልግና ስድቦችን እንደምትለጥፍብኝ እርግጠኛ ሆኜ ጠየኳት::

‹‹እኔ ነኝ ወደብልግና የምመራቸው? ራሱ መከራው፣ ስቃዩ፣ መሮጫ ማምለጫ ማጣቱ ሳይወዱ በግድ ወደዛ ይመሯቸዋል:: ስማ! ማንም መሸርሞጥ ፈልጎ አይሸረሙጥም:: ማንም ለመሸርሞጥ ብሎ ከሀገሩ አልወጣም..›› እንባዋ ተንደርድሮ ዋትራስ ልብሴን አጠመቀው:: ላባብላት አልሞከርኩም:: የስደት እንባ ማፍሰስ እጣቢ ውሀ የመድፋት ያህል ቀላል ነው፤ እኔም እስኪበቃኝ ቀምሼዋለሁ::

ጋደም ካለችበት ቀና ብላ በአትኩሮት ስታየኝ ቁስሏን እንደነካኋት ታወቀኝ እና ተጸጸትኩ:: ቢሆንም ቁስሏንም፣ ያቆሰላትን ታሪክም ለማወቅ ጓጓሁ:: እናም የበለጠ ልቧን እንዳላደማው እየፈራሁ በጥንቃቄ ጥያቄዬን ሰነዘርኩላት:: በአንዴ ቅላትን ባስተናገደ ድፍርስ አይኗ ገልመጥ አድርጋኝ

‹‹ምን ማወቅ ፈለግህ? ለምንስ?..›› አስተያየቷ ያስፈራል:: ቢሆንም ከጀመርኩ ወደኋላ ማለቱ ይብስ ነገሮችን ማወሳሰብ ስለመሰለኝ ረጋ ብዬ ሃሣቤን አስረዳኋት:: ‹‹ከነገርኩህ ትጠየፈኛለህ፣ እንደሰው አታየኝም ግን ምንም አይመስለኝም:: ደግሞም መስማት ከፈለክ ጆሮህ እስኪግል እነግርሃለሁ:: ያኔ ወደሽ ነው የሸረሞጥሽው ካልከኝ ለእንተም ቪዛ እልክልሀለሁ ናና ከነአለማየሁ ጋር(ወንድኛ አዳሪዎችን ነው የጠራችልኝ) ሊፒስትክህን ተቀብተህ ወደህ ሸርሙጥ::››

‹‹በፍፁም ወደሽ የምታመጪው ነገር እንደሌለ አውቃለሁ›› አልኳት:: በእርግጥም እስካሁን ካነጋገርኳቸው ልጆች የተረዳሁት ነገር ይህንኑ ነው:: አይኖቿ እንባ ጨርሰው እስኪደርቁ እያለቀሰች አወጋችኝ:: እግዚአብሄር ይመስገን አገዝኳት:: የእኔም እንባ እጢዎች ስራ አልፈቱም:: እዚህ ጋር አንዳንድ ጸያፍ ቃላትን በራሴ ቋንቋ ለማለዘብ ሞክሬያለሁ::

‹‹ጠባ.. ጠባ.. ስላልኩ ነው የገረመህ? ረጅም ታሪክ አለው:: ግን ድርጊቱን እየፈጸምኩ ጠራሁት አልጠራሁት ምን ለውጥ አለው? ይሄ ባህላችን፣ ስርዓታችን.. ቅብርጥሴ የምትሉትን ነገር አስበህ ከሆነ ተወው:: ባህል ስርዓት ቅብርጥሴ እያለ የሚጀነነው ማህበረሰብ እንገዋሉ ከተፋቸው





ምስኪኖች ተወልጄ ነው ለዚህ ሁሉ መከራ የተዳረኩት:: ታዲያ ወግ ስርዓት ለእኔ ምኔ ነው? ቁርስ አልሆነኝ ምሳ...››

ቀጠለች እኔም የእሷን ታሪክ ቀጠልኩ..... ‹‹ለኮንትራት የቤት ሰራተኝነት ነው ዱባይ የሄድኩት:: ሴትዮዋ በስራ የምታሰቃየኝ አንሶ ለወሲባዊ ስሜቷ አሳሬን ታሳየኛለች:: ስራዬን አስትታ ሻምር እንግባ ትለኛለች፤ መኝታ ቤት አስገብታኝ በር ትዘጋለች:: ሰውየው ደግሞ በሌላ በኩል ፍዳዬን በላሁ:: ሌሊት ይመጣና ሴንጢ ደቅኖብኝ ‹‹..እርጂ ቆሻሻ ውስጥ እጥልሻለሁ..›› ብሎ ብልቱን አፌ ላይ ይደቅናል:: ያለቻቸውን አንድ ጥሪት የቤት ካርታ አሲዘው ብር ተበድረው ታሳልፍልኛለች ብለው የላኩኝ ቤተሰቦቼ ነገር ትዝ ይለኝና ብድራቸውን እንኳን ሳይከፍሉ ባለእዳ አድርጌያቸው ቤታቸውን አስወርሼ ጎዳና ተዳዳሪ አድርጌያቸው ልሞት? እልና የታዘዝኩትን እፈፅማለሁ፤ እሱም የፈቀደውን ያደርጋል:: ማዳሚ በልምምጥም ገንዘብ በመስጠትም የተጣባትን መጥፎ አባዜ ትወጣለች:: በአንድ ወቅት ለሳምንት ወደአቡዳቢ ሊዝናኑ ሲሄዱ እሱም ለራሱ ሲል እሷም ለራሷ ስትል አብሬያቸው እንድሄድ ፈለጉ:: ልጆቹ ደግሞ ለእኛ ማን አለን ሲሉ ቅሪ ተባልኩ:: እግራቸው ወጣ እንዳለ እሱም በበኩሉ ያስቸግረኝ የነበረው ትልቁ ልጅ ሰባት ጓደኞቹን ለአራት ስለጠራ ምግብ እንዳዘጋጅ ነገረኝ:: የቻልኩትን ሰራሁ::

ልጆቹ ማታ ላይ ተሰባሰቡ:: በሉ ጠጡ ሙዚቃ ከፍተው ይጨፍሩ ጀመር:: አንዴ እንዲህ አድርጊ ሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲህ አድርጊ ሲሉኝ ሰደክም አመሸሁ:: እስካሁንም ያልገባኝ ነገር ያጨሳሉ:: ሀሺሽ አልመሰለኝም:: በኋላ ጠርተውኝ ስሄድ መሀል አስገብተው ይጎነታትሉኝ ጀመር:: እንደአሻንጉሊት አደረጉኝ:: አንደኛው ከኪሱ የሆነ ብልቃጥ አውጥቶ መሀረብ ላይ ሲያፈስ አየሁት:: ሁለቱ እጄን ግጥም አድርገው ሲይዙኝ አፌና አፍንጫዬ ላይ አድርጎ አፈነኝ:: ከዚህ በኋላ ምን እንደተፈጠረ አላውቅም:: ከስንት ቀን በኋላ እንደ ነቃሁ እግዚአብሄር ይወቅ:: ስነቃ የተኛሁበት ቦታ በደም፣ በሽንትና የቀጠነ ሰገራ ተጨማልቋል:: ሽንቴም ምኔንም እዛው ስለቀው ነበር ማለት ነው:: ሰውነቴ ላይ ሁሉ ደርቋል:: ሽታው ለራሴ አስጠላኝ:: ለመነሳት አልቻልኩም:: ጭኔ መሀል ያለው ቁስለት በዋዛ የሚያንቀሳቅሰኝ አልመሰለኝም:: ያለሁበትን ቦታ ማወቅ አልቻልኩም:: በጣም የቆሸሸ፣ አቧራ የጠገበ እና በአሮጌ እቃዎች የተሞላ ነው:: ግራውንድ መሰለኝ:: በዚህ ቤት አራት ወር ከአስራ ሰባት ቀኔ ነው:: ግን አደጋው እስከተፈጸመብኝ ሰዓት ድረስ ቤቱ ግራውንድ እንዳለው አላውቅም::

ሁለቱም እግሬ ስላልታዘዘልኝ እየተንፏቀኩ ደረጃውን እንደምንም ወጣሁት። ሁለቱ የሴትዮዋ ልጆች ሲያዩኝ እንደመዝናኛ ፊልም በእንፋቅቂ ይስቁብኝ ጀመር። አለቀስኩ አይዞሽ ባይ በሌለበት በጣሙን አምርሬ አለቀስኩ። ለቅሶዬ ለእነሱ ደስታ ፈጥሮባቸው ሲንከተከቱ እኔን ግን ለበለበኝ። ተመልሼም ወደነበርኩበት ግራውንድ ወረድኩ። መታነቅ ነው ፍላጎቴ....ገመድ ብፈልግ ከየት ላግኝ? መርዝ ነገርም ፈለኩ። ግን ምንም አላገኘሁም። ወይ አለመታደል ለካ ራስን ማጥፋትም ከባድ ኖሯል ደግሞም ፀሀባቤ እናቴ ታየችኝ። አባቴ በዘበኝነት የሚያገኛትን ገቢ የሚጠብቁ ታናናሾቼም ታዩኝ። የበለጠ ደግሞ ወታደር እያለ የሰራትን ቤት እንደሚያጡም ሳስብ ሰቀጠጠኝ። ሞቴ ብዙ ነገራቸውን እንደሚያጨልመው ፀተቃራኒው ተስፋቸው፣ በልቶ ማደራቸው፣ መጠለያ ይዞ መቆየታቸው ሁሉ በእኔ ላይ የተጣለ ሀላፊነት እንደሆነ ሳውቅ ራሴን ጠላሁት።

እንደምንም እግሬን አንፈርክኬ ለመቆም ሞከርኩ። አቃተኝ እና ወደኩኝ። ሰወድቅ ጓ!... የሚለውን ድምጽ ሰምተው ልጆቹ መጡ። ሲመታኝ አለመጎዳቴን አይተው የሚበላ ነገር አምጥተው እንደውሻ በሰሀን ወረወሩልኝ። እህሉን ሳየው ጠንከር ያለ ርሃብ ተሰማኝ። ሽንቴን ሽንቼ የተጨማለቀ ሰውነቴን ታጥቤ ለመብላት ግርግዳ ተደግፌ እየተሯመድኩ መጸዳጃ ቤት ገባሁ። ሽንቴ የምጥ ያህል ሲያስቃትተኝ ቆይቶ ያደናገጠኝ ነገር ዳግም ገጠመኝ። ሰሸና ማቃጠሉ እና በደም መታጀቡ ብቻ ሳይሆን ከሰገራዬ ጋር ተቀላቅሎ መሆኑ አደናግጦኝ ነበር። ይበልጥ ደግሞ ያደናገጠኝ ህመሙና ማማጡ ነው። አሁን ራሴን የማጥፋቱ ፍላጎት ዳግም ውስጤ አቆጠቆጠ። ቁስለቱም ከውስጤ ይቆጠቁጠኝ ጀምሯል። በዚህ አይነት ሁኔታ እንደማያኖሩኝ ታሰበኝ። ይጠርዙኛል ችግራቸውን አብዝቼ እንዲህ ሆኜ አይተው ሰቀቀን ከምሆንባቸው ራሴን ማጥፋቱን መረጥኩ።

በእንደዚህ አይነት ሁኔታ መኖር አልፈቅድም። የፍራሹን ጨርቅ ባለ በሌለ ሀይሌ ቀድጄ ሸምቀቆ አድርጌ አሰርኩና የደረጃው መደገፊያ ብረት ላይ አሰርኩት። እንደምንም ራሴን ከተትኩት። ግን እንዴት ያስፈራል? ጣር ይዞኝ የማውጣውን ድምጽ ሰምተው ተሯሩጠው ገመዱን በጠሱት። ተዝለፍልፌ መሬት ስወድቅ አንደኛው በእርግጫ ጠለዘኝ። ለሁለት እንጠልጥለው የመኪናው የኋላኛው እቃ መጫኛ ውስጥ ከተቱኝ። አንደኛው ምን ሊያመጣ እንደሆነ እንጃ ሮጦ ወደ ውስጥ ሲገባ በኮቴው ድምጽ ታወቀኝ። ከፊት አደረገና የሆነ ፌስታል አምጥቶ ላዬ ላይ ጣለው። ከተማውን ስለማላውቅ ወዴት እንደወሰዱኝ አላውቅም። የሆነ ዘዋራ ስፍራ ላይ ከመኪና አውርደው ሲጥሉኝ ፌስታሉንም አጠገቤ አስቀመጡልኝ። መኪናቸውን አስነስተው ሲሄዱ ያለሁበትን አካባቢ ዞር ዞር ብዬ ቃኘሁት።

ቆሻሻ መጣያ ቦታ ነው። ገንዳዎች አሉበት።





አንዲት እንጀራ ፍለጋ ከሀገሯ የተሰደደች ምስኪን ከርታታ ቆሻሻ ተብላ ቆሻሻ ቦታ ብትጣል እነሱ ምን ተዳቸው? እኔ ግን በድህነቴ፣ በእድሌ አለቀስኩ። በፈጣሪዬ አዘንኩበትና አለቀስኩ። ለምን እንዲህ ሲያደርጉኝ ዝም አለ? ለምን ፈጠረኝ አልኩ። እኛ ለአረብ መጫወቻ ነው የተፈጠርነው ስል አለቀስኩ። አልቅሼ... አልቅሼ... አልወጣልሽ አለኝ። ምን ያህል ሰዓት እንደቆየሁ አላውቅም። በለቅሶው፣ ድካምና ህመሙ የተነሣ አሸለበኝ። አጠገቤ አንድ ሰው ቆሞ ሲያናግረኝ ነው የነቃሁት። የምችለውን ያህል ነገርኩት። በታክሲ ወስዶ ከሀበሻዎች ጋር አገናኘኝ። /ከተኙት ሁለት ሴቶች አንዷን አሳየችኝ። አፏን ገርበብ አድርጋው ያለሀሳብ ተኝታለች/ መጀመሪያ ካገናኘኝ ሁለት ልጆች አንዷ ናት። አዘኑልኝ አጥበው የሚበላ ነገር አበሉኝ። ሳይጠየፉ ገላዬን አጠቡኝ።››

‹‹አይኗ ዳግም በእንባ ተሞላ። ሳግ ይተናነቃት ጀመር። ከተጋደመችበት ተነስታ ጫፉ ላይ አልጋ ላይ ሸርተት ብላ መሬት ሸርቆጥ ብላ ተቀመጠች። ግራ ገባኝ። አለመጠየፋቸው እንደሆነ ያስለቀሳት ገመትኩ። ሁኔታዋ ውስጤን ነካው እኔም የመን ውስጥ በእስር ሳሳልፍ አስታማሚ በሌለበት ታምሜ ለሽንት ደግፎ የሚያነሳኝ አጥቼ የተከሰተውን አስታውሼ እሷን በማባባል ፋንታ አጋዥ ሆኜ አረፍኩት። ሁለታችንም ባሳለፍነው መከራ ትዝታ ተሰንገን አላቀስኳት ወይም አላቀሰችኝ።

‹‹..ገብቶሀል ግን ለምን እንደማለቅስ? ማንም ሰው ብሉ አያየኝም። ከእንግዲህ ተስፋ የለኝም ያልኩትን ሴት፣ ግማቱ ለራሴ ያስጠላኝን ቆሻሻዬን፣ እላዬ ላይ የደረቀ ቆሻሻዬን ሳይጠየፉ ላስቲክ ጓንት አድርገው አስለቀቁልኝ። የወቀስኩት ፈጣሪዬ ለካ አልረሳኝም። ለካ ወገንም ለወገኑ አይጨክንም አልኩ። አጣጥበው ልብስ ሊለውጡልኝ ፈልገው ከእኔ ጋር አብረው የጣሉትን ፌስታል ሲከፍቱት ውስጡ ፓስፖርቴን አገኙት። ከገባሁበት ቪዛ ውጪ መኖሪያን አላሰሩልኝም። ልጆቹ ግን ያን ያደረጉት ይዛ ጠፋች እንዲባል መሆኑን አስጠጊዎቼ ነገሩኝ። ለምን ቆሻሻ መጣያው ጋር እንደጣሉኝ እና ምን እንዲህ እንዳደረገኝ ጠየቁኝ። የደረሰብኝን ሁሉ እውነቱን ስነግራቸው አዝነው አይዞሽ እኛ አለን አሉኝ። በእርግጥም ብዙ ነገር ረዱኝ። ለሽንት መጸዳጃ በገባሁ ቁጥር አንደኛውን ለይቼ ማስተናገድ አቃተኝ። ሁሌ ተቅማጥ እንደያዘው ለአንደኛው ስቀመጥ ተቀላቅሎ ይወጣል። ህጋዊ ስላልሆንኩ በግልጽ ሆስፒታል ሄጄ መታከም አልችልም። ስለዚህ አንደኛዋ ልጅ የምታውቀው ዶ/ር ሄደው በድብቅ ህክምና እንዲሰጠኝ አናገሩት። ትንሽ ካገገምኩ ከሳምንት በኋላ መረመረኝ። የፊስቱላ ችግር ስለተከሰተብኝ ህክምናው በቀላሉ ሊሰጥ እንደማይችል ነገራቸው።

ለሰው ልጅ የተፈጠረውን መከራ ሁሉ ለብቻዬ ያሸከመኝ መሰለኝ:: ከማልወጣው አረንቋ ውስጥ መዘፈቄን አስቤ ተስፋ ቆረጥኩ:: መፍትሄው በድብቅ የግል ክሊኒክ ውስጥ ለጊዜው የሚሆን ከፍተኛ ህክምና መውሰድ እንዳለብኝ ዶክተሩ ተናገረ:: ለዚህ የሚሆን ገንዘብ ደግሞ ማግኘት ከባድ ነበር:: 4 ወር ከ17 ቀን ብሰራም ሰባራ ሳንቲም አልሰጡኝም:: ብከስ ተጎጂዋ እኔ ነኝ:: ደግሞስ የትና ማንን ነው የምከሰው? ቤቱን አላውቀው... ባለቅስ አልወጣልሽ አለኝ::

ልጆቹ የሚችሉትን ያህል እንደሚሞክሩ ካልሆነ ወደሀገር የምመለስበትን መንገድ እንደሚያመቻቹ ነገሩኝ:: ከዛ በፊት ግን ለመታከሚያ የሚሆን ገንዘብ ለሰው ሁሉ እየነገሩ ቤተክርስቲያንም፣ ኮሚኒቲም.. በቻሉት ቦታ ሁሉ ለመኑልኝ:: ዶ/ሩ ግን ገንዘቡን ብቻ ህክምናዬን ለሚከታተልበትም ሆነ በድብቁ ክሊኒክ ለሚደረገው ህክምና እንዲረዳኝ አላደረገም:: ብቅ ባለቁጥር ውለታ እንድውልለት ይጠይቀኝ ጀመር:: ለስሜት ውጥረቱ.. ሆጽ ላለ ገላው ማስከኛ አፌን ላበድረው ይፈልጋል:: እምቢ ብለው አንድ ሊያሲዘኝ ይችላል:: ሁለት ታክሜ ድኜ ለመስራት እፈልጋለሁ:: ሰርቼም የቤተሰቦቼን ቤት ከዕዳ ነፃ ማድረግ አለብኝ:: ስለዚህ ያለኝ ይሄ ዶክተር ብቻ በመሆኑ እንቢ እንዳልለው ራሴ ለራሴ መከርኩት:: ቀን እስኪያልፍ... ብዬ ጀመርኩት:: ህክምናውንም እየተከታተልኩ ለእነሱ ሽክም መሆን ከበደኝ:: በዱባይ ኑሮ ሁለት ወር ሙሉ ተሸከሙኝ:: ከዛ በኋላ እነሱ ገላቸውን ሸጠው ቁጭ ብዬ መብላቱ ተናነቀኝ:: ሰው ቤት ተቀጥሬ እየሰራሁ በየጊዜው ህክምናውን ማግኘት ከባድ መሆኑን ስረዳ እኔም እነሱ የሆኑትን ለመሆን ሞከርኩ:: ፈራ ተባ እያልኩ አንድ ቀን ከአንዱ ጋር ሄድኩ:: ያልጠበኩት አሳፋሪም ድርጊት ፈጸምኩ:: ወሲብ ሲፈጽም ሽንትና እንትኔ ከቁጥጥሬ ውጭ ሆኖ ፈሰሰ:: አልጋውን አበላሸሁበት:: ጠፍጥፎ አንሶላውን አሳጥቦ እንኳን ሊመልሰኝ ከጊቢው ብቻ አስወጥቶ ጣለኝ::

ለጓደኞቼ ደወልኩላቸው:: በታክሲ መጥተው ወሰዱኝ:: አጽናኑኝ:: ሌላ ጊዜ በአፍ ብቻ መፈጸም ለሚፈልግ አንድ ሰው መስራት ጀመርኩ:: አንዴ ከገባህበት ደግሞ የበሰበሰ ዝናብ አይፈራም ነው:: እንዲህ እንዲህ እያልኩ ሳንቲም ተርፎኝ ለቤተሰብ መላክ ጀመርኩ:: ..ደንበኞቼ በረከቱ:: አፌ ተግባሩ በዛ መብያና መናገሪያ ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ ስራ ተመደበለት:: እንደማንኛውም ሰው ለሄዋን በተፈቀደው ቦታ ወሲብ መፈጸም አልችልም:: ፈራሁምም:: ዳግም ያን ካደረኩ ሽንትና ሰገራዬ ተቀላቅሎ ይፈሳል ስል ፈራሁ:: ይህ ሁኔታ በክሊኒክ ውስጥም በድብቅ ህክምና ቢደረግልኝም ሙሉ ለሙሉ አልቆመም:: ምናልባት አሁን ሀገሬ ስገባ የተሻለ ህክምና አገኛለሁ ብዬ ነው የማስበው::





ታዲያ እንዲህ አይነት አስጠሊታ ህይወት እየኖርኩ ያን ቃል ተናገርኩት አልተናገርኩት ምን ለውጥ ሊያመጣ? እርግጥ ይህን በማድረጌ ታዝንብኛለህ? ይህን ባላደርግ ኖሮስ? የቤተሰቦቼን ካርታ አስለቅቅ ነበር? በልተው እንዲያድሩ ማድረግ እችል ነበር? እኔስ በምን አይነት..››

አሁንም እንባ አቋረጣት:: እኔም እንደተለመደው አጀብኳት::

ወደኋላ ተመልሼ ባስታውስ ‹‹...ይሄ ባህላችን፣ ስርዓታችን.. ቅብርጥሴ የምትሉት ነገርን አስበህ ከሆነ ተወው:: ባህል ስርዓት ቅብርጥሴ እያለ የሚጀነነው ማህበረሰብ እንገዋሉ ከተፋቸው ምስኪኖች ተወልጄ ነው ለዚህ ሁሉ መከራ የተዳረኩት:: ታዲያ ወግ ስርዓት ለእኔ ምኔ ነው? ቁርስ አልሆነኝ ምሳ....›› ይህ አባባሏ ለእኔ የተንጠፈጠፈ እውነት ነው:: ልክ እንደኑግ ዘይት የጠራ... ምክንያቱም በርሃብ፣ በችግር ለተተበተበ ሰው ምኑ ነው? የሶስት ሺህ ዘመን ታሪክ አለን እያልን ሶስት ሺህ ዘመን ስናወራ ሳንሰራ ቀርተን ድህነት እጣፋንታችን ይመስል ተጎብሮብን እንደሸማ ለብሰነው፣ እንደኩታ አጣፍተነው አብሮን ከርሟል:: ይህን ስል ታሪካችን ባህላችን አያስፈልግም ማለቴ አይደለም:: ማዕረጋችንም ጌጣችንም ነው:: ግን ማዕረግም ጌጥም የሚደምቀው ተርበው ተቸግረው አይደለም:: ሲኖረን.. ሰርተን ስንለወጥ ነው እንጂ በችግር ሰዓት ታሪክ፣ ባህል ወግ ስርዓት ችግር የሚቀርፍ ፓውንድ አይደለም:: አይሆንምም:: የቸገረው፣ የራበው ሰው ያን መጠበቂያ ትዕግስትም አቅምም አይኖረውም:: የዚህች ልጅን ትንፋሽም የተረዳሁት ከዚህ አንጻር ነው:: እናንተስ ምን ትላላችሁ??? ምን ማድረግ ነበረባት??

ይሄን አሳዛኝ ታሪክ ስልኬን ከፍቼ እየቀዳኋት እንደነበር ነገርኳት:: ‹‹ለምንህ ነው? ለምን ቀዳኸኝ?..›› ስትል ተገርማ ጠየቀችኝ:: ነገርኳት:: ‹‹ስሜን እንዳትጠቅስ! ከምንም በላይ አባቴ አውቆ እንዲያዝንብኝ አልፈልግም:: አይረዱኝም:: ወይም ምን ሆኜ ምን ሰርቼ እንዳኖረስኳቸው አውቀው በሀዘን እንዲኮራመቱ አልፈልግም›› አለችኝ::

እኔም ይህን ቃሏን ጠብቄ ይኸው ስሟን አልጠቀስኩም::

# ክፍል ሦስት

# የሞት ጉዞ

# - 19 -

# ሠይጣን የሚቀናባቸው ጭራቆች

እንባ ስዋጡልኝ ሙሾዬን ሳወርደው
የተንጻሁትን እኔ ነኝ የማውቀው
ቅኔ ደርድሩልኝ ስንኙንም ቋጥሩ
እኔ እነን ጠሳሁት ውስጤ በማረሩ

ከአንድ ሺህ በላይ ኢትዮጵያዊያን በቡድን በተቀናጁ ሰዎች የመን ውስጥ ታፍነው እንዳሉ ተይዘው የተለቀቁና ጉዳት የደረሰባቸውን በማግኘቴ አወኩኝ። ሌሎች ሰዎችን ‹‹ወገኖቻችን ታግተዋል..›› በማለት አስተባብሬ ጉዳዩ ይመለከታቸዋል ብለን ወደ አሰብነው ክፍል ስሞታ አቀረብን። ክስ ካቀረብንባቸው ቦታዎች መካከል የየመን ሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ትኩረት ሰጥቶን 128 የታፈኑ ኢትዮጵያዊያንን አስለቀቀ።

156 በህገ-ወጥ መንገድ አስገቢዎች እና አፋኞች በጀልባ ከማሳፈር ጀምሮ፣ ስድስት የሳዑዲ አረቢያ እና አራት የየመን ድንበር ጠባቂዎች፣ በአራት ሽፍታ፣ 12 በዘረፋ የተሰማሩ፣ 4 ህግ አስከባሪዎች ሆነው በቅንጅት ነበር አፈናውን ሲፈፅሙ የቆዩት። እነዚህ ሰው መሰል መሳሪያ የታጠቁ ጭራቆች በጅቡቲ አድርገው ቀይ ባህርን ተሻግረው ወደየመን የሚገቡትን ኢትዮጵያዊያንን በማገት የያዙትን ነገር በሙሉ ከመንጠቅ አልፎ ተርፎ ወደ ወዳጅ ዘመዶቻቸው ስልክ ደውለው 1000 እና 1500 ወይም ከዛም በላይ የሳዑዲ አረቢያ ሪያል እንዲያስልኩ የሚያደርጉ አፋኞች ናቸው። ያገቱት ሰውን ለማስለቀቅ ገንዘብ የሚልክለት ሰው ካልተገኘ ግን ታጋቹ ላይ ከተራ ድብደባ እስከ መግደል የደረሰ ቅጣት ይፈጽማሉ። ‹‹..እኛ ሀገርማ እንዲህ አይነት ሰብዓዊነት የጎደለው የሀራም ስራ አይሰራም። የሰውን ልጅ

ወዳድ ሀገር ነው...›› ያሉኝ የሁማን ራይት ሰራተኛ ይህን ዝርዝር የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር ይፋ ሲያደርግ ምን ብለው ይሆን?

ነፃ ከወጡት እነዚህ 128 ኢትዮጵያውያን ውስጥ ወንዶች፣ ሴቶች፣ የ11 አመት ልጅ ጨምሮ ህፃናት እና ከስልሳ አመት በላይ ዕድሜ ያላቸው ሽማግሌዎች ይገኙበታል። በህይወት ከተፈቱት ሌላ የሞቱም እንዳሉ ለማወቅ ተችሏል። ከወር በላይ ታግተው ሲደበደቡና በእሳት ሲቃጠሉ የቆዩት እነዚህ ኢትዮጵዊያን የሁለት የመናዊ ግለሰቦች ቤት በሀይል እርምጃ ሲፈተሽ ነው የተገኙት። በዱላ የተጐዱ፣ በርሃብ ብስቁልቁል ያሉ፣ ድካም እንግልት ያጠቋቆራቸው፣ አብዛኛዎቹ ያለሰው እርዳታ መራመድ ያልቻሉ ነበሩ። የመጀመሪያው የአጋቾቹ አለቃ አብደላ አብዶ አል-ዋህሺ ቤት 49 ኢትዮጵያዊያን ናቸው ታፍነው የተገኙት። በሁለተኛው የአፋኞች አለቃ ካልድ ሞሀመድ አብሲ ቤት ደግሞ 79 ኢትጵያዊያን ተገኝተዋል። ሰው ላይ ሊፈጸም የማይገባው ኢ-ሰብአዊነት በተላበሰ ሁኔታ ግፍ የተፈጸመባቸው መሆኑን የየመን ሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር አስታውቋል።

ከእነዚህ ከተለቀቁት 128 ኢትዮጵያዊያን ሌላ 72 ኢትዮጵያዊያን ደግሞ አንድ ቤት ውስጥ ታፍነው ተገኝተዋል። ሰባ ሁለቱ ኢትዮጵያዊያን ስለተፈቱበት ሁኔታ የገለጸው አል-አደድ ጋዜጣ የሁማንራይት ባለስልጣናትን፣ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትርን፣ ሀረጥ አካባቢ ያለ ፖሊስ ጽ/ቤትን ምንጭ አድርጎ ጠላፊዎቹ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ተጠላፊዎቹ ላይ እንደሚፈጽሙ አስፍሯል። በእነዚህ 70 ወንዶችና 2 ሴቶች ላይ አፋኞቹ ታይቶ የማይታወቅ ግፍ እንደፈፀሙባቸውና እንደደፈሯቸው መታወቁንና ሁሉም ደግሞ አንድ ቤት ውስጥ እርቃናቸውን በጋንት ብቻ መገኘታቸውን ፖሊስ አሳውቋል ሲል ጋዜጣው ዘግቧል። (እስቡት የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትርም በመግለጫው ወንዶች ጥምር መደፈራቸውን አምኗል።)

የታፈኑበት ቦታ ሀረጥ የተባለ በባህር የሚገቡበትና ወደ ሳዑዲ አረቢያ የሚሄዱበት መካከል ወደቡ አቅራቢያ ነው። ይህ ቦታ ይበልጥ የሚታወቀው ከሞካ ወደ ሳዑዲ መንገኛ ጠረፍ መሆኑ ነው። እዚህ ቦታ ላይ አለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት /IOM/ እና ቀይ መስቀል የመሰረቱት አንድ ካምፕ አለ። ባህር አቋርጠው የየመንን መሬት የረገጡትን ወደዚህ ካምፕ እንዲገቡ ታስቦ ነው የተዘጋጀው። በአካባቢው ላይ ግን ሌላ ለዘረፋ የተዘጋጀ ሀይል አለ።

ታጋቾቹ ኢትዮጵያዊያን በአጋቾቹ በደረሰባቸው ድብደባና በእሳት የማቃጠል ጭካኔ ከፍተኛ ጉዳት የገጠማቸው ከ57 የሚበልጡ ሰዎች ህክምና ወስደዋል። በከፍተኛ ሁኔታ ጭንቅላቱ ላይ በደረሰበት የዱላ ድብደባ የመርሳት ችግር የተከሰተበት/ባት እንዳለ፣ ማን እንደሆነ፣ ቤተሰቦችን..





አብረውት ያሉትን ጓደኞቹን ሁሉ ማስታወስ ያልቻለ ልጅ አለ። /እስካሁን ራሱን ያላወቀ ከመሆኑም ሌላ ለምን ያህል ጊዜ በዚህ ሁኔታ እንደሚቀጥል ለማወቅ አልተቻለም። ፎቶግራፉም ይህን ያሳያል።



‹‹አልአደድ›› የተባለው የየመን ጋዜጣ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴርን ገለጻ ጠቅሶ እንደዘገበው ከሆነ ከጠላፊዎቹ ውስጥ ሁለቱ በእጥር ዘለው አምልጠዋል። አፋኞቹ ታፋኞቹ ኢትዮጵያዊያንን በጎማ ይደበድቧቸው፣ በሲጋራ ያቃጥሏቸውና በሰው ልጅ ላይ የማይደረግ ነውር ያደርጉባቸው እንደነበር፤ ይህንን ግፍ ከፈፀሙት ውስጥ የሀረጥ ፖሊስ በቁጥጥር ስር ያዋላቸው እንዳሉ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ገልጸዋል። በመግለጫው መሰረት 20 ሴቶች እስካሁን የገቡበት እንዳልታወቀና[19] ፍለጋው ግን እንደቀጠለ አትቷል። አስገድዶ መድፈርና አስከፊ ሁኔታ እንደተፈጸመባቸው በምስክሮች ተረጋግጧል። በምስክሮች ቃል መሰረት ከ3000 የሚበልጡ ኢትዮጵያዊያን ባለፈው አመት ብቻ ጥቃት እንደደረሰባቸው ከእነዚህም መካከል ያረገዙ ሁሉ እንዳሉ የሚኒስትር መስሪያ ቤቱ መግለጫ አስፍሯል።

[19] ሁሌም ገድለው በየቦታው ስለሚቀብሯቸው ብዙ ጊዜ ምንም ፍንጥ ሳይገኝ ይቀራል።

ከምስክሮቹ መሃል አንዲት ስሟ እንዲጠቀስ ያልፈለገች ኢትዮጵያዊት እንደተናገረችው ‹‹ቤተሰቦችዋ 5000 ብር እስኪልኩላት ድረስ ታፍና ለ8 ወር ሲጠቀሙባት ከቆዩ በኋላ ተለቃለች፡፡ ስትለቀቅ እርግዛ ነበር፡፡ ባሏ ሳያውቅ እንዳስወረደችው ተናግራ በፍፁም ባሌ እንዲያውቅ አልፈልግም፡፡ ይህ ልጅ መወለድም የለበትም፡፡ ሌላው ቀርቶ ሀረጥ ላይ የተፈፀመብኝን ግፍ ጭምር ባለቤቴ እንዲያውቅ አልፈልግም ብላለች ሲል አል-አደድ ጋዜጣ ዘገባውን ቋጭቷል፡፡

ከዓመት በፊት የየመን ሁለተኛ ከተማ ወደሆነችው አደን ስጓዝ ያገኘሁት ልጅ በባህር ሲመጣ አፍነው ኩላሊቱን[20] እንደሰረቁት ሲነግረኝ ውስጤ ሁሉ ነበር በሀዘን የተርገደገደው፡፡ ይህን ሁኔታ በውስጤ ይዤ ተጨማሪ መረጃዎችን ማፈላለግ ያዝኩኝ፡፡ ታዲያ አንድ አጋጣሚ ያገናኘን ሀረጥ እሚባል የሳዑዲ አረቢያ ጠረፍ የመብራት መስመር ዝርጋታ ስራ ላይ የተሰማራ ወዳጄ ‹‹…ከባህር እንደወረዱ በፒክ አፕ ሀረድ ድረስ በሁለት መቶ የየመን ሪያል እናድርሳችሁ ይሉና ይጭኗቸዋል..›› አለኝ ያ-አጋጣሚ ያገናኘን ትውልደ ኢትዮጵያዊ ወዳጄ፡፡ ምን ክፋት አለው ሀያ ኪሎ ሜትር በሁለት መቶ ሪያል ከወሰዷቸው ብዬ ወሬውን እንዲቀርጥ ላደርገው ሳሞጠሙጥ

‹‹…በሰላም ቢያደርሷቸው ጥሩ ነበር..›› አለና ልቤን እንጠልጥሎት እርፍ፡፡ ‹‹መሀል ላይ መንገድ ቀይረው ወደሚፈልጉት ቦታ ይወስዷቸዋል፡፡ እግተው ይይዟቸው እና ስልክ እየሰጡ ከቤተሰባቸውም ሆነ ሌላ ቦታ ካለ ዘመዳቸው ገንዘብ እንዲያስልኩ ያስደርጋሉ፡፡ የራሳቸው እስር ቤት አላቸው፡፡ እዚያ ወር እና ከዛም በላይ የታሰሩ ሰዎች እንዳሉ ሰምቻለሁ..›› የሚያወራው እውነት ለመሆኑ ግንባሩ ላይ የሚነበብ ይመስል ትክ ብዬ አየሁት፡፡ የሰማሁት አሞኝ ነው ትክ ብዬ ማየቴ እንጂ እንዳልኩት የሚነበብ ኖሮ አይደለም፡፡

ደግሞም በአጋጣሚ ወደትዕዝ ከተማ የሄድኩ ጊዜ አንድ አጋቾቹ ባደረሱበት ድብደባ ሳቢያ እጁን የተሰበረ ልጅ አግኝቼ አነጋግሬው ነበር፡፡ እናም ይህን በድብደባ እጁን የተሰበረ ልጅ ማስረጃ አድርጌ ሁማን ራይት፣

[20] አንድ ሁለቴ የየመን ጋዜጠኞች ስብሰባ ላይ በተገኘሁበት አጋጣሚዎች የማውቀው የመናዊ የግል ጋዜጣ አዘጋጅ ጋዜጠኛ መሀመድ ደርማን ጋር ለመማከር ቀጠሮ ያዝንና ነገርኩት፡፡ የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ መረጃ አሰባሰበ፤ እኔ ያላገኘሁትን ሁሉ አገኘ፡፡ በባህር ከሚገቡት ኩላሊት መሰረቁን ግን ሁላችንም ያገኘነው ነገር የለም፡፡ በረቀቀ መንገድ የሚያደርጉት ስለሆነ የተገኘ ተጨማሪ መረጃ የለም፡፡ ተሰረቅሁ ያለው ልጅ ተመርምሮ ለመታየት ተስማማ፡፡ ያለው አማራጭ ጭላንጭል ቢሆንም ከዳር መድረሱ አይቀርም፡፡ የሚያሳዝነው ግን የያዝነው የማጋለጥ ተግባር ከግቡ እንዳይደርስ ለመመርመር ፍቃደኛ የነበረው ስደተኛ ወደ ሳዑዲያ መሳፈሩን ሰማን፡፡





ሀገር ውስጥ ሚኒስቴር፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ ሁድ የሚባለው በተቃዋሚዎች የሚመራው የኖቤል ተሸላሚዋ ከረማን ያለችበት የሰብዓዊ መብት ድርጅት አመለከትን፡፡[21] ይህን ዘገባ የተወሰነውን ፌዝቡክ እና የተለያዩ ማህበራዊ ድረ-ገጾች ላይ አቀረብኩት፡፡ ከዚህ ዘገባ በኋላ ድንገት አንድ በ00251114....የሚጀምር ስልክ ጥሪ ደረሰኝ፡፡

መቼም ከኢትዮጵያ የሚደውል ወዳጅ ዘመድ ነው ብዬ በጉጉት ተወጥሬ ‹‹ሀሎ!..›› አልኩ በጎርናና ድምጼ፡፡ ለስለስ ያለ የሴት ድምጽ ‹‹ህይወት እባላለሁ..ፌስቡክ ላይ Hiwi mare (በአሁኑ ጊዜ የማሪያም ልጅ Yemariam liji) በሚል ነው የምጠቀመው..›› በሚል መልዕክቱን ማንቆርቆር ጀመረች፡፡

‹‹..ሀበሻ በየመን የሚለው ፅሁፍህ ላይ አብዱል ገዊ በሚባለው ሰውዬ ስለተያዙት ልጆች አነበብኩ፡፡ የእጎቴ ልጅ ሀብታሙ ተይዞ ገንዘብ ላኩ ተብለናል...›› አለችና ልጁ ደውሉ የሰጣትን ስልክ ቁጥር ሰጠችኝ፡፡ ስልኩ ከሰውየው ጀሌዎች ውስጥ የአንዱ ነው፡፡ የዋናው አለቃ ስሙ ዘይን አሊ አብዱራህማን ይባላል፡፡ መኖሪያው አደን ከተማ ውስጥ ነው፡፡ በመጀመሪያ ከስ ያቀረብኩበት ሞካ አካባቢ ያለው አብዱል ገዊ ለጊዜው ሸሽቶ ወደ ጅቡቲ አምልጦ አዩ የሚባል ቦታ ተቀመጠ፡፡ ጅቢቲም ሆኖ ግን በጀልባ የሚሚኑትን እያየ ደውሉ በዚህ ሰዓት ይገባሉ ብሉ ስለሚነግራቸው ሰራተኞቹ ማገቱን ቀጠሉ፡፡ አካባቢው ላይ በአጠቃላይ ከአስራ ዘጠኝ የሚበልጡ ቡድኖች ኢትዮጵያዊያንን እያገቱ 50.000 የየመን ወይ 1000 የሳዑዲ ሪያል አለያም የኢትዮጵያ 5000 ብር እንዲያስልኩ ታጋቾቹን ወደ ዘመዶቻቸው እያስደወሉ ያሰቃያሉ፡፡ በእሳት ያቃጥላሉ፣ የፈላ ውሀ ውስጥ ይነክሯቸዋል፡፡ በዱላ ይደበድቧቸዋል፡፡ ይህን አሰፀያፊ ስራ የሚሰሩ ቅጥረኛ ኢትዮጵያዊያን መኖራቸውን መስማት ደግሞ የበለጠ ልብ ያደማል፡፡ በዚህ አማካኝነት ያገኘሁትን ስልክ ቁጥር ነው በአንድ UNHCR በጠራው ስብሰባ ላይ ለሀገር ውስጥ ሚኒስትር ተወካይ ሰጥተናቸው እዛው በራሴ ስልክ ደውለን ያናገሩት እና ሁኔታውን የተረዱት፡፡ ከሳምንት በኋላ ለጊዜውም ቢሆን ደስ የሚል ዜና ሰማን፡፡

ይህንን በተመለከተ አንድ የመን ውስጥ የሚታተም ‹‹አልብላግ›› የተባለ ነፃ ጋዜጣ እንደአቋም መግለጫ ርዕስ አንቀጽ አድርጎ በጃንዋሪ 2012 እትሙ ላይ በግልፅ ያሰፈረው ጽሑፍ ትርጉሙን እነሆ...

[21] እዚህ ጋር የማላልፈው አብረውኝ የተሯሯጡ ሌሎች ልጆችም አሉ፡፡ አብይ አበበ፣ ሰብለ ዮሐንስ፣ ነብዩ ተስፋዬን እና ቋንቋ በማስተርጎሙም ጭምር ነጅብን.. ሁሉንም በስሱ አመሰግናለሁ..ይድረሳቸው፡፡

በርካታ አፍሪካዊያን በባህር በሞካ (የየመን የወደብ ከተማ) በኩል አድርገው ወደየመን ሲገቡ በተቀናጀ ሀይል ዘረፋ እየተደረገባቸው ነው:: ሞካ በዘራፊዎች የታጠረች ስትሆን በርካታ ስደተኞች ለስቃይ፣ ለመከራ እየተዳረጉ ነው:: በተለይ ኢትዮጵያዊያን ለከፍተኛ መከራ፣ መታሰርና መደብደብ ተዳርገዋል:: አብዱል ገዊ የተባለ አንድ የመናዊ በርካታ ጋሻ ጃግሬዎችን አሰማርቶ ይዘርፋል፣ ያስራል፣ ይደበድባል:: ይህን የሚያደርገው በባህር ወደየመን የሚገቡ ኢትዮጵያዊያን ላይ መሳሪያ የታጠቁ ተከታዮቹን እያሰማራ ነው:: የራሱ የማሰቃያ እስር ቤት ያለው መሆኑም ታውቋል::

በዚህ እስር ቤቱ ውስጥ የደበደባቸው፣ የገረፋቸው፣ ጀርባቸው ቁስል በቁስል የሆነ ሞልተዋል:: በግርፋት ሰውነታቸው የደማ፣ የቆሰለ፣ የተላ እና ጠባሳ የያዘ ሆነው ከእስር ቤቱ ውስጥ ስለሚወጡ በሞካ ጠረፍ በኩል የገባ ሀበሻ ሁሉ አብዱል ገዊን ያውቃል:: በእሱ ያልተያዘ፣ ያልተገረፈ፣ ያልተዘረፈ ሀበሻ አይኖርም:: ከድብደባው፣ ከስቃዩ ለመገላገል ሲሉ ያላቸውን ሁሉ ይከፍላሉ:: የሌላቸውም ከሳዑዲም ሆነ ከሌላ ቦታ ገንዘብ ሊልክ የሚችል ዘመዳቸው እንዲልክ አስደርገው ከፍለው ይወጣሉ:: መውጣት ካልቻሉ ታስረው ይበሰብሳሉ:: ተዘርፈው ባዶ የቀሩት በእግር ከሞካ ተነስተው ረድዓ ድረስ ሄደው ነው ሰርተው ማግኘት የሚችሉት:: ሀረጥ መጥተው ካምፕ ይገባሉ:: አብዱል ገዊ የተባለው ግለሰብ ባደረሰው ዘረፋ ብዙዎች ተሰናክለዋል:: አካል አጥተዋል፣ ሞተዋል.. ስለዚህ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ፍትህ ሚኒስቴር፣ የየመን ሰብዓዊ መብት ቢሮ(ሁማን ራይት).. ወንጀለኛው አብዱል ገዊን[22] ለፍርድ እንዲያቀርቡ ጋዜጣው ጠይቋል:: አያይዞም የወንጀለኛው እስር ቤት ተፈትሾ ያሉት እስረኞች ነፃ እንዲወጡ ሲል አበክሮ ጠይቋል:: ይህን ጥያቄ ይዘን ለማናገር የሞከርናቸው ባለስልጣናት ከአፍ ያልዘለለ ጥሩ ተስፋ ሰጥተውናል::

ይኼ በባህር የሚደረግ ጉዞ ስቃዩን እለት ከእለት እየጨመረ መምጣቱ ብቻ ሳይሆን አፋኞቹን ለማስቆም ምንም አይነት ጥረት አለመደረጉም አሳሳቢ እየሆነ ነው:: እነሱም በማን አለብኝነት ጭካኔያቸውን

[22] አብዱል ገዊ አሁን በህይወት የለም:: አንድ ኢትዮጵያዊ ገሎት ሞቷል:: ለአሟሟቱ የሚሰጠው ምክንያት ብዙ ቢሆንም የገደለው ግን ኢትዮጵያዊ መሆኑ የታመነ ነው:: ገዳይ ሳዑዲያ ሆኖ ሚስቱን ገማሾች እንደሚሉት ደግሞ እህቱን ነይ ይሳል:: አስቡት በዚህ መንገድ የተጓዘ ስቃዩን ያየ ሰው እንዴት ቢሳውን ይጠራል? ደሄ የገንዛቤ ችግር ነው የሚባለው? ወይስ ግዴለሽነት? ወይስ እኔ ያየሁትን እዩ ነው? ገሬ ይገባል:: ታዲያ በሴቱች የደረሰው እጣ ደረሳትና ተያዘች:: ይዘው ምንም ሳያደርጉ መልቀቅ ደግሞ በእነሱ ህጢያት ነው መሰል ሴቶቹ ብቻ አግተው አስቀምጠው መጠቂያ ማድረጋቸው የታወቀ ነው:: ይህችም ልጅ እጣዋ ሆና ከሚያከርሟቸው ጋር ሆነች:: አረገዘችም:: ተጠቃሁ ያለው ልጅ በቀጥታ ወደ ሀረጥ ገስግሶ አብዱል ገዊን የሚጠበቅበትን ብር ከፍሎ ሊያስለቅቃት አስመስሎ ሊያናግረው በስለት ወግቶ ገደለው:: እሱንም የእሱ ተከታዮች ሳይገድሉት ራሱን አጠፋ የሚል መረጃ ነው ያለኝ::





እየጨመሩ የፈለጋቸውን እያደረጉ ነው:: በወቅቱ ከሶማሊያዊያን ይልቅ ይበልጥ እየተሰደዱ ያሉት ኢትዮጵያዊያን መሆናቸውንና ለጉዳት ተጋላጭ እየሆኑም እንደሆነ ቀይ መስቀል፣ አለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት /IOM/ እና በጉዳዩ በጥምረት እየሰሩ ያሉ ድርጅቶች አስታውቀዋል:: እለት ከእለት ወደየመን የሚፈልሰው ስደተኛ ቁጥር እየጨመረ መምጣቱ እንዳሳሰባቸውም አክለው ገልጸዋል:: ጉዟቸው በመረጃ ያልተደገፈ እና ህጋዊ ባልሆነ መንገድ/ህገ-ወጥ/ በመሆኑ ለዘራፊዎች ከመጋለጣቸውም ባሻይ ለሞት እየተዳረጉ መሆኑንም ድርጅቶቹ አስምረውበታል::

እኔም በበኩሌ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ከ10 አመት ጀምሮ ያሉ ህፃናት በሚያስገርም ሁኔታ በጅቡቲ በኩል ፍልሰቱን የተያያዙት መሆኑን ያናገርኳቸው የአይን እማኞች ይገልፃሉ:: አንዳንዶቹም ህጻናቱን ይዘው ሳዑዲ የሚጓዙት በአብዛኛው በእድሜ የገፉ እንደሆኑና ለአፀያፊ ነገር መፈፀሚያ አሳልፈው ሊሸጧቸው እንደሆነ ገልጸውልኛል:: ገዢዎቹ አረቦች እየተጠቀሙባቸው እረኝነትም እንደሚያሰሯቸው ሳዑዲ ያሉ ኢትዮጵያዊያንም በይፋ ይናገራሉ:: ይህ የሳዑዲ አረቢያ ጉዞ የብዙዎችን ህይወት የቀጨ፣ የትም ያስቀረ እና ብዙዎችን ለግብረ-ሰዶምነት የዳረገ ጠንቀኛ ነገር ሀገራችን ውስጥ የዘራ መሆኑ አይካድም::

ያም ሆኖ ይህ እነዚህ ሳዑዲ አረቢያ ለመግባት የሚፈልጉ ህገ-ወጥ ኢትዮጵያዊያን ተጓዦች በአጋቾች ከደረሰባቸው ጉዳት ሲያገግሙ ወደ ሀገራቸው ለመመለስ አለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት /IOM/ መቶ ሀያ ስምንቱንም እንደ ተረከባቸው ለማወቅ ተችሏል:: እንደ ድርጅቱ ቃል አቀባይ አባባል ከሆነ ከUN ጋር በመተባበር ከእገታ ነጻ የወጡትን ሰዎች ወደ ሀገራቸው መልሰዋቸዋል:: የወንጀለኞቹን ጉዳይ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በኩል በህግ እንደሚከታተሉ ገልጸዋል:: ይህ ሁኔታ የመጀመሪያ ሳይሆን ከጁንዋሪ ፣ ቀን 2011 እስከ 24 — 2012 ድረስ 170 ጉዳት የደረሰባቸው ኢትዮጵያዊያን ከየቦታው እያገኙ ወደሀገር መመለሳቸውን የአለም አቀፉ ስደተኞች ድርጅት ቃል አቀባይ አቀብለውናል:: ካቀበሉን ወሬ መካከል በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ 90 ወንዶች፣ 10 ሴቶች፣ 50 ህፃናት፣ 20 ሽማግሌዎች ጉዳት ደርሶባቸው አግኝተው ወደሀገራቸው መመለሳቸውን ነው:: አይናቸው ጠፍቶ፣ እጃቸው ተሰብሮ ወደሀገር መመለሳቸውን እንጂ አጋቾቹን በህግ ለመፋረድ እንዳልሞከሩ ነው:: እንደምክንያት ያስቀመጡት ሀገሪቷ ያለችበት ሁኔታ አስቸጋሪ በመሆኑ እንደሆነ ነበር::

በዚህ ዙሪያ ማለት የምፈልገው አለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅትም /IOM/ ሆነ ቀይ መስቀል ከመግለጫ የዘለለ ሊያደርጉ የሚገባቸውን ነገር ባለማድረጋቸው ያስወቅሳቸዋል:: በህግም መጠየቅ ይገባቸዋል::

# - 20 -

# የታጋቾቹ ሰቆቃ

ወንት አቆሰሉት፣ ብልቱን ቆረጡት
በእሳት አቃጠሉት በቁሙ ቀበሩት
በስቃይ አሰቃይተው በስቃይ ለቀቁት
ሙሉ የነበረውን አካሉን አጉድለው
ሚስቱን ፊቱ ደፍረው ወንድነቱን ገለው

በየመን ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ የሚፈፀመው ኢ-ሰብዓዊ ድርጊትና ግፍ ተጠናክሮ ቀጥሏል። የሳዑዲ አረቢያ መንግስት ኢትዮጵያዊያኑ ስደተኞች ወደሀገሬ የገቡት በየመን በኩል ነውና ወደየመን ነው የምመልሰው ብሎ አፍሶ እያመጣ የመን መሬት ቀይ ባህር ዳርቻ ላይ ይጥላቸው ጀመር። የሳዑዲ ተመላሾቹ ደግሞ ገንዘብ ይዘዋል። ባይዙ እንኳን እዛ ካለንደኛ ወዳጅ ዘመድ ያስልካሉ ብለው እያፈኑ ማሰቃየቱን በግሩፕ የተደራጁት የመናዊያንና ኢትዮጵያዊያን ገፍተውበታል። ከሳዑዲ ተመላሾቹ ለማምለጥ ሲሮጡ በጥይት ከመምታት ጀምሮ በመኪና ሁሉ እየገጩ በመግደል መጫወቻ አድርገዋቸዋል።

ይህን ስራ በትብብር አብረዋቸው የሚሰሩ ኢትዮጵያዊያን እንዳሉ ያነጋገርኳቸው ልጆች ነግረውኛል። እንዲያውም ኢትዮጵያዊያኑ ሆን ብለው ሳዑዲ በመግባት ይታሰሩና ሲመለሱ የት የት ጋር እንደደረሱ ደበቅ ብለው እየደወሉ ለታጣቂዎቹ ይነግሩዋቸዋል። ታጣቂዎቹም ተዘጋጅተው ይጠብቃሉ። ያናገርኩት ልጅ ሲነግረኝ.. ‹‹ከሳዑዲያ እስር ቤት ከ400 በላይ ነን የተመለስነው። አብረውን ከነበሩት ሁለቱ ደበቅ እያሉ ሲደውሉ ወደ ሳዑዲ መመለሻ ገንዘብ ሊያስልኩ የፈለጉ ነበር የመሰለን። በኋላ ግን አፋኞቹ መጡ። አብረውን ያሉት 2 ልጆች ‹ለካ ሊያስይዙን ወደ አፋኞቹ ኖሯል የደወሉት› ብለው በመናደድ ሊመቷቸው ሲሉ ከአፋኞቹ መኪና ላይ





የነበረ መሳሪያ አንስተው ታጠቁ። እንዳትንቀሳቀሱ አሉን። ስንበታተን የመናዊያኑ ወደሰማይ ሲተኩሱ ኢትዮጵያዊያኑ ወደእኛ ተኩሰው ብዙ ሰው አቆሰሉ፣ ገደሉ። የመናዊያኑ አፋኞች በመኪና እያባረሩን የደረሱብትን ያዙ ያቃታቸውን እየገጩ ጥለው ሄዱ..›› ብሎኛል።

ከባህር ወርደው ታግተው እህታቸውና ወንድማቸው ከሳዑዲ አረቢያ ገንዘብ ልከውላቸው የተለቀቁ ሶስት ልጆች ሀረጥ ካምፕ ገብተው እንደነበር ስለነገሩኝ ያለውን ሁኔታ ጠየኳቸው። ‹‹ብልቱን የተቆረጠ፣ አይኑ የጠፋ፣ ጆሮው የተቆረጠ፣ እግር እጃቸው የተሰበረ፣ የተደፈሩ፣ በመኪና ተገጭተው የቆሰሉ.. ልጆች ካምፕ ውስጥ ያለህክምና ይሰቃያሉ...›› አሉኝ። ይህ ምን ያህል እውነት እንደሆነ እዛ ያለ የማውቀው ሰው ደውዬ ጠየኩት።

‹‹እውነታው የነገሩህ ነው። ጉዳት ከደረሰባቸው ውስጥ በሞባይል እያናገርኩ የቀዳኂቸው እና ፎቶ ያነሳኂቸው አሉ። ኢሜልህን ስጠኝ እልክልሀለሁ። በጣም ዘግናኝ ነው። እንዲያውም የሚገርምህ ነገር ካምፑ ውስጥ ያሉት በመቶ ቤት ሳይሆን በሺህ የሚቆጠሩ ጉዳት የደረሰባቸው ናቸው። ያለህክምና ያለምግብ እንዲሁ ተቀምጠዋል..›› ሲለኝ አንድ ሾፌር የመናዊ ሀረጥ ደርሶ ሲመለስ ያለኝ ትዝ አለኝ እና ጠየኩት። የአለም አቀፉ ስደተኞች ድርጅት (IOM) ‹‹መመገብ አልቻልኩም፣ ከአቅሜ በላይ ነው›› በማለቱ ካምፑ ውስጥ ያሉት በርሃብ አልቀዋል። ከተማ ውስጥ እየለመኑ ነዋሪው ተማርሮባቸዋል። ምግብ ቤት ገብተህ አዘህ ልትበላ ስትል ከየት መጡ ሳይባል ኢትዮጵያዊያኑ ወረውህ ምግብህን ይበላሉ ይባላል። ይህን ከአምስት ወር በፊት ወደዛ የመጣሁ ጊዜ አይቻለሁ። አሁን ግን ብሶባቸው ሆቴሎች በራቸው ላይ ዱላ የያዘ ሰው ለማቆም ተገደዋል። በርሃብ መንገድ ላይ ሁሉ ወድቀው ይታያሉ ብለውኛል እውነት ነወይ?›› አልኩት።

‹‹እውነት ነው። እንዲያውም አንተ ከመጣህበት ጊዜ አሁን በጣም የከፋ ሆኗል። ምንም የሚሰጣቸው ነገር የለም። በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያዊያኑ ስደተኞች መረራቸውና ዛሬ በ28/1/2013 ሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ። መፍትሄ ይሰጠን ወደሀገራችን መልሱን ነው የሰልፉ ዓላማ›› ሲል አረጋግጦልኛል። እኔም በወቅቱ ይሄን ጉዳይ ትኩረት እንዲሰጠው በማለት ለVOAው ጋዜጠኛ አሉላ ከበደ ደውዬ ስልኩ አልነሳ ቢለኝ መልዕክት ጽፌ ላኩለት። ለDW ሬድዮ ዘጋቢ ነብዩ ሲራክም[23] መልዕክት ላኩኝ።

---

[23] በእርግጥ ነብዩ በኢሜል ስላኩለት መልዕክት ወዲያው ምላሹን ጽፎልኛል። ልጁ ብልቱን ሲቆረጥ ያየ የአይን ምስክር የነበረ ልጅ አገናኝተነው ቃለ-ምልልስ አድርገለት በጀርመን ድምጽ ሬድዮ አቅርቦታል።

በነገራችን ላይ ሀረድ ውስጥ ያሉ ቁስለኛ ስደተኞች ከሳዑዲ የተመለሱ ብቻ አይደሉም:: እንዲያውም አብዛኛው ከባህር ሲወርዱ በተደራጁት አፋኞች ተይዘው ጉዳት የደረሰባቸው ናቸው:: አመት እና ከዛ በላይ የቆዩ ከአራት ሺህ በላይ ኢትዮጵያዊያን አሉ::

# የጊቢ ሞት ኦፕሬሽን

የየመንን መገናኛ ብዙሃን ትኩረት የሳበው ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ እየተፈጸመ ያለው አስቃቂ ግፍ ሲሆን ከችግሩ ጀርባ ያለውን እውነታንም በይፋ እየተናገሩ ነው:: እስከዛሬ የነበረ ድምጻችን፣ መፍትሄ ይፈለግ ጥያቄያችን ሰሚ አግኝቶ የየመን መንግስት በየቦታው ያሉ ታጋቾችን ማስለቀቅ ጀምሯል:: ሰኞ 8/4/13 ዓ.ም የየመን ሀገር ውስጥ ሚኒስቴር የሀረጥ አውራጃ ደህንነቶችን፣ ድንበር ጠባቂዎችን፣ ሁለት ብርጌድ የተውጣጣ ወታደር አድርገው አፋኞቹ ያሉበትን አካባቢ በመክበብ 158 ኢትዮጵያዊያንን ነጻ አውጥቷል:: ከእነዚህ ውስጥ 25 የሚሆኑት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸው በመሆናቸው ሆስፒታል መግባታቸውን ተልዕኮውን የመሩት የድንበሩ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ኮሎኔል አሊ ኡመር ይስለም ገልጸዋል:: እንደ ኮሎኔሉ አባባል በአካባቢው ያሉ ባለስልጣናት በአብዛኛው ከአፋኞቹ ጋር በጥቅም የተሳሰሩ እና አፋኞችን የሚረዱ በመሆኑ የማስለቀቁን ትግል ከባድ እንዳደረገው ገልጸዋል:: በመሳሪያ ትጥቅም በኩል ቢሆን ከመንግስት ሀይል የላቁና የተደራጁ መሆናቸውን አስምረውበታል::

የሚገርመው የተጓዡ መጠን በጨመረ ቁጥር የአፋኞቹም ቁጥር መጨመር ብቻ ሳይሆን መደራጀት እና ማን አለብኝነት ከማየሉም በላይ ከIOM ካምፕ ውስጥ ሁሉ ገብተው መጥለፍ ጀምረዋል...›› ብለዋል:: ጉዳት ስለደረሰባቸው ኢትዮጵያዊያን ሲናገሩም መሀመድ ስለተባለ ልጅ ‹‹..አስረውት በጣም አሰቃዩት:: ከየትም ይሁን ገንዘብ አስልክ ብለው ደበደቡት:: በገመድ አስረው ብረት ላይ ሰቅለው ተጫወቱበት:: መኪና ላይ አስረው መሬት ለመሬት ሲጎትቱት ራሱን ስቶ ሲወድቅ እጁ ከክንዱ ተላቆ ከጥቅም ውጭ ሆነ...›› ሌላኛው ከአጋቾች እጅ የወጣ ስለሳደኛው የተናገረውን ሲገልጹ ‹‹...ራቁቱን አስተኝተው ሲጋራ ላዩ ላይ እየተረኮሱ ስስ ብልቱን በእሳት እያቃጠሉ ሲጫወቱበት ቆይተው ገደሉት:: ሬሳውን አውጥተው የት እንደጣሉት አይታወቅም:: አሁን ነጻ ካወጧቸው መካከል

ይህ እንዲሆን የፈለኩበት እና ለየመናገናኛ ብዙሀኑ የሳኩበት ምክንያት ህዝብ ሰምቶ የፍልሰቱ ቁጥር በአንደም ሁለትም እንዲቀንስ ነበር:: ምን ያህል እንደተሳካልኝ ባላውቅም::





3 ሰዎች ተገለዋል:: 8 የባንግላዲሽ ዜጎች ጠፍተዋል›› በማለት ለጋዜጠኛው ቃል ሰጥተዋል::

እሁድ 11/4/13 ዓ.ም በአፋኞቹ ላይ በተደረገ ከበባ 180 ኢትዮጵያዊያን መለቀቃቸውንም የገለፁት እኚሁ ባለስልጣን ለአል-መስዳር ጋዜጣ ሪፖርተር ስለሁኔታው ሲገልጹ ‹‹ጠንካራ ዘመቻ እና ትግል አድርገናል›› ብለዋል:: ‹‹...2 ብርጌድ የተውጣጣ ወታደር፣ ድንበር የለሽ የህክምና ቡድን፣ የክፍለ ሀገሩ ደህንነት፣ ድንበር ጠባቂዎች... ሆነን በ11 መኪና ሞልተን ነው ዘመቻውን ያካሄድነው:: ከአንድ ጊቢ ውስጥ ብቻ 180 ኢትዮጵያዊያን በአፋኞች ታግተው ተገኝተዋል:: አፋኞቹ ውስጥ 3 ያህሉ የአለም አቀፉ ስደተኞች ድርጅት (IOM) ሰራተኞች ሆነው ተገኝተዋል...›› ሲሉ አጃኢብ ያሰኘ ወሬ አድርሰውናል:: ኮሎኔሉም አያይዘም ‹‹በስደተኞቹ የማረፊያ ካምፕ ውስጥ አስተርጓሚ ሆነው የሚሰሩት እነዚህ ሰዎች ለአፋኞቹም አስተርጓሚ ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው:: ስደተኞቹንም ከካምፕ አውጥተው ይሸጡላቸዋል:: በሁኔታቸው ተጠራጥረን ስንከታተላቸው እውነትም ሆኖ አግኝተናቸዋል..›› በማለት ገልጸዋል::

እዛው ሀረጥ አካባቢ ነዋሪ የሆነው የአል-መስዳር ጋዜጣ ሪፖርተር ጋዜጠኛ መሀመድ ደርማን እንደነገረኝ ከሆነ በጣም ተጎድተዋል:: ይህ ወዳጄና የሞያ አጋሬ የሆነው ጋዜጠኛ መሀመድ ደርማን ኢትዮጵያዊያኑ በህገ-ወጥ አጓጓዮች እየታገቱ የሚደርስባቸውን ስቃይ እና እውነታውን ከመረጃ ጋር ካሳየሁት በኋላ ነበር በቁጭት እሳት ተርመጥምጦ ከሞት ጋር ለመታገል ቆርጦ የተነሳው:: ይሄ ሰብዓዊነት የተላበሰ ሀሳቡም ነው ያገናኘን:: ያግባባን:: ከላይ በጠቀስኳቸው የየመን መንግስት ወታደሮች ከአጋቾቹ ጋር ተናንቀው ኢትዮጵያዊያኖቹን ነጻ ባወጡባቸው ቀናት ቦታው ድረስ በመገኘት ዘግቧል:: በአካል አግኝቶ ካናገራቸው (ቃለ-ምልልስ ካረገላቸው) ተጎጂዎች መካከል ለማሳያነት ያህል እነሆ፡-

ሚሚ ትባላለች:: የ19 አመት ሴት ነች:: አካባቢዋ ላይ ያሉ ልጆች በዚህ በኩል ወደ ሳዑዲያ ሲጓዙ ስላየች እንደተጓዘች ነው ለጠያቂዋ የነገረችው:: ከሀገር ጀምሮ የተለያዩ ፈተናዎች ቢገጥሟትም ባህሩን አልፋ የየመን ጠረፍ እንደረገጠች በአጋቾች እጅ ወደቀች:: አንደኛው አጋች ነይ የእኔን ክፍል አጽጂ ብሎ ወደአንድ ክፍል አስገባት:: ከዛ በሚሰቀጥጥ ሁኔታ ለብዙ ሆነው ደፈሯት:: ይህን በተመለከተ ስለጉዳዩ መግለጫ የሰጡት ባለስልጣን ኮ/ል ሲናገሩ ‹‹..ሰቅጣጭ በሆነ ሁኔታ ነው የደፈሯት...›› ብለዋል::

ዮርዳኖስ፡- ሌላኛዋ ሴት ደግሞ ዮርዳኖስ ትባላለች:: ድብደባውን በጸጋ ብትቀበልም ገመድ አንገቷ ላይ አጥልቀው እየሰቀሉ ደብድበዋታል::

አንቀዋት ትንፋሽ ሲያጥራት አውርደው መኪና ላይ በማሰር ጊቢው ውስጥ መሬት ለመሬት በመጎተት ሰውነቷ እስኪላላጥ ጎድተዋታል፡፡ ይህን ድርጊት ኮ/ል አሊ ኡመር ይስለም ‹‹የሰው ልጅ ላይ ሊፈጸም የማይገባ ነውር›› ብለውታል፡፡

ሀፊዝ ይባላል፡፡ ከባህር እንደወረዱ ስደተኞቹን በማገት የሳዑዲ ከ1000-1500 የሚያስከፍሉት ጋር ይዘውት ገቡ፡፡ የሚከፍለውም ሆነ የሚያስልክበት ቦታ ስለሌለው የደረሰበትን ድብደባ መቀበል ግድ ብሎት ቆይቷል፡፡ በግድ ቀጥቅጠው ስልክ ሲያስደውለት ያለበትን አካባቢ ለደወለላቸው ሰዎች ሲናገር ሰሙት፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ የተናገረበትን ምላሱን ቆርጠውት ጣሉት፡፡ ሀረጥ ሆስፒታል በህክምና ሲረዳም የተለወጠ ነገር የለም፡፡

የአል-መስዳር ጋዜጣ ሪፖርተር ጋዜጠኛ መሀመድ ደርማን ስላየው ሁኔታ ሲገልጽ ደግሞ ታጋቾቹ ኢትዮጵያዊያን ነጻ ከወጡ በኋላ ያለውን እንዲህ አስፍሮታል፡፡ ‹‹ያረፉበት ግቢ ስገባ 7 ሴቶች አየሁ፡፡ ድካም እና ርሀብ በጉልህ ይስተዋልባቸዋል፡፡ ያሳዝናሉ የሚለው ቃል ከሚገልጸው በላይ ተጎድተዋል፡፡ ከሰባቱ አንደኛዋ አራስ ነች፡፡ ከወለደች ስድስት ቀኗ ነው፡፡ (ለ10 ወር ያህል በአጋቾቹ እጅ ስለቆየች በድብደባ ያለጊዜዋ እንደ ወለደች ይገምታል፡፡) በሙቀቱና በርሃብ ልጇ እንዳይሞትባት ፈርታለች፡፡ ርሀቡን እሷም መቋቋም አቅቷታል፡፡ የጣቢያው አዛዥ ጠጋ ብሎ ‹‹ተመልከት›› አለኝ፡፡ ለደከሙት የተሻለ ክፍል ፖሊሶቹ ሰጥተዋቸዋል፡፡

የፖሊሱ አዛዥ እንደሚለው ከሆነ ‹‹ይህን አይነት አስቃቂ ነገር እኛ በየጊዜው ከማየት የተነሳ የለመድነው ነገር ነው፡፡ አፍሪካውያኑ ስደተኞች ወደዱም ጠሉም የእነሱ ግብ የሆነው ሀገር (ሳዑዲ አረቢያ ማለታቸው ነው) ለመሄድ ያለው መንገድ ይሄ ብቻ ነው፡፡ እኛም ወደድንም ጠላንም የተጎዱትን ማየቱን ተገደናል፡፡ ለምደነዋል፡፡ በጣም የሚገርመው እና የሚያሳዝነው ከ100 ኪሎ ሜትር በላይ በማይታመን እና ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ሲጓዙ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ይህን ሁሉ ጊዜ ሲጓዙ ከሞት ጋር እየታገሉ ነው፡፡ በፈለጉ ሰዓት ሽፍቶች እየያዙ ይጫወቱባቸዋል፡፡ ዘይት አፍልተው ይደፉባቸዋል፡፡ ላስቲክ በእሳት እያቃጠሉ ሰውታቸው ላይ በማንጠባጠብ ያሰቃዩዋቸዋል፡፡ በመጨረሻም በመደፈርም በዱላም ይሞታሉ፡፡ በውሀ ጥም፣ በርሃብም ይሞታሉ፡፡ እየሞቱም በየመንገዱ ይቀራሉ፡፡ ከቻሉ አሸዋውን ጫር ጫር አድርገው ይቀብሯቸዋል፡፡ (ይህንን እድል ማግኘት መታደል ነው፡፡ አውሬ ነው የሚበላቸው ወይም አካባቢው ላይ ሽታ ሲያስቸግራቸው ይቀብሯቸዋል)

ከሞት የተረፉትም ቢሆን ቋንቋ ባለማወቃቸው በምልክት ብቻ ነው የሚበላ የሚጠይቁት፡፡ በርሃብ ተጎድተው ነው የሚደርሱት፡፡ አል-መሀዝ የምትባል ቦታ ላይ እንደልብ ሱቅ እና እቃ መግዣ ቦታ የለም፡፡ እዚህ





አካባቢ ምግብ ቤት ገብተህ መብላት አትችልም፡፡ ይህን ሁሉ መከራ ሊቀበሉ ግድ ያላቸው ከሚመጡበት ሀገር (ከኢትዮጵያ ማለታቸው ነው) ስቃይ እና ግፍ ችግር ስላለባቸው ነው፡፡...

በዚህ ሳቢያ ኢትዮጵያዊያን የሚደርስባቸው ግፍ እና ስቃይ የዛኑ ያህል እየበረታና አሰቃቂ እየሆነ ነው፡፡ ማንም አስታውሶ የሚከራከርላቸው አልተገኘም፡፡ እንዲያውም አፋኞቹ ምን ያህል እየተጠናከሩ እንደመጡና ትንሽ ሲነኳቸው እስከማጥፋት ድረስ ርቀው የሚሄዱ መሆናቸውን አንድ ምሳሌ እዚህ ጋ ላንሳ፡-

ቀኑ ረቡዕ ነው፡፡ ምሽት ላይ ተንቀሳቃሽ ስልኬ ደጋግሞ አንቃጨለ፡፡ የጋዜጠኛ መሀመድ ደርማን ቁጥር ነው፡፡ ስልኬን አነሳሁት...

‹‹አሎ! ኬፍ አለክ ያ-አኪ ጉሮም አነ መሀመድ ደርማን...›› (እንደምነህ ወንድሜ ግሩም እኔ መሀመድ ደርማን ነኝ) የሚለውን ቃሉን አቀበለኝ፡፡ ‹‹አረፍት ኬፈክያ-ሪጃል ሰሀፊ!›› (አውቄሀለሁ አንተ ወንድ (ጎበዝ) ጋዜጠኛ) አልኩት

‹‹አልዩም ሸዩ መርቡሽ አሽን ከወፉኒ ሙጅሪሚን...›› (ዛሬ ትንሽ ተረብሻለሁ፡፡ አሸባሪዎቹ ረበሹኝ) አለኝ እና ነገ እንገናኝ የሚለውን አስከተለ፡፡ በማግስቱ በተቀጣጠርንበት ሰዓት ቤቴ መጣ፡፡ የተረበሸው አጥምደውባቸው ሳይፈነዳ ለደህንነቶች ጠቁመው መክሸፉን ነገረኝ፡፡ ቀጣይ በዚህ ጉዳይ ላይ የበለጠ እንዲሰራ አደረጉት እንጂ ፈርቶ ወደኋላ እንደማይል ነገረኝ፡፡ ያበርታህ የሚለውን በሆዴ አልጎመጎምኩ፡፡ ይህን ያነሳሁት አፋኞቹ ምን ያህል የጠነከሩ ሲነኳቸው እስከማጥፋት ድረስ ርቀው እንደሚሄዱ ለማሳየት ነው፡፡

አጠቃላይ ዘገባውን ስቃኝ ደግሞ... ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ብቻ ባህሩን ተሻግረው የመን ከገቡ ኢትዮጵያዊያን መካከል በአጋቾች ከተያዙት ውስጥ ወደ 1000 የሚሆኑት ነጻ ወጥተዋል፡፡ በሀረጥ ዙሪያ ካሉ አካባቢዎች ድንበሩን ጠባቂዎች እና የመንግስት ወታደሮች (የመከላከያን ሰራዊት) በማስተባበር አካባቢውን በመፈተሽ ከአንድ ግቢ ብቻ 210 ሊያስፈቱ ችሏል፡፡ በ22/04/13 እሁድ ዕለት ከተያዙት ውስጥ 89 ሴቶች ሲሆኑ 10 ህጻናት ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ በግርፋት፣ በድብደባ፣ በእሳት ማቃጠል፣ በመደፈር.. የተጎዱ አካላቸው የደቀቀ እና የተጎሳቆሉ ናቸው፡፡›› ሴቶቹ በአጠቃላይ ተደፍረዋል፡፡ ለወራት ያህል ዘግተው ይዘው እንደፈለጋቸው ሲጫወቱባቸው በቀን ከ20 ጊዜ በላይ

የሚደፈሩበት ጊዜ እንዳለ ሁሉ ዘገባው ገልጸዋል፡፡ ከአፈና የተፈቱት የሰጡትን ቃል ስንመለከት ደግሞ፡-

ለስምንት ወር የታገቱት ካህሳይ ሚኬሌ እና ወንድሙ የደረሰባቸው ግፍ በጣም ሰቅጣጭ ነው፡፡ ‹‹..በጣም በጣም ነው የደበደቡን፡፡ በብረት ሁሉ ደብድበውናል፡፡ ላስቲኩን በእሳት እያቃጠሉ ሰውነታችን ላይ ያንጠባጥቡታል፡፡ ስልክ ስጥተውህ ለዘመዶችህ ደውል ይሉሀል፡፡ ከዚያ ዘመዶችህ ተቃጥለህ ስትጮህ እንዲሰሙ እላይህ ላይ የቀለጠውን ላስቲክ ጠብ እያደረጉ ያስቃዩሃል፡፡ በዚህ ስቃይ መሀል ነው ወንድሜ ህይወቱ ያለፈው፡፡ ገንዘብ ለማግኘት ወጥተን ወንድሜን በሞት አጥቼ ሌሎቻችንም አካላችንን ለመክፈል ተገድደናል›› በማለት ተናግሯል፡፡

አካባቢው ላይ ያለ አንድ ባለስልጣን ሲናገር ደግሞ ‹‹..ሆስፒታል ውስጥ 27 ሬሳ ፍሪጅ ውስጥ በስብሷል፡፡ የእነዚህ ሰዎች አሟሟት በስቃይ ለመሆኑ በሰውነታቸው ላይ ያለው ምልክት ያስረዳል፡፡ እስካሁንም ሬሳው ፍሪጅ ውስጥ ነው፡፡ መቅበር አልቻልንም፡፡ ፍርድ ቤቱ እንዲቀብሩ ቢፈርድም እስካሁን ከሶስት ወር በላይ ሆኗቸዋል አልተቀበሩም፡፡ ይህ የሆነው ግን መቅብሪያ ስላጣን ነው፡፡ በኋላ ላይ ግን አለም አቀፉ የስደተኞች ጽ/ቤት IOM እና UNHCR አንድ ላይ መሬት ሊገዙ ተስማሙ፡፡ እኛ ሁኔታውን ለማወቅ ከሆስፒታሉ ጋር መረጃ እንለዋወጥ ነበር፡፡ ይገዛል የተባለው መሬት ተገኘ አልተገኘ እንጠይቃለን፡፡ በኋላ መሬቱ ተገኘ ተስማሙ እና ተገዛ፡፡ በሳምንቱ ለመቅበር በቦታው ተገኘን፡፡ የሆስፒታሉ ሰራተኞች አምጥተው ሊቀብሩ ሲሉ የአካባቢው ሰው አይቻልም እዚህ አይቀበሩም አሉ፡፡ ዳግም ሆስፒታል ተወስደው እዛ ነው አሁንም ሬሳቸው….›› ብሏል ባለስልጣኑ፡፡

ጋዜጠኛው ራሱ ሲመሰክር ‹‹..ማዳ የተባለ ቦታ ብዙ የስደተኞች ሬሳ አገኘን፡፡ አሰቃይተው በእሳት ካቃጠሉዋቸው በኋላ ነው የሚጥሏቸው››[24] ብሏል፡፡ ይህን በተመለከተ አል-ተውራ ተብሎ የሚጠራው የሀገሪቱ ዋነኛ የመንግስት ጋዜጣ በየቦታው የኢትዮጵያዊያኑ ሬሳ ቀባሪ አጥቶ በየመንገዱ ወድቆ እንደሚታይ እና ጸሐፊው ራሱ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ ማየቱን ተናግሯል፡፡ በዘገባውም ሀረጥ አል-ዘሀራ የተባለ ቦታ 48 የታፈኑ ሰዎች አሉ፡፡ በተደጋጋሚ የመንግስት ወታደሮች ሊያስለቅቋቸው ሞክረው እነዚህን አጋቾች ሊረቱ ስላልቻሉ 48 ሰዎች እስካሁን እንደ ያዙዋቸው ነው፡፡ የመንግስት ወታደሮች ሲናገሩ አጋቾቹ ሊያስጠጉን አልቻሉም፤ ስለዚህ ምን ማድረግ እንዳለብን አላወቅንም ብለዋል፡፡

[24] ጋዜጠኛ መሀመድ ያነሳቸውን ፎቶዎች ሰጥቶኝ በርካታ ድረ-ገጾች ላይ ሰው እንዲያቸው ለቅቄያለሁ፡፡ አይቶ የሚማር ካለ በሚል፡፡





ይህ የሀገሪቱ ከፍተኛ የመንግስት ጋዜጣ የሚባለው አል-ተውራ ለችግሩ መንስኤ አካባቢው ላይ ያሉ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለስልጣናት በዝምታ መለጎማቸውና የመንግስት ቁጥጥር መላላት ለዚህ እንዳደረሰ ዘግቧል፡፡ ይህ ወንጀል በሚሰራበት አካባቢው ያሉት የወታደር እና የደህንነት ሰዎች ዝም ማለት የፈለጉት አፋኞቹ (ሀገ-ወጥ አንጓዮቹ) ከጀርባቸው ትላልቅ የመንግስት ባለስልጣናት ስላሉ መሆኑን ዘግቧል፡፡[25] እንዲያውም በቦታው ላይ ያሉትን ሀላፊዎች ሲያናግራቸው ‹‹ከፍርሃት የተነሳ አንድም ቃል አልሰጡንም፡፡ ለነፍሳቸው ፈሩ..›› ብሏል - ጋዜጣው፡፡ አለም አቀፉ የስደተኞች ድርጅት (IOM) ጊቢ ውስጥ ሲገቡ ያዩት በጣም ሰቅጣጭ እንደነበረ የገለጸው ጋዜጠኛ ብረት አግለው ሰውነታቸውን ከጠበሷቸው አንስቶ አስፈሪ እና ሰቅጣጭ ሁኔታ የተፈጸመባቸውን ለማየት በቅቷል፡፡ የድርጅቱ ሰራተኞች ግን በአስጸያፊ ስድብ በፖሊስ ከጊቢ እንዳስወጧቸው ዘግቧል፡፡ እንዲያውም እንዳንገባ እና ጉዱን እንዳናይ ዱላ ቀረሽ በሆነ ሁኔታ መለሱን›› ብሏል፡፡ (ይህ ሁኔታ ለእኔም ገጥሞኛል፡፡)

ጋዜጣው በመግቢያ ፅሁፉ ላይ…አባስ ሰዒድ የተባለ ጽዳት የሚሰራ ኢትዮጵያዊ ከስድስት ወር በፊት በሶማሊያ በኩል በባህር ተሻግሮ ወደ የመን ስለገባበት ሁኔታ ሲነግረው ‹‹እናንተ ሀገር ማንም በርሀብ የሚሞት የለም፣ ኢማን አለ፡፡ አዛኞች ናችሁ፣ የሰው ክብር አለ…እኛ ሀገር ግን..›› ብሎ አነጻጸረልኝ፡፡ ዛሬ አባስ ይህን የማቀርበውን ዘገባ ስታይ ኢማን አለ? ደጎች ናቸው? ፈሪሀ አላህ ያላቸው ናቸው ያልካቸው ሰዎች አለመሆናቸውን ስታውቅ ምን ትለኝ ይሆን? እኔስ እንዴት ብዬ በሙሉ አይኔ አይሃለሁ?..ምን አንገት የሚያቀና ነገር ሰሩና?..›› እያለ በሰፊው አትቷል፡፡ አባስ የተባለውም ሆነ እሱን መሰል አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ስደተኛ የስብዕና እና የማንነት ማጣት ችግር የተበተባቸው ናቸው፡፡ መስለው ለመኖር የሀገራቸውን ክብር አውርደው፣ የራሳቸውን ማንነት አዝቅጠው ለህሊናቸው ሳይሆን ለሆዳቸው ያወራሉ፡፡ ራሳቸውን አንቋሸው ያልሆነውን ይክባሉ ማንነትን ማዝቀጥን የመሰለ አስጠሊታ ነገር የለም፡፡ እኔ ያልሆነውን ሆነ ብለው የሚክቡትን የምጠላው ልክ እንዲሁ ገብተውም ሀገር ውስጥ ያለውን በዚሁ አመለካከታቸው ነው የሚሰብኩት፡፡ ለዚህ ጋዜጠኛ ያወራለት ሀባስም ከሚለው (ከካባት፣ ከቆለላት) በተለየ መልኩ ናት

[25] እኔ እስከማውቀው ደግሞ ይህ ብቻ አይመስለኝም፡፡ አይደለምም፡፡ አካባቢው ላይ ላሉ ባለስልጣናት ብቻ ሳይሆን ድንበር ጥበቃ ላይ ያሉት ሰዎች በባህር በገባው ስደተኛ ልክ ማለት በአንድ ሰው ሂሳብ እንዳላቸው የሚታወቅ ነው፡፡ እንዲያውም ከዚህ በፊት ባናገርኳቸው ሰዎች መረጃ መሰረት ጀልባው ቀድሞ ሲመጣ እንኳን ደውለው እንደሚጠሯቸው ነው፡፡ ሲታሰሩ እንኳን በገንዘብ ሀይል እንደሚወጡ የታየ እውነታ ነው፡፡

የመን፡፡ ‹‹..እናንተ ሀገር ማንም በርሀብ የሚሞት የለም እኛ ጋር ግን...›› ሲለው ምን ሊቀጥል እንደሚችል አስቡት፡፡ እውነታው ግን ሳያውቃት በካባት የመን ውስጥ ከ7 ሚሊዮን በላይ የዕለት የምግብ ሽሩን የሌለው በቀን አንዴ የሚበላ ህዝብ የያዘች ሀገር ነች - እንደአለም ጤና ቢሮ ገለጻ፡፡ አብዛኞች፣ የዋሆች ናቸው የሚለውም ቢሆን ከከተማ ውጭ ያለውን ነዋሪ የሚገልጽ ነው፡፡ በእርግጥም አብዛኛው ህዝብ ጥሩ ነው፡፡ መጥፎ ለመሆን ሲፈልጉ ደግሞ ሴጣን ራሱ በጭካኔያቸው የሚቀናባቸው አረመኔዎች ናቸው፡፡ ‹‹የሰው ክብር አለ እናንተ ሀገር›› ላለው ክብር መሰደብ፣ መዋረድ የሆነለት እባስ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ያጠራጥረኛል፡፡ የሚገርመኝ የሰብዓዊ መብት ተሟጋች የሚባሉ ሁሉ ችላ ያሉት ሀገር ጭቆና እና የቀለም መድልዎ የሚካሄድበት ለመሆኑ ካድም ተብለው በሚጠሩት ጥቁሮች ላይ የሚደረገው በቂ ማስረጃ ነው፡፡ ይህን አይነት ነገር እያለ ለመኖር ሲባል ብቻ ያልሆነ የሚቀላምዱት አይነቶች ናቸው ጋዜጠኛውን ያሳፈሩት፡፡

ለማንኛውም ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከ1000 በላይ በአጋቾች የታገቱ ስደተኞች ቢፈቱም ህጋዊ የሆነ ነገር አልተደረገላቸውም፡፡ አል-ዘሀራ የተባለ አነስተኛ መንደር ውስጥ የታገቱት 48 ኢትዮጵያዊያን አሁንም ከአጋቾቹ ማስለቀቅ እንዳቃታቸው ነው፡፡ ይህ ሁሉ ሲደረግ መንግስትም ያላወቀ መስሎ ዝም ብሏል፡፡ በይበልጥ ግን መረጃው ያለው የቶለያዩ እርዳታ ድርጅቶች ውስጥ ነው፡፡ እነሱ ጋ እውነቱ አለ፡፡ በጣም ብዙ ማስረጃዎችም አሏቸው፡፡ ግን ሊያወጡት አይፈልጉም፡፡ በጣም ሰቅጣጭ እና የተደረገባቸው ድርጊት የሚቀፍ ስለሆነ ህዝብ እንዲያውቀው አልተፈለገም፡፡ አይፈልጉም፡፡ አሁንም ቢሆን የበለጠ መረጃ ያለው እነሱ ጋር እንደሆነ አበክሬ እናገራለሁ፡፡ ጉዳዩን ግን ደብቀውታል፡፡ ይህ ደግሞ ጉዳቱ፣ መከራው እንዲቀጥል አድርጓል፡፡

እንደእኔ እንደእኔ ከሆነ ለምንድን ነው የሚደብቁት የሚለውን እንዳስስ ከተባለ ብዙ ምስጢር አለው፡፡ ሀገሪቱ ውስጥ ያሉት በልምምጥ ከመሆኑ የተነሳ ከሀገሩ ውጡ እንዲባሉ አይፈልጉም፡፡ ማድረግ የሚገባቸውን አለማድረጋቸውም ሌላው ህፀፃቸው ነው፡፡ የስደተኛው መብት ተገፎ ይህን ያህል ጭካኔ ሲፈጸም መጠየቅ ያለባቸውን አካል እንኳን ለምን ይህ ይሆናል ብለው አለመጠየቃቸው እና ይህ ሁሉ የደረሰው ስራቸውን ዘንግተው በመሆኑ ማንን ተጠያቂ ያድርጉ? ስለዚህ ምስጢር ጠብቀው ማቆየት ይፈልጋሉ፡፡ ይህ የእኔ ሀሳብ ነው፡፡ ጋዜጣው የዘገበው ደግሞ ‹‹በጣም የሚቀፍ እና ሰዎች ቢያዩት የሚሰቀጥጥ በመሆኑ ነው›› ከሚለው አንጻር ነው፡፡ ሌላው ‹‹መንግስትን ላለመወንጀል ነው›› ብሏል፡፡

በዛው ወቅት ሁሴን አሊ ሀምዛ የተባለ ሰው ተያዘ፡፡ የ31 አመቱ ሁሴን 210 ኢትዮጵያውያንን ይዞ ነው ያገኙት፡፡ 10 ልጆች ሲሆኑ ወደ 63





ሴቶች ነበሩ፡፡ ሁሉም ላይ ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ አንድም ሳይቀር ምልክት አለባቸው የተጎዱበት፡፡ የተገረፉበት፣ በእሳት የተቃጠሉበት ምልክት ሰውነታቸው ላይ በየቦታው ይታያል፡፡ ያለ ምንም ማንገራገር ወደ ሚግሬሽን ነው የወሰዷቸው፡፡ አጋቹም እስር ቤት ገባ አሉ፡፡ ሌሎችም የተያዙ ነበሩ ባለስልጣኖቹ ስም መጥቀስ አልፈለጉም፡፡ ምክንያቱም ሊከሷቸው አይፈልጉም፡፡ ሌላው ቀርቶ ይሄ ሁሉ የተያዙት በወታደሮቹ ጉብዝና አይደለም፡፡ በኢትዮጵያዊያኖቹ የተለያየ ጥረት ነው፡፡ ይህ በህገ-ወጥ አንጓዦች የታገቱት ስደተኞችን የማስለቀቅ ስራ የሚከናወነው ወደ ከሰዓት ላይ አጋቾቹ ቅመው መርቀን በሚሉበት ሰዓት ነው፡፡ ሀረጥ ሀጃ የሚባለው አካባቢ 160 ሴቶች እና ህጻናት ያሉበት ታጋቾች ተለቀዋል፡፡ ይሄንን መከላከያ ሚኒስቴር እንኳን መግለጫ አልሰጠም፡፡ አሳፈራቸው፡፡ በየጊዜው በየቀኑ፣ በየቦታው የሚለቀቀውን ቁጥር ሲያዩት መግለጫ ማውጣት አሳፈራቸው፡፡ ባለፈው ሳምንት ብቻ 535 ሴቶች እና ህጻናት ያሉበት የኢትዮጵያዊያን ስደተኞች ሀረጥ አካባቢ አስፈትተዋል፡፡ ግን አልተናገሩም፡፡ ዜና ሊቀርብ ተዘጋጅቶ ሳለ ከሰዓት ያነሰ ጊዜ ሲቀረው ስበው አስቀሩት፡፡ ማንኛውም ሚዲያ እንዳያወራው.. እንዳይገልጸው ደበቁ(ከለከሉን)፡፡ /ልብ ይባልልኝ ወዳጆች ይህ መንግስት የከለከለውን መረጃ ለህዝብ መታገዱንም ሆነ መከልከሉን የሚነግረን አል-ተውራ (ህዝባዊ) የተባለው የመንግስት ጋዜጣ ነው፡፡ እንዳይተላለፍ የከለከሉበትን ምክንያት ስናይ ደግሞ በየጊዜው የሚለቀቁት ታጋቾች ብዙ በመሆናቸው እፍረት ነው፡፡ እነዚህ የሰው ልጆች ላይ የተፈጸመው ነገር አውሬ ላይ እንኳን ሲደረግ የማይገባ በመሆኑ ተሰምቷቸው፣ ራሳቸውን እንኳን ይቅር እንደማይሉ ተሰምቷቸው.. በይሉኝታ፣ በእፍረት...ይሆን? ሲፈጸም ዝም ብለው ያዩት አሰቃቂ ድርጊት እንኳን ኢትዮጵያዊያኑ ራሳቸውም ለራሳቸው ይቅርታ የማያስደርግ ነው፡፡ አሰቃቂ ነገር በሀገራቸው ውስጥ መሰራቱ አንገታቸውን አስደፍቷቸዋል፡፡

ይህ ብቻ ነው ብሎ ማሰብም አይቻልም፡፡ ከዚህ መግለጫ ያልተሰጠበት ድብቅ ወንጀል ጀርባ ብዙ ነገር አለ፡-

1. እነዚህ ሰዎች የሚሰሩትን ጭካኔ ለመደበቅ (ለማጥፋት)
2. ከመንግስት የሚጠበቀውን ሀላፊነት ያለመወጣት ችግር፣ ችላ ማለትን..ለመደበቅ
3. አካባቢው በመንግስት ችላ ባይነት የተነሳ የስቃይ እና የወንጀል ቦታ መሆኑ
4. መንግስትም፣ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትርም፣ በእምነቱም፣ በህጉም ፊት ችላ ብለውት በሀገሪቷ ወንጀል የሚፈጸምበት ቦታ መሆኑ አሳፍሯቸው

5. ከራሳቸው ሀላፊነቱን ለማውረድም ነው እነዚህ ሰዎች እንዳይከሰሱ እና በህግም የጥፋታቸውን እንዳያገኙ ችላ አሉ፡፡ ለአፋኞቹ መደበቅ እና ሽፋን ለማድረግ እና ህግ ፊት እንዳይቀርቡ በሚያደርጉት ጥረት አስቀያሚ ሌላ ወንጀል ይሰራሉ፡፡ ለምሳሌ ያስፈቷቸውን እስረኞች መሀወር፣ መላኪጥ፣ ምስራቅ ሀረጥ፣ ሰብስበው አስገቧቸው፡፡ ከ50 አፋኞች ጋር ነው የገቡት፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 9 ኢትዮጵያዊያን ናቸው፡፡ ሁሉንም ወደ ሰነዓ ኢሚግሬሽን አመጧቸው፡፡ የቀሩትንም ወደ ሀገራቸው ሊመልሷቸው ፕሮሰስ ጀመሩላቸው፡፡ ‹‹ግን ይህ ነው ህግ?...›› በማለት ጋዜጠኛው ሀሊናዊ ሙግት የሚፈጥር ኢትዮጵያዊያን ልንጠይቀው ይገባን የነበረውን ጥያቄ ያቀርባል፡፡ እነሆ፡-

‹‹...ግን ይሄ ነው ወይ ህግ? እንደዚህ ከተጎዱ በኋላ ያለምንም ፍትህ በቀላሉ ወደ ሀገራቸው መመለስ ውጤት ነው? ሀቁ ይህ ነው?...ያፈኗቸው እንዲህ የጎዷቸው፣ አካላቸውን ያጎደሏቸው ለፍትህ ሳይቀርቡ ውጤቱ ሳይታወቅ እነሱን ማሳፈር ማስረጃውን ማራቅ ነው፡፡ በትንሹ የጎዷቸውን፣ ያሰቃዩዋቸውን ለህግ ሳያቀርቡ የሰው ልጅ ክብር ባለው ሁኔታ እንኳን ትንሽ ሳያርፉ እና ምንም ሳይደረግላቸው ወደ ሀገራቸው መመለስ አግባብ ነውን? ባይሆን እንኳን ለእያንዳንዳቸው ለተጎዱበት 500 ዶላር ለእጃቸው ማገገሚያ ካሳ ሳይደረግላቸው መሸኘት ከእምነትስ አንጻር ልክ ነው? ይሄን ለማድረግ ባይቻል እንኳን ከሀጃ ክ/ሀገር ባጀት ተቀንሶ ሊሰጣቸው ይገባ ነበር፡፡ በእነሱ ክልል በእነሱ ሰዎች የተፈጸመባቸው ናቸው እና በእምነት እንኳን ካየነው ትንሽ ሀጢያታቸውን (ወንጀላቸውን) ለመቅረፍ ይረዳቸው ነበር›› ብሏል፡፡

ስለእነሱም የሚጠይቅ አካል ባይኖር ዝም መባሉ ልክ ነው ወይ? የሚለውን ስናይ ትክክለኛ ነገር ነው፡፡ በእርግጥስ አካላቸው ሁሉ ጎሎ በባዶ እንዲመለሱ ሲደረግ በዝምታ ከመቀበል ውጭ ማንስ ምን አለ? ሰብሳቢ የሌለው ዜጋ......





# - 21 -

# ወደመጥፊያችን የምንሮጥ የእሳት ራቶች

ያሉትን ይበሉ ብልማ
ጥንድ..ጥንዱን አንገቸቅዥቁ
ህቅ!!! ባልኩ ተንሰቅስቄ
ሀዘኔ በወጣ በታወቀ ለሰው
አምቁ ከማልመስምሰው
እርዱኝ...እርዱኝ እባካችሁ
ትርፍ እንባ ያላችሁ
አልቅሱልኝ ለእኔ እሮ ሞተ ብላችሁ....

## ‹‹የኮንትሮባንድ ዕቃ››

ለኖ ታህሳስ 29 ቀን 2005 ዓ.ም በዓልን በገመድ ታንቀው ሲደበደቡ ከነበሩና ከሞት ተርፈው ሰነዓ ከገቡ ልጆች ጋር አሳለፍኩ፡፡ ሰውነታቸው ላይ በድብደባ ያረፈውን ቁስል እያየን አንገታቸው ላይ ገመዱ የከረከራቸው ምልክት ሰቅጥጦን ከሞት እንዴት እንደተረፉ እያወጉን በእንባ ስንታጠብ አሳለፍን፡፡

እንግዲህ ሁሌም እንደማደርገው በዓልን ለማክበር ከሰዓት በኋላ ቤቴ ተሰባስበን ምሳ በልተን እንጨዋወታለን፡፡ ካልድ ለገሰ የተባለ ጓደኛዬ ስልክ ደወለልኝ፡፡ ‹‹..ከባህር የመጡ ሁለት ልጆች አግኝቼ ነበር ይዣቸው ልምጣ ወይ?›› አለኝ፡፡

‹‹ይዘሀቸው ና በዓልን አብረውን ያሳልፉ›› አልኩት፡፡ እኔ ያሰብኩት ብዙ ተንገላተው ደክመው፣ ተርበው ስለሆነ የሚመጡት ለራሳችን ያዘጋጀነውን ተቃምሰው በደስታ አብረውን ይዋሉ ብዬ ነው፡፡

‹‹በአብዱልገዊ ሰዎች ተይዘው በገመድ ታንቀው የተረፉ ናቸው፡፡ ብዙ ተደብድበዋል›› ሲል ካልድ አከለልኝ፡፡ ደነገጥኩ ከዚህ በፊት እዛ ቦታ

ተይዘው፣ ተደብድበው የመጡ• ብዙ ልጆች አናግሬያለሁ። እርግጠኛ ነኝ ከአንድ ሰው እንኳን በስህተት ጥሩ ነገር አልሰማሁም። ውስጤ የነበረው በዓል የማክበር ፍላጎት እሳት እንደነካው ላስቲክ ኩምትር ሲል ታወቀኝ። በበዓሉ ዋዜማ እሁድ ታህሳስ 28 ቀን በነበረኝ ቀጠሮ መሰረት UNHCR ቢሮ ሄጄ ያየኋቸውን ሁለት ኢትዮጵያውያን እያስታወስኩ ስለእነሱም አሰላስል ጀመር። UNHCR ቢሮ ውስጥ ካገኘኋቸው ሁለት ሴቶች አንደኛዋ ግፋ ቢል ከፍ አድርጌ ብገምታት 16 አመት የሚሞላት ልጅ ነች። ከባህር እንደወረዱ በሚያግቱት አፋኞች ተይዛ ከድብደባ ብዛት መስማት ተስኗታል። የቢሮው ሰራተኞች በምን መንገድ ቃለ-ምልልስ እንደሚያደርጉላት ግራ ተጋብተዋል። መሄድ መራመድ ሁሉ አትችልም። እግሯን እንፌርክካ ገተት.. ገተት ትላለች። ጾታዊ ጥቃት እንደደረሰባት ከሁኔታዋ ገመትኩ። ጆሮዋ ብቻ ሳይሆን ራስ ቅሏ ላይም በድብደባ ችግር ተከስቶባታል። ፍዝዝ ቅዝዝ... ያለች ናት። ቁጭ ባለችበት እንቅልፍ ይዟት ጭልጥ ይላል። ብትት ትልና እንደገና ጭልጥ ትላለች። ምክንያቱ ደግሞ ሌሊት ራሷን እና ጆሮዋን የተመታችው ሲጠዘጥዛት ስታቃስት፣ ስታለቅስ እንቅልፍ አጥታ ስለምታድር ነው።

ይዛት የመጣችውን ሴት ላናግራት ብሞክርም ኦሮሚኛ ባለመቻሌ በቋንቋ መግባባት አልቻልንም። ምስጋና ለኡስማን አብዳ ፊቶ ብዙም እንኳን አማርኛ መናገር ቢያስቸግረውም አስተርጉሞልኝ ነው ይህን ያህልም የተረዳሁት። ኡስማን ወደ ሁለተኛዋ ሴት እያሳየኝ «...እሷ ደግሞ እዛ አግተዋት በነበረ ሰዓት እንደፈለጋቸው ሲያደርጓት (ሴትነቷን ሲጠቀሙ) ከርመው አርግዛ ነው የመጣችው። ...ይሄው ወልዳ አራስ ነች» አለኝ።

ኢንተርሶስ የተባለ በሴቶች ጉዳይ የሚሰራ ግብረ ሰናይ ድርጅት ውስጥ በአንድ ቀን 8 ሴቶች ተደፍረው መጥተው ህክምና ሲደረግላቸው አይቻለሁ።

ይሄ ሁሉ ለምን? ምነው ረሳኸን.... ከፈጣዬ ጋር ሙግት ይዤ ስንገታገት የቢሮው ሰራተኛ የሆነው ነቢል የሚሉት መጣ። ልጅ ይዛ ሲያያት «ባለፈው ኢንተርቪው ስትገቢ ልጅ የለሽም ነበር አሁን ከየት አመጣሽ? የማነው?..» ሲል ይጠይቃታል። ተገዳ በመደፈሯ ምክንያት ስትመጣ እርጉዝ እንደነበረች በሰዓቱ መናገሯን ገለፀች። አሁንም በስቃይ በኦፕሬሽን እንደ ወለደችው ስትነግረው ሰማሁ። ወደውጭ ሳይሆን ወደውስጥ አልቅሼ ምንም ላደርግላቸው ባለመቻሌ እርጉም ደሀ ኪሴን ረግሜ ቤቱ ገባሁ።

ዛሬ ደግሞ..... በዓልን በዓል ለማስመሰል ተሰባስበን ሳለ በነገሩኝ ነገር ተረብሼ በዓሉ በዓል አልመስል አለኝ። ከእነሱ የሰማሁት አሳዛኝ ታሪክ ደግሞ እነሆ:-





የቡታጅራ ልጆች ናቸው። መሀመድ ሁሴን እና ወርቅዬ ይባላሉ። ወርቅዬ ሰውነቱ ደልደል ያለ ነው። አብሮት ያለው መሀመድ ደግሞ በተቃራኒው ቢያስነጥስ ድፍት የሚል ለንቋሳ ነገር ነው። ሁለቱም ቡታጅራ ባለ ደላላ አማካኝነት ነው እያንዳንዳቸው ስምንት ሺህ ብር ከፍለው ለጉዞ የተነሱት። ደላላዎቹ በቅብብል የሚሰሩ ናቸው። ከእነሱ ጋር ሌላም የቡታጅራ ሰው አለ። ያውም የ8 ልጆች አባት። ይህ ሰው ከሰመራ ተነስቶ ደዋሌ በሚባለው ቦታ አድርጎ ለስምንት ቀን የኢትዮጵያን ድንበር አልፎ ወደጅቡቲ የሚኬደውን የእግር መንገድ አቅቶት ሜዳ ላይ ወድቆ ቀረ። እነሱ ስቃያቸውን አይተው አዩ ከሚባለው የጅቡቲ የባህር ጠረፍ ተነስተው የየመን ድንበር ባብል መንደብ ይደርሳሉ። መኪና ቆሞ ነበር የጠበቃቸው። ይሄ ደግሞ በተደጋጋሚ ከሚያዙ ሰዎች እንዳጣራሁት ጀልባ ጫኞቹና አፋኞቹ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ ተነጋግረው ከጀልባ ሲወርዱ ይጠብቋቸዋል። መኪና ላይ ጭነዋቸው ለሶስት ሰዓት አካባቢ ተጓዙ።

• በግንብ ከታጠረ ትልቅ ግቢ ውስጥ ከተቷቸው። «...ሳዑዲ ያ የሚቀበላችሁን ሰው ስልክ ቁጥር ስጡን ደውለን 1000 የሳዑዲያ ሪያል ከላኩ ትፈታላችሁ። ያለበለዚያ አንለቃችሁም... እስከዛው በሰላም የያዛችሁትን ሳንቲም ራሳችሁ አውጡ...» ይሏቸዋል። ሁሉም ያለውን በተለያየ ቦታ ደብቆ ስላስቀመጠ አይገኝብኝም ብሎ ዝም፣ ጭጭ... ስልክ ቁጥር ስጡን አሁንም ዝም፣ ጭጭ። ይኸኔ እያንዳንዱን በየተራ ልብሱን... ፓንት እንኳን ሳይቀር ማስወለቅ ጀመሩ።»

በጣም የሚያሳዝነው ይህን የሚያደርጉት ለነሱ ተቀጥረው የሚሰሩ ኢትዮጵያዊያን መሆናቸው ነው። ኦሮሚኛ፣ ትግሪኛ፣ አፋርኛ የሚያስተረጉም ከተለያየ ብሔር ሠራተኛ አላቸው። ታዲያ ሥራቸው ማስተርጎም ብቻ እንዳይመስሎት እህል ውሀ የማያስኝ አጣና ይዘው ፌሮ ብረት ይዘው ወገናቸውን ይቀጠቅጣሉ። አካል ያጎድላሉ።

እነዚህ ወገናቸውን የሚያሰቃዩትን በተመለከተ የተከሰተ ነገር እዚህ ጋ ላነሳ ወደድኩ። እዮኤል ይባላል። ትክክለኛ ስሙ አይደለም። ሁሉም የሚያውቁት በዚህ መጠሪያው ነው። ሳዑዲያ ድንበር ላይ ለደላላዎች ተቀጥሮ የሚሰራ ሀይለኛ ገራፊ ነው። እዮኤል ብዙዎችን አካል በማጉደል የሚታወቅ ጨካኝ ነው። ወደኢትዮጵያ ለመግባት ከሳዑዲያ መጥተው የመን ከሚቆዩት ጋር ተደባልቆ ሰነዓ ከተማ ገባ። ሀሳቡ ወደኢትዮጵያ ለመግባት ነበር። ይሁንና በሱ ተደብድበው ብዙ ስቃይ የደረሰባቸው ተሰባስበው ኤምባሲ ከሰሱት። ውሸታቸውን ነው ብሎ ስለካደ ኤምባሲው በነጻ ለቀቀው። ልጆቹ ኢትዮጵያ ድረስ ተከታትለው ጠቁመው አስያዙት። መንግስትም ትኩረት ሰጥቶ አጣርቶ ወህኒ አውርዶታል።

ወርቅዬ ታሪኩን ቀጠለልኝ ‹‹...ወንዱንም ሴቱንም መለመላችንን እያስቀሩ ያወለቅነው ልብስ ላይ ስማችንን ጽፈን እንድናስቀምጥ ተደረገ:: ሁላችንንም፣ ሴቱንም ወንዱንም አንድ ክፍል ውስጥ ነው ያጎሩን:: ራቁታችንን እያዩን ሳቁብንና ልብሳችንን አንድ በአንድ ፈተሹ:: ምንም ሳንቲም ሳያስቀሩልን ወሰዱ:: ሌላው ቀርቶ ስልክ ቁጥር ጽፎ ይዞ ደብቆ የተገኘ ይገደላል አሉ::

‹‹እኔ ይሄ የእህቴ ነው ዱባይ ያለች ዘመዴ ነው አልኩ:: አንዱንም ሳዑዲያ ያለ ጓደኛዬን ስልክ ሰጠሁ ለመትረፍ ብዬ:: ከልጅቷም ጋር ዱባይ ደወልኩ:: መነሳትህን አላወኩም ያለኝን ገንዘብ ኢትዮጵያ ላክሁት አለችኝ:: ሳዑዲያ ያለው ጓደኛዬም እሺ እልካለሁ ብሎ በአረቢኛ ካናገራቸው በኋላ ሲደወልለት አላነሳም አለ:: ልብሳችንን ከመለሱልን በኋላ ተጠራሁ እና የተንጠለጠለው ገመድ ውስጥ አንገትህን ክተት ተባልኩኝ:: አማራጭ የለኝም መሳሪያ ይዟል:: ከተትኩ:: ገመዱን ሳቡና አንጠለጠሉኝ:: ትግሪኛ አስተርጓሚው ‹ገና ነው ህይወቱ አልወጣም..› እያለ አቆዩኝ:: በቃ መተንፈስ አቅቶኝ....››

የእሱን ንግግር አቋርጦ መሀመድ ቀጠለ ‹‹ሱብሐናላህ ፍርግጥ ፍርግጥ.. አለ:: በቃ! እኔማ ሞተ ብዬ ነበር... አወረዱት የተወሰነ ሰዓት ራሱን አያውቅም ነቃ:: ...እሱ ሲነቃ ደግሞ እኔን አንጠለጠሉኝ:: ይሄውልህ አንገቴ...›› አንገቱ ተከርክሮ ቆስሏል:: ማጅራቱ ላይ ገመዱ የሸመቀቀው ቆዳው ሁሉ ተልጧል:: ምኑን አይተህ አለና ሸሚዙን ወለቅ አደረገው:: ጀርባው የተገረፈበት ተተልትሏል:: በዓል እናከብራለን ብለን ተሰብስበን አለቀስን::

በመሀመድ ቁስል እና ጠባሳ በማልቀሳችን፣ አይናችን እንባ በማቆሩ ገና ምን አያችሁና የሚል ይመስል ወርቅዬ ትረካውን ቀጠለ:: ‹‹ገና አፋር ሰመራ ደላላው ቤት እያለን ሚስቱ ‹እናንተ እኮ እቃ ናችሁ:: የኮንትሮባንድ እቃ!.. ለምን ትሄዳላችሁ› ስትል እንድንመለስ ነግራን ነበር:: አልገባንም እንጂ በገባንም ለመመለስ አልፈለግንም:: ለማንኛውም በተለያየ ጊዜ ስድስቱ ነው የተሰቀልኩት:: አልሞት እያልኳቸው ያወርዱኛል:: በኋላ ላይ ዱላ ይዞ መጣና ግራ ትከሻዬን እስኪበቃው ወገረኝ:: እጄ የሞተ መሰለኝ ዝልፍልፍ ሲልብኝ በቀኝ ትከሻዬ ላይ ድብደባውን ቀጠለ:: ቀኙም እጄ ደንዝዞ አልታዘዝህ አለኝ:: በዚህን ጊዜ ጀርባዬ ላይ ይነርተኝ ገባ:: ብጮህ ማን ይድረስልኝ? በመጨረሻ ፌሮ ብረት አንስቶ የጀርባ አጥንቴን ሰበረው:: ለሁለተኛ ጊዜ ደገመኝ...››

አሁንም ብዙውን ሰዓት በዝምታ የሚቆዝመው መሀመድ አቋረጠው::





‹‹እሪሪ.. ብሎ ጮኸ.. በቃ ተዝለፍልፎ ወደቀ:: በዚህን ጊዜ በለው... በለው የሚለው አማርኛ ትንሽ ትንሽ የሚችለው አረብ እግር ስር ወድቄ ነበር:: እንዲህ ቢመቱኝ እኔማ ሟች ነኝ ብዬ ‹እንዲያው በእናትህ እኔስ እሞታለሁ:: ያለኝን የወንድሜን ስልክ እሰጣለሁ አታስመታኝ› ብዬ እግሩን ሳም አደረኩት:: ደገምኩ እና ምጥጥ አድርጌ እግሩን ሳምኩት:: በዚህ ሰውነት ይሞት ነበር:: እዩት እስኪ ሰውነቱን...›› የወርቅዬን ልብስ ገልጦ ጀርባው ላይ በብረት መተውት ያሳበጡትን እና መቀመጥ መቆም ያቃተው የተሰበረ አጥንቱን ቦታ አሳየን:: ‹‹እሪሪ....›› ብጮህ ወደድኩኝ:: ግን ወደየት? ለማን? ምን ሰሚ ማን ተከራካሪ አለንና?..

‹‹ይሄ ሁሉ ስቃይ የተቀበልነው ‹ለእያንዳንዳችሁ በጀልባ ላመጧችሁ የሳዑዲ 200 ሪያል ከፍለናል:: ስለዚህ ብር ሳይላክላችሁ አንለቃችሁም› በሚል ነው›› ብለውኛል:: በጣም የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ተምረው ዲግሪ፣ ዲፕሎም ይዘው ስራ አጥተው ስደትን ለመሞከር የወጡ መሆናቸው ነው:: ከእነዚህ ውስጥ ታደሰ አብሯቸው የነበረ የትግራይ ልጅ ነው:: የ2004 አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ዲግሪ ምሩቅ ነው:: ጥሩ የስፖርተኛ አይነት ፈርጠም ያለ ሰውነት ስላለው ይማታ ይሆናል ብለው ፈሩት:: ቀድመው እጅ እና እጁን እግርና እግሩን በብረት ሰባበሩት:: ሽንት ቤት ሲሄድ እየተንፏቀቀ ነበር:: ሳዑዲ ዘመዶች ስላሉት 1000 የሳዑዲ ሪያል ላኩለት:: ሲለቁት እንዴት ይሂድ! በጣም ሲሰቃይ ለሽንት እንኳን ደግፌ የምረዳው እኔ ነበርኩ›› ሲል ወርቅዬ ነግሮኛል::

## ከነህይወት እየቀበሩ መቅጣት..

## ያ ረቢ ኑ ባሲ!!!..ያረቢ ኑ ባሲ...

አንድ ወዳጄ የእህቱ ልጅ በባህር ወደ የመን ሲመጣ መያዙን ነገረኝ:: ትንሽ ቆየ እና እህቱ ማለት የተያዘው ልጅ እናት ደወለች:: እናት ጉዷን አላወቀችም:: የመን መጥታ ችግሩን አላየች በምን ትወቅ? ደግሞስ ችግሩን ለማወቅ የግድ የመን መምጣት አለባት እንዴ? የለባትም:: በየጊዜው ይጻፋል:: ግን ማንበብ ሌላ ማስተዋል ሌላ:: ልጇም ያን ነው የሆነው:: ልጅ በሚውልበት እናት አትውል:: በዛ ያለ ሰው እየሰማ እያየ ነው መልሶ በባህር የሚመጣው:: ልጇ ደላሎች ጋ እንዳለና ወደ ሳዑዲ ሊገባ እንደሚፈልግ፣ ግን ደላሎቹ እሱን እዚያ ለማድረስ 3500 የሳዑዲ ሪያል መጠየቃቸውን ነገረችኝ:: ወዲያው የገባኝን ያህል ገባኝ:: የተባለውን ገንዘብ ብትልክላቸው እንደማያደርሱት አውቃለሁ:: በዛ ላይ ልጁ ገንዘብ

የሚልክልህ ሰው ስልክ ቁጥር ንጎረን እያሉ ሲያዋክቡት፤ ሲያስቃዩት እናቱ ጋ አስደወለ:: ስልኩ ስላልተነሳ ይመቱታል:: ለቤተሰቦቹ አጓጓዥ ደላሎች ሳይሆኑ አፋኞች እንደሆኑ ብናገር ማን ሰምቶኝ! ኧረ አይደሉም ደላሎች ናቸው አለ:: ክርክሩን በዝምታ አልፌ ልጁ እኔ ወደ አለሁበት ሰነዓ እንዲመጣ በተሰጠኝ ስልክ ቁጥር ደወልኩ::

‹‹እህ ማነህ ጻል..ምን ኮነክ ነው? ማንን ፈለክ..›› የሚል ገጠርኛ ቃና ያለው አማርኛ ተናጋሪ አወራኝ:: ልጁን እንዲያቀርብልኝ ስሙን ነገርኩት:: ማውራት ያለብኝን ያህል አወራሁ:: አክል አድርጌ ወደ ሳዑዲ ሳይሆን ሰነዓ እንዲመጣ ምን ያህል ክፍያ እንደሚጠይቁ ተነጋገርኩ:: ሁኔታዎችን እኔ በማውቀው መንገድ ለማስኬድ ከአፋኞቹ ጋር ተደራደርኩ:: 1500 የሳዑዲ ሪያል እንድልክ ነበር የተስማማነው:: ገንዘቡም ተላከልኝና ላክሁኝ:: ይህም ሆኖ ልጁን ለመልቀቅ ጥቂት ማንገራገራቸው እንደማይቀር ስለማውቅ ታግሼ መጠባበቅ ጀመርኩ:: ገንዘቡ ከተላከላቸው እንደማይደበድቡት በተደጋጋሚ በሰማሁት መረጃ አውቃለሁ:: ወዲያው ባይሆንም አንገራግረው ከቀናት በኋላ ለቀነዋል ይደውልልሀል ተባልኩ::

ሁለት ሶስት ቀን ምንም የለም:: የሚያደርሱት ሀረድ የተባለው ቦታ ድረስ ነው:: ይህን ያህል ርቀት ብቻውን ከመጣ ድጋሚ በሌሎች እንዳይያዝ ወይም ለእነሱ ስለተከፈላቸው ለሌላ አፋኝ ቡድን አሳልፈው እንዳይሰጡት ካደረብኝ ስጋት አንፃር 750 ኪሎ ሜትር አካባቢ ተጉዤ፣ መክፈል ያለብኝን መስዋዕትነት ከፍዬ ልጁን ለማምጣት ጉዞ ሀረድ ወደሚባለው ቦታ አደረግሁ::

ወደዚህ ወገኖቻችን ወደሚሰቃዩበት ቦታ ሀሙስ የካቲት 7 ቀን 2005 እንደሚፈልጉኝ እያወኩ ስለሆነ የምሄደው ካልድ ለገሠ ከሚባል ጓደኛዬ ጋር ነው አካሄዴ:: የእናትንም ሆነ የወዳጄን ጭንቀት ስላወኩ ስራዬን ትቼ፣ ካለችኝ ሳንቲም ላይ ቀናንሼ፣ ራሴን ለውጪ..ነው ችግር ቢገጥመኝ ብዬ ካልድን አስከትዬ ጉዞዬን የጀመርኩት:: አሳዛኙ ነገር ተግባብተን አልተግባባንም:: ወይም አልተማመንም መሰለኝ:: ያለምንም ጥቅም ይህን ያህል መስዋዕትነት ለመክፈል መዘጋጀቱ፣ ለትራንስፖርት ማውጣቱ፣ ስራዬን ጥዬ መሄዴ..ምን ቢጠቀም ነው ሊያስኝ ይችላል:: ከዚህ በፊት በዛ ያለ ሰው ጥቅምህ ምንድን ነው? የሚሉኝ ስላሉ አይገርመኝም:: ግን የህሊና እርካታን በምን አይነት ጥቅም እንለካው ይሆን? የጀመርኩት ጉዞ ትዕዝ የሚባለው የየመን ሶስተኛ ከተማ ላይ ተገደበ::

ትዕዝ ከተማ ውስጥ በድብደባ እጁን የተሰበረ ተአጣዬ አካባቢ ልጅ አግኝቼ አነጋግሬ ነበር:: ስሜነህ ይባላል:: እንደማንኛውም ስደተኛ በጅቡቲ ነው የመጣው:: ወደ ሀረጥ ስሄድ ሆቴል ቤት በር ላይ ቆሞ ከሰው የሚተርፍ ምግብ ሲጠብቅ ነው ያገኘሁት:: ጠቆር ያለ ቆዳውን ጸሀይ





የበለጠ አክስሎታል:: ስማ...!! ሲለኝ እና ዞር ስል የፊቱ አሳዛኝ ገጽታ አንጀት ይበላል:: እጁ ላይ የተጠመጠመው ፋሻ ቆሽሻዋል:: ምንድን ነው? አልኩና ወደ እጁ አሳየሁት:: የእሱ ቅኝት የእሱ ፍላጎት ሌላ ነበርና እንደራበው ነገረኝ:: እንዲከተለኝ ስነግረው አብሮኝ ያለው አቡሽ ‹‹ስንቱን አብልተህ ትችላለህ? ይሄ መንገድ ላይ የምታየው ሁሉ ተርቦ ነው›› አለኝ:: ለካ እውነቱን ነው:: እሱ ሲከተለን ከ30 በላይ ሰዎች ተከትለውን መጡ::

ምግቡ ቀርቦልን ገና አንዴ ስጎርስ ተሻምተው መብላታቸው አንሶ ከነሰሀኑ ወሰዱት:: የሆቴሉ ሰራተኞች መጥረጊያ ይዘው ያባርሯቸው ጀመር:: ከብዛታቸው አንጻር ብፈራም ባለኝ የዛሬን እንኳን ምሳ ልጋብዛቸው አሰብኩ:: ወደ ሰነዓ መመለሻም ሆነ ለሌላ መንቀሳቀሻ እንደማይተርፈኝ አውቄያለሁ:: ከሰነዓ ላኩልኝ ብዬ ላስልክ አሰብኩና የሆቴሉ ሰራተኞች ስደተኞቹን እንዳያባርሯቸው ነገርኳቸው:: ሁሉም ገብተው መሬት ተደረደሩ:: ሩዝ ለሁሉም እንዲሰጧቸው አቡሽ ነገራቸው:: በነገራችን ላይ አቡሽ የአካባቢው የሽፋን ስሙ እንጂ አረጋይ ነው ትክክለኛ ስሙ:: የአዲግራት እንቲጮ ልጅ ነው::

በስነ-ስርዓት ተደርድረው እንዲሰለፉ እና ለሶስት ሁለት ሰሀን ሩዝ ማባያ እና ግማሽ ዶሮ እንዲወስዱ አደርግን:: መጨረሻ ላይ እኔንም ሆነ አቡሽን እጃችንን ራሳችንን ትከሻችንን... ኧረ ምን ያልሳሙን ቦታ አለ:: የተጠቀምንበትን ሂሳብ ስጠይቅ ባለሆቴሉ ወደ እኔ መጣ:: ኢትኒዮ አርባይን ነፈር ሩዝ...ዋሂዶ አሽሪን ዲጃጅ..ቢከም ላህስብልክ? (42 ሰሀን ሩዝ 21 ዶሮ ነው በስንት ላስብልህ?) ማለቱ ገረመኝ:: ከሩዙም ሆነ ከዶሮው ዋጋ ላይ አንድ አራተኛውን ቀነሰልኝ:: ምክንያቱ ደግሞ ‹‹አላህ የሚወደው ስራ ስለሰራህ እኔም ላግዝህ ይገባል›› ብሎ መሆኑ አስደሰተኝ:: ሂሳቡን ሰርተው ሲነግሩኝ ግን ደነገጥኩ:: ቢሆንም 35 ዶላር አካባቢ ቅናሽ ስላደረገልኝ ፈጣሪዬን አመሰገንኩት:: ወገኑ ያልሆነው ባለሆቴል ሂሳብ ሲጋራኝ እኛ ለወገናችን የሚጠበቅብንን አለማድረጋችን አበክሮ ታሰበኝ:: እንግዲህ ባብል መንደብ የሚባለው አካባቢ ሄጄ ለማየት ያሰብኩት በሳንቲም እጥረት ሊስተጓጎል ሆነ:: ከሰነዓ ላኩልኝና ስመለስ እከፍላለሁ ለማለትም ዳዳኝ:: ማታ ላይ ግን ኢንተርኔት ቤት ስገባ አስገራሚ ነገር ገጠመኝ:: ጋዜጠኛ ደረጀ ሀብተወልድ 125 ዶላር እንደላከልኝና መቀበያ ኮድ ቁጥሩን አስፍሮ የላካትን የኢሜል መልዕክት አገኘሁ:: ፈጣሪዬንም ደረጄንም አመሰገንኩ:: አሁን ቀልቤ መለስ ሲል ከስሜነህ ጋር ወሬዬን ቀጠልኩ::

‹‹..እጅህን ምን ሆነህ ነው?..›› ለካ ቅድም ነግሮኝ ነበር:: ልብ ብዬ አለመስማቴ ገርሞት ‹‹አልሰማኸኝም እንዴ ነገርኩህ እኮ!..ደግሞም እዚህ የምታየው ሁሉ ጉዳት የደረሰበት በእነዚህ ብር አምጡ የሚሉት

ሰዎች ነው፡፡ አታይም እንዴ ይሄ ሁሉ አፎ-ስማይ! ያልተጎዳ ማን አለ? እኔማ እጅና እጄን አስረው ዛፍ ላይ ስላንጠለጠሉኝ ነው፡፡ ያውም ግማሽ ቀን ይሆናል፡፡ ሰውነቴ ዛለ፡፡ በዛ ላይ በዱላ ሲያቀምሰኝ ቅንጥስ አለ፡፡...20 ቀን አሰቃይተው ቢለቁኝም እዚህ ካምፕ እስክደርስ ያየሁት መከራ ተወኝ እስኪ ብቻ ፈጣሪ ለሀገሬ ያብቃኝ እንጂ...››

‹‹..አሁን ህክምና እንዴት ነው?..›› አልኩት፡፡

‹‹ኤም.ኤስ.ኤፍ የሚባለው ድርጅት ህክምና ሰጥቶኛል፡፡ በቃ! ከዚህ የዘለለ ምንም ሊደረግ አልቻለም፡፡ እጄ ከዚህ ውጭ ምንም ሊደረግ እንደማይችል ነግረውኛል፡፡ በቃ! ሰባራ ሆኜ መቅረቴ ነው..›› አለኝ ቅዝዝ ብሎ፡፡

ቀኑ ሊያመሻሽ በሚንደረደርበት ሰዓት (12 ተኩል አካባቢ) ላይ የነበርንበት ሆቴል ውስጥ የተቀጣጠርኩት ካምፕ ውስጥ የሚሰራው ወዳጄ መጣ፡፡ ወደ ባብል መንደብ ያሰብኩት ጉዞ መስጊ እንደሆነ እና ነገ ጠዋት ከአራት ሰዓት በኋላ ግን ከእነሱ ጋር መሄድ እንደምችል ነገረኝ፡፡ ተስማማሁ፡፡

ትዕዝ ላይ ያገኘኋቸው ሰዎችና የሰጡኝ መረጃ ግን ኢትዮጵያዊያን ምን እየጠበቅን ነው? ከዚህ በላይ ጭካኔስ በአለማችን ላይ ይኖር ይሆን? ያሰኛል፡፡ ትዕዝ የሚባለው ቦታ ተቀብሎ ያስተናገደን ልጅ ጋር የመጣ አንድ እንግዳ.. (ውይ እንግዳ አልኩ እንዴ? ታክሲ ስላለውና መንገዱን ያውቃል ስለተባለ ያስጠራነው እኛ መሆናችንን ዘንግቼ) በጨዋታ ጨዋታ በዓይን በብረቱ ስላየው እና ስለሚደረገው ግፍ ያወጋን ነበር፡፡ በስንተኛው ዙር ወግ ላይ እንደሆን እኔንጃ ‹‹..እነዚህ የሚያግቱት እኮ ሰው በቁሙ እየቀበሩ ማሰቃየት ጀምረዋል›› አለ፡፡ ሰውነቴን ውርር አደረገኝ፡፡ እስካሁን ያልሰማሁት በመሆኑ ደነገጥኩኝ፡፡ በእርግጥ በአንድ ወቅት ወደ እዛ ስሄድ የሞተ ኢትዮጵያዊ የሚቀብሩበትን ቦታ አይቼዋለሁ፡፡[26] በጣም በጣም ሰፊ ነው፡፡ ግን እንዲህ በህይወት ያለ ሰው ይቀብራሉ ሲባል አልሰማሁም፡፡ የመጀመሪያዬ ነው ስሰማ፡፡

‹‹ቅብር!..ቅብር?...በምን አወክ አንተ አይተሀል?›› ስል ጠየኩት፡፡ አላንገራገረም፡፡ አብሮት የመጣውን ልጅ ‹‹እሱ ከባህር እንደመጣ ይዘውት

26 ካልድ ለገሰ(መንግስቱ ለገሰ)፣ ጸሀይ በየነ፣ ሄለን ገ/እግዚአብሄር፣ አስመረት ገ/እግዚአብሄር፣ ነብዩ ተሰፋዩ፣ ሰብለ ዮሐንስ እና ፋዓድ ነን ትዕይንቱን ለማየት የታደልነው፡፡ በእርግጥ ከዚህ በፊት አይኑ የጠፋ፣ እጅ እግሩ የተሰበረ... ለበርካታ ሆነው ደፍረዋት ሽንቷን መቆጣጠር ያቃታት ሴት... የጡቷን ጫፍ በላይትር ለኩሰው ያቃጠሏት... ራሱን በመዶሻ በርቅሰውት ራሱን የሳተ፣ ብረት አግለው ብልቷን የተኮሷት... አይቻለሁ አናግሬያለሁ፡፡ አሁን ደግሞ አዲስ የሰማሁት በገመድ አንቀው እያሰቃዩ መግደል...





ከእነሱ ጋር ለመስራት ሞክሮ ነበር፡፡ አሁንም ሄድ-መለስ ይላል›› አለና ልንቁስ ያለ ልጅ አሳየኝ፡፡ ወገኑን ከሚያሰቃዩ ጋር በመስራቱ ከሱ ጋር ማውራት ተጠየፍኩት፡፡ በጠላትኛ አየሁት ግን የሚሰጠኝን መረጃ እፈልገዋለሁ እና ሞባይል ስልኬን የተደወለልኝ አስመስዬ ነካካሁና ሪከርድ የሚለው ላይ አደረኩኝ፡፡ እንዲነግረኝ ጠየኩትም፡፡

‹‹አዎ! ግን ያየሁት ልጁ ራሱን ነው፡፡ የተቀበረውን፡፡››

‹‹ከተቀበረ ከየት አየኸው?››

‹‹እስከ አንገቱ ድረስ ቀብረውት አሰቃይተውት ከዚህ ከወገቡ በታች አልታዘዝልህ ብሎት እየተንፏቀቀ ህክምና እንዲያገኝ ሀረጥ ካምፕ ሲገባ አይቻለሁ›› አለኝ፡፡

‹‹አላናገርከውም?›› ስለው የሰጠኝ መልስ በጣም ሰቅጣጭ ነበር፡፡

‹‹ልጁ በተፈጥሮው መስማት የተሳነው ስለሆነ እንዴት ላውራው? ደግሞም እዚህ ትዕዝ ውስጥ ትላንት የገባ ልጅ አለ፡፡ እዚህ ማር መሸጫ መደብሩ፣ መኪና ከሚያጥቡት ልጆች ጋር አሁን ስመጣ ራሱ አይቼዋለሁ፡፡ ቀብረውት አሰቃይተውት አንድ አይኑን አጥፍተው ነው የለቀቁት፡፡››

አይኑን አጥፍተውት ሲባል የሚሰማውን ስሜት አስቡት...በዚህ ምክንያት ከዚያ በኋላ ቀልቤ ፈጽሞ ከእነሱ ዘንድ አልነበረምና ካልድን ጠቅሼው መጣን ብለን ወጣን፡፡ ልጁን አፈላልጌ ለማግኘት ቢከብድም ከብዙ ድካም በኋላ አገኘነው፡፡ ሊያወራልን ፍቃደኛ አልሆነም፡፡ እንዲያወራልን በተደጋጋሚ ያደረኩት ሙከራ ስላልተሳካ ተቃራኒውን አውርቼ ሀቁን እንዲነግረኝ ማድረግ እንደ አማራጭ አደረኩት፡፡

‹‹እንዴት አይንህን ሊያጠፉህ ቻሉ? ገንዘብ እንድታስልክ ሲሉ በጣም ይንከባከባሉ ሲባል ነው የሰማሁት፡፡››

‹‹ምንድን ነው የምታወራው? የምታወራውን ታውቃለህ? እብድ..እነሱ ናቸው የሚንከባከቡት?... እንኳን ሊንከባከቡህ ገና ጊቢው ውስጥ ስትገባ ነው ዱላው የሚጀምረው፡፡ አስደውለውህ የሚልክልህ ቦታ ካለህ ትደውላለህ፡፡ ግን ደውለህም እኮ ይደበድቡሀል፡፡ ቶሎ እንድታስልክ እየደበደቡ ነው የሚያስደውሉህ፡፡ ቶሎ ነው ማስላክ ያለብህ፡፡ በጊዜው እኔ ደግሞ ማንም የለኝም፡፡ ብዙ ተደበደብኩ፡፡ ከየትም አምጥቼ አልሰጥኋቸውም፡፡ እይ!..ይህን አየኸው...ይንከባከባሉ ያልካቸው ናቸው ያቃጠሉኝ፡፡››

ደረቱ ላይ በሲጋራ ያቃጠሉትን አሳየን፡፡ የበለጠ እንዲያዋራኝ ፈልጌ ‹‹ለመጀመሪያ ጊዜ ካንተ ሰማሁ፣ አየሁ..›› አልኩት፡፡

‹‹ሂድና ሀረጥ እይ… ሦን ታደርቀኛለህ? ይሄን ታዲያ ራሴ ነኝ ያጠፋሁት? ምን ማለት ፈልጋህ ነው?..›› አለና አይኑን አሳየኝ፡፡ ‹‹እንዴ እንዲህ ያደረጉኝ እነሱ ናቸው ብቻ እንዳትለኝ?..›› አልኩት በግርምት እንዳላወቀ ሆኜ፡፡

‹‹እየነገርኩህ? ገንዘብ የሚልክ ዘመድ የለኝም፡፡ በሲጋራ አቃጠሉኝ፡፡ መቀመጫዬ ላይ ላይተር ለኩሰው አቃጠሉኝ፡፡ የሌለኝን ዘመድ ከየት ላምጣ ጉድጓድ ቆፍር ብለው አስቆፈሩኝ፡፡ እስከ አንገቴ ድረስ ቀበሩኝ፡፡ እኔስ ተርፌያለሁ፡፡ ከነህይወታቸው ሙሉ ለሙሉ የቀበሯቸው አንድ ሴት እና ሶስት ወንዶች ልጆችን አይቻለሁ፡፡ እኔን አንገቴ ድረስ ቀብረውኝ እነሱ ጫታቸውን እየቃሙ በእኔ ስቃይ ይዝናናሉ፡፡..››

‹‹ልጆቹን በህይወት እያሉ እንዴት ሊቀብሯቸው ቻሉ?›› ጠየኩት፡፡ ከሌላው የተለየ ምን ሰርተው ይሆን? የሚለው ስንን ይዞኛል፡፡

‹‹..እነሱማ ደውለው ከዘመዶቻቸው ሊያስልኩ ነበር፡፡ ዘመዶቻቸው ለመላክ አልፈለጉም የለንም አሏቸው፡፡ እየደበደቡ አስደወሏቸው፡፡ ምንም ታጣ፡፡ ጉድጓድ አስቆፍረው ሶስቱንም አስገብተው እያስፈራሩ አስደወሏቸው፡፡ ምንም ጠብ የሚል ጠፋ፡፡ ሌሎች ልጆችን ጠርተው አፈሩን መልሱ ብለው ላያቸው ላይ አስመለሱት፡፡ በቃ!! አፈሩን የመለሱት ልጆች እያለቀሱ ነበር፡፡ በዚህን ጊዜ እኔ ‹‹ያረቢ ኑ ባሲ!!!..ያረቢ ኑ ባሲ…›› (ፈጣሪዬ አውጣኝ..ፈጣሪዬ አውጣኝ) እያልኩኝ ነበር በሆዴ፡፡ አፌን አውጥቼማ እንዴት ይገሉኛል፡፡ ለእኔም አልቀረልኝ፡፡ ፈጣሪ ልመናዬን ሰምቶ ቢቀብሩኝም አልጨረሱኝም፡፡ በመጨረሻም ለ22 ቀን አሰቃይተውኝ እንደነገ ሊለቁኝ … እንደዛሬ የሀይላንድ ውሀ ላስቲኩን ክዳኑን ከፈተው እና አፉን አይኔ ላይ አደረገው፡፡ በቀዳዳው እይ አይንህን ግለጽ አለኝ፡፡ ያው ያዘዙህን ማድረግ ግዴታ ነው ገለጥኩ፡፡ በቂጡ በኩል በሀይል ሲመታው ራሴን ስቼ ወደኩ፡፡ ምን ያህል ጊዜ እንደቆየሁ እንጃ ፊቴ ሁሉ ደም ለብሷል፡፡ እንዲሁ አሞኝ ዋልኩ፡፡ አይኔ መውጣቱን ያወኩት ስነቃ ነው፡፡ በማግስቱ ሲለቁኝ መሄድ ሁሉ አልችልም ነበር፡፡ የወጣው አይኔ የሀይላንዱ እቃ ውስጥ እንደተቀመጠ ከድኖት ‹አላስልክም ባልከው ብር ታከምበት..› ብሎ ሰጠኝ፡፡››

ምን እንደተሰማኝ አላውቅም፡፡ እንኳን ያኔ አሁንም ቢሆን መናገር አልችልም፡፡ አጥወልውሎኝ የምወድቅ መሰለኝ እና ካልድ ለገሰን ለመያዝ ዞር ስል በሁለት እጁ ራሱን ይዞ ያለቅሳል፡፡ እኔ ግን ማልቀሱም ሆነ በቅጡ ማሰብ አልሆነልኝም፡፡ እዚህ ጋ በአንድ ወቅት ሶማሊያ እያለሁ የሚሰቃዩትን አይቼ የጻፍኳትን ግጥም ዳግም ብጠቀማት ወደድኩ..ዋ!!





ያሉትን ይበሉ ብልማ
ጥንድ..ጥንዱን አንገርቅኘርቄ
ሀቅ!!! ባልኩ ተንሰቅስቄ
ሀዘኔ በወጣ በታወቀ ለሰው
አምቄ ከማልመሰምሰው
እርዱኝ…እርዱኝ እባካችሁ
ትርፍ እንባ ያላችሁ
አልቅሱልኝ ለእኔ አሮ ሞተ ብላችሁ….

ከማረርም በላይ ሆኖብኛል፡፡ አፌን ሁሉ ደም ደም አለኝ፡፡ ምሳ እንብላ ብለውም እሺ አላለም፡፡ አሁን ምን አሰብክ? ወደ ስነዓ ከሆነ የምትሄደው አብረን እንሄዳለን አልኩት፡፡ ረድዓ የሚባለው ቦታ ሄዶ ባለእርሻዎች ጋ ተቀጥሮ ትንሽ መስራትና ወደ ሳዑዲ አረቢያ መሄድ እንደሚፈልግ ነገረኝ፡፡ እንዴት ረድዓን የምትባለውን ቦታና እዛ ስራ እንዳለ እንዳወቀ ካልድ ጠየቀው፡፡ ከዚህ በፊት እንደመጣና ሳዑዲ አንድ አመት ቆይቶ ተይዞ ድጋሚ እንደተመለሰ ነገረን፡፡ ወደ ቦታው ለመሄጃ ከዛሬው ጋር ሁለት ቀን መኪና እንዳጠበ ነግሮን ከቻልን ሳንቲም እንድንሰጠው ጠየቀን፡፡[27]

## ‹‹ወንድነትክን እንዳውቅልህ ካላደረግክ ቆርጬ እጥልልሃለሁ!››

ነሀሴ 20 ቀን 2005 ጠዋት ላይ ነው፡፡ ያለሁበት ሱቅ በር ላይ ቁመታም ጠይም ሀበሻ መጥቶ ቆመ፡፡ ምንም መናገር የፈለገ አልመሰለኝም፡፡ ዝም፡፡ በዝምታ እቃ ሊገዛ መስሎኝ ምን ፈለክ አልኩት፡፡ ምግብ እንደሚፈልግ በእጅ ምልክት ነገረኝ፡፡ መናገር የማይችል መስሎኝ ግራ ተጋባሁ፡፡ እንዴት እኔ ጋ ልትመጣ ቻልክ? ስለው በዋናው መንገድ ሳልፍ ሱቁ በር ላይ የተቀባውን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ አላማ አየሁ፡፡ ሀበሻ ናቸው ብዬ መጣሁ አለ፡፡ አጠገቤ ካለ የየመናዊያን ምግብ ቤት አምጥቼ የሚበላ ሰጠሁት፡፡ ይስሀቅ መብራቱ ይባላል፣ የመቀሌ ልጅ ነው፡፡ በልቶ ሲጨርስ አዲስ ነህ? በየት መጣህ? ስንት ጊዜ..ሆነህ?…የሚሉ ጥያቄዎችን ደረደርኩለት፡፡ ሲነግረኝ ጅማ ዩንቨርስቲ በቢሮ አስተዳደር (በኦፊስ ማንጅመንት) ባችለር ዲግሪውን አግኝቷል፡፡ አዲስ አበባም ሆነ መቀሌ ለእሱ የስራ በራቸውን ሊከፍቱለት አልቻሉም፡፡ በመጨረሻም የቅርብ

[27] ከዚህን ልጅ ጋር ያደረኩት ቃለ-ምልልስ በዩቱዩብ ላይ ይህን ሊንክ በመከተት ፈልገው ይመልከቱ… https://www.youtube. com/watch?v=vi0LEXscKCY

ዘመዱ የሆነ ሳዑዲ አረቢያ የሚመላለስ ልጅ እዛ ስራ ብትሞክርስ? አብረን እንሂድ ይለዋል፡፡ ስራ ካልተገኘስ ብሎ ስጋቱ ስላደረበት ዘመዱ ቀድሞ ሄዶ ስራ ካገኘ በኋላ እንዲጠራው ይነጋገራሉ፡፡ በተነጋገሩት መሰረት ልጁም ይሄድና ሳዑዲ ውስጥ አንድ ድርጅት ያለው የሚያውቀው መጠጥ ይገዛው የነበረ ደንበኛውን ወንድሜ ተምሮ ተመርቆ ስራ አጣ ይለዋል፡፡

‹‹ይምጣ ኢንሻአላህ ስራ እናስገባዋለን...›› ስላለው ደውሎ ና ስራ ተገኝቶልሀል ይለዋል፡፡ ትንሽ ገንዘብም ልኮለታል፡፡ እሱም ፈላልጎ ሳንቲም ጨምሮ በጅቡቲ በኩል ይመጣል፡፡ ‹‹..ችግር የገጠመኝ ከድሬደዋ ጀምሮ ነው...›› ሲል አጫወተኝ፡፡ ድሬ ደሞ ሀገር አማን ብላ በሰላም ትቦርቃለች ምን አጋጠመህ? አልኩት፡፡ የሆነች ልጅ አይቶ እንደወደዳት...እሷን ለማናገር ሶስት ቀን አድሮ በአይኑ ተከትሎ በአይኑ ሸኝቶ ጉዞውን ሊያስተጓጉል ሁሉ ፈልጎ ነበር፡፡ ግን የስራው ማግኘት ሁኔታን አስቦ ልቡን ድሬ ላይ ጥሎ ወደ የመን ነጎደ፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለኢትዮጵያዊያን ስደተኞች የከፋው የየመን ድንበር ለእሱም ጎምዝዞ ተቀበለው፡፡ እንደ ሌሎቹ ሁሉ ከባህር ሲወርድ በአጋቾቹ ተያዘ፡፡ ስልክ ቁጥር አምጣና ደውለህ የሳዑዲ 1500 ሪያል አስልክ ተባለ፡› ቁጥር የለኝም በማለቱ ያየውን ስቃይ ሲነግረኝ በጣም የከፋ እና አሳዛኝ ነበር፡፡

እንዴት ላሳይህ ሰውነቱ ላይ በሙሉ በሲጋራ ያቃጠሉኝ 13 ቦታ ጠባሳ በጠባሳ ሆኛለሁ፡፡ በዛ መቼ በቃ ብለህ ነው፡፡ አንገቴ ውስጥ ገመድ ከተው አንጠለጠሉኝ፡፡ ሁለቴ አንጠልጥለው ሞትን ቀምሼ መለሱኝ፣ አወረዱኝ፡፡ አልሞት ብዬ አጣጥሬ ነቃሁ፡፡ እጄን በገመድ አድርገው መኪና ላይ አስረው መሬት ለመሬት ጎተቱኝ፡፡ መሀል ላይ ድንጋይ እጄን ሲመታኝ ገመዱ እየጎተተኝ ስለነበር እጄን ሰበሩኝ፡፡ የያዝኩትን ብር መጀመሪያ ሲፈትሹኝ 1250 ወስደውብኛል፡፡ ዱላው ሲበዛብኝ ይልክልኛል ያልኩት ሳውዲ አረቢያ ያለው ልጅ ጋ ደውዬ ነበር፡፡ እንዴ አንስቶ አወራኝ እና በኋላ ስልኩን ከነአካቴው አላነሳም አለኝ፡፡ ደበደቡኝ..ደበደቡኝ፡፡ እይ... (የተሰበረ እጁን ገልጦ አሳየኝ፡፡)

በሲጋራ 13 ቦታ እንዴት እንዳቃጠሉት ጠየኩት፡፡

ለነገሩ በሲጋራ ነው አልኩህ እንጂ ብልቴ ላይ ላስቲክ አቅልጠው ነው ጠብ..ጠብ ያደረጉብኝ፡፡›› ብልቱ ላይ፣ መቀመጫው ላይ፣ ደረቱና ሆዱ ላይ እንዳቃጠሉት ነገረኝ፡፡ አሁን ምን ታስባለህ ወደ ሀገር መመለስ ወይስ ሳዑዲ አረቢያ ትሄዳለህ? ስለው ‹‹..ኧረ.! ሀገሬ መመለስ ነው የምፈልገው..›› አለኝ እየተንገፈገፈ፡፡ ታዲያ ወደ ሀገር መመለስ ከፈለክ ሀረድ IOM ካምፕ ለምን አልገባህም? አልኩት፡፡ እውነትም ሀገር ለመግባት ሰነዓ ከተማ ከመሞከር ይልቅ ካምፑ ይቀላል ብዬ ነው፡፡ እዛም ግን ችግር እንዳለ እና ቶሎ እንደማይመልሷቸው አውቃለሁ፡፡





‹‹መጀመሪያማ እዛ ነው የገባሁት፡፡ ግን ከእኔ በፊት የገቡ በጣም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አሉ... ሶስት አመት የተቀመጡ አሉ፡፡ እዛም እድሜ መፍጀት ነው የሆነብኝ፡፡ እኔ ገና ሰባት ወሬ ነው፡፡ በዛ ላይ በጣም ለተጎዱት ቅድሚያ ይሰጣሉ፡፡ ስለዚህ እዚህ ያለውን አማራጭ መሞከር ፈልጌ መጣሁ›› አለኝ፡፡ ሰባት ወር ያህል ከቆየህማ ካምፕ ውስጥ ብልቱን የቆረጡት ልጅ ነበር ብለውኛል፡፡ ከተቆረጡት አንዱም ራሱን አጠፋ ብለውኛል አይተሀቸዋል? አልኩት፡፡ ‹‹ካምፕ ውስጥ ብቻ አይደለም ያየኋቸው ስንያዝም አብረን ነበርን፡፡ ሲቆረጡም አይቻለሁ፡፡›› የምናገረው ጠፋኝ፡፡ አፌን ደም ደም አለኝ፡፡ በሰፊው ላውራው ፈለኩ፡፡ እንደምንም ብዬ እስኪ ስለሁኔታው ንገረኝ አልኩት የታሪኩን ፍሰት ሳልስት ለመያዝ በንቃት እየጠበኩት፡፡

‹‹ነገሩ ሰቅጣጭ ነው፡፡ በሁለት ጀልባ የተጫንነው 80 አካባቢ እንሆናለን፡፡ ከበዛ 90 ብንሆን ነው፡፡ ገና መሬት ከመርገጣችን ወዲህ ኑ..እያሉ መኪና ላይ ጫኑን፡፡ የሆነ ግቢ ውስጥ አጎሩን፡፡ ፈተሹን፡፡ ብር ብቻ አይደለም የሚፈትሹት፡፡ ስልክ ቁጥርም ይፈልጋሉ፡፡ ሳዑዲ ማን ነው የሚቀበላችሁ? ስልክ ቁጥሩን አምጡ..እያሉ ቁም ስቅል አሳዩን፡፡ እኔ ስልክ ቁጥር ጽፌበት የነበረውን ብጫቂ ወረቀት አኘክ..አኘክ አድርጌ ጆሮዬ ውስጥ ወተፍኩት፡፡ ሲፈትሹኝ ያገኙትን ገንዘብ ወሰዱብኝ፡፡ ድብደባው ተጀመረ ልብሳችሁን እያወለቃችሁ ለየብቻ መሬት ላይ አስቀምጡ ተባልን፡፡ የሚገርመው ነገር ይህን አይነት ነገር የሚሰሩት ኢትዮጵያዊያን ናቸው፡፡ ብጫቂ ወረቀት ይሰጡሀና ስምህን ጽፈህ ያወለቅከው ልብስ ላይ ታደርጋለህ፡፡ አንድ ክፍል ውስጥ ራቁትህን ትገባለህ፡፡ አስብ ያሳፍራል ሴቱም ወንዱም ፓንት እንኳን ሳታደርግ አንድ ክፍል ውስጥ መለመላህን መታጎር፡፡

‹‹..ፈትሸው ሲጨርሱ ውጡ ተባልን፡፡ ከያዛት ብጫቂ ወረቀት ላይ ‹ፋኖስ› ብሎ ተጣራ፡፡ ኢትዮጵያዊ ነው የሚጣራው፡፡ አንዲት ልንቁስ ያለች ከ16 ዓመት የማትበልጥ ልጅ ራቁቷን ብድግ አለች፡፡ ሰውነቷ በፍርሃት ይንቀጠቀጣል፡፡ በሁለት እጆቿ ሀፍረቷን ሸፍና ጭንና ጭንዋን እያፋተገች ወደ እሱ ሄደች፡፡ ‹ነይ ወደዚህ አንቺ ብልጥ ሆነሽ ልታታልይን ነው? ስልክ ቁጥሩን በየቦታው በታትነሽ ደብቀሽ የጻፍሽው?› ብሎ ከየልብሷ ላይ የሰበሰበውን ቁጥር ‹አገጣጥሚ እና ደውይ..› ብሎ ወረቀቱን ሰጣት፡፡ በሁለት እጇ ሸፍና የነበረውን ሀፍረቷን እንዴት ለቃ ትቀበለው? እፍረትም ይዟታል...ብቻ በጥፊ ሲያጎናት ድንጋጤው ነው መሰለኝ ለቀቀችውና በአንድ እጇ ወረቀቱን በአንድ እጇ ሞባይል ስልኩን ተቀበለችው፡፡ ያኔ ነጻ አገኛት በጣቱ ነካካት፡፡ ዋይ ብላ እሱን ለማስተው ወደኋላ ስታፈገፍግ›..ዝም ብለሽ ደውይ ብሎ በጥፊ መታት፡፡ ብልቷ አካባቢ እያቆጠቆጠ ያለውን ፀጉር

በያዘው ሲጋራ አቃጠለው፡፡ በዚህን ሰዓት ‹.እእ!..› ብላ ወደ ላይ ስትዘል የያዘችውን ሞባይል ለቀቀችው፡፡ አረቦቹ ደስ ብሏቸው በትዕይንቱ ይስቃሉ፡፡ ይሄ ሙክታር የሚባል የጅማ ልጅ ግን ልጅቷን በዱላ አላስተረፋትም፡፡ በጠረባ ጣላትና ጣቱን እንትኗ ውስጥ ለመክተት ሲታገል አንዱ አላስችል ብሎት ‹ምነው አንተ! ከሰውም አልተፈጠርክ! ሴት ልጅ፣ ያውም ያገርህን ልጅ እንዴት እንዲህ ታደርጋለህ?..ነውር አይደለም እንዴ!› ይለዋል፡፡

በቀጥታ ቁጭ ብለው ከሚስቁት የትዕይንቱ ታዳሚዎች የመናዊያን ቀጣሪዎች ወገባቸው ላይ ከሚታጠቁት ስለት ነገር (ጃንቢያ ይባላል) ተቀብሎ መጥቶ ‹‹ና ወደዚህ›› ብሎ ጠራው፡፡ ፈራን፤ ሁላችንም ፈራን፡፡ እነዚህ ሰዎች ደም የለመዱ ደም የጠማቸው ናቸው፡፡ ምንም አማራጭ ስለሌለው እሱም ሀፍረቱን በእጆቹ ሸፍኖ ተጠጋው፡፡ ‹‹አዘንክላት? እዚሁ እያየንህ አርጋት (ተገናኛት)›› አለው፡፡ ፈጽሞ አላደርገውም ከፈለክ ግደለኝ፡፡ ወገኔ ናት እኮ አለው፡፡ ናጥ ያደርገው የነበረውን ስሜት ስታይ የመናዊያኖቹ ክላሽ ስለያዙ ባይፈራቸው የያዘውን ስለት ነጥቆ እሩን የሚያበላው ይመስል ነበር፡፡ በእርግጥም ተናነቁ..የመናዊው ተነስቶ ክላሽ ደቀነበት፡፡ በዚህን ጊዜ እጁን ወደላይ ሰቀለ፡፡ ሙክታር ተብዬው የልጁን ብልት በእጁ ይዞ ‹እኔ ላይ ወንድ ልትሆን አይደል ወንድነትህን እንዳውቅልህ ካላደረካት እቆርጥልሀለሁ› አለው፡፡

‹‹ወንድነቱን ግፍ በመስራት አይደለም የማሳይህ፡፡ ይሄን የደቀናችሁብኝን መሳሪያ አውርዱትና ላሳይህ፡፡ ያለበለዚያ ቁረጠኝ እንጂ እሷንስ አላደርግም..› አለው፡፡ ጭካኔውን ተወኝ ሙሽልቅ ሲያደርገው ሁላችንም ደነገጥን፡፡ አንደኛው ግን ከመሀላችን እእእእእእ!!!! ብሎ ዛር እንዳለበት አጓራ፡፡ ድምጹን ከፍ አድርጎም ‹..እናንተ አውሬዎች!› እያለ ተሳደበ፡፡ እሱንም ጠርቶ ‹‹ተገናኛት! ያለበለዚያ እቆርጥሀለሁ!›› ሲለው ፈራ፡፡ ልጅቷ መሬት እንደወደቀች በፍርሃት ትንቀጠቀጣለች፡፡ ብልቱን የተቆረጠው ልጅ ይንደፋደፋል፡፡ ይሄኛውንም ብልቱን ይዞታል፡፡ ቆረጠውም፡፡ በዚህን ጊዜ ካሳሁን የተባለ የሮቤ ልጅ የሚንደፋደፉትን ለመርዳት ሲጠጋቸው በደም ማፍሰስ ደስታ ላይ የነበረው ሙክታርን በጥፊ ብሎት ከእጁ ስለቱን ሊነጥቀው ሲል ያኛው ባለመሳሪያው በሁለት ጥይት ደረቱን ብሎ ደፋው፡፡ ሌላኛው ደንግጦ ይሁን እንጃ ብድግ ሲል እሱንም በጥይት መታው፡፡ ‹..እስኪ ወንድ ናችሁ አስጥሏት!› ብሎ ያችን አንድ ፍሬ ልጅ ራቁቷን እንደተኛች በጣቱ ይጫወትባት ጀመር፡፡ ምን እናድርግ ዝም አልን፡፡....በኋላ ቅበሩ ብለውን ከግቢ ውጭ መሳሪያ ደግነው ቆፍረን ቀበርን፡፡ ልጅቷን ግን ከዛ ግቢ እስክንወጣ እየተፈራረቁ ተጫወቱባት፡፡ ሌሎቹንም ሁሉ ተጫወቱባቸው፡፡››

‹‹..ከዛ መዓት ውስጥ አንተ እንዴት ወጣህ?›› አልኩት፡፡





‹‹ይሄውልህ..ሳውዲ የጠራኝ ዘመዴ ስልኩን ሲዘጋብኝ በድብደባ ልሞት ነበር፡፡ አማራጭ ሳጣ ከ20 ቀን በኋላ ቤተሰብ ጋ ደወልኩ፡፡ ቀጥታ ከኢትዮጵያ አንቀበልም ስላሉ ሳዑዲ ያለ ሰው ተፈለገና የእኔ ቤተሰቦች ገንዘቡን ለእሱ ቤተሰቦች ሰጡ፡፡ እሱ ልዋጬን ከሳዑዲ በሪያል ላከ፡፡ በጨለማ ብልታቸውን ከተቆረጡት ልጆች ጋር አውጥተው ካምፑ አካባቢ ጥለውን ሄዱ፡፡...ካምፕ ከገባን ከ24 ቀን በኋላ ያች ህጻን ልጅ ደብድበዋት ፊቷ ሁሉ አባብጦ መጣች፡፡...››

የሚነግረኝ ነገር ሁሉ ውስጤን የሀዘን ከል ቢያለብሰውም ብቻዬን ምን ማድረግ እችላለሁ? ምንም፡፡ እኔም ምንም ነኝ፡፡ እና ምንም ማድረግ አልቻልኩም፡፡

## ጡት ተልታዩ ደፋሪ

ሶፊያ ትባላለች፡፡ ፊቷ በላልሂል፡፡ ብዙ በጣም ብዙ እንደተደበደበች ያስታውቃል፡፡ በየመናዊው ጋዜጠኛ መሀመድ ደርማ አማካኝነት ነው ያገኘኋት፡፡ መቼም ሴቶችን በባህር መጥተው ሳናግራቸው የመደፈር አደጋ አጋጥሞሻል ወይ የሚለውን ጥያቄ መዝለል ጀምሪያለሁ፡፡ አልተደፈርኩም የሚሉ ገጥመውኝ አያውቁም፡፡ እንዲያው ቢያፍሩ እና ቢያድበሰብሱት እንኳን ያው... ታውቀዋለህ ብለው በውስጠ-ምስጢር ይገልጹታል፡፡ እና መጠየቁ ማሸማቀቅ ብቻ ሆነብኝ፡፡ አሁንም እንደወትሮው ይሆናል ብዬ እንደዋዛ ነው የሰማኋት፡፡ በተደጋጋሚ ከመስማቴ የተነሳ ለቅጥጦኝ ነው የምሰማው፡፡ ስለዚህ ባልሰማ ይሻላል የሚል አመለካከት አለኝ፡፡ ግን የሶፊያ የሚለይበት ብቻ ሳይሆን ወይ ሰው መሆን የሚያሰኝ ነው፡፡ ጋዜጠኛው ወዳጀ ‹‹ኧረ! በደንብ ስማት! ታዝናለህ! እኔ እንኳን በደንብ ሳይገባኝ አልቅሼ ልሞት›› አለኝ፡፡ አሁን ይበልጥ ጆሮዬ ተጠንቀቅ ብሎ አንቴናውን አቁሞ የመስማት ጉጉት ወጠረው፡፡ ‹‹እስኪ ከመነሻ ጀምሮ ስላለው ነገር ንገሪኝ›› አልኳት፡፡ ከቤቷ ስትወጣ ጀምሮ ያለውን ብትነግረኝም ለማሳጠር ስል ከጅቡቲ በኋላ ያለውን ነው ያስፈርኩት፡፡

በጅቡቲ ነው መጣሁት፡፡ ጅቡቲ እያለን ከሆኑ ልጆች ጋር ተቀራረብን እና ጓደኛማቾች ሆንን፡፡ ሳራ የአዲግራት ልጅ ነች፡፡ አይሻ የወሎ ልጅ፡፡ እኔ ደግሞ የመጣሁት ከወሊሶ ነው፡፡ ማዕበል ነው ወቅቱ ተብሎ ጅቡቲ አዩ የሚባለው ቦታ 3 ወር ስንቆይ ነው የተዋወቅነው፡፡ የሶስት ወር ቆይታውን ቆይታ አትበለው ካርቶን አንጥፈን ካርቶን ለብሰን ነበር የምናድረው፡፡ እዛ የነበረው ነገር ራሱን የቻለ ትልቅ ስቃይ ነው፡፡ የፈለገው ሲፈልግ ይጎትትሀል፡፡ የምትበላው የምትጠጣው ያስፈልግሀል፡፡

የከፈልነውን ያህል መስዋዕትነት ከፍለን በመጨረሻ ወደ የመን በጀልባ ተሻገርን፡፡ ገና ከጀልባ ወርደን መሬት ስንረግጥ ጀምሮ ሲያል ሆነብን፡፡ ሁለት ክላሽ የያዙ ሰዎች እና ሦስት ሰዎች ሆነው ተቀበሉን፡፡ በትንሽ ፒካፕ መኪና ከአርባ በላይ ጭነውን አንድ ግቢ ነገር ውስጥ አስገቡን፡፡

ሌሎቹን ቀሪዎቹን ደግሞ ሌሎች ወሰዷቸው፡፡ በዚህን ጊዜ አይሻ የት እንደገባች አላውቅም፡፡ ከእኛ ጋር አልነበረችም፡፡ ግቢው ውስጥ እንደገባን በፊት የነበሩ ልጆች ቆሳስለው ሳይ ደነገጥኩ፡፡ አይኑ የጠፋ ልጅ ነው መጀመሪያ ያየሁት፡፡ ትኩስ ቁስል ስለነበር ገና ስቃይ ላይ ነበር፡፡ አንድ ህጻን የያዘች ሴትም አለች፡፡ አራስ መሰለችኝ፡፡ ሁለት ከፍ ከፍ ያሉ ልጆችም ይዛለች፡፡ ልጆቹ የሚበላለጡት በአንድ አንድ አመት ብቻ ነው፡፡ ሌላኛዋ ደግሞ እጇን ተሰብራ በጨርቅ ጠቅልላዋለች፡፡ ሰዎቹ (አጋቾቹን ማለቴ ነው) ሁሉም አንድ አይነት በጭካኔ የተሞሉ ናቸው፡፡ መሳሪያ ከስለት ጋር የታጠቁ ናቸው፡፡ እንደሚሸጥ ከብት እየተዘዋወሩ አዩን፡፡ እኔ ቀደም ብሎ ሳዑዲ ኖሬ ስለነበር አረቢኛ እችላለሁ፡፡ ግን እንደማይችል ነው የሆንኩት፡፡ በጣም ያስፈራሉ፡፡ በአንድ ኢትዮጵያዊ አስተርጓሚነት ‹‹ሳዑዲ ስትገቡ የሚቀበሏችሁን ሰዎች ስልክ ቁጥር አምጡ፡፡ ደውለን እዛ ድረስ የምናደርስበትን ዋጋ እንደራደራለን...›› አሉ፡፡ ፈራን..ሁላችንም ያለንን ስልክ ቁጥር ሰጠን፡፡ ተቀባይም የማውቀው ሰው ስልክ ቁጥር የለንም ያሉትን ለብቻ ለዩዋቸው፡፡ ዱላው እዛው ተጀመረ፡፡ በሰጠናቸው ስልክ ቁጥር ደወሉ፡፡ እኔ አብሬያት እኖር የነበረ ልጅ ስልክ ነበር የነገርኳቸው፡፡ 1000 የሳዑዲ ሪያል ላኪ አሏት፡፡ የሌሎቹንም እንደዛው ካደረጉ በኋላ ሁላችሁም ልብሳችሁን አውልቁ አሉን፡፡

ከመቶ ሰው በላይ የቆመበት ቦታ ላይ ልብሱን ለማውለቅ ፍቃደኛ የሚሆን ሰው የሚኖር አይመስለኝም፡፡ እኛ ግን በግድ በዱላ እየተመታን አወለቅን፡፡ አቤት ሲያሳፍር..ግን ሆነ፡፡ ያወለቅነው ልብስ ላይ ስማችንን እየጻፍን አስቀመጥን፡፡ ከየመን አልፌ ሳዑዲ እደርስበታለሁ ያልኩት ገንዘብ ወሰዱት፡፡ እንዲያው ወዲያው ለቀውኝ የምሄድ ስለመሰለኝ በምን እሄዳለሁ? የሚል ሃሳብ ያዘኝ፡፡ የቻሉትን ያህል ደበድበውን ሲያበቁ በየጥጋጥጉ ሆነው ጫታቸውን ይቅሙ ጀመር፡፡

ከምርቃና በኋላ ለሴቶቹ መከራው መጣልን፡፡ የሆኑ 3 ሰዎች ከግቢው ውጭ መጡ፡፡ የጠፉበት ዘመዳቸው እንዳለ ሁሉ ሴቶቹ ወደተቀመጥንበት መጥተው በአይን ይመርጣሉ፡፡ ለምን እንደሆነ የገባኝ መጀመሪያ እኔን ለጠቆመው ሰው እኔ ተሰጠሁት፡፡ አረቢኛ ስለምችል ‹‹እሷን ነው የምፈልገው ስንት ታስከፍለኛለህ?›› ብሎት ሲደራደሩ ሁሉ ሰምቻለሁ፡፡ እየጎተተ ወደ አንደኛው ክፍል ወሰደኝ፡፡ እንቢ ባልኩበት ሰአት ሁለቱ በጥፊ አቅምሶኛል፡፡ በእጁ ሳይሆን በድንጋይ የመታኝ እስኪመስለኝ





ድረስ አሞኛል፡፡ ባዶ ትንሽዬ ቤት ውስጥ ካስገባኝ በኋላ ግን እሺም አልኩ እንቢ ምንም ዋጋ የለው፡፡ በታጠቀው ስለት የለበስኩትን ቀዳደደው፡፡ አንድ ነገር ባደርግ እንደሚገድለኝ በምልክት ያሳየኛል፡፡ የፈለገውን አደረገ፡፡ የመጨረሻው ድርጊት ግን በጣም ጎዳኝ፡፡ ጡቴን በእጁ ጭምቅ ጭምቅ አድርጎ የእናቱን ጡት እንደተራበ ህጻን በአፉ ጎረሰው፡፡ አመመኝ፡፡ ስጮህ በጥፊ ለጋኝ እና መልሶ መጥባቱን ተያያዘው፡፡ በመጨረሻም በሃይል ሲነክሰኝ ጩኸቱን ለቀቅኩት፡፡

ራሴን ስቼ በስንተኛው ሰዓት ወይም በስንተኛው ቀን እንደሆነ እንጃ፣ ስነቃ ልብሴ በደም ተለውሷል፤ ሶስት ልጆች የያዘችዋ ልጅ አጠገቤ ተቀምጣለች፡፡ ምን እንደተፈጠረ ለማወቅ ቀና ስል ደረቴን እንደሸክም ከበደኝ፡፡ ቆስያለሁ፡፡ በተተለተለ ጨርቅ በወገቤ ዙሪያ ታስሮልኛል፡፡ ምንም አይነት ህክምና ሳላገኝ ለሳምንት ያህል ተኛሁ፡፡ ሶስት ልጆች የያዘችው[28] ሴት አስታመመችኝ፡፡

የነገረችኝ ታሪክ ግን ህሊና የሚሰቀጥጥ ነበር፡፡ ተስፋ ቆረጥኩ፡፡ እዛው አግተዋት 2 አመት ሆኗታል፡፡ በቀን ከአምስት እስከ አስር ሰው ታስተናግዳለች፡፡ በ11 ወር ልዩነት 2 ወልዳለች፡፡ አንዷን ግን ከሶማሊያ ይዛት እንደመጣች ነገረችኝ፡፡ ሶማሊያም ቢሆን አግብታ ሳይሆን ተመሳሳይ እንደዚሁ የመደፈር አደጋ ደርሶባት ነበር፡፡ እድሏ አሳዘነኝ፡፡ ለነገሩ የእሷን አልኩ እንጂ የእኔስ እድል መቼ ታወቀ?..ደግሞስ ይሄው ታምሜ የተኛሁት የሰው ጅብ ገጥሞኝ አይደል? በኋላ ሲነግሩኝ ጡቴን መንከስ ብቻ ሳይሆን ጩኸቴን ሰምተው ሲሰበሰቡ ሁሉ አልለቅም ብሎ ጎትተው፣ ደብድበው ሲያነሱት አፉ ደም በደም ሆኖ ስጋዬን ተልትሎ ነው የጣለኝ፡፡ ቁስሉ እየጠዘጠዘኝ ነው፡፡

...ያለምንም ህክምና ለስድስት ወር እዛው መከራዬን አየሁ፡፡ በቀን ከ12 ሰው በላይ አስገድዶ ይገናኙኛል፡፡ ምግብ እንድናበስል ይደረጋል፡፡ 4 ጊዜ አርግዤ አስወርጃለሁ፡፡ አሁን ይሄ ጓደኛህ..(ጋዜጠኛውን ነው) በህመም የሚያሰቃየኝ ጡቴንም ሆነ የተገኘውን መድሀኒት እየወሰድኩ ሳስወርድ ማህጸኔ ላይ የተከሰተውን ችግር ህክምና እንዳደርግ እየረዳኝ ነው፡፡ ጡቴ ላይ ግን የተከሰተው በጥርስ የመተልተል ጉዳት ህክምና ሳላገኝ በመቆየቱ ወደ ካንሰር ተለውጧል ብለውኛል፡፡

---

[28] ይህች 3 ልጆች ይዛ የተባለችውን ልጅ አንድ ጨምራ 4 ልጆች ይዛ ስነዓ ኢሚግሬሽን እስር ቤት በር ላይ አግኝቼያት በቪዲዮ የተደገፈ ቃለ-ምልልስ አድርጌላት ዩቲዩብ ድረ-ገጽ ላይ ለጥፌዋለሁ፡፡ ለማየት የፈለጋችሁ https://www. youtube.com/watch?v=vi0LEXscKCY ብላችሁ ከከፈታችሁ በኋላ ግሩም ቪዲዮ 30 ስቃይ በየመን..በሚል ፈልጉት፡፡

ይህ ሁኔታ እስከመቼ ይሆን የሚቀጥለው? ሁሌ እንደ እሳት እራት ወደ መጥፊያችን ስንሮጥ እንዳንከርም መንግስትም ሆነ ሌሎች የሚመለከታችሁ እና ህዝቡን ማስተማር ያለባችሁ አካላት ብርቱ እንቅስቃሴ ልታደርጉ ይገባል ብያለሁ በሰዓቱ። አሁንም እላለሁ። ነገር ግን አንሰማም አለመስማት ለምደብናል። መጥፎ ነው ስንባል ወደዛ መሮጥን፣ አደጋ ስንባል ሞክረን ካላየን ማለት፣ ያለማመን ተጠናውቶን የለ? እንደ እሳት እራት በመጥፊያችን ዙሪያ ያሽከረክረናል... ተሽከርክረን ተመስገንበት እንቀራለን። ተዉ ስንባል አንሰማም። አሁን እንኳን ይሄን ጽሁፍ ካነበበ በኋላ እግሩን ለስደት የሚያነሳ ሰው በርግጠኝነት ሞልተዋል። ምን ተሻለን?





# - 22 -

# ጥቂት ስለ ቤይሩት

**የእህቴ ጥቃት ተሰምቶኝ**
**አነባሁኝ....አነበሁኝ**
**መፍትሄ ስላጣሁኝ**
**ምን ይሆን መጨረሻው?**
**ተበታትነን ስቀረነው**

ቤይሩት ተሰምቶ የማያልቅ ፍዳ የሀበሻ ልጅ የበላባት ቦታ ናት። አሁንም ፍዳውን እየበላባት ነው። የኢትዮጵያ መንግስት በቅርቡ ወደቤይሩት የሚደረገውን ጉዞ ከልክሏል/ሰርዟል/። ህገ-ወጥ አንጋጎች ግን ሌላ መስመር ቀይሰው ያወጣሉ። መንግስት አንድ እርምጃ ሲራመድ ህገ-ወጥ አንጋጎቹም ሌላ መንገድ ይቀይሳሉ። በእርግጥ ከልብ ነበር ወይ የተከለከለው? አሁን ህገ-ወጥ አንጋጎቹ የሚሰሩት ስራን መንግስት አያውቅም ወይ? ያውቃል። ታዲያ ለምን በህገ-ወጥ መንገድ ሲወጣ ዝም አለ? ደላሎቹ ሌላ መንገድ ሌላ ዘዴ ሲቀይሱ ተጓዡም የሚደርስበት ስቃይ በዛው ልክ ይጨምራል። መንግስት ሲከለክል በድብቅ የሚደረግ ነገር የበለጠ ጉዳት እንደሚኖረው ግንዛቤ መውሰድ ተገቢ ነው። ከ2 አመት በፊት ነው አንድ የስልክ ጥሪ ከወደ አውሮፓ ምድር ሲበር መጥቶ ስልኬን ኮረኮራት። አጓራች። የሚያስቅ ኮሚክ ነርቧን ነካክቶ ቡርቅ ብልጭ ፍንድቅ አስደረጋት። መልዕክቷን ለመስማት በጣቴ OK የሚለውን ድንቁል አደረኳትና ‹‹ሀሎ!.. ሀሎ!..›› አልኩ። ደዋይዋን የድምጼ ውፍረት አስደንግጧት ነው መሰል በዝምታ ዝምታዋን አሰማችኝ። ደጋግሜ ሀሎ የሚል ጎርናና ድምጼን ወረወርኩ። ምላሽ አገኘሁ።

‹‹አቶ ግሩም? አታውቀኝም። እገሊት... እባላለሁ። ስልክህን ጓደኛህ ጋዜጠኛ ፋሲል የኔአለም ነው የሰጠኝ እባክህ አንድ ነገር ላስቸግርህ?›› ግራ ገባኝ። አውሮፓ ያለሰው ከእኔ ፈልጎ የሚያስቸግረኝ ነገር ምን ይሆን? በሰከንድ አለም ጥግ ድረስ አሰብኩ። በዛች ስብርባሪ ሴኮንድ ውስጥ ከእኔ የሚፈለግ እርዳታ ምን ይሆን ስል ራሴን ጠየኩ።

‹‹ምን ልርዳሽ?›› ውስጤ ግን ድንቄም እኔን ብሎ ረጂ ሲል አዘመረ።

‹‹እባክህ እናንተ ጋር ኤርፖርት የተያዘች እህት አለችኝ።›› በቅስፈት በህሊናዬ የተሳለችው ኢሚግሬሽን እስር ቤት ሆኜ ስትመጣ ብስቁልቁል ብላ ያየኋት ልጅ ነች። ሻንጣዋን በቅጡ መያዝ አቅቷት ዛል ብላ ነበር። በዛች ጠባብ መስኮት አጨንቁሬ ነው ከእንግሊዝ ወደ ኢትዮጵያ ሄዳ ከርማ ስትመጣ ቪዛው ልክ አይደለም በሚል የመን ላይ ያስወረዷት መሆኑን ያወራችኝ። ለ15 ቀን ኤርፖርት ውስጥ አስረዋት መፈጠርን የሚያስጠላ ስቃይ አይታለች። የተፈጸመባትን በዝርዝር ያወጋችኝ ግን በተላላኪዎቹ ልጆች ወረቀት ልኬላት ነው። በደፈናው ‹‹ኧረ!.. አውሬዎች ናቸው ተጫወቱብኝ..›› ነበር ያለችኝ። ሞባይል ካርድ ገዝተን እንግሊዝ ካሉት ጉዳይዋን ሊያስተካክሉ ከሚችሉ ሰዎች ጋር ተገናኘች።

አሁን ቀልቤን ወደስልክ ደዋዬ ሰብሰብ አድርጌ ተነጋገርን። እህቷን የምታገኝበትን እዛ ጽዳት የሚሰራ ልጅ ስልክ ቁጥር ሰጥታኝ ተለያየን። ለእህትየዋ ደወልኩላት። ባለስልኩ ሰው ከስራ ወጥቶ ቤቱ እንደሆነ ነገረኝ። በማግስቱ ደወልኩ አገኘኋት። ስታወራኝ ሰቅጣጭ ነው። ከአውሮፓ/ኖርዌይ/ ከደወለችልኝ እህቷ ጋር በተነጋገርኩት መሰረት የተከፈለውን ያህል ብር ከፍዬ ላስፈታት ብፈልግም ታሳሪዋ ቤይሩት መሄድ እንጂ የመን እንደማትፈልግ ነገረችኝ። በስልኩ ይመለከታቸዋል የተባሉትን ሰዎች ልጁ አገናኝኝ እያልኩ አናገርኩ። በማግስቱ ኤርፖርት ልሄድ ወሰንኩ። የመን በጦርነት የምትናጥበት ወቅት በመሆኑ ወዲያው ካለሁበት አካባቢ መሄድ ባለመቻሌ ነበር ለማግስቱ እመጣለሁ ያልኳቸው። በማግስቱ ስሄድ ከሶስት ቀን እስር በኋላ ማታ ተሳፈሩ ተባልኩ። ያገኘኋቸው ሁለት ልጆች ግን ማታ ላይ እስራ አምስቱ ሲሳፈሩ ብቻቸውን አግኝተው ዝም እንደማይሏቸው ስጠይቃቸው እያፈሩ በሰም የተለወሰ እሬት አወጉኝ።

ይሄ እንግዲህ የህገ-ወጥ ጉዞ ውጤት ነው። ሁሌ መንግስት ይህን አላደረገም ብለን መውቀስ ብቻውንም ዋጋ የለውም። ሲከለክልና ህገ-ወጥ አጓጓዦች ሌላ መስመር ሲቀይሱ ተባባሪ የምንሆን ከሆነ የእሳት እራትም የምንሆነው እኛ መሆናችንን ማሰብ አለብን። በእርግጥ ችግር ቀን አይሰጥም። ሎሬት ጸጋዬስ ‹‹ርሃብ ስንት ቀን ይሰጣል?..›› አይደለ ያለው?





ቢሆንም በጭፍን ባወጣ ያውጣው የሚለውን መስመር ባንከተል እና ከመሞት መሰንበት የሚለውን ብናስብ መልካም ነበር።

ለማንኛውም አሁንም ወደቤይሩት የሚደረገው ጉዞ እንደቀጠለ ነው። ስለዚህ ጉዞ እዛ ያለች ሰምሃል የምትባል ልጅ ያወራችኝን ላውጋችሁ። 2አመት አለፋት ከሄደች። ከተከለከለ እንዴት ወጣችሁ? ነበር የመጀመሪያ ጥያቄዬ። ልብ በሉ በቻት ነው የምንመላለሰው። ያውም ለአራት ቀናት ተከታታይ ያለቻትን ግማሽ.. ግማሽ ሰዓት ኮምፒዩተር ላይ መቆየት የምትችልበትን ጊዜ ሰውታልኝ ማለት ነው።

‹‹አወጣጣችን ብዙዎቻችን ኬንያ ጉብኝት በሚል ነው። ብዛታችን ከ80 እንደምንበልጥ ነው ግምቴ።..›› ግራ ገባኝ ኬንያ ተብሎ እንዴት የመን መምጣት ይቻላል?

ጠየኳትም።

‹‹..የተሳፈርነው በየመን አውሮፕላን ነው። በረራው ወደኬንያ ነው ይባል እንጂ የመን ነው የመጣነው ይህን የሚያውቁት እነሱ ናቸው።››

የመን ስትደርሱ ችግር አልነበረም? አልኳት። ምንም ችግር እንዳልገጠማቸው እና ሁለት ቀን ብቻ የመን ማደራቸውን፣ ከእነሱ በፊት ከ130 በላይ አየር ማረፊያ ውስጥ እንደነበሩ ስታወራኝ ገረመኝ። በሁለት እና በሶስት በረራ ይህን ያህል ቁጥር ያለው ሰው ከወጣ በወር እና በአመት ምን ያህል ሊወጣ እንደሚችል አሰላሁት። ሂሳብ ላይ ፕሮፌሽናል ደደብ ስለሆንኩ ስሌቱን እናንተ ሞክሩት።

‹‹..እዛው ኤርፖርት ውስጥ በአንድ ክፍል ውስጥ ይበላል፣ ይጠጣል፣ ወንበር ላይ ይተኛል። የገማ ሽንት ቤት አለ እዛ ይገባል። ከ200 በላይ ብንሆንም የምንጠቀመው 5 ሽንት ቤት ነው። ውሀ የለም። ምግቡ የየመናዊያኑ አልተስማማንም። ብዙዎቻችን ታመናል። ከእኛ በፊት እዚያ የደረሱት በተለይ መቋቋም አቅቷቸው ይወድቁ ሁሉ ነበር። ብቻ የመን ምንም ጥሩ ነገር አለ ማለት አይቻልም። ግን ቤይሩት ያለውን ስታይ የመን ይግደለኝ ትላለህ። ቤይሩት ኤርፖርት በስድብና በዱላ ነው የሚቀበሉህ። ህይወት ያስጠላኝ ቤይሩት ኤርፖርት ነው። እዚያ የደረስነው ጠዋት ሁለት ሰዓት ተኩል አካባቢ ነው። ሎተሪ የወጣለት ሰዎቹ መጥተው በጊዜ ይወስዱታል። ያለበለዚያ 6 ሜትር በ4 የሆነ ቤት ውስጥ መታጎር ነው እጣ ፋንታህ። የእኛን እጥፍ የሚሆኑ ባንግላዲሽ፣ ሲሪላንካ፣ ፊሊፒንስ.. ምን አለፋህ አንድ ሀገር ህዝብ ታጉሯል። ውሀ አይታሰብም የኤርፖርቱ ሰራተኛ እንደ እቃ ነው የሚያይህ ሲያሻው ይሰድብሀል። ሲያሻው ይመታሀል። ..ከሚመታኝ ቢሰድበኝ እመርጣለሁ። ቋንቋውን

አላውቀው የፈለገውን ቢል። የእኔ ሴትዮ የመጣችው ማታ ላይ ነበር። ወደ 50 የሚሆኑት ሰዎቻቸው አልመጡላቸውም ነበር። ካልመጡ እንደዛው ታጉረው ያድራሉ። ያ-ደግሞ ራሱን የቻለ በሽታ ነው።

‹‹ከዚህ ከእስር ቤት የከፋ ክፍል ወጥቼ የገባሁበት አፓርትማ ምግብ፣ ውሀ የለም። ሰው እንኳን አያይህም። ወይ ጉድ ይሄን ለማየት ነው ሰው የሚሰደደው? ያውም ስንትና ስንት ከፍሎ›› አልኩ።

አባባሏ አሳዘነኝ። ማን የተመኘውን አገኘ? በተለይ ኢትዮጵያዊያን እያየን ያለነው መከራ... አልኩ እኔም በውስጤ። ቀጠለች ‹‹...ያለሁበት አፓርትማ ላይ ሁለት ሀበሻዎች አሉ። አንዷ ወረቀት የላትም። /መኖሪያ ፍቃድ ለማለት ነው/ አንድ ወንድ ጋ ነው የምትሰራው። አንዷ ደግሞ ቤተሰብ ጋ ነው የምትሰራው። ወረቀት የሌላት ከሚከፈላት የማይከፈላት ወርሃዊ ደሞዝ ይበልጣል። ሰዎቹ እርስ በእርስ ተገናኝተን እና እንድንነጋገር አይፈልጉም። ተደብቀን ነው የምንገናኘው...›› አቋረጥኳት።

‹‹ወረቀት ከሌላችሁ ችግር ነው ማለት ነው?›› አልኳት። በዚህ በኩል የመን ችግር የለም። ሁሉም እንደልቡ ነው።

‹‹በጣም እንጂ...›› ስትል ጀመረች። ‹‹..የሉብናን ፖሊስ ካገኘህ አለቀልህ ማለት ነው። በጣም የሚያስጠላ እስር ቤት አለ። እዛ ከተው የመከራ ቋት እያሽተትክ ትታሻለህ። በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን በእዚህ እስር ቤት ይሰቃያሉ።[29] ይህች ልጅ ወረቀት ባይኖራትም ወደኢትዮጵያ መመለስ አትፈልግም። ምክንያቱም የቤተሰቦቿን ነገርና ችግርን ሸሽት። እነሱ ሲቸገሩ ማየት እጅ አጣጥፎ መቸገርን ትፈራለች። ኢትዮጵያ አንድ ልጅ አላት። አብራቸው ሆና የልጇንም ችግር ላለማየት የማንም ማላገጫ ሆናለች። ባል ነበራት። ስትወልድ ጥሏት ሄዶ ነው ወደዚህ የመጣችው የምታሳድግበት ስታጣ። ቤተሰብ ላይ ሌላ ችግር ደርቤ አልቀመጥም ብላ ነበር አመጣጥዋ። ከመጣች 5 አመት ሆኗታል። እዚህ መጥታ ግን የባሰ ነበር የገጠማት። እንደመጣች የገባችበት ቤት ስራ ብዙ ስለሆነ አልቻለችም። ላመጣቻት ልጅ ስትነግራት ሌላ ሰው ቤት (ባልና ሚስት ቤት) ትቀይራታለች። ሴትዮዋ ብዙ ጊዜ ስራዋ ከሉብናን ውጭ ነው። ይሄንን አጋጣሚ ተጠቅሞ የሴትዮዋ ባል ሁሌ ሚስቱ ሳትኖር የሚሰቀጥጥ ወሲብ ይፈጽምባት ነበር። አሁንም ላመጣቻት ልጅ ስትነግራት የተሰጣት መልስ ጥሩ አልነበረም። እዚያ ሀገር ያሉ አስቀጣሪ ቢሮ የሚሰሩት ኢትዮጵያዊያን ተቆርቋሪነታቸው ለሀገራቸው ዜጎች ሳይሆን

---

[29] ስለዚህ እስር ቤት አሁን ካናዳ የምትኖር ህቢና የምትባል ልጅ በፊት የምታውቀው መሆኑን ነግራኛለች። ካናዳ ያሉ ኢትዮጵያዊያንን አስተባብራ እስረኛ በማስፈታት ተግባር ተሰማርታለች። በዚህ በኩል ሪሃል ዘገየም ክገኗ ሆና እየተባበረቻት፣ እየደከመችም ነው።





ለሀገሩ ህዝብ ነው።[30] በዚህ የተለያዩ መረጃዎች ቢኖሩኝም ከእሷ ዘንድ ሌላ አገኝ ይሆን ብዬ ለምንድን ነው ለሀገራቸው ህዝብ የማይቆረቆሩት? አልኳት።

‹‹አብዛኛዎቹ ለሉብናናዊያኑ አቃጣሪ ናቸው። ነገ ሌላ ሰራተኛ አምጡ እንዲሏቸው፣ ጥሩ ጉርሻ ስለሚሰጧቸው ብዙ.. ብዙ ያስተሳሰራቸው ጥቅማ-ጥቅም አለ። ከነአካቴው ምን እንደሚሉህ ታውቃለህ? አገርሽ እንዲህ---አይደለሽ? /ዳሽ ያደረኩት ጸያፍ ቃል ስለሆነ ነው/ ሀገርሽ የምትበይው አጥተሽ አይደል የመጣሽው፣ ብትመለሽ የምትበይው የሌለሽ ርሃብተኛ መሆንሽን አትርሽ.... የመሳሰለ አስጠሊታ ነገር ይናገሩሀል። ታዲያ አብዛኛዎቹ አልኩህ እንጂ ሁሉንም አይደሉም። የሰውዬውም ድርጊት መሯት ነው ጥላ የወጣችው።

በተከታታይ በፌስቡክ ቻት ሳጥኔ ላትታክት እየጻፈችልኝ ያለችውን እህቴ ሰምሀርን ደግሜ ላመሰግናት ወደድኩ። ቀጠልኩ.. ‹‹..ከላይ እንደገለጽኩልህ ልጅቷ የተሰጣት መልስ ጥሩ ስላልሆነ መፍትሄም ስላጣች ያላት አማራጭ መጥፋት ነበርና ጠፋች። ጠፍታም ለረጅም ጊዜ የተለያየ ቤት ሰርታለች። ካንዱ ስትወጣ ስራ አጥታ ረጅም ጊዜ ስትቀመጥ ብዙ ተቸግራለች። አሁን ያለችበት ቤት ሁለት አመቷ ነው። ሰውዬው ደስ ሲለው ይከፍላታል ሲያጣ ይከለክላታል። እንደዛም ሆና እንደነገረችኝ ልጅዋን በጥሩ ሁኔታ እያስተማረች ነው። ወላጆች ግን ልጇ ምን ሰርታ ነው ብሩን ያመጣችው አይሉም።

የእኔውን ቤት ጉድ ደግሞ ልንገርህ እኔ የነበርኩበት ቤት 3 ሰው ብቻ ነው ያለው። ቀን ቀን አይውሉም። ሴትዮዋ መጥፎ የምትባል አይደለችም። ልጁ ተማሪ ነው፣ እሷ ስራ አላት። ወንድሟ ደግሞ የቤተሰብ ድርጅት ውስጥ ይሰራል። ታዲያ ግን ቤት ውስጥ ስራው ማለቂያ የለውም። የምተኛው ሌሊት 7 ሰዓት ነው። የቀኑን ወደ ሌሊት ገልብጠውታል። ቀን ቀን ቤት ስለማይውሉ ስራ ብዙም አያስቸግረኝም። ከ10 ሰዓት በኋላ ግን መቀመጥ እስኪያቅተኝ በስራ ያጣድፉኛል። በዛ ላይ ሌሊት ከ7 ሰዓት በኋላ ያለውም ቢሆን መተኛት አትበለው። ልጁ ቀበጥ ነገር ነው። የ11 አመት ልጅ ቢሆንም አጠገቡ ያለውን ውሀ ማንሳት አይፈልግም። መጥሪያውን ተጭኖ ይጣራል። እንደሰው መተኛት ያለብኝ አይመስለውም። እሱስ ባልከፋ እንቅልፍ ነው የነሳኝ። ሉሰኛ የሆነው ወንድሟም ሌላ ፈተናዬ ነበር። ፍላጎቱ የተወጠረ ስሜቱን ማርገብ ነው።

---

[30] ይህ ሁኔታ በቤይሩት ብቻ ሳይሆን በየቦታው ያለ ነገር ነው። ምክንያቱ የተለያየ ቢሆንም የዚህ ሁሉ ዋነኛው ችግር ሰዎቹ የወገናዊነት ስሜት የሌላቸው ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ሰውን የሚሸጡ መሆናቸው ነው።

ለእኛ ያለው አመለካከት በንቀት የተሞላ ነው። በቃ! ለሰሜት ማስከኛ የተፈጠርን እቃዎች ነው የምንመስለው።

አንዳንዶቹ በፍርሃትም ይሁን በፍላጎት ፍቃደኛ ስለሚሆኑላቸው መሰለኝ ‹..አንቺ ከሌሎቹ በምን ትበልጫለሽ? በፊት ከነበሩት ውስጥ እከሊትን.. እከሊትን እንዲህ አደርግ ነበር› ይለኛል ስማቸውን እየጠራ። እሺ እንደማልለው ሲያውቅ ሁሌም ይዝትብኛል። ለሴትዮዋ የሆነ ያልሆነውን ይነግራታል። በዚህ ምክንያት ከማንም ጋር እንዳልገናኝ ቤት ትቆልፍብኝ ነበር። በዚህ በጣም ስማረር ቢሮ ሌላ ቦታ እንዲቀይሩኝ ነግሬ ተቀየርኩ። የተቀየርኩበት ቤት የሚገርምህ ጥቁር አትወድም። የወሰደኝ ባልዋ ነበር። ከእኔ በፊት የነበረችው ማዳጋስካራዊ ቀላ ያለች ነበረች። ከእኔ ጋር አንድ ፊሊፒንሳዊ ተቀጥራለች። ሁለት ነን ማለት ነው። እኔ 4 ልጆቿን እይዛለሁ። ፊሊፒንሷ ቤት ታጸዳለች። ምግብ ቤት ውስጥ አይሰራም። እዛ ፎቅ ላይ ያሉት ሁሉ ቤተሰቦች ናቸው። ልጆቹ አያቶቻቸው የሰሩትን ነው የሚበሉት። አባትየው የት እንደሚበላ አናውቅም። እሷ ከልጆቹ ጋር ትበላለች። እኔና ፊሊፒኗ በመሀል ፍዳችንን በላን። አንድ ሴጣናም ልጅ አላቸው እሱን ይጎፍ ስንቀዋለል ነው የምውለው። ከፊሊፒንስዋ እንዲያውም እኔ እበላለሁ። ምክንያቱም ልጆቹ አያት ቤት ያለችው ሀበሻ ነች። እሷ ትሰጠኛለች።

በመጨረሻ የምግቡ እና የልጁ ሁኔታ ሲመረኝ ጠፋሁ። ከመጥፋቴ በፊት እሰራበት የነበረው ቦታ ከፊት ለፊት ያለው አፓርትማ ላይ ያለችው ደግሞ ጠዋት 11 ሰዓት ተነስታ ስራ ትጀምር እና ሌሊቱን ሁሉ አትተኛም። ስራ ባይኖር እንኳን እህቶቿ ጋር ትወስዳታለች። ሌላም እታች ያለች ኢትዮጵያዊት ከማንም ጋር እንድትገናኝ አትፈቅድላትም። መውጫ ሰዓታቸውን ጠብቃ ነው ወደእኛ የምትመጣው። የእሷ አሰሪ ደግሞ ሌላው ቀርቶ ፓንቷን እንኳን ማውለቅ አትፈልግም። ለሁሉ ነገር ጥሪ ነው። ቤቱን ካጸዳች በኋላ ሴትዮዋ ቼክ ታደርጋለች። በዚህን ጊዜ አውቃ ግርግዳው ላይ ወይም ሶፋ ስር ቆሻሻ ታደርግና አልጸዳም ብላ ታስቃያታለች። ከጨረሰች እኛ ያለንበት አፓርትማ ላይ እህቷ ስላለች እሷም ጋ ታሰራታለች። ከጠፋሁ በኋላ ግን ምን ሁኔታ ላይ እንዳለች አላውቅም።

አሁን የምሰራው ከከተማ ወጣ ያለ ቦታ ነው። እዚህም ኢትዮጵያዊያን አሉ። ስራቸው ግን ያስጠላል። ሴትነታቸውን ይሸቅጣሉ። ከተማውን እንደጨረስክ ያለው ቦታ ነው የሚሰሩት። እዚህ ያሉት ሶሪያዊያን ሲነግሩኝ በ50.000 የሉብናን ገንዘብ ነው የሚሰሩት። ይህ ማለት 27 ዶላር ሲሉ ራሳቸውን ይሸጣሉ። አንዳንዷ ግን ቢዝነስ ቢሰሩ አይገርመኝም። ምክንያቱንም ቤት ሰራተኛነት ከጀርባው ያለውን ችግር





ስታይ የግድ የሚገፋቸው ሁኔታ እንዳለ ትረዳለህ። የዛኑ ያህል የሚያናድዱኝ በነጻ ቪዛ መጥተው በሴተኛ አዳሪነት የሚተዳደሩቱ ናቸው። አሁን የምሰራበት ቦታ ሶስት ወንዶች ናቸው የሚሰሩት። እኔ ብቻ ነኝ ሴት። በየአመቱ ለሶስት ወር የምታግዛቸው አንዲት ሴት ይቀጠርላቸዋል። ልክ አሁን እኔ እንደተቀጠርኩት። ታዲያ ከባንግላዲሾች እና ሶሪያዎች ጋር በማይረባ ብር ይተኛሉ። ሁሉ እንደእነሱ ስለሚመስላቸው በእርካሽ ትገኛላችሁ ይሉልሀል።››

ሉብናን (ቤይሩት) ውስጥ አስከፊ ነገር ብዙ ነው። ስለቤይሩት ከማጠቃለሌ በፊት በቅርብ ጊዜ የገጠመኝን ላውጋ። አዜብ የተባለች የፌስ ቡክ አንባቢዬ ስልኬን አንኳኳች። ስከፍተው ጠላታችሁ ክፍት ይበል ልብ የሚያለሰልስ ብርጭቆ ወረቀት የሆነ ድምጽ በጆሮዬ ተንኳሰለ። ‹‹ግሩም ተ/ሀይማኖት?›› ስሜን ከእነአባቴ ስትጠራው.. ት/ቤት ክፍል ውስጥ የሚደረግ ስም ጥሪ መሰሉኝ ‹‹አቤት!›› ብዬ በጩኸት ላደምቀው ስል ‹‹..ነህ?..›› የሚለውን ጨመረችልኝ። አቤት የኔ ቆንጆ ቲቸር ማን ልበል? አልኳት። የተደወለልኝ ቁጥር ከየመን ስለሆነ የሚያውቁኝ ናቸው ብዬ ለመቀለድ የሆነ ደስ በሚል ቅላፄ ‹‹አታውቀኝም እዚህ የመን መጥቼ ነው። ችግር ገጥሞናል።..›› ሳግ ነገር የተናነቃት መሰለኝ። ..‹‹ሸሸሸ...›› የሚል ድምጽ ተሰማኝ። ‹‹የለተሀረኩ.. የለ.. የሚል ድምጽም ሰማሁ። ግራ ተጋባሁ። ‹‹አናግሪው ቶሎ በይ..›› የሚል ደከም ያለ ድምጽ ከጀርባ ይሰማኛል።

‹‹ሄሎ ከኤርፖርት ይዘውን ሚግሬሽን እስር ቤት ሊወስዱን ነው። ምን ትረዳናለህ .እባክህ እርዳን ወደሀገር ሊመልሱን ነው። መመለስ አልፈልግም እባክህ...›› ድምጿ በለቅሶ ታጀበ። አይኔ ባያነባም ውስጤ ግን ድቅቅ ብሏል። መጠየቅ ስለነበረብኝ የት ኤርፖርት ነው የያዟችሁ ወዴት ስትሄዱ.. ‹‹ሰነዓ ኤርፖትርት ላይ ነው የያዙን ወደቤይሩት እየሄድን ነበር...›› ተቋረጠ። ሜግሬሽን እስር ቤት ሄጄ ላገኛቸው ፈለኩ። ያለሁበትን ሉቅ የሚጠብቅልኝ ሰው ስፈልግ ቆየሁና አገኘሁ። በዚህ አገር አጠራር ጀዋዛት የሚባለው እስር ቤት ሄድኩ። አሁን ስላወኩት ከፊት ተጠቀምኩኝ እንጂ በሰዓቱ ስሟን ስላልነገረችኝ ማን ብዬ ላስጠራት። ወደሴቶች ክፍል ተጠጋሁና አሁን ከኤርፖርት በመጡ ልጆች ተደወሉልኝ ነበር። ማን ነው የደወለልኝ ስል ‹‹አዜብ..›› አሉ እና ጠሯት።

ትንሽዬ ልጅ መጣች። እድሜዋ ያለማጋነን 16 ወይም 17 ቢሆን ነው። ግራ መጋባትና ፍርሃት የተራኮቱበት ፊቷን ሳይ አሳዘነችኝ። ተጨባበጥንና ‹‹ስሜ አዜብ.... ነው። ፌስቡክ ላይ ጓደኛህ ነኝ። የምትጽፋቸውን የአረብ ሀገር ስቃዮች ባነብም አማራጭ ስላጣሁ ብቻ

ቤይሩት ለመሄድ መጣሁ:: ኤርፖርት ላይ የእናንተ ቪዛ የተስተካከለ አይደለም ብለው 15 የምንሆን ያዙን አሁን ወደሀገር ሊመልሱን ነው እባክህ አግዘኝ ስንት ከስክሰን...›› እንባ ቀደማት:: ለስደት ህይወት ማጀቢያው እንባ፣ ብስጭት፣ ፀፀት እና ጭንቀት ናቸው:: የጀመረችውን ትጨርስ ብዬ በዝምታ ዝምታ ውስጥ ሰፍሬ አይኔን ከአንዳቸው አንዳቸው ላይ እያንቀዋለልኩ ጠበኳት:: ብዙ አወራን::


ይመለከተዋል ያልኩትን ሰው ፈልጌ ላናግር ሞከርኩ:: እንደ ጅብ ቆዳ ቅኝቱ ‹‹እንብላው.. እንብላው..›› ብቻ ሆነብኝ:: እዚህ ሀገር ግልጽ ሙስና ነው ያለው:: ያበደረህን ገንዘብ የሚጠይቅህ ነው የሚመስለው:: ‹‹ለአንድ ሰው 400 ዶላር ክፈል እና እፈታልሀለሁ..›› ተባልኩ:: ኪሴ ያለችኝ 4000 ሪያል ናት:: በዶላርኛ ስትሰላ 20 ዶላር ማለት ነው:: አስቡት ልዩነቱን:: ተመለስኩኝና ይህንኑ ነገርኳት:: የሚበሉ፣ የሚጠጡት ነገር ገዛዝቼ አቀበልኳቸው እና ብር ከላኩልኝ ደውልላቸው ላለችኝ ሰዎች ደዋወልኩኝ:: አንድ ብር ያስከረው ጉንጩን በጫት የወጠረ ሰው መጣና ‹‹አንተነህ እክሴን ያናገርከው?›› አለኝ:: ቢጨንቀኝ እንጂ የማወጣበት ገንዘብ እንደሌለኝ ነገርኩት ‹‹...ሁሉን ከፍዬላቸዋለሁ ማታ ወደቤይሩት ይሄዳሉ...›› ማንም አይወጣም ሲል ድንፋታ የምትመስል ነገር ወርውሮልኝ ሄደ::

ውስጤ እያዘነ ተሰናብቻቸው ከሚግሬሽን እስር ቤት ወጣሁ:: መቼ ነው ፈጣሪ የሚሰማን? መቼ ነው እንባችን ስፍሩን የሚሞላው? መቼ ነው በቃ! የሚለን? እውን መንግስት ቤይሩት መሄድን አስቦበት ነው የከለከለው? ከሆነ ይህን አይነት ድርጊት ሲፈጸም እንዴት አያውቅም? በኬንያ ቪዛ እንዴትስ የመን ሊመጣ ይችላል? የመሳሰሉትን አሰብኩ:: ከማሰብ ውጭ ግን ምን አመጣለሁ? በቀረችኝ ሳንቲም ታክሲ ተሳፍሬ ጉዞዬን ስቀጥል ስለቤይሩት የሰማሁትን ማሰላሰል ጀመርኩ:: ያሰላሰልኩት ብዙ ነው ብዙ..... በቅርቡ ራሷን አጠፋች የተባለችው አለም ደቻሳን ጨምሮ ስንት ወገኖች ረገፉ? ራሷን አጠፋች የተባለችው ያወኳት ራሷን አጥፍታለች ብዬ ባለማመኔ ነው:: ስንቱ በየአትክልቱ ቦታ ተቀበሩ? ከሞቱ በኋላ ገመድ አንገታቸው ላይ እየተጠለቀላቸው ራሳቸውን አጠፉ የተባሉ የሉም? ከፎቅ የተወረወሩ፣ የፈላ ውሀ ተደፍቶባቸው የተመሳለጡ ብሎም የሞቱ፣ ለብዙ ተደፍረው.. ተገለው ቆሻሻ ቦታ ተጥለው የቀሩ የሉም? ሰበብ አልተሰጣቸውም? ለስንቶች ስንት ሰበብ ተሰጣቸው? በአሁኑ ሰዓት ራሱ ስንቶች ናቸው በአስጠሊታ እስር ቤት ሰቆቃ ውስጥ የሚገኙት?








ልዩ መታሰቢያነቱ
በሳዑዲ አረቢያ እጅግ አሳዛኝ
በሆነ መልኩ በአደባባይ በአሰቃቂ
ሁኔታ ለተገደሉት ወገኖቻችን እና
ራሳቸውን አጠፉ በሚል
ምክንያት እየገደሉ በገመድ
ላንጠለጠሏቸው ብሎም ባለው
ጭንቀት ራሳቸውን ላጠፉ
ወገኖቼ ሁሉ ይሁንልኝ፡፡

# - 23 -

## ሳዑዲ
## ጭካኔ፣ ሰቆቃ፣ ውርደት፣ ሞት...

ደልቶኝ መስሎሽ ከሆነ ስደቱ
ማን በነገረሽ በሰቀቀን ስለማንባቱ
በዝቶብን በየቦታው እንግልት፣ ሞቱ
በትዝታ ታስሬ በናፍቆት ተቃጥዬ
መምጣት አለመቻል ሰፍር በላዩ
በእህህ ቀዘማ..እህህን እንብቼ
የሚሞላ መስሎኝ ከስደት ገብቼ

ከዚህ በፊት ባለው ታሪክ ላይ ወደ ሳዑዲ አረቢያ ለመሄድ እና ባህሩን ተሻግረው ስላለው ሁኔታ ነበር ያስፈርኩት። አሁን ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ የተከሰተውን ነገር እንይ....

አመንክም አላመንክም፣ አመንሽም አላመንሽም ማንም ሰው ቤቱን፣ ሀገሩን፣ ቤተሰቡን፣ እናት አባቱን፣ እህት ወንድሙን...ጥሎ ያለምክንያት አይሰደድም። እውነት እውነት እልሀለሁ በማታውቀው ሀገር ልትኖር የምትመኘው የገዛ ሀገርህ እንጀራ እናት ስትሆንብህ ነው። ያለበለዚያማ የማታውቀውን የሰው ሀገር፣ የማታውቀውን የሰው ባህል ናፍቀህ እግርህን አታነሳም። ያንተ ያልሆነውን የኔ ይሁን ብለህ በሰው ሀገር አትሰቃይም። ተሰድበህ፣ ተንቀህ ሀገርህን ለቀህ በህሳብ ሀገርህን እየቃኘህ መሽቶ በነጋ ቁጥር በስደት አንገት ደፍተህ መኖር አትመኝም ነበረ እውነቱን እንነጋገር ከተባለ።

አትፈልግምም።





ማንነትህን ቀብረህ በሰው ማንነት ተሰንገህ፣ በቤተሰብ ናፍቆት እየዋለልክ ውለህ ታድራለህ? ብትችል አንዷንም ቀን አታድርም። ያኔውኑ ብርርር..ክንፍፍፍፍፍ...ብለህ ሀገርህ ትገባ ነበር። ስደት ከፊትም ከኋላም አስፈሪ ነው። አንዴ ከወጣህ በሀገርህ የመኖር ህልም የለህም። አይኖርህም። አሁን አሁን የአንተ እኩዮች ኢትዮጵያ የእነሱ አትመስላቸውም። ለምን ትምሰላቸው? ሁሉ ጥሿት ሲሰደድ ሲያዩ፣ አሳሳች ደላላውን ሲሰሙ፣ ከስደት ተመላሹ (ዲያስፖራው) የሚያደርገውና የሚናገረው ሲጠልፋቸው ምንም መረጃ ሳይኖራቸው እነሱም ለመሰደድ ይነሳሉ። ሀገሬ ከማለት ሌላ የሚያደርገውም ሆነ የሚደረግለት የሌለበት ዜግነት ይዘው እንዴት የእነሱ ትምሰላቸው? ግን ስህተት ነው። ሁሉም የሚቆጨው ሲያልፍ ነው። በስደት ወጥተው ሲያልፍላቸው ሀገራቸውን ያልማሉ። ካላለፈላቸውማ «ምን ይገፔ ልመለስ?» የሚለው ልጓም ሸብቦ ያስራቸዋል። ስለዚህ ይዘው የሚመለሱት ያስባሉ። ግን ከጥቂቶች በስተቀር ብዙዎች በበቂ ሳያልሙ የእሳት ራት ይሆናሉ። ስደት እንዳሰብክው ሆኖ አታገኘውም። እንዳላሰብከው ሆኖ በዘፈቀደ ይመራሀል። ስደት መሮ ጣፍጦ ያባክንሀል። ስንቶች ተሰደን ባከንን? ስንቶች ተሰደን ተመለስን?

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖች በሱዳን፣ በኬኒያ፣ በሊቢያ፣ በጅቡቲ፣ በቀይባህር፣ በህንድ ውቅያኖስ ወደ የመን፣... የመከራ ፅዋቸውን እየተጎነጩ ተሻግረዋል። ሌሎች ደግሞ በየመንገዱ ሞተው ሬሳቸው የዱር አውሬ መጫወቻ ሆኗል። በመቶ ሺህ ባህር ላይ ቀርተዋል። እነዚህ ዜጎች አብዛኞቹ የቤተሰብ ብሎም የራሳቸውን ህይወት ለመለወጥ እንዲሁም አስተዳደርና ፍትህ በማጣት ከገጠርና ከከተማ የተሰደዱ ወጣቶች ናቸው። በተለይ ከዚህ 10 አመታት ወዲህ ለትንግርት ተሰድደናል፤ እየተሰደድንም ነው። ስደታችን ምክንያቱ፣ ሰበቡ ብዙ ነው። ይብዛም ይነስም እያንዳንዱ ለስደቱ የራሱ ምክንያት አለው። ፈልገንም ሆነ ሳንፈልግ ተሰደናል። በመላው ዓለም ተበትነናል። ደሃ ከሚባለው ሀገር ጀምሮ በስልጣኔ እስከመጠቁት፣ በካፒታላቸው እስካደጉት ሀገራት ኢትዮጵያውያን ያልገባንበት የለም። አንዳንዴ ራሱ የሀገሩ ዜጋ ለመኖር ባልቻለበትና ጥሎት ስደት በወጣበት ሀገር ሁሉ ተሰድደን እየኖርን እንገኛለን። ለምሳሌ በጦርነት ከሀያ አመት በላይ ስትታመስ በኖረችውና አሁንም ገና በቅጡ ባልተንሰራራችው ሶማሊያ ሳይቀር ተሰደናል።

መሰደዳችን አይደለም ችግሩ። በተሰደድንበት ቦታ ሁሉ ጥሩ ፊት የማይገጥመን መሆኑ ነው። በእርግጥ ይህ የስደት አንዱ ገጽታ ቢሆንም ለእኛ ደግሞ ይበልጥ መረር፣ ኮምጠጥ ይላል። በአረብ ሀገራት የተሰደደ ኢትዮጵያዊ አንድም ቀን ክብር አግኝቶ መብቱ ተጠብቆለት አያውቅም። ለሚሰቃየው፣ ለሚበደለው፣ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ለሚፈጽምበት ጠያቂ፣

ተቆርቋሪ የለውም። አንድም ዜጌ ፍትህ አግኝቶ ለበደሉ ተክሶ አያውቅም። ለምሳሌ በድብቅ የተደረገውን የመቶ ሺህዎች ዜጎቻችንን ሰቆቃ ትተን አለም ያየው፣ አለም የተነጋገረበት በሊቢያው መሪ ሞአመር ጋዳፊ ቤት አሲድ የተደፋባት መሰረት ነገር ተድበስብሶ ቀርቷል። መንግስት እከሳለሁ ቢልም የፍርሃት ካባ ደርቦ ይሁን ቶምን ቸገረኝ አዶከብሬውን ደልቶ ዝምታ መርጧል። በሌሎችም አረብ ሀገራት ነዋሪ ዜጎቻችን ላይም ይሄው ነው የተፈጸመው። ይህም ሁሉ ሆኖ እንደሰው አለመቆጠር..የመሳሰሉት ሁሉ ቢፈጸምብንም ስደት ከመውጣት አልተቆጠብንም። መንግስትም በዝምታ የዜጎቹን ጥቃት ያዳምጣል። ለምን ብሎ አንድ ጊዜ እንኳን ወገኔ ተነካብኝ የሚል ድምጽ ሲያሰማ አልተሰማም። ይህ ደግሞ ባለቤት እንደሌለው ክብት የፈለገ የፈለገውን እንዲያርድ፣ የፈለገውን እንዲያደርግ እድል ሰጥቷል።

በዚህ ሁሉ ጊዜ ኧረ! ወገኔን የሚል በመጥፋቱ ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ ጠባሳ የጣለ ነገር ተከሰተ። በነዳጅ ዘይት ምርቷ በዓለም ቀዳሚነቱን ይዛ የምትገኘው ሳዑዲ አረቢያ የቆዳ ስፋቷ 2 ሚሊዮን ስኩዌር ኪ.ሜ ገደማ ሲጠጋ በ2010 በተካሄደ ቆጠራ መሰረት 27 ነጥብ 5 ሚሊየን ያህል ህዝብ አላት። ከእነዚህ መካከል 19 ሚሊየኑ የሳዑዲ አረቢያ ዜጋ ሲሆን ቀሪው 8 ነጥብ 5 ሚሊየን ደግሞ በተለያዩ ጊዜና ሁኔታ ወደ ሀገሪቱ-የገባ የውጪ ሀገር ዜጋ ነው። ከነዚህም መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ህጋዊ የመኖሪያ ፍቃድ እንደሌላቸው ሲገመት ለሰሞኑ አስደንጋጭ ክስተትም ሆኗል።

ይህ ክስተት ከመፈጠሩ በፊት ሳዑዲ አረቢያውያን ለሀበሻ ጥላቻቸው እያደገ ሔዷል። የሳዑዲ አረቢያ አሰሪዎች ኢትዮጵያውያን የቤት ሰራተኞቻቸውን ድሮ ድሮ ያከብሩ ይወዱ፣ ታማኝ ናቸው ይሉ ነበር። ያኔ የታፈርን፣ የተከበርን፣ ጥሩዎች እንዳልተባልን አሁን..አሁን ሀበሾች "ጨካኞች፣ የማይታመኑ" እያሉ ጥላቻቸውን መግለጽ ጀምረዋል። ለዚህ ደግሞ የመገናኛ ብዙሐኖቻቸው ትልቁን አስተዋጽዖ አበርክተዋል።

ከMBC1 ጀምሮ አንድ ዜና ተቀባብለው ሲያራግቡ የእነሱ ዜጋ ብቻ ሰው ሌላውን እቃ አስመስለው ነበር።.... November 14, 2013 የወጣው አረብ ኒውስ recent clashes make Saudis wary of Ethiopian maid's በሚል ርዕስ ስር "የሳዑዲ አሰሪዎች ኢትዮጵያዊያን ሰራተኞችን ለማባረር እየዛቱ ነው" ሲል አስፍሯል። ይህ የአረብ ኒውስ ዘገባ ሀበሻዎቹ ላይ የሚደርሰውን በጣም አሰቃቂ ድርጊት አንድም ቀን ዘግቦ የማያውቅ ሲሆን እነሱ ላይ የተደረገውን አንድ ድርጊት ግን መላልሶ ዘግቦታል።

በዚህ በዚህ ሰበብ ጭምር የተፋፋመው የሪያድ መንፋሃን ግጭት ለብዙዎች ህልፈት ሆኗል። ግጭቱን ተከትሎ ለኢትዮጵያን የተሰጠው ወደ ሀገር የመግባት እድሏ ለመጠቀም ከ20 ሺህ በላይ ኢትዮጵያዊያን የሪያድ





መጠለያዎችን አጨናንቀዋል። ከዛ በኋላም በሺዎች የሚቆጠሩ መጠለያ ለመግባት እየጎረፉ ታይቷል። በመጠለያው የምግብና የመጠጥ ውሃ እጥረቱ ደግሞ ኢትዮጵያውያኑ ችግር ሆኖ አጥር ሰብረው እንዲወጡ አስገድዷል።

ዛሬ ውጣ ሊባሉበት ነው የተሰፋ ምድር፣ ብር የሚታፈስበት ያደረጓት ሳዑዲ አረቢያ ለመግባት ስንት ወገን ባህር ላይ ቀረ? በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ በቀይባህርና ህንድ ውቅያኖስን ተሻግረው፣ ተሰቃይተው የመጡት ያልፍልኛል ብለው ነው። ባህሩን ሲሻገሩ ወደ ባህር ተጥለው የሞቱ፣ የሚሻገሩበት ጀልባ እየሰመጠ ባህር ላይ የቀሩ ኢትዮጵያውያን ስፍር ቁጥር የላቸውም። ባህሩንም ተሻግረው ወደ የመን ሲገቡ የሚፈጸምባቸው ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ለከት የለውም ነበር። እሱንም አልፈው ሳዑዲ አረቢያ ሲገቡ በህገ-ወጥ መንገድ ከሚያጓጉዙት ጀምሮ አሰሪዎቻቸው ግፍ የሚፈፅሙባቸው ቀላል አይደለም። ከፎቅ የሚጣሉ፣ የሚገደሉ (ስንቶችን እየገደሉ አንገታቸው ላይ ገመድ በማድረግ ራሳቸውን አጠፉ ብለውናል?)፣ በእሳት የሚቃጠሉ፣ ያላቅማቸው ሲሰሩ በበሽታ ተጠቅተው የሚሞቱ፣ በእስር ቤት ማቀው በሽታ ሸምተው የሚገቡ፣ አሳዛኝና ዘግናኝ፣ አሳፋሪ ተግባር የሚፈፀምባቸው ብዙ ናቸው።

ስደታችንን ስናየው ሁላችንም የወጣነው የጎደለ ለመሙላት ነው። ግን ልንሞላ አይደለም ጎድለንም ለመመለስ ጭንቅ ሆኗል። ብዙውን ጊዜ እንደወጣን እየቀረን ነው። ለእናት ለአባቶቻችን በሙሉ ጤንነት የተመለስን ስንቶች ነን? የከፋ የአካል ጉዳት እንኳን ባይደርስ በምንጠቀማቸው የኬሚካል አይነቶች ብዛት የአፍንጫ ሳይነስ ያላስከተለበት፣ የልብ ህመምተኛ ሆኖ ሀገሩ ያልገባ ማን አለ? እሱም ሞልቶለት አልያም ሞላም አልሞላም የሀገሬ ጅብ ይብላኝ ብሎ ስደትን ቆርጦ የተሰናበተ ልበ-ቆራጥ ካለ ነው።

ይህ ሁሉ ሆኖ ሞልቶ ላይሞላ መሰቃየታችን እንዳለ ሆኖ ሳዑዲ አረቢያ ውስጥ ህገ-ወጦች ከሀገራችን ውጡ በሚል ሰበብ ኢ-ሰብዓዊ ጭካኔ ዜጎቻችን ላይ ተፈጽሟል። የሌሎች ሀገር ዜጎች እንዲወጡ ቢደረግም እኛው ላይ የተፈጸመው ከሁሉም የተለየ ግፍ ነው። በአደባባይ ወገኖች መጫወቻ ሆነዋል። ማንኛውም ሀገር በህገ-ወጥ መንገድ ወደ ሀገሩ የገቡ ዜጎችን ወደ ሀገራቸው መመለስ ይችላል። ወይም የራሱ ያልሆኑ ዜጎች ወደ ግዛቱ በማናቸውም መንገድ እንዳይገቡ አቅሙ የፈቀደውን ያህል ጥበቃና ቁጥጥር ማድረግ ይችላል። ይህን ጥበቃ አልፈው (ጥሰው) ወደግዛቱ ለመግባት ሲሞክሩ ከያዛቸው አሊያም ገብተው ካገኛቸው በህገ-ወጥነት ወንጀል ክሶ እንደ ሀገሪቱ ህግና ደንብ መሠረት ተገቢ ነው ያለውን

ቅጣት ይቀጣል። ከሀገሩ ማስወጣትና ወደመጡበት መመለስ ይችላል። የተለያዩ ሀገራት በተለያየ ወቅት ይህንን ሲያደርጉ በሚገባ አይተናል። አሁንም እየታየ ነው።

ታዲያ ዋናው እና ሊታይ የሚገባው ሁሉም የየሀገሩን ህግ አፈፃፀም ያማከለ ነው። አንዳንዶቹ ሀገራት ከግዛታቸው የሚያባርሯቸውን ህገ-ወጥ ሆነ ህጋዊ ስደተኞች ሰብዓዊ መብትና ክብራቸውን ለመጠበቅ የቻሉትን ሁሉ ሲያደርጉ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ስደተኞቹን ማናቸውንም አይነት ዘዴ ተጠቅመው ማባረራቸውን እንጂ ለሰብዓዊ መብታቸውና ክብራቸው መጠበቅ ቁብ የለሽ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ አንዷ ሳዑዲ አረቢያ ናት። በህገ-ወጥ መንገድ ወደ ግዛቷ ዘልቀው የገቡ ስደተኞች ህጋዊ እንዲሆኑ የሰባት ወር የጊዜ ገደብ አስቀምጣላቸው ነበር። በዚህ ጊዜ ውስጥ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ በህገ-ወጥ መንገድ ወደ ሀገሪቷ የገቡ የየመን፣ የባንግላዲሽ፣ የስሪላንካ፣ የፓኪስታን፣ የህንድ፣ የፊሊፒንስ፣ ወዘተ... ስደተኞች ህጋዊ መሆን ችለዋል። የዚያኑ ያህል ደግሞ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ህገ-ወጥ ስደተኞች ህጋዊ መሆን ሳይቻላቸው ቀርቷል። የሳዑዲ አረቢያ መንግስት ያወጣው የሰባት ወር የጊዜ ገደብ መጠናቀቁን ተከትሎ በወሰደው የኃይል እርምጃ በተለይ በህገ-ወጥ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ የተፈጠረው ሁኔታ ያረጋገጠልን እውነታ ይህንኑ ቁብ የለሽነታቸውን ነው።

በሳዑዲ አረቢያ ከሚገኙትና በወጣው የጊዜ ገደብ ውስጥ ህጋዊ መሆን ያልቻሉ ህገ-ወጥ ስደተኞች ውስጥ ከሁሉም በበለጠ ቁጥርና ከሁሉም እጅግ በከፋ ሁኔታ የሳዑዲ አረቢያ ፖሊስና የሳዑዲ ስርዓት አልበኛ የመንደር ዱርዬዎች (ሸባቦች) አሰቃቂ የግድያ፣ የድብደባ፣ አስገድዶ የመድፈር፣ የዘረፋና፣ የእስር ሰለባዎች የሆኑት በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ናቸው።

እንደ እውነቱ ከሆነ የሳዑዲ አረቢያ መንግስት እንኳን ህገ-ወጥ ናቸው ላላቸው የሌላ ሀገር ዜጐች ይቅርና ለራሱ ሀገር ዜጐች የሰብዓዊ መብት መከበር ምንም ደንታ የሌለው መንግስት መሆኑ አለም ያወቀውና ፀሀይ የሞቀው ጉዳይ ነው። ይሁን እንጂ ያሳንዳች ጥበቃና ከለላ በእጁ የሚገኙትን ስደተኞች በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ ያን የመሰለ እጅግ ወራዳና ሰቅጣጭ ግፍ በአደባባይ ይፈጽማል ተብሎ ጨርሶ አልተገመተም ነበር። በርካታ ሳዑዲ ውስጥ ነዋሪ የነበሩ እና ወደ የመን ሸሽተው የገቡትን ሳናግር ‹‹ፈጽሞ ያልጠበቅነው ነው። ከዚህ በፊት ህገ-ወጦቹን እናስወጣለን ቢባልም እንደዚህ የጨከነ ርምጃ ሲወሰድ ስላልታየ እንዴት ይህን ያደርጋሉ ብለን እንጠብቅ? ግፉ ቢል ከዚህ በፊት





እንደሚያደርጉት ለቅመው ያስወጣሉ እንጂ እንዲህ አይነት ሰብዓዊነት የጎደለው ነገር ያደርጋሉ ብለን አልጠበቅንም...›› ብለውኛል።

በእርግጥስ ማን አሰበ? የሳዑዲ ጎረቤት በሆነችው የመን በኩል ብዙ ስደተኞች ወደ ሳዑዲ አረቢያ ገብተዋል። በተለይም ጅዛን የሚባለው የሳዑዲ ግዛት ለየመን ቅርብ ቦታ ነች። ቅርብ መሆን ብቻም አይደል ቀደም ሲል የየመን ድንበር የነበረ ሲሆን ወዲህና ወዲያ ያሉት አንድ አይነት ጎሳዎች ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦችም ሆነው ድንበሩን ይጋሩታል። በሁለቱም አገራት ያሉ የህግ አስከባሪ አካላትም የሚዛመዱበት አጋጣሚ ብዙ ነው። በተቀነባበረ የኮንትሮባንድ ስራ (የህገ-ወጥ የሰው ዝውውር) ፖሊሶችና ድንበር ጠባቂ ሀይሎች ሰዎችን በህገ-ወጥ መንገድ በማስገባት ይተባበራሉ። የሳዑዲ መንግስት ድንበሩ ላይ ያሉ የህግ አስከባሪዎች ላይ በቂ ቁጥጥር ባለማድረጉ ተጠያቂ ነው።

ስደተኞች ወደ ሳዑዲ ሲገቡ የሀገሪቱን ግዛቶች አቋርጠው ከቦታ ቦታ እንዲዘዋወሩ የኮንትሮባንድን ስራ (ህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር) የሚሰሩት የሳዑዲ ዜጎች ናቸው። ለምሳሌ አንድ ስደተኛ ከየመን ድንበር ወደ ሪያድ ወይም ወደ ጂዳ መግባት ሲፈለግ በጭነት መኪና ከእቃ ጋር ተደብቆ እንዲገባ ያደርጋሉ። አልያም ወንዱ እንደ ሴት ቀሚስ-ሻሽ-የፊት መሸፈኛ እንዲለብስ ያደርጉ እንደሚስታቸው ወይም እንደ ልጃቸው ጭነው በኮንትሮባንድ ከቦታ ቦታ ያዘዋውሩታል። በዚህ ተግባር ፖሊስ (ሹርጣ) እና ድንበር ጠባቂው ተባባሪ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ። አስታውሳለሁ በ2012 በቁጥጥር ስር የዋሉበት ጊዜም ነበር። ለእዚህ ህገ-ወጥ ተግባር ከሳዑዲ ዜጎች እና መንግስት ሌላ ማንም ተጠያቂ ሊሆን አይችልም።

ለማንኛውም ይህን ሁሉ በሚያካክስ መልኩ የሳዑዲ መንግስት የምህረት ጊዜ ብሎ ህጋዊ ላልሆኑ ህጋዊ እንዲሆኑ የሰባት ወር ጊዜ ሰጥቶ ነበር። ስደተኛው ምን ያህል ህጋዊ ለመሆን ጥሯል? ኤምባሲው ምን ያህል የሄዱለትን ሰዎች አስተናግዷል? ሁለቱም ጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚከት እና ሁለቱም የሚወቀሱበት ነው። የምህረት አዋጅ ጊዜ ገደቡ አልቆ በሪያድ መንፉሃ አለምን ያሳዘነ ሰቆቃ ተፈጸመ። በድርጊቱ...ስጋት ነግሶ፣ በጭንቀት አምጠን፣ ጨንቆን፣ ጠቦን ከርመናል። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ተጨንቆ፣ ተጠቦ፣ ሁኔታውን ተከታትሎታል። ያላለቀሰ፣ ያላዘነ፣ ያልተጨነቀ የለም። በዚህ ክፉ ቀን ወገን ወገኑን ለመርዳት ደፋ ቀና በማለቱ ረገድ የሀገሬን ልጆች ኮርቼባቸዋለሁ። ከጫፍ እስከ ጫፍ በቁጭት ስሜት ሲንቀሳቀስ ህብረቱ የፖለቲካ ልዩነቱን አስወግዶለታል። በብሄር፣ በጎሳ፣ በእምነት

ሳይከፋፈል ድምጹን ያሰማበት ዉቅት ቢኖር ሳዑዲ አረቢያ የነበሩ ወገኖቻችን ላይ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ሲፈጸም ነው።

ሌላው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ብሄራዊ ቡድን ለአፍሪካ ዋንጫ እና ለአለም ዋንጫ ማጣሪያ ሲጫወት በተለይ የደቡብ አፍሪካን ቡድን ካሸነፈ በኋላ ህብረቱን (አንድነቱን) አሳይቷል። ኢትዮጵያዊያንን ከጫፍ ጫፍ ያስነሳ ቁጣ ቢሆንም.. ዘግይተናል እላለሁ። ምክንቱም የመን ውስጥ የነበረውን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት እያነሳን ስንጮህ ዝምታ ነበር የተመረጠው። ኧረ!.. የመንግስት አካሎች የታላችሁ? ኧረ! ኢትዮጵያዊያን የት ናችሁ? ኧረ! የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችስ ዝምታችሁ ምንን ያማከለ ነው? ኢትዮጵያን እንወዳለን የምትሉ፣ ለወገን ተቆርቋሪዎች ሁሉ ዝምታችሁ ምንድን ነው? ወገን አለቀ! ኢትዮጵያ መሬቱን፣ አፈር ድንጋዩን ብቻ ነው የምትወዱት ወይ? ብዬ ደጋግሜ ጩኸቴን አሰምቻለሁ። ያም አልፎ አል-ጀዚራ እና ቢቢሲ ያን የመሰለ ሰቅጣጭ ዘገባ ሲያቀርቡ አንድ ሴት ታፍና በቀን ከ20 በላይ ሰው እንድታስተናግድ ስትደረግ... የጅምላ መቃብሮች ሲታዩ፣ ሲቀበር ያየ የአይን ምስክር ሲመሰክር በዝምታ ውስጥ ተሸሽገን ዝም ብለን ነበር። ይሁን፤ አሁንም ቀሪውን ለማትረፍ የተደረገው ርብርብ የሚያስመሰግን ነው።

የሳውዲ አረቢያ ወሮበሎችና ህገወጦች ኢትዮጵያውያን ዜጎችን በየመንገዶች ሲያሳድዱ፣ ሲያጠቁና ሲገድሉ የሚያሳየው የቪዲዮ ምስል ለኩነቶቹ እውነታዊነት ምንም ዓይነት ማብራሪያ አላስፈለገውም። የሳዑዲ አረቢያ ወሮበሎችና የመንደር ዱርዬዎች በኢትዮጵያውያን ላይ ይፈጽሙት የነበረውን በቪዲዮ ማስረጃነት ተደግፎ ቀረበ። የሰብዓዊ መብት ረገጣ ወንጀል በአደባባይ መፈፀሙ በጣም የሚዘገንንና በሰለጠነው አለም የሰው ልጅ ህሊና ሊታሰብ የማይችል ነገር ነው። እውን ሰው ናቸው ወይ እውን በሰለጠነው አለም ውስጥ እየኖሩ ነው ወይ ያሰኛል። በዚህ ፈታኝ ወቅት መፈተን ግድ ያለን በስደት የምንዕቃይ ስደት ላይ ያለን ብቻ አይደለንም። ሀገር ውስጥ ያለውም ወንድም፣ እህቱን፣ ወገኑን አስቦ አንብቷል። ትላንት እንደቀልድ ዝም የተባለው ስደታችን ነው ለዛሬ ዋይታችን ያበቃን። የዜጎች እንግልት ከሪያድ አልፎ ወደጅዳና አካባቢው ሲሸጋገር በርካታ ወገኖች በግልና በቡድን በመሰባሰብ በጎ አድራጎት (ወገንን ለመርዳት) መንቀሳቀስ ጀመሩ።

ይህ የሳዑዲ አረቢያውያን እንስሳዊ ድርጊት በሀገር ውስጥና በውጭ የምንኖር ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ የውርደትና የመጠቃት ስሜት ነው የፈጠረብን። ወገኖቻችን በአደባባይ ሲደበደቡ፣ ባንዲራችንን እንዳሰረ አንዱን ብዛት ያላቸው ጋጠ-ወጦች ሲደበድቡትና በስለት ሲጫወቱበት የሚያሳይ ይህ ቪዲዮ ቀርጸው ለቀውልናል። ይህ ቁጭት ያልፈጠረ ምን





ብንደረግ ቁጭት ይፍጠር? በዚህም ምክንያት የተሰማቸውን ከፍተኛ ቁጣ ከዳር ዳር በአንድ ድምፅ አሰምተናል። የሳዑዲ አረቢያን መንግስት በኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ በፈፀመው እጅግ ነውረኛ ድርጊት በማውገዝ በርካታ የተቃውሞ ሰልፎች ተካሄዱ።

ከየቤቱ እየታደኑ ከመጨፍጨፍ እና በየአደባባዩ ደማቸውን ከማፍሰስ በጅዳ ሽረፍያ የሚባለው ቦታ "ወደሃገር እንግባ! ሀገራችን አስገቡን.. እኛም ሀገር አለን" ብለው ድልድይ ስር በተቀመጡ ዜጎች መካከል የተለያዩ ችግሮች ታዩ። አንዲት በቅርቡ የተወለደች ህጻን እናቷ ሜዳ ላይ ጥላት ሄዳ ተገኘች። ብዙዎችን ጉድ አስባለ። ከድልድዩ የቅርብ ርቀት አንድ ወንድም በድንገት በመኪና አደጋ ሞተ። ሽረፍያ ታመሰች። ያንኑ ቀን የማታው ንፋስ (ብርድ) እና የቀኑ ጸሀይ ያደከማቸው ወገኖቻችን አስቆጣ። ጸጥታ አስከባሪዎች አካባቢውን ከበቡት። ይህን በተመለከተ ለቦታው ቅርበት የነበረው ጋዜጠኛ ነብዩ ሲራክ ስለሁኔታው ሲዘግብ ‹‹..ፍጥጫ ነገሰ! በሁኔታው ግራ የተጋቡት ፖሊሶች ጥይት ወደ ሰማይ በመተኮስ ሁከቱን ለማረጋጋት ሞከሩ። ሁሉም ሆኖ አመሻሹ ላይ ከጅዳ ቆንስል የተላኩ የድርጅት አባላት ሁከቱን ለማረጋጋት ሞከሩ።

በተፈጠረው ግርግር የተደናገጡት በድልድዩ ስር ሁለት ሳምንታትን በመከራ የገፉ ወገኖች "ለደህንነታችን ስጋን.." ሲሉ በዚያው ምሽት ወደጅዳ ቆንስል ተመው በመሄድ ቆንስሉ ጽ/ቤት አካባቢ ባለው ሜዳ በአሳዛኝ ሁኔታ የወዳደቀ እንጨትና ፕላስቲክ እየለቃቀሙ ጎጆ ሰሩ። በክፉ ቀን ያልታሰበውና ያልተገመተው ሁሉ ይሆናልና ያላሰብነው ሁሉ ሆነ። ውሎ ሲያድር የሰው ቁጥር እየበዛ የጅዳ ቆንስል በከፋቸው ዜጎች ተጥለቀለቀ... ይህን ጊዜ ነበር ሰው ለሰው ልብሱ መሆኑን የታዘብኩት።

የከፋቸውን ለማጽናናት፣ የጠማቸውን.. የደረቀ ጉሮሯቸውን ለማርጠብ፣ የራባቸውን... በርሃብ የታጠፈ አንጀታቸውን ገርገብ ለማድረግ ምግብ በማቅረብ በመታደግ ተጀመረ። በተለይም ህጻናትን ለመታደግ የተደረገው ርብርብ ፍጹም ልዩነታችን ያስረሳ ልዩ የታሪክ አጋጣሚ ነበር።... ፍጹም ከህሊናዬ የማይጠፋ ህብረት!...

በዚህ መንገድ በቆንስላው ለቀናት የቆዩት ወገኖች ወደመጠለያ ተላኩ ብለን ደስታችን ወሰን ባጣበት ወቅት ከመጠለያው ሳይገቡ ለ3 እና 4 ቀናት እንግልት እንደደረሰባቸው ሰምተን ተከፋን። አዘንንም። እኔም እንደ ለመድኩት በሰላም የሸኘናቸውን ወገኖች ሮሮ መስማት ጀመርኩ። በቀጣይ ቀናት በግልና ከኮሚቴው ጋር በመቀናጀት የውሃ፣ የምግብና የመጸዳጃ ጥያቄውን ለሚመለከታቸው ለማቅረብ ያደረግነው ሙከራ ሳይሳካ ቀረ።

የውሃ አቅርቦቱን ለማከናወን በተደረገው ሙከራ በአርባ አውቶቡስ የሞላውን ወደሶስት ሺህ የሚሆን ወገን ማስተናገድ ተገደድን:: ማታውኑ የእርዳታ አስተባባሪዎች ባደረጉት ጥረት የስሜንና ደቡብ "ዋይት" ማህበር አባላት ለአርብ ጠዋት የምግብ እና ውሃ እንዲያቀርቡ ተጠይቆ በማህበሩ ይሁንታን አግኝቶ አርብ ጠዋት አቅርቦቱን ለመከወን ቀጠሮ ተያዘ...[31] በየመን ያለውን ደግሞ ስናይ...በወር አንድ ጊዜ ኢሚግሬሽን ያሉትን እስረኞች የመጠየቅ ፕሮግራም አለን:: ምግብ፣ የገላና የልብስ ሳሙና፣ ቫዝሊን፣ ንጽህናቸውን የሚጠብቁበት ምላጭ፣ ለሴቶቹ ደግሞ ወርሃዊ የተፈጥሮ ግዴታቸውን የሚወጡበት ሞዴስ፣ ከሰው የምናሰባስበውን ልባሽ ልብስ እናድላለን:: በዚህ ፕሮግራም ላይ እንዲካፈሉ ብዙ ሰዎችን የጋበዝኩ ቢሆንም አቅም ከማጣት አንጻር ሊሳተፉ አልቻሉም:: የየመን ኑሮ ጠብ ሲል ስደኛን አይነት ነውና:: ልባሽ ልብስ ከሚሰሩበትም ሆነ ከተገኘው ቦታ ሁሉ የሚሰበስቡልኝ ፀሀይ በየነ፣ ሄለን ገ/እግዚአብሄር፣ አስመረት ገ/እግዚአብሄር፣ አለም መንግስቱ...ሁሌም የማልረሳው ውለታቸው አለብኝ:: እነዚህ ልጆች ወጪ መጋራቱም ላይ 30 ከመቶ ያህሉን ያግዙኛል:: የሚገርመው ደግሞ የጸሀይ በየነ አስሪ (የመናዊት ናት) ሀናን ሁሌን..ለሴቶቹ ሞዴስ እና የገላ ሳሙና በመላክ በተደጋጋሚ አግዛኛለች::

አሁንም ልክ እንደ ሁሌው አድርገን ለጥየቃ ስንሄድ የሰነዓው ኢሚግሬሽን እስር ቤት ከአቅሙ በላይ ሞልቶ አገኘነው:: እንደወትሮው መስሎን የያዝነው ነገር የሚያንስ ነውና ተደናገጥን:: የወሰድነውን እንዲቃመስ አድርገን ውስጣችን በሀዘን ተቆራምዶ ‹‹ከየት መጣችሁ? መቼ ገባችሁ?..›› ወደመሳሰለ ጨዋታ ገባን::

ሀሰን ወሎ የሚሉት (ትክክለኛው ስሙ ሀሰን አህመድ የተባለ ልጅ) አብዛኛዎቹ ከሳዑዲ አረቢያ መምጣታቸውን ነገረኝ:: ሌላ ጊዜ ከባህር ወርደው ከሚመጡት ጉስቁልቁል ከሚሉት የባሰ ክስት፣ ጥቁርቁር ያሉ፣ የለበሱት የተቀዳደደ እና የነተበ ነው:: አንዳንዶች ከነአካቴው የሚለብሱት አጥተው ሸርጥ ያገለደሙ ሁሉ አሉ:: ስለሁኔታው እንዲነግረኝ ‹‹እንዴት ወደዚህ መጣችሁ?›› ስል ጠየኩት::

‹‹ለየመን ቅርብ የሆኑ ቦታዎች ማለት ከሚስምሽት፣ ጂዛን..አካባቢ ነበርን አብዛኛዎቻችን:: ከዛ ተነስተን ጂዳና ሪያድ ሄደን እንደሌሎቹ ሀገራችን አስገቡን ማለት አንችልም:: ያን ያህል መንገድ ስንሄድ በየመንገዱ

[31] ይህን ዘገባ ቆረጥ አድርጌ ያስገባሁት የወገን ትብብሩን ለማሳየት ያህል ነው:: ‹‹ዋይት›› የሚለው ውሃ አመላላሽ መኪናዎችን ነው::





እንደሚገሉን ነው ያሰብነው:: ህዝቡ ትኩረት የሰጠው ጂዳ እና ሪያድ ለተደረገው ጭፍጨፋ ነው እንጂ እኛ የነበርንበት ቦታ የተደረገውን ያወቀም የለ:: በየጫካው አስረው ሲገርፉ እና ሲያሰቃዩ የሚታየውን የበፊት ነው ብለው ከስሩ የጻፉ ፌስ ቡክ ላይ አይቻለሁ:: ግን ከሪያድ እየጠፉ በየመንገዱ እየያዙ እንዴት እንዳደረጉ ተወኝ:: ስንቶች ሞተዋል..›› ንግግሩን አቋርጦ ሁኔታውን በሀሳቡ እያየ መሰለኝ አይኑን ቡዝዝ አድርጎ በሀሳብ ነጐደ::

‹‹ስትመጡ መንገድ ላይ እንዴት ነበር?›› የሚል ጥያቄ አቀበልኩት::

‹‹ምን እሱንማ ተወው፣ ጉድ ነው:: በየመንገዱ የሚገጥምህ ችግር ራሱን የቻለ ፈተና ነው::..በየቦታው ይፈትሹሀል፣ ይመቱሀል...ብቻ ተወኝ እስኪ. ዝም ብዬ ልርሳው በቃ እርስት ላርገው...›› ንግግሩም ትቶ ራመድ ብሎ ቆመ:: እኔም ብዙ ላስጨንቀው አልፈለኩም:: ዞር ዞር ስል አንድ በፊት ሰነዓ ይኖር የነበረ ልጅ አገኘሁ:: ‹‹እንዴ! አንተ ደግሞ ምን እዚህ አመጣህ?›› አልኩት::

‹‹አመት አለፈኝ ሲያቀብጠኝ ሳዑዲ ሄጄ ነበር:: አሳሬን አይቼ መጣሁ:: እጄን አታየውም?..›› አለኝና ገለጥ አድርጎ አሳየኝ:: በዱላ ተመቶ የበለዘበትን ቦታ ነው ያየሁት:: ‹‹..ስሄድ ሀረድ ላይ ያን ሁሉ ስቃይ ማየቴ ነው ያናደደኝ:: ስመለስ አሁን ከሚስምሽት ላይ ይዘው ቀጠቀጡን:: እኔ ዱላውን መቋቋም አቅቶኝ ራሴን ሳትኩ:: በዚህን ጊዜ ወንዶቹን ሁሉ ነበር የደበደቡን:: አብረውን የነበሩትን ሴቶቹን አምስቱንም ደፍረዋቸዋል...››

※※ ※※ ※※ ※※ ※※ ※※

ነኢማ የምትባል ሰነዓ ነዋሪ የሆነች ሴት ከ4 ልጆቿ ጋር እዚያው አገኘኋት:: ገና ስታየኝ እንባዋ የመጣ መሰለኝ:: ‹‹ከሀገሬ ከወጣሁ 17 አመት ሆነኝ፡ ባለቤቴ ጥሎኝ ሄደ በቃ! እኔም ወደ ሀገር ለመግባት ቆረጥኩ:: በዚህን ሁሉ ጊዜ ጠብ ያለልኝ ነገር ቢኖር፣ እነዚህ ልጆች ብቻ ናቸው::›› አሳዘነችኝ:: ጥቂት ሳንቲሞች ለልጆቿ አንዳንድ ነገር እንድታደርግበት ሠጠኋት:: አጠገቧ ያለችውም ሴት እጇን ዘረጋችልኝ:: ሁለት ጉስቁልቁል ያሉ እና ንጽህናቸውን ያልጠበቁ ልጆች ይዛለች:: እንዱ ሰባት አንደኛው አምስት አመት አካባቢ ይሆናሉ ብዬ ገመትኩ:: ‹‹አንቺም ከዚህ ነው የምትገቢው ወይስ ከሳዑዲ አረቢያ?››

‹‹ኧረ! ከሳዑዲ ነበር:: መንገዱን ሁሉ በሰቆቃ በችግር መጣንና ባዶ ቀረን:: አሁን በዚህ ሳምንት ወደ ሀገር ያስገቡናል ልጆቼ ራቁታቸውን ናቸው::››

..አይኔ ልብስ ምግብ ወደሚያድሉት ጓደኞቼ ተወረወረ። ለልጆች ያዘጋጀነውን ልብስ ማደል አልጀመሩም። ልጬስሯ ያስቀመጠቻቸው ልጆች ጋር ሆኖ እግሬ የልጆች ልብስ ወዳስቀመጥንበት አመራ። ልብሱን የያዝንበትን ላስቲክ አንስቼ ወደነሱ ተመለስኩ። አደልኳቸው። ‹‹ከሳዑዲ የት አካባቢ ነው የመጣሽው?››

‹‹ኢትዮጵያዊያን እንደጉድ ከተጨፈጨፉበት ሪያድ ከተማ። ለስምንት አመት እዛ ኖሬያለሁ። ግን የኖርንበት ሳይመስለን እያለቀስን ወጣን። ብዙዎች ሞተዋል። አብረሀ የኖርከው ሰው በየሜዳው ወድቆ ሀዘንህን ሳትገልጽ፣ ሀዘንህን ሳትወጣ መሸሽ ያሳዝናል። የልጆቼን አባት እንኳን ጥዬ ነው የመጣሁት። ምክንያቱም ልጆቼን ማዳን ስላለብኝ ነው። አብሮን ቢሆን ይገሉብኛል እኔን ልጆች ስለያዝኩ አይነኩኝም ብዬ ከሪያድ ድንበር ድረስ 3000 ሪያል ከፍዬ ነፍስ እውጭኝ አልኩ። በየቀኑ ሁለት ሶስት ሰው የሚሞትበትን ይህን እልቂት ማስቆም ካልቻሉ እዛው ያሉት ኢትዮጵያውያን ማለቃቸው ነው። እስካሁንም ብዙ ሰው ሞቷል። ተደፍሯል። ተደብድቧል።

***ወደ የመን እንዴት ተመለስሽ?***

ውጡ ሲባል... ረብሻ ሲነሳ.. ጓደኞቻችን ሲሞቱ.. ሲደፈሩብን.. ገና ከመጀመሪያው ከዚህ እሳት ከነልጆቼ መትረፍ አለብን ብዬ ተመልሼ መጣሁ። ብዙ ኢትዮጵያዊያን ችግር ላይ ናቸው። ልጆቼን ይዤ ሸሽሁ እንጂ አካሌ እዛ ነው። የልጆቼ አባት እዛ ነው። ወደ ሀገር ያስገቡት ይሆን እንጃ!.. ከዱላው ቢተርፉም ይሄኔ ብርዱም ፀሃዩም ሲፈራረቅባቸው.. ይሞቱ ይሆናል።

***እስቲ ስለእስሩ ንገሪኝ...***

ብዙ ቀናት ያለምግብ ያለውሃ ነው የመጣነው። አሁን ግን ባይጠግብም ምግብ ሰጥተውናል። ብዙዎቹ ግን አሁንም እዚህ እስኪደርሱ እየተያዙ በየቦታው ባሉ እስር ቤት እየገቡ ከእኛ የባሰ ችግር ላይ ናቸው። ካምፕ ያልተቀበሏቸው መጠለያ ያላገኙ አሉ። እዛ ያሉት በምድረ ዱርዬ እየተደፈሩ፣ እየተደበደቡ ነው።

***ወንዶችና ሴቶች ለብቻ ነበር የተቀመጣችሁት?***

የተቀመጣችሁት አትበይ! የታሰራችሁት በይ። ... የሴት እስር ቤት ለብቻው ነው በሴቶችና በህፃናት ለቅሶ የተሞላ ነው። እኔ ራሴ ስድስት ያበዱ ሴቶችን ይዤ መጥቻለሁ... /ለቅሶ/

***አሁን ቤተሰብ እየጠበቀሽ ነው?***





ነበረ ግን ሻንጣዬ ጠፋብኝ። በርግጥ ጤነኛ ሆኖ መምጣትም ቀላል አይደለም። እዛ ያሉትን ጥለናቸው ስንመጣ እያለቀስን ነው። እስር ቤቱ ውስጥ አንድ እርጉዝ ሞታብናለች። እዛው እስር ቤት እያለን ምጥ አጣደፋት፤ ግን የህክምና እርዳታ ባለማግኘትዋ ሞተች።

***እስር ቤት ያለት ምን ያህል ይሆናሉ?***

ስማኒያ ክፍል አለ.. በየክፍሉ ስልሳ አምስት ስልሳ አምስት ሰው ነው የታጎረው። መካሲመሺ እስር ቤት ይባላል። የወንድና የሴት እስር ቤት የተራራቀ ነው። በጣም ረጅም ከመሆኑ የተነሳ በመኪና እንጂ በእግር አይሞከርም። በአሁኑ ሰዓት በከተማው ያለው እስር ቤት ሞልቶ የመዝናኛና የስብሰባ አዳራሹን ሁሉ እስር ቤት አድርገውታል። የተደፈሩት የሞቱት.. ሴቶች ብዙ ናቸው። አንዷን እርጉዝ ለሶስት ሲደፍሯት ሞታለች።

***የሴሎች ሰገር ስደተኞችም እየወጡ ነው ተብሏል...***

አዎ። ኢትዮጵያዊው ከበደሉ ብዛት የተነሳ እየተናነቀው እኮ ነው ግጭቱ የሚከረው። ሚስቱን እህቱን ከእጁ መንትፈው ሊወስዱበት ሲሉ ነው ጦርነት የሚነሳው። አበሻ ወንድ እየሞተ ያለው ‹‹ሴቶቻችንን አትንኩብን..›› ስለሚል እኮ ነው። ኤምባሲው ሊደርስላቸው ይገባል።

፨፨ ፨፨ ፨፨ ፨፨ ፨፨ ፨፨

**ስምሽን ንገሪኝ..?**

*ሀያት አህመድ*

**እስቲ ስካሄድሽን ንገሪኝ ...**

ከደሴ ነው በኤጀንሲ የሄድኩት። የምሰራው በጠለብ/በህጋዊ መንገድ ነበር። ስዎቹ ሳይመቹኝ ሲቀሩ.. ብዙ ጓደኞቻችን ችግር ሲደርስባቸው ሳይ፣ ስልካችንን ቀምተው ቤተሰቦቻችን በሃሳብ ሲያልቁ፣ እኔም ነገሩ ስላልተመቸኝ ጥዬ ጠፋሁ። ከዛም በሃጂና ኡምራ የሄድኩ አስመስዬ ተቀጥሬ መስራት ጀመርኩ።

**በኮንትራት ስንት ጊዜ ሰራሽ?**

ሶስት ወር።

**አሰሪዎችስ ቤት የሚደርስብሽ ችግር ምን ነበር?**

በቤት ውስጥ ያሉ ወንዶች ያስቸግሩኝ ነበር፤ አስገድዶ ለመድፈር ይተናነቁኛል:: አሰሪዬ በስራዬ እትደሰትም ያጠብኩትን ነገር እንደገና እጠቢ ትለኛለች::

**"የኢትዮጵያ ሰራተኞች ሞያ የላቸውም፣ "ሞዲስ እንኳን በአግባቡ መጠቀም አይችሉም፣ በዚያ ላይ ወንዶቻችንን ያባልጋሉ" የሚል ክስ ከሳኡዲ ሴቶች ይሰማል:: አንቺ ምን ትያለሽ?**

በጭራሽ! እኛ ደልቶን ይሄን ልናስብ? አንገታችንን ቀና አድርገን እንኳን ለመሄድ እንቸገራለን:: እዛ ቦታ ላይ እኛን ብታይ ኢትዮጵያዊነት ያስጠላሻል:: አለባበሳችን ምንድንነው፣ ሁኔታችንስ፣ ኑሮዋችንስ.. እኛ የእነሱን ባል የምናባልግ ምን አምሮብን፣ እንዴት ሆነን ነው? እኛን እኮ ይጠየፉናል:: በምን አንገታችን ቀና ብለን ነው የእነሱን ወንዶች የምናባልገው? እኛ እኮ ለህይወታችን እየሰጋን ነው እያንዳንዷን ቀን የምናሳልፈው:: በርግጥ የገጠር ልጆችም ይሄዳሉ:: እንግዲህ በንፅህና የሚታሙት እነሱ ናቸው:: ግን ስንቱን አእምሮውን አሳጡት.... ወይኔ!!.. አሁን ስንመጣ እንኳን ጅዳ ኤርፖርት ውስጥ ሰባት ያበዱ ልጆችን አይቻለሁ:: ‹‹ይዛችኋቸው ሂዱ›› ሲሉን ነበር፤ እንዴት አድርገን እንይዛቸዋለን? ጥለናቸው መጣን:: አይ ዜጎቻችን! እየቀወሱ፣ እየተደፈሩ፣ እየተደበደቡ፣ እየተጣሉ ነው ሜዳ ላይ ....ተመልካች አጥተው::

**ጣትሽ ላይ የጋብቻ ቀለበት አያለሁ ... ባለትዳር ነሽ?**

ፈትቻለሁ:: የአስር ዓመትና የስምንት ዓመት ልጆች አሉኝ:: እነሱን ላሳድግ ብዬ ነው በሰው አገር የተንገላታሁት:: ገንዘብ እልክ ነበር:: ሆኖም እኔም አልተለወጥኩም፤ ለልጆቼም አልሞላልኝም:: አንድ ጊዜ ሆድ ብሶኝ ራሴን ለማጥፋት ሞክሬ ነበር:: ታውቂያለሽ... ልጆቼ በዓይን በዓይኔ መጡብኝና ... ከድርጊቴ ታቀብኩ:: አይኔ እንቅልፍ ካጣ ስንት ጊዜው ሆነ መሰለሽ... አይኔ ስር ጥቁር ብሎ የምታይው፣ የበለዘ የሚመስለው እኮ በእንቅልፍ እጦት የተፈጠረብኝ ነው:: ጀርባዬን ያመኛል:: ብዙ ሰዓት የምቆምበት እግሬንም እጅግ ታምሚያለሁ:: አሁን ለትንሽ ጊዜ ማገገም አለብኝ::

**ጂዳ ኤርፖርት ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት የሚጠባበቁ በርካታ ኢትዮጵያዊያን አሉ ይባላል...?**

በጣም ብዙ እንጂ! 'ኢትዮጵያዊ ሁሉ አገር ነቅሎ ነው እንዴ የወጣው ብዬ ተደንቂያለሁ:: በጣም ያዘንኩት ግን ወደዚህ ስመጣ ኤርፖርት ሰባት ያበዱ ልጆች ስመለከት ነው:: እዛ ያለው ኤምባሲያችን እንዴት ወደአገራቸው አይመልሳቸውም? ‹‹እህ›› ብሎ ችግራቸውን የሚያደምጣቸው ይፈልጋሉ:: እስቲ አስቢው... ሰባት ሴቶች አብደው





አይቻለሁ፤ በአይኔ በብረቱ:: አንዷ ልጅዋ በርሃብ ሞታባት ነው የቀወሰችው:: ስድስቱ ደግሞ በስራ ቦታቸው ቀውሰው፣ አሰሪዎቻቸው ናቸው አምጥተው የጣልዋቸው:: የምናየው ነገር ሁሉ ይዘገንናል::

**ከዕረፍት በኋላ ምን ልትሰሪ አቀድሽ...?**

አሁን ጤንነት አይሰማኝም፤ ካገገምኩ በኂላ እንግዲህ ... እንጃ ምን እንደምሰራ:: አንድ ዓመት ከሶስት ወር ተቀምጬ ነው የመጣሁት:: ከአስርና አስራ አምስት ዓመት በላይ የኖሩትም ‹ምንድነው የምንሰራው?› የሚል ነው ጥያቄያቸው:: ብዙ ጊዜ ኖረው ቢመጡም ምንም የያዙት ነገር የላቸውም:: በጣም ያሳሰበኝ ይሄ ነው::

**ከእሁን በኋላ ወደሳኡዲ የመመለስ ሃሳብ አለሽ?**

አላህ ያውቃል::

※ ※ ※ ※ ※ ※

*ከሳዑዲ የተመለሱትም ሀገር ውስጥ ለሚታተሙ ጋዜጦች ታሪካቸውን እያጫወቱ ነው:: እስኪ አዲስ አድማስ ጋዜጣ ላይ ያገኘሁትን በአጭሩ ላቅርብላችሁ... ችግሩን በጉልህ የሚያሳይልኝን ብቻ ስለምፈልግ አሳጥሬዋለሁ..::*

※ ※ ※ ※ ※ ※

**ስምሽ ማን ነው?**

ፀጋ ኪዳኔ ገብረኪዳን

**ምን እየጠበቅሽ ነው?**

**ዘመድ አለችኝ አዲስ አበባ የምትኖር፤ እሷ እስክትመጣ እየጠበቅሁ ነው::**

**ሳዑዲ ምን ያህል ጊዜ ቆየሽ?**

ከአንድ ዓመት ቆይታ በኂላ ነው ከሪያድ የመጣሁት:: ከኢትዮጵያ ስሄድ በኮንትራት ቢሆንም በባህር ከሄዱት (ከህገ-ወጦቹ) ስደተኞች የተለየ ክብር አላገኘሁም:: ጭቅጭቅ፣ ስድብና ድብደባ ሲበዛብኝ ከተቀጠርኩበት ቤት በስምንተኛ ወሬ ጠፋሁ:: የሄድኩት ለአንድ ስራ እና ተዋውዬ[32] ነበር::

---

[32] አዲስ አበባ ላይ ሲዋዋሉ ውሉ ለአንድ ስራ ብቻ በቀን ለስምንት ሰዓት ያህል ብቻ ይበል እንጂ ይህ ግን በፍፁም ተግባራዊ አይሆንም - ደራሲው

በቀን የምተኛው ከሁለት ሰዓት ቢይበልጥም ነበር፡፡ ሥራ ብቻ ነው 24 ሰዓት…

እስቲ ስለደረሰብሽ ችግር በዝርዝር ንገሪኝ?

በ700 ሪያል ተቀጥሬ ነበር ከዚህ የሄድኩት፡፡ አሰሪዬ ቤት አራት ትላልቅ ወንድ ልጆች አሏት፡፡ የእህቷ ልጆችም እዚያው ነው የሚኖሩት፡፡ ‹‹ወሲብ ካልፈፀምን..››[33] ብለው ያስቸግሩኛል፡፡ በጣም ተሰቃየሁ፡፡ ከአቅሜ በላይ… ለህይወቴ በጣም አስፈሪ… ሲሆንብኝ፣ ሲያንገፈግፈኝ ጊዜ ሁለት ወር የሰራሁበትን ገንዘብ ጥዬ ወጣሁ፡፡ ኤጀንሲው ለሌላ ሰው ሸጠኝ፤ በአስር ሺህ ሪያል ነው የሸጠኝ፡፡ እዚያም አልተመቸኝም፡፡ አምስት ሰው እንኳን የማይችለው ስራ ነበር የምሰራው፡፡ አንድ ኩንታል ዱቄት አብኩቼ፣ ለሱቅ የሚሸጡት ብስኩት ጠብሼ፣ ሰባት መቶ ሪያል ነበር የሚከፈለኝ፡፡ ሁለት ወር ሙሉ እንደምንም ድምጼን አጥፍቼ ሰራሁ… በእንቅልፍ እጦት ልወድቅ እየተንገታገትኩ፡፡ ፊታቸው ላይ ግን ደስተኛ እመስል ነበር፡፡ ሰውነቴ እየመነመነ መጣ፡፡ ይሄኔ ድጋሚ ለመጥፋት ተዘጋጀሁ፡፡ አንድ ቀን ረመዳን ካፈጠሩ በኋላ ቤተሰቡ ተሰብስቦ ሊዝናኑ ወጡ፡፡ ደስ አለኝ፡፡ ቶሎ ብዬ የሴትየዋን ሙሉ ልብስ ለብሼ፣ ሽፍንፍን ብዬ ወጣሁ፡፡

ሻንጣ ምናምን ሳትይዢ?

ባዶ እጄን፡፡ የሰራሁበት ገንዘብ እንኳን በእጄ የለም፡፡ በቃ ዝም ብዬ ወጣሁ፡፡ ፓኪስታናዊ የታክሲ ሾፌር አገኘሁ፡፡ ‹‹ምን ሆንሽ?›› ብሎ ሲጠይቀኝ በዝርዝር ነገርኩት፤ አዘነ፡፡ ‹‹ሪያድ የሀበሻ ሃገር ነው፤ ብዙ ኢትዮጵያዊ አለ›› ብሎ እዛ (በነፃ) ወሰደኝ፡፡ ብዙ ኢትዮጵያውያን አገኘሁ፡፡

እዚያ መኖር ጀመርሽ ማለት ነው?

ሳያቸው በጣም አለቀስኩ፡፡ አገሬ የገባሁ መሰለኝ.. መሬት ሁሉ ስሚያለሁ፡፡ ከኢትዮጵያ በባህር (በህገ ወጥ መንገድ) የመጡ ሴቶች ነበሩ፡፡

[33] እዚህ ጋ ዱባይ ያለች ጓደኛዬ የነገረችኝን ገጠመኝ ከቃለ-ምልልስ ለጨዋ ጋር ስለሚመሳሰል ሳቀርበው ወደድኩ፡፡ ልጅት ስራ ሰርታ እናቷን ልትረዳ ነው ወደ ዱባይ የሄደችው፡፡ የወሰዷት ሰዎች ቤት ሁለት ግዙፍ ጎረምሶች አሉ፡፡ ጤነኞች አይደሉም፡፡ የአዕምሮ ዝግመት ነገር አለባቸው፡፡ ለስራ የሄደችውን ልጅ ሁሌ ያስቸግሯታል፡፡ ማስቸገር ብቻም አይደለም ሴትዮዋ ስትወጣ ገብተው የፈለጉትን አደረጉ፡፡ ለሴትዮዋ ልጆችሽ ያስቸግሩኛል ዛሬ እንዲያውም ከዛም አልፈው ዛሬ አስገደደው… አደረጉ፡፡ ሴትዮዋ ለትሰማት ቀደታ ሳቅ ብላ ‹‹ጥሩ ነዋ ልጆቼ ሞኞች ናቸው ሴሰኞችም ናቸው፡፡ ውጭ ሴት ፍለጋ ሲሄዱ አንድ ነገር ከሚሆኑብኝ እንቢ አትበያቸው ብቻ ለእኔ ንገሪኝ እኔ እከፍልሻለሁ..›› እንዳለቻት ነገረችኝ፡፡ ይህን ስትነግረኝ በጣም ደነገጥኩኝ፡፡ እዚህ የመን ውስጥ ደግሞ የልጅቷን ስም መናገሩ ጥሩ ባለመሆኑ ልዝለለውና… ልጅቷ ኮንትራት ስራ ለመስራት የመጣችበት ቤት ያለ ልጅ ደፈራት፡፡ ስታለቅስ ውላ በንዴት እቃ ሰባብራ ሴትዮዋን ትጠብቃታለች፡፡ ጉዳዩን የልጁ እናት እንደሰማች ‹‹ጥሩ ነዋ የእኔ ልጅ እኮ የመኔ ስለሆነ አግኝተሽ ነው፡፡ ክብር ነው ላንቺ ምን እንዲህ አደርገ እቃ ያሰብርሻል? ትከፍያታለሽ›› እንዳለቻት ሰምቻለሁ፡፡ የተሰበረውን ትከፍያለሽ ብትላትም የእቃውን ዋጋ ግን አላስከፈለቻትም--ደራሲው





ከእነሱ ጋር አንድ ቤት በስድስት መቶ ሪያድ ለስድስት ወር ተከራይተን አብረን እየኖርን እንሰራ ጀመር፡፡

ቤቱን ስንት ተከራያችሁ?.....

አስር ነበርን፡፡ ሁለት ወር እንደሰራሁ ግን በአካባቢው ግጭት ተነሳ፡፡ እግሬ አውጪኝ ብለን በየፊናችን ተበታተንን፡፡

ምን ዓይነት ግጭት?

መንግስት የሌለበት አገር ይመስል ጐረምሶች በር እያንኳኩ በሽጉጥ፣ በካራ፣ ሰው መግደል ጀመሩ፡፡ ስለዚህ ‹‹እጃችንን እንስጥ›› ብለን ተማከርን፡፡ ሌላው ችግር ፖሊስ፤ ትዳር መስርተው የሚኖሩትን የሀበሻ ወንዶች እየወሰደ፣ ሴቶችን ለብቻቸው ይተዋቸው ነበር፡፡ በቤቱ ወንድ አለመኖሩን የተገነዘበ የሀገሩ ዱርዬዎች (እንኳን ለሀበሻው ለመንግስትም ልባቸው ያበጠ ነው) ሴትዮዋን ለአራትና ለአምስት እየሆኑ መድፈር ያዙ፡፡ ከእኛ ጎን የነበሩትን ሲያሰቃዩዋቸው አይተናል፡፡ ወንዶቹን ፖሊስ ሲወስዳቸው ጎረምሶቹ ተከትለው ይገቡና ሴቶቹን መጫወቻ ያደርጓቸዋል /በቅቦ/፡፡ አንድ ያየሁትን ልንገርሽ../ረጅም ትንፋሽ/ እነዚህ ጐረምሶች… ሶስት ሴቶች ያሉበት ክፍል ውስጥ ገብተው ለሰባት ደፈሯቸው፡፡ /ማውራት አልቻለችም፤ ሳግና እንባዋ እያቋረጣት/.. ከሶስቱ አንዷ የሰባት ወር ነፍሰጡር ነበረች፤ ሲገናኟዋት ሞተች፡፡ አንዷን ደግሞ ለሰባት ደፈሯትና ገድለ ውጥለዋት ሊወጡ ሲሉ ሹርጣ /ፖሊስ መጣ፡፡ ከፖሊስ ጋር ተኩስ ገጥመው እርስ በርስ ተገዳደሉ፡፡ የሀበሻ ወንድ ከእህቱ ወይንም ከሚስቱ ሊለዩት ሲመጡ አልለይም ይልና ይገደላል፤ ይደበደባል … በቃ እልቂት ይሆናል፡፡ አዲስ አበባ ብለሽ ካራ ቆሬ እንደምትይው.. ሪያድ ብለሽ ሞንፋ የሚባል አካባቢ በርካታ አበሾች ይኖራሉ፡፡ እኔ እንኳን የማውቀው … ከአምስት በላይ ሴቶች እንደተገደሉ ነው፡፡ መላ አካላቸውን ቆራርጠው ነው የጣሏቸው፡፡ ግን ይሄ ሁሉ መከራ ምን አድርገን ነው?

አንቺ እንዴት መጣሽ ወደ አገርሽ?

እጄን ሰጠሁ፡፡ አሰሪዬ ‹‹የት ልትሄጂ ነው?›› ብላ ስትጠይቀኝ ‹‹አንድ ጓደኛዬ ልትወልድ ነውና ልጠይቃት..›› ብዬ የሰራሁበትንም ሳልቀበል ወጣሁ፡፡ ምክንያቱም ብትገለኝስ ብዬ ፈራሁ፡፡ አብዛኛው ሀበሻ ከስራ ወደቤቱ ሲሄድ እየተያዘ ነው የሚመጣው፡፡ የሰራበትን የለፋበትን ሳይዝ ባዶ እጁን፡፡ እኛም ነገሩ ስላስፈራን እጃችንን ሰጠን፡፡ በቃ እኔም ወደእዚህ መጣሁ፡፡

ዛሬ ላይ ሆነሽ ስታስቢው ወደዛ በመሄድሽ ምን ይሰማሻል?

መጀመሪያ ከዚህ ስሄድ ፃጣም ደሷ ብሎኝ ነበር። የራሴንና የቤተሰቤን ህይወት ላሻሽል ተስፋ አድርጌ። ከዛ በኋላ ግን ከስራው ብዛት የተነሳ ከጥቅም ውጪ ልሆን ነው ብዬ እጅግ አምርሬ አለቅስ ነበር። በጣም ስጋት ያዘኝ። ግን ከሞት ተርፌ ወደዚህ ስመጣ አምላኬን አመሰገንኩ።

**ቤተሰብሽ መምጣትሽን ስውቀዋል?**

አላወቁም። ምን እያሰቡ ይሆን? ይሄን ሁሉ ነገር እየሰሙ። እናቴ መንገድ መንገድ እያየች ይሆናል። ደሞ ከእኛ አካባቢ ልጆች ብዙ የሞቱ አሉ። ..አሁን እኔ ራሴ የሁለት ሰው መርዶ ይዤ መጥቻለሁ። እናቴም ሰው ሲመጣ ‹‹ልጄን አይታችኋል?›› ትል ይሆናል። እኔስ መጣሁ.. በረሃ ላይ ተደፍተው ለመምጣት ወረፋ እየተጠባበቁ ያሉ ህጻናትና ሴቶች ብዙ ናቸው። እዚህ የመጣነው እኮ ግማሽ አንሞላም። በሳኡዲ የኢትዮጵያውያን እንባ ያሳዝንሻል። ብዙዎቹ በሃዘን ላይ ናቸው፤ ድረሱላቸው።





# - 24 -

# መደምደሚያ

“የዳመናው ችግር ሰማዩ እስኪጠራ፣
ከሀገር ተሰደድን በተራ በተራ፤
አንድ ቀን ይታየናል ታብሶ የኛ እንባ፣
እጅ ለእጅ ተያይዘን ሀገር ቤት ስንገባ።

ስለስደት ስናወራ ለስደት የሚያበቃንን ችግር ማሰብ ግድ ነው። ከሀገር የሚያሰድድ ኢኮኖሚያዊ ችግር፣ ሀገር አስጥሎ የሚያሰድድ ፖለቲካዊ ችግር..በተዛባ መረጃ ተታሎ በሠው ሀገር መሰቃየት፣ አካል ማጣት፣ የአውሬ ቀለብ መሆን፣ የትም ዱር ጫካ ወድቆ መቅረት፣ ባህር መስመጥ..ለዚህ ሁሉ የሚያበቃ የተሳሳተ መረጃ ማግኘት። እውነተኛ መረጃ የማጣት ችግር አለ። መረጃ ማጣት ነው ብሎ መደምደምም አይቻልም። መረጃ ሳይጠፋ በጭፍን፣ አማራጭ በማጣት የሚገቡበትም ሁኔታ አለ። በአረብ ሀገራት ስለሚደረጉ(ስለ የሚፈጸሙ)ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች የመገናኛ ብዙሀን ብዙ ብለዋል። አሁንም ይላሉ። ችግር የጋረደው ህሊና ልሞክረው ይላል። አንዳንዱ አይፈረድም። «ረሀብ ስንት ቀን ይሰጣል?» የሚለው የሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን ግጥምን ማስታወስም ያስፈልጋል።

በዚያም አለ በዚህ ግን እንደጉድ እየተሰደድን ነው። ወደ ስደት የሚጎርፈው ህዝባችን ከእለት ተለት እየጨመረ ነው። በ2011 ዓ.ም 82000 - በ2012 ዓ.ም ደግሞ ወደ 85000 ኢትዮጵያዊያን ባህሩን ተሻግረው ወደ የመን እንደገቡ ብሎም ግማሹ ወደ ሳዑዲ አረቢያ

እንደተጓዙ አለም አቀፉ የስደተኞች ጽ/ቤት (IOM) የሚባለው ድርጅት መግለጹ ይታወቃል፡፡ አብዛኛውም ከወሎ፣ ከአርሲ፣ ከሀረር እና ባሌ አካባቢ ነው የሚሰደዱት፡፡ ይህን ያህል ኢትዮጵያዊ የሚሰደደው በኑሮ ችግር ምክንያት መሆኑ እሙን ነው፡፡ ለዚሁም እማኙ በወሎ ቦረና ወረዳ መካነሰላም የሚባል አነስተኛ ከተማ ውስጥ ከዋለልኝ መኮንን ትምህርት ቤት ከ9 እና 10ኛ ክፍል ብቻ በዚህ አመት በ(2004) ከ500 ተማሪዎች በላይ አቋርጠው ስደት ወተዋል፡፡ ከዚህ ውስጥ አብዛኞዎቹ ቤተሰቦቻቸው በዝቅተኛ ኑሮ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ በኩር የተባለው የአማራ ክልል ጋዜጣ ያሰፈረውን ይህ ዜና እንደቀልድ የሚታይ ነገር አይደለም፡፡ የፍልሰታችን አስፈሪ ሂደት ወዴት እየተጓዝን እንደሆን ያመላክታል፡፡ ሰዒድ የተባለ ወዳጄ ከገጠር ትምህርት ቤቶች በየአመቱ ትምህርት የሚያቋርጠው ተማሪ ብዛት አስደንጋጭ መሆኑን ጽፎልኛል፡፡ ይሄው ወዳጄ ከጻፈልኝ በተጨማሪ አያይዞ የላከልኝ በኩር ጋዜጣ ላይ ከወረዳው አስተዳደር በተገኘው መረጃ በ2004 በአጠቃላይ ብዛት ያላቸው ተማሪዎች ከወረዳው ትምህርት ገበታቸው እንዳቋረጡ ዘግቧል፡፡ ጋዜጣው ትምህርት የሚያቋርጡበት ምክንያት በቀጥታ ላለመጥቀስ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ አረብ ሀገር ልከው ገንዘብ የማግኘት ፍላጎታቸው ማየል ነው ሲል ዘግቧል፡፡ ከነዚህ መሃል ደግሞ ብዙዎች የሚታለሉት ሌላው ተበድሮም ተለቅቶም፣ በአጋጣሚ ቀንቶት..ለቤተሰቦቹ የሚያደርገውን እያዩ በመሆኑ አዘንኩ፡፡ እውነቱን አይናገሩም፡፡ ስቃዩን ሳይሆን ብር እንደልብ መገኘቱን በመናገራቸው ብዙ-ዎች ስህተት መግባታቸውን ይበልጥ ያወኩት የመን ከገባሁ በኋላ የሁሉን ኑሮ ኖሬ ሳየው ነው፡፡

ለማንኛውም ይህን ሁሉ ግፍ እንድንቀበል የሚያረገን ድህነትና አለማወቅ ነው፡፡ ለመሰደዳችን ዋነኛ ምክንያት ግንዛቤ ማጣትና የኢኮኖሚ ችግር አርገን እናስባለን፡፡ ትክክል ነው፡፡ ግን ለኢኮኖሚና ግንዛቤ ማጣት ችግር መከሰት ዋነኛ ምክንያት ብልሹ የፖለቲካ ስርዓት ነው፡፡ እኛ ደግሞ እንደ አለመታደል ሆኖ የሚገጥመን ሁሉ ዞረህ ..ዞረሽ..የሚያሰኝ ነው፡፡ ለመሆኑ ምን አይነት አስከፊ ችግር እና ርሃብ ላይ ብንሆን ነው ሶማሊያና ጅቡቲ.. የመን የተሰደድነው? የሚል እሳቤ ውስጤ ስንቅር ይላል፡፡

የተዛባ መረጃ በመስጠት በኩል አብዛኛው ከስደት ተመላሽ ተጠያቂ ነው፡፡ ራሱን ለመቆለል ሲል ያየውን መከራ ሳይሆን ሁሉ አልጋ በአልጋ እንደሆነ አድርጎ ይደሰኩራል፡፡ በብድርም በእቁብም የሰበሰበውን ጥቂት ዶላሮች አመነዛዘሩ አይን ይስብና ሰው ገደል ይከታል፡፡ የሚገርመው ነገር ሀገር ሲገቡ ሰው ፊት የሚመዙትን ዶላር ለማጠራቀም ተርበው፣ ተጠምተው የሚከርሙ፣ ሳንቲም ቆጥበው በእግር የሚጓዙ አሉ፡፡ በሀገር ቤት ግን ዶላር አመዛዘዛቸው የደላቸው መስለው የስንቶችን ቀልብ ስበዋል? ሰው እንዲያሞግሳቸው ለጉራ ይሁን ራሳቸውን መካብ ፈልገው ጥሩ ጎኑን





ሲያወሩ ስንቱን ገደል ከተዋል? አንቀጽ ተጠቅሶ በህግ ባያስቀጣም ከህሊና ፍርድ አንጻር ሰውን ወደ እሳት፣ ወደ ስቃይ መላክ ወንጀል ነው፡፡

ጥቂት የቀናቸውን አይተው፣ በደላላዎች የሰላ-ምላስ ተታለው ብዙዎች እሳት ውስጥ የሚገቡበት የአረብ ሀገራት ስደት ዋነኛው አስከፊና የብዙዎችን ህይወት ያበላሸ ነው፡፡ የአስከፊነቱ ሁኔታ የሚጎላው ጥሩነቱ ወይም ጥሩ ጎኑ ያነሰ..በጣም ያነሰ እንዲያውም አለ ወይ? የሚያሰኝ አይነት በመሆኑ ነው፡፡ ከሌላው የለየውም ይሄው ነው፡፡ አደጉ በሚባሉ ሀገራት መጥፎ ጎን ሳይኖረው ቀርቶ አይደለም፡፡ አለውም፡፡ ጥሩ ጎኑ የተሻለ ሁኔታ ስላለው ነው፡፡ ቢያንስ መማር፣ ሰርቶ መብላትና ሀገር ቤት ላለውም ትንሽ ማጉረስ የሚቻልበት እድል ይኖራል፡፡ ከዚህ የዘለለ ሊገጥምም ይችላል፡፡ ይገጥማልም፡፡

ወደ አረብ ሀገራት የሚደረገው ስደት ግን ብዙ በጣም ብዙ የሚለየው ነገር አለ፡፡

<u>አንደኛ</u>፡- እናትና አባቷ ታሳልፍልናለች፣ ትረዳናለች ብለው እቁብ ገብተው፣ ካርታ አስይዘው፣ መሬት ሸጠው፣ ወዳጅ ዘመድ አስቸግረው አይገቡ ገብተው ተበድረው..ነው የሚልኳት፡፡

<u>ሁለተኛ</u>፡- አውሮፓ እና አሜሪካ ለመጓዝ ከሚጠይቀው ብር ቀነስ ያለ በመሆኑ ፊታቸውን ወደዛ እንዲያዞሩ ያደርጋቸዋል፡፡

<u>ሶስተኛ</u>፡- ለቤት ሰራተኛነት ስለሆነ የተማረም ያልተማረም ስለሚሰራው

<u>አራተኛ</u>፡- በህገ-ወጥ መንገድ በየመንደሩ ባሉ ደላሎች ቪዛው በቀላሉ ስለሚገኝ

<u>አምስተኛ</u>፡- በርካታ ሰዎች በአንዴ ሊሄዱ ስለሚችሉ..ብቻ በብዙ አማራጭነት ትኩረት ወደ አረብ ሀገራት ይሆናል፡፡ አማራጭ ባይሆን እንኳን ኑሮን ለምልወጥ ሲባል ወደ አረብ ሀገር የግድ ይኬዳል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እንዳሰቡት ሳይሆን ይቀርና ነገር ተገልብጦ ኑሮ ትለውጣለች ተብላ የተላከች ልጅ አካሏን አጥታ፣ ጤንነቷ ተቃውሶ የቤተሰብ ሸክም ሆና የምትመለሰው ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ አመት ሁለት አመት ብሎም ከዛ በላይ ጉልበቷን አፍስሳ ስድብ ዱላዋን ችላ ቤሳ ቤስቲን ሳትይዝ የምትመለስም አለች፡፡ የተለመደም ነው፡፡ «እንኳን በሰላምና በጤና መጣሽ.. ከፎቅ ተወርውሮ፣ ተደብድቦ፣ የፈላ ውሀ ተደፍቶበት፣ አካል አጥቶ መመለስም አለ..» መፅናኛ ቃል ሆኗል፡፡

አብዛኛው (ከ60% በላይ) አረብ ሀገር የሚሄዱ ሀበሻዎች አገባባቸው በደላሎች የተጭበረበረ መንገድ ነው፡፡ ህጋዊ ስላልሆኑ ሲደበደቡ፣ የሰሩበትን ሲከለከሉ.. መክሰስ መጠየቅ ጉዳቱ ያመዝናል፡፡ የባሰ መታሰር መደብደብ

ይኖራል:: ለነገሩ ህጋዊስ ቢሆኑ ማን ከሰው ቅጥር፣ ማን ለሚ፣ ማን ተከራካሪ ኖሮ ፍትህ ይገኛል? ለእዚህ ጥሩ ምሳሌ እንዲሆነኝ ከማቀርበው ሀሳብ ጋር በአንዳንድ ሁኔታ በመመሳሰሉም ኢቦኒ መፅሄት ላይ ያገኘሁትን ታሪክ በጥቂቱ ቀንጭቤ ላቀርብ ወደድኩ:: መጽሔቱ በ2ኛ ዓመት ቁጥር 23 እትሙ ላይ «አረቦች እንደ እንሰሳ ነው የሚያዩን» በሚል ርዕስ ባለታሪኳ ዳናዊት ሀዱሽን ቃለ-ምልልስ ሲያደርግላት ከሰጠችው መልስ ውስጥ «..በደላላ ነው የሄድኩት:: በህገ-ወጥ መልኩ ማለት ነው:: ከዚህ ስሄድ 8500 ብር ከፍዬ እዛ ሄጄም የሁለት ወር ደሞዜ ተቆርጦብኛል:: እዛ ያለችው ወኪሏ ናት የተቀበለችኝ:: እኔ ምንም ያወኩት ነገር የለም:: ለቤተሰቤ ብር ልልክ ስጠይቃቸው አሰሪዎቼ የምን ደሞዝ አለሽ? የሁለት ወር ደሞዝሽን የምትወስደው ያስገባችሽ ናት አሉኝ:: ከዛ ስደውልላት ቴሌፎኑን ትዘጋዋለች:: ..እዚህም ብር ከተቀበሉኝ በኋላ ነው የሁለት ወር ደሞዜን የቀረጠፉት...» የሚል ይገኝበታል::

ይህ ገጠመኝ በትንሹ ነው:: ህገ-ወጥ ደላሎች የሚሰሩት ግፍ ራሱን የቻለ ትልቅ ራስ ምታት ነው:: አሳልፈው ለወንድ መጠቀሚያ የሚሸጡም አሉ:: በጥቅማ ጥቅም የተሳሰሩ፣ የተደራጁ በመሆናቸው «ለምን ይህን ታደርጋላችሁ? ለምን በወገን ላይ..» ሲባሉ ጉዳት የሚያደርሱ ጨካኞች ናቸው:: የወገናቸውን ደም መጣጮች ብዙ ናቸው:: ተገፍተው፣ ተደፍተው ያገኙትን ለመንጠቅ ያሰፈሰፉ ጅቦች፣ ወገናቸውን ለአረብ ወንድ ሸጠው የሚያስደፍሩ ውሾች ሞልተዋል:: ሀበሻ በአረብ ሀገር ለየት የሚያረገው ይህን መሰል እርስ በእርስ የመተራረድ፣ ጭካኔ የነገሰበት መሆኑ ነው::

ሁለት አመት ያለ እረፍት፣ ያለ እንቅልፍ ቀን ከሌት የሰሩበትን ተከልክለው ጊዜና ጉልበታቸውን ለአረብ ሲሳይ አድርገው እያለቀሱ ባዶ እጃቸውን የገቡ ሴቶችን አውቃለሁ:: ወደ ሀገር ለመመለሻ ጠፍቶ ቤተሰብ ንብረት ሸጦም ይሁን ተበድሮ ገንዘብ ልኮላቸው የተመለሱም አውቃለሁ:: ከዚህ ባስ ያለም አለ:: አካላቸው የሚሰረቅ፣ ሞተው ቀባሪ ያጡ፣ አብደው በሰው ሀገር የሚንከራተቱ አይቻለሁ:: ታመው ሆስፒታል ሄደው በመርፌ ህይወታቸውን ያጡ አሉ:: በHIV ተይዘው ማቀው የሞቱ ሞልተዋል:: በመኪና ተገጭቶ እግሩ ተሰብሮ ገጪው ሳይሆን ተገጪው ታስሮ ህክምና ሳያገኝ እስር ቤት ሲሰቃይ ለማየት ችያለሁ::

ሰቀቀን ለማየት የታደለው አይኔ እስኪጠግብ ድረስ አይቷል:: ጆሮዬም የስቃይ ጣር መስማት እስኪሰለቸው ሰምቷል:: ለኮንትራት ስራ መጥታ ሳባ የተባለ ሆስፒታል አራት ልጅ በአንዴ የተገላገለች ኢትዮጵያዊት አይቻለሁ:: ቀርበን እንዳናናግራት አሰሪዎቿ ሰራተኛ አስወለዱ ተብሎ ስማቸው እንዳይጠፋ ጥብቅ ጥበቃ ያስደርጉ ነበር:: በቀይ መስቀል በኩል ከሆስፒታሉ ማስረጃ ለማግኘት እና በምን ሁኔታ ላይ እንዳለች ለማወቅ ያደረግነው ሙከራ አልተሳካም:: ማርገዝና መደፈር





ከተነሳ እዚሁ ከላይ የጠቀስኩት መጽሔት ላይ በቃለ-ምልልሱ ውስጥ ይህን በሚመለከት ባለታሪኳ ዳናዊት ሀዲሽ ከተናገረችው ጨምሬ ላስነብብ ወደድኩ::

«..እየመጡ ለወሲብ ጥያቄ ያቀርቡልኛል:: እምቢ ስላቸው እንደ እንስሳ ነው ያለ ርህራሄ የሚደበድቡኝ:: ሰውነቴን ብታየው ያልቆሰለ ቦታ የለም:: ብጮህም የሚረዳኝ ሰው የለም:: ..ለእናትየው ስነግራት እኔማ ምንም ማድረግ አልችልም:: ለሚስቶቻቸው ንገሪላቸው አለችኝ:: ለሁለቱም ሚስቶች ስነግራቸው አንደኛዋ የሆነ ጥቃት ካደረሱብሽ እኔ ጋ ትሆኛለሽ እወስድሻለሁ አለችኝ:: እሷ ጋ እያለሁም በሌለችበት ሰዓት አንዱ ይመጣና ልብሴን ሊያወልቅ ይታገለኛል:: አይሆንም ብዬ ስታገለው በጥፊ ይመታኛል:: ሌላኛው መጥቶ ማደንዘዣ መርፌ ይወጋኛል:: ከዚያ በኋላ የሆንኩትን አላውቅም:: ለሶስት አደንዝዘው ተጫወቱብኝ:: ተጫውተውብኝ በተኛሁበት ትተውኝ ሄደው 3 ቀን ሙሉ ህሊናዬን ሳላውቅ ያለምግብ ያለ ውሀ ነው የቆየሁት:: ስነሳ ራሴን ሳውቅ እግሬ አብጧል፣ ፊቴ በልዟል፣ ጭኔ ቆስሏል:: ደግሞ አደንዝዘው የወሰዱኝ እንደ መጋዘን የሆነ ቤት ውስጥ ነው::

አንድ ኢትዮጵያዊት ሰራተኛ አለች:: ስትመጣና የሆንኩትን ስታይ ደነገጠች:: ከዛ ወደ ሆስፒታል ልትወስደኝ ስትል አይሆንም ብለው እሷን አባረሯት:: ሆስፒታል ከሄድኩ ዶክተሮቹ ለፖሊስ ስለሚያሳውቁና ስለሚታሰሩ አትሄድም ብለው የራሳቸው የሆነ ዘመድ ዶክተር እንዲከታተለኝ ያደርጋሉ:: ራሴ ላይ ተመትቻለሁ:: ትንሽ ራሴን ሳውቅ መኖሬ ሁሉ አስጠላኝ:: በሄድኩ በ4 ወሬ ነው ይህ የገጠመኝ:: በዚህ የተነሳ የሆነ ምንነቱን ያላወኩት መድኃኒት ዋጥኩ:: ራሴን ለማጥፋት ስል:: እናቴ በእሷ ሰው እሆናለሁ ብላ ተበድራ ልካኝ ይሄ ነገር ሲደርስብኝ ህይወቴ አስጠላኝ:: መድኃኒቱን ስውጠው ሰውነቴ በሙሉ አጥንት ሆነ:: ጥርሴ ሁሉ ወደ ውጭ ወጣ:: ራሴን ሳትኩ ሲብሰባቸው ሆስፒታል ወሰዱኝ:: ከሆስፒታል ከወጣሁ በኋላ የወር አበባዬ ቀረ:: ሁኔታውን ለሴትዮዋ ነገርኳት:: መድኃኒት ሰጠችኝና ውጨው ጽንሱ ተወገደ» ብላለች::

ዳናይት የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ተርፋ ለመናገር በቃታለች:: ሞተው በየጓሮው እና በየአትክልቱ ስር የቀበሯቸውን ከፈጣሪ ውጭ ቁጥራቸውን ማን ሊያውቅ ይችላል? ይሄ ነው ተብሎ ተቆጥሮ የማያልቅ ፍዳ የሞላበት ህይወት ለመግፋት ሀገር ጥሎ መሰደድ?

የመን ውስጥ ከሞያዬ ውጭ ሆኖብኝ እንጂ ጥናት የሚያስፈልገው አንድ ችግር አለ:: በርካታ ሴቶች ታመው ህክምና ሲሄዱ የሚባለው የማህጸን ችግር ነው:: ኦፕሬሽን ያደረጉ 11 ሴቶች አውቃለሁ:: ምንድን ነው

ችግሩ? እንዴት ሁሉም በተመሳሳይ ሁኔታ የማህጸን ችግር ያጠቃቸዋል? እዚህ ጋር ማረጋገጫውን ለማግኘት አልቻልኩም እንጂ ኪኒን መሆኑን አንድ ዶክተር ሹክ ብሎኛል:: ሴት አሰሪዎች ባሎቻቸውን እንዳይነጠቁ በመስጋት ስሜት እንዳይነሳሳ የሚያደርግ ኪኒን ከምግብ ጋር ይሰጧቸዋል ይባላል:: ከታመሙት ውስጥ ሁለቱ ኦፕሬሽን ያደረጉት ኢትዮጵያ ሄደው ሲሆን 9 አካባቢ የሚሆኑቱ ደግሞ የመን ውስጥ ነው::

በዛ ላይ ህክምና ላይ ኩላሊት በመስረቅ በኩል ችግር እንዳለ የሚታወቅ ነገር ቢሆንም ኦፕሬሽን የተደረጉትን እንዲመረመሩ ከመምከር ውጭ ማድረግ የምችለው ነገር የለም:: ኩላሊት ስርቆትን በተመለከተ «..የኩላሊት ቀበኞች» በሚል ያኔት መጽሄት በቁጥር 2 ቅጽ 17 ህዳር 2002 ዓ.ም ዕትሙ ካተመው ላይ «ኩላሊት ይሰረቃል» ያልኩት ሀሳቤን ስለሚያጠናክርልኝ ቦጨቅ አድርጌ ላሰፍር ወደድኩ::

«..አንድ የስራ እድል ባህር ማዶ መገኘቱን ጓደኛዬ ሹክ አለኝ:: ..ሀገሩ የመን ነው:: ስራው ደግሞ ጋርድነት::[34] ወደ አምስት የምንሆን ወጣቶች በምስጢር በደላላው አማካኝነት ከየመናዊው ሰው ጋር ተገናኘን:: ተነጋገርን::

ተስማማን::

የጉዞ ዝግጅት ማድረግ ጀመርን:: አካሄዳችን ህገ-ወጥ አይመስለኝም:: ፓስፖርት አውጥተን ቪዛ ተመቶልን ስለሆነ በአየር መንገድ በኩል ነው የወጣነው:: ጉዟችን ህገ-ወጥ ስላልሆነ[35] ችግር ይገጥመናል የሚል ህልም ፈጽሞ አልነበረኝም:: ሰንዓ ለሁለት ቀን ተቀመጥን:: የስራው ቦታ ጋታ ወደምትባል የወደብ ከተማ በተሽከርካሪ አመራን:: እዛ እንደደረስን ትልቅ ግቢ ነገር ውስጥ ተቀመጥን:: ነገሩ ግራ አጋባን::

«ስራው የት አለ?..እዚህ ትልቅ ጊቢ ውስጥ ግዞተኛ ይመስል እስከመቼ ነው ልንቆይ የምንችለው የሚለው ጭንቀት አዕምሮዬን ረበሸው:: ግቢው ጭር ከማለቱ የተነሳ ምንም አይነት እንቅስቃሴ የለውም:: አልፎ.. አልፎ ብቻ በፓትሮል 2 ነጭ ጀለቢያ የለበሱ መልካቸው ወደ ጠይምነት የሚያደሉ አረቦች መጥተው በአስተርጓሚ የባጥ የቆጡን ይጠይቁና ተመልሰው ይሄዳሉ:: ..በዚህ አይነት መልኩ ወደ 3 ሳምንት ያህል

[34] ለኩላሊት ስርቆት መሆኑን ባላውቅም የጋርድነት ስራ አለ ተብሎ የሚመጡ ወንዶች እንዳሉ አውቃለሁ::

[35] እዚህ ጋ የልጅቱን አባባል ልብ በሉ:: ፓስፖርት ስላወጣና ቪዛ ስለተመታለት ህጋዊ ነን ብሏል:: የአብዛኛው ሰው ችግር ይህ ነው:: ፓስፖርት ስለተያዘ ህጋዊ የተሆነ ነው የሚመስለው:: ቪዛው የስራ ቪዛ ነው ወይ? በተለይ የመን በ1 ወር የጉብኝት ቪዛ ነው ኮንትራት እየተባለ የሚገባው:: በእርግጠኛነት መናገር የሚቻለው ያቺ አንድ ወሯ እስኪታልቅ ብቻ ነው ህጋዊነት:: በዚህ ጊዜ እንኳን ሲሰሩ ቢያዙ ቪዛው የስራ አይደለምና ሊታሰሩ ይችላሉ::





እንደተቀመጥን አንዱ ጓደኛችን ተዝለፍልፎ ሲወድቅ ጠባቂያችን ስልክ ደውሎ ከዛን ጊዜ በፊት አይተናቸው የማናውቅ ሰዎች መጥተው በመኪና ይዘውት ሄዱ:: ከዚያን ቀን በኋላ ስለጓደኛችን ምንም ያወቅነው ነገር የለምና ሁኔታው ስጋት ፈጠረብን::

ምን አድርገውት ይሆን? ስለእሱ ስናስብ ስለራሳችን እንጨነቃለን:: በጓደኛችን ወጥቶ መቅረት ጭንቀት ውስጥ እያለን ሌሎች ከሌላ ሀገር የመጡ ሰዎችም ከእኛ ጋር ተቀላቀሉ:: በምልክት ካልሆነ አንግባባም:: በመሀል ምን እንደነካኝ ሳላውቅ ተዝለፍልፌ ወደኩ:: ምን እንደ ተፈጸመ ወዴት እንደወሰዱኝ አላውቅም:: ምን ያህል ጊዜ እንደቆየሁ ሳላውቅ ነቅቼ ወደ እዝነ ልቦናዬ ስመለስ 1 ክፍል ውስጥ ብቻዬን አልጋ ላይ ተኝቻለሁ:: ቀስ ብዬ አይኔን ገልጬ ዙሪያዬን ቃኘሁ:: ክፍሉ ጽዳት የጎደለው ደም በየቦታው የተንጠባጠበበት የሚከረፋ ክፍል ነውና ተደናገጥኩኝ:: ምን ልሁን? አልጮህ ስቅስቅ ብዬ አላለቅስ ነገር በሰው ሀገር ያውም አደጋ ውስጥ ነኝ:: ትንፋሼን አሰባስቤ ከተኛሁበት ለመነሳት ያደረኩት ሙከራ ሆዴ አካባቢ በተሰማኝ የስቃይ ስሜት ተገታ:: ግራ ገባኝ ምን አድርገውኝ ነው? ቀስ ብዬ እጄን ህመም ወደ ተሰማኝ ሆዴ ላኩት በፕላስተር ታሽጓል:: ደነገጥኩ ምንድን ነው? አልኩኝ ለራሴ በለሆሳስ ሆዴን እንደ ቀደዱኝ ተገንዝቤያለሁና በቃ!.. ለየልኝ ከእንግዲህ ህይወት ኖሮኝ ሰው ሆኜ መኖር አልችልም ስል አሰብኩ::

በዚህን ወቅት ማድረግ የምችለው ወደ ፈጣሪዬ በእንባ ታጅቤ መጸለይ ብቻ ነው:: በመጸለይ ላይ ሳለሁ ያለሁበት ክፍል በድንገት ሲከፈት ጸሎቴን ሳላቋርጥ አይኔን ብቻ ወደ በሩ ወርወር አደረኩኝ:: ሰማያዊ ልብስ የለበሱ አፋቸው ላይ የሽታ መከላከያ ያሰሩ ወደ እኔ ሲመጡ ተመልክቼ አይኔን ጨፍኜ በጸሎቴ ተጋሁ:: የተኛሁበት አልጋ ጋር ተጠግተው በማላውቀው ቋንቋ ከተነጋገሩ በኋላ አንደኛው ከላይ የለበስኩትን ገለጥ አድርጎ ተመለከተና ለሌሎቹ በአረቢኛ የሆነ ነገር ተናገራቸው::..አልፎ አልፎ የማጓራት የስቃይ ድምጽ ከሌላኛው ክፍል ስለሚሰማኝ እኔም ይብስ በስቃይ መራድ ጀመርኩ::

መጀመሪያ ያረፍንበት ቤት ውስጥ ተዝለፍልፈን በየተራ የምንወድቀው ውስጣዊ የሰውነት ክፍላችንን (ኩላሊታችንን) ለመውሰድ በሚዘጋጁበት ወቅት የሚያደክም፣ የሚያዝለፈልፍ መድኃኒት ከምግብ ጋር እየሰጡን ነበር:: እኔም አንድ ኩላሊቴን አስረክቤ በሁለተኛው ቀን ጥርሴን ነክሼ ከአልጋው ላይ ወርጄ የውጭው. . . "

አሁንስ በቃ!!!!!...

ለመሆኑ ኢትዮጵያዊያኑ ላይ ከእግዚአብሄር ውጭ ሁሉ የጨከነባቸው ለምን ይሆን? ከራሳቸው ሀገር መንግስት ጀምሮ ኤምባሲ፣ የመገናኛ ብዙሀኑ፣ ለጩኸቱ ምላሽ የነፈገው ህዝብ… ማህበራዊ ድረ-ገጾቹ በደተኛው ላይ አደጋ ደረሰ ሲባል ዜና መጻፍ አለመፈለጋቸውን ጨምሮ ማን ይሆን አስታዋሹ? በ2011 የመን ውስጥ የሚገኙ ጋዜጦች ትኩረት ሰጥተው ኢትዮጵያዊያኑ ላይ እየደረሰ ያለውን ስቃይ፣ መከራ እና ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ማጋለጥ ሲጀምሩ፣ የእኛዎቹ መገናኛ ብዙሃን ግን ይህን ጩኸት እየሰሙ ጆሮ ዳባ ልበስ ነበር ያሉት፡፡ የኛ ማህበራዊ ድረ-ገጾች ለዘብተኛ እና የእነሱን ፍላጎት ያልተከተለ የህዝብ ጩኸት ከሆነ ቦታም የላቸው፡፡ ከጥቂቶች በስተቀር አብዛኛዎቹ በአንድ አቅጣጫ የሚነፍሱ በመሆናቸው መረጃ አግኝተውም ዝም ነው፡፡ ምን ተሻለን ወገን!!!

ኡኡኡኡ!!!!! ምሬት የወለደው የብሶት ጩኸቴን ስሙኝ፡፡ ኡኡኡኡ የወገን ያለህ!!!!!! ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ነኝ የምትሉ ወገኖች ዝም የማይባልበት ሰዓት ላይ ደርሰናል፡፡ እያንዳንዳችን የየበኩላችንን ልናደርግ ይገባናል፡፡ መንግስት እንዲሰማ ትኩረት እንዲሰጥ ማድረግ የምትችሉ ሁሉ እባካችሁ በርካታ ወገኖች በየቀኑ እያለቁ፣ አካለ ጎዶሎ እየሆኑ፣ መታከሚያ እያጡ በችግር እየተሰቃዩ ነውና እባካችሁ… ኢትዮጵያዊ ነኝ የምትሉ፣ ኢትዮጵያን እወዳለሁ የምትሉ ሁሉ ደጋግሜ እንደምናገረው ኢትዮጵያ ያለህዝቧ ባዶ መሬቷን አይደለም የምትወዱት፡፡ ህዝቡ እያለቀ ዝም የሚል ሀገር ወዳድነት ምኑ ላይ ነው፡፡ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችስ ይህን ጉድ ዝም ካላችሁ ለየትኛው ህዝብ ነጻነት ነው የምትታገሉት? አሜሪካ ላለው? አውሮፓ ላለው? ለኢንቨስተሩ?…. ኪሱን ላደለበው? ..ዝም ካላችሁ ድምጽ ማሰማትም ሆነ መፍትሄ መፈለግ ግድ ካልሰጣችሁ ስልጣን ላይ ተቀምጦ ካለው ስርዓት በምን ትሻላላችሁ? ስል በተደጋጋሚ ጥሪ ባቀርብም አሁንም ደገምኩት፡፡ ነገም እደግመዋለሁ፡፡

እባካችሁ አሁንስ በቃን እንበል!!!!!...

ስደት የወለደው ሰቆቃ የቀጣቸው ወገኖቼን እያየሁ፣ ታሪኩን እየሰማሁ እስኪበቃኝ ሀዘንን አጣጥሜያለሁ፡፡ አንብቻለሁ፡፡ መቼ ነው ማብቂያው? መቼ ነው ፈጣሪ የሚሰማን?… ሁሌም መሪር እንባዬን ሳፈስ የማነሳው ጥያቄ ነው፡፡ እኛ ኢትዮጵያዊያን ከአለም ህዝብ የተለየን ኀሰሀ የማይሽረው ጥፋታችን ምንድን ነው? መቼ ነው?…. መቼ ነው? ማብቂያው? በቃ! የሚለን?…



ሠናይት የጨርቆስ ልጅ ነች፤ የምንተዋወቀው ራቅ ያለ ዝምድና ስላለን ነው፡፡ ባለትዳርና የልጅ እናት ናት፡፡ ሳዑዲ አረቢያ ሄደች ሲባል እሷን እዚህ ማግኘቴ እጅግ ገርሞኛል፡፡ ባሏና ልጇስ ብዬ እያሰብኩ ሳለ፡-

«ሠናይት...ሠናይት... አሪፍ ቢዝነስ አገኘሁልሽ፡፡ ያ ጣጤው ሱማሌ ዛሬ አብሮሽ ማደር ይፈልጋል...»

እያለ አንድ ልጅ ገባ፡፡ ደንግጬ ዞር ስል ሠናይት በሀፍረት አቀርቅራ ፊቷን በሻርፕዋ ሸፍናለች፡፡

* * *

ለኦሮሞ ሕዝብ ያለውን ፍቅር አውርቶ አይጠግብም፡፡ እስር ቤት ውስጥ የአርሲ፣ የጅማ፣ የሐረር. . . በማለት ተከፋፍለው የሚጣሉትን የኦሮሞ ልጆች ሰብስቦ ያስተምራል፡፡ «እኛ አንድ ሳንሆን የምንታገለው እንዴት ነው? መጀመሪያ አንድ እንሁን» ይላቸዋል፡፡ ሰላሳ ዓመት መታገሉን ነግሮኛል፡፡ አንድ ቀን በድንገት ትላልቅ አንቴና ያለው ሬዲዮ የጨበጡ ሰዎች መጡና «ተነስ... ተነስ...» ብለው ይዘውት ወጡ፡፡ በዚህን ጊዜ እቃውን እያዘገጃጀ ምስጢር ያላቸውን ወረቀቶች ጠዋት ሚስቱ ስትመጣ እንድሰጥለት አቀበለኝ፡፡ አቡዳቢ ላለው ካናዳ ኤምባሲ እንድታሳውቅለት እንድነግራትም ነገረኝ፡፡ በዚህን ሰዓት የተሰማኝ ፍርሃት ዛሬ ሳስታውሰው ይሰቀጥጠኛል፡፡ ኮሎኔል መሀመድ የጻፈውን ደብዳቤም በራሴ ማስታወሻ ላይ ገልብጬ ያስቀረሁት በዚህ ወቅት ነበር፡፡

* * *

«እዘንከላት? እዚሁ እያየንህ እርጋት (ተገናኛት)» አለው፡፡

እነዚህ ሰዎች ደም የለመዱ ደም የጠማቸው ናቸው፡፡ እናም ምንም አማራጭ ስለሌለው ሀፍረቱን በእጆቹ ሸፍኖ ተጠጋው፡፡

«ፈጽሞ አላደርገውም! ከፈለክ ግደለኝ፡፡ ወገኔ ናት እኮ!» አለው፡፡

«እንግዲያውስ እዚሁ ወንድነትህን እንዳውቅልህ ካላደረካት ጎምጀ እጥልልሀለሁ!!» እንደፎከረውም ሙሽልቅ ሲያደርገው ሁላችንም ደነገጥን፡፡ በተለይ ከመሀላችን አንደኛው ግን አአአአአአ!!!! ብሎ ዛር እንዳለበት አጓራ፡፡

ዋጋው ብር60.90

አታፋዘር አታሚዎች 011-8 49 53 81